

የቴሌግራም ቻናላችንን ይቀላቀሉ፤
ምርጥ ምርጥ መጽሀፍ በ pdf
እንዲሁም በትረካ ያገኛሉ

@Ethio_Terka

ኢትዮ ትረካ

ቆዳውን ሸንሽነው ቆርጠው፣ ከተጠረበ እንጨት ጋር እያሰሩ መኝታን መስራትና፣ ያንኑ ቆዳ አንጥፈው እንደ ፍራሽ ተጠቅመው፣ ከጥጥ በእጅ የተሰራን አልበሳት ለብሰው መተኛት ይችሉ ነበር። የግንድን ልጥ በእጅ ገምደው የእንስሶች ማሰሪያ ማድረግ፣ የእንስሶችን ጭራ ቆርጠውና ገምደው የሙዚቃ መሳሪያ ማበጀት ይችሉ ነበር።

"ያለ ፋብሪካ፣ ኑግና ሱፍን በእጅ ፈጭተው፣ በውሃ አርሰው፣ ዘይት ማድረግና ወጥን ማጣፈጥ ይችሉ ነበር። በጌሾ፣ በጥራጥሬና በማር፣ ጣፋጭ የአልኮል መጠጥ መስራት፣ ሲታመሙ በቅጠል ታሽቶ መዳን፣ ሰንበሌጥን አያይዞ ሰፍቶ የመመገቢያ ትሪ ማድረግና መገልገል መቻል፣ እንዲህም እየሆኑ መኖር! በእንዲህ አይነት የአኗኗር ዘይቤ ሕይወትን በደስታ መምራት ለሚችልና ለቻለ ሕዝብ በእርግጥም ገንዘብ ላያስፈልገው ይችል ይሆናል።

"ኢትዮጵያውያን በዚህ አይነቱ የበላይ አካሉ ገድቦ ባስቀመጠው የአኗኗር ሕግጋት እየተመሩ የኖሩ ህዝቦች ናቸው። በዚህ አይነቱ ኑሯቸውም ደስተኛ ሆነው፣ይህን አስደሳች ኑሮ የሰጣቸውን የበላይ አካሉን እያመሰገኑ፣ ለእርሱ እየተገዙ፣ በእርሱ ታምነውና ተማምነው የመጡ ህዝቦች ናቸው!

"ይህ ሁሉ ግን እመኑኝ ነበር ሆኗል። ወይም በቅርቡ ሙሉ በሙሉ ነበር ሆኖ እንዲቀር ይደረጋል።

"በገንዘብ በሚገዙ ነገሮች ብቻ ካልሆነ በቀር በሌላ በዘረዘርኩት አይነት ዘዴ ሕይወቱን መቀጠል የሚችል አንድም ዜጋ በዚያች አገር ሊኖር እንዳይችል ይደረጋል። ሰፊ ስራችን ብለን ይፋ ያደረግነውም እሱኑ ነው።

"ይህ ከሆነ ስጋትህና ስጋታችሁ ሙሉ በሙሉ ከስጋት ነፃ ሁን፣ነፃ ሁኑ! ማለት እፈልጋለሁ።

"በዚያች አገር የገጠር ሰው፣ የገዳም ሰው፣ ዓሣ አጥምዶ እሱኑ ብቻ እየበላ የሚኖር፣ ከንሮው ካልሆነ ሌላ ነገር የማይቀምስ፣ ጥሬ ቆርጥሞ የሚያድር አባት፣ በዋሻ የሚኖር፣ የበቃ፣ የነቃ፣ ገለመሌ፣ ገለመሌ የሚባል ታሪክ ከዚህ በኋላ ሊኖር አይችልም! አይገባምም!! ሁሉም በረቂቁ ፍልስፍናችን በገንዘብ የበላይነት ይገዛል! ያለ ገንዘብ መኖር እንዳይችል ይደረጋል!

"እንድም ለዚህ ነው ምግባቸውንም የአኗኗር ዘይቤያቸውንም ቀድመን በኛ ቁጥጥር ስር ማድረግ የሚኖርብን!

"ይህን ያለ ገንዘብ መኖር የመቻልን አካሄድ በዚያች አገር ሙሉ ለሙሉ ለማስቀረት የሚያስችለንን ስራ ጭምር ለመስራት እኮነው ያንን የተቀናጀ የግብርናና የገጠር ልማት ንድፍ ያረቀቅነው። ስለዚህ በኢትዮጵያም ብቻ ሳይሆን፣በሌላውም አገር የሚኖር ኋላቀር ዜጋ በቀድሞው አይነት የአደን ህይወት፣ በቀድሞው አይነት የግብርና ዘዴ፣ ኑሮውን መቀጠል የሚችልበት ሁኔታ አይኖርም።

"ገንዘብ! በሚባል ክብ ውስጥ ይገባል። ወደ እዚህ ሲስተም ከገባ በኋላም በወረቀት ገንዘብ መገበያየቱን እየተው፣ በዲጂታላዊው አሰራር ተጠቃሎ፣ቁጥር ብቻ እየቆጠረ፣ በቁጥር እየከፈለ፣ ቀሪ ሂሳቡን በቁጥር ብቻ እያወቀ፣ ሽያጭ ሲያከናውን ትርፉን በቁጥሩ እያሰላ፣ ሀብትና ንብረቱ በቁጥር እየተለካ፣ ቁጥሩን ከስልክ ወደ ስልክ እያስተላለፈ፣ ቁጥር ልኮ ግዥ እየፈፀመ፣ ቁጥር ተልኮለት እየሸጠ፣ በቁጥር ተስማምቶ እየለወጠ፣በእጁ የሚቆጥረው የሚዘረዝረው የወረቀት ገንዘብ ሳይኖር፣ በኪሱ የሚሸከመው ሳንቲም ሳይኖር፣ በቁጥርና በቁጥር ብቻ ተወስኖ፣ በቁጥር ቁጥጥር ስር ውሎ፣ ህይወቱም ቀልጦለት የሚኖርበት አሰራር ነው የሚዘረጋው፣ክቡራን!

"ይህ ነው የገንዘብ ትክክለኛው ፍልስፍና ክቡራን! በዚህ አይነት የቁጥር ዘዴ፣ የዓለምን ህዝብ በቁጥር ቁጥጥር ስር ካዋልን በኋላ ነው ወደ ዋናውና ወደ መጨረሻው የማይክሮችፕ ገጠማ የምንሸጋገረው! ህዝቡ የቁጥር ሃብቱን እጁ ላይ በሚገጠምለት ማይክሮችፕ እያሰላና እየተቆጣጠረ፣ በኛ የሚቀርብለትን ምግብ ተመግቦ፣ በእኛ ቴክኖለጂ በተዘጋጀለት በቁጥር የመክፈያ ዘዴ ተጠቅሞ ካለው ቁጥር ቀንሶ ለእኛ እየከፈለ የሚኖርበትን አሰራር ነው የምንዘረጋው ክቡራን! ረቂቁ የገንዘብ ፍልስፍና ሄዶ ሄዶ መጨረሻው ይህ ነው! ስለዚህ ሁሉንም ነገር በገንዘባችን በቁጥጥር ስር ማዋል ይቻለናል ወይ? አዎን በደንብ ይቻለናል እንጂ! እደግመዋለሁ፣በደንብ ይቻለናል! ግልፅ ነው?"

"አዎን ንግስት ሆይ።"

የተለመደው የጋራ ሞብጨባ እዳራሹን ናጠው.....። ንግስቲቱም የጋለ ሞብጨባው ጋብ እስኪል ጠበቀው ቀጠሉ።

"ጥሩ፣....‹‹ከበላይ አካሉ ጋር ጥብቅ ቁርኝት ያላቸው መንፈሳዊ ሰዎች ቢቃወሙና ህዝቡ ላይ ሜና ቢፈጥሩ፣ ህዝቡም የእነሱን

ምክርና ተቃውሞ ተቀብሎ ቢያምፅ፣ እምቢ ቢል፣ መንግስታቸውም ሜና በዝቶበት ከእምቢ ባዮች ጎን ቢቆምና በሰላመጨረሻ የምናደርገውን የማይክሮ ቺፕ ገጠማ ቢቃወሙ.....›› የሚል ነገርም አንሰተሃል።

"ምን ነካህ ሀንድ? ሀግ የሚባል ነገር እንዳለ ዘነጋህ ልበል? ዓለማችን የምትመራው በህግ ነው ከቡራን! እኛ እኮ ዘመናዊ የትምህርት ስርዓትን በዓለም ላይ በመዘርጋትና አገራቱን በጂኦግራፊ ቀበጣ በመሸንሸን፣ ለየአገራቱ ካርታ በማበጀትና ህዝቡን በማሰልጠን ብቻ ተወስነን የቆየን አይደለንም።።የነገሮች ሁሉ ማሰፈሠሚያ የሆነውን ህግ የተባለውን ፍልስፍናም በዓለም አገሮች እኩል ሰናሰርፅና ሰናለማምድ የመጣን ነን!

"ቀደም ሲል ብዙዎቻችሁ እንዲሁ ላይ በላይ እንጂ የተለየ ትኩረት ሰጥታችሁ አሰባችሁት ሰለማታውቁት ሰለ ቀላል መሳዩ ከባድ የገንዘብ ፍልስፍና አንስች፣ እንዴት የዓለምን ሕዝብ መጠቅለልና ወደ አንድ ወደ ልዑላችን ዓላማ ለማምጣት እንደምንጠቀምበት ገልጫለሁ።። ልክ በዚያው መጠን ሊሎች ተመሳሳይ የሆኑ በርካታ ፍልስፍናዎችም አሉ።። ከእነሱ ውስጥም አንዱና ዋናው የፖለቲካ ሕግ ነው።። የሕግ የበላይነት ነው።። ሕግ ምን ማለት ነው? የሕግ የበላይነትስ ምንድን ነው?

"በምድራችን ላይ ከ ‹‹ህግ›› አጋጊው ከሃሙራቢ ዘመን ጀምሮ ሕጎች ይረቀቁና ይደነገጉ ነበር።። ሕግ የሰው ልጆች ሲመሩበት የነበረና አሁንም ድረስ እየተመሩበት ያለ፣በየጊዜው እየተሻሻለ፣ እየዘመነ የቀጠለ ነው።።

"የሕግ የበላይነት በማንበረሰብ ደረጃና በዓለም አቀፍ ፖለቲካ ደረጃ ሲተረጎም ግዙፍ ልዩነት አለው።። የሕግ የበላይነት በማንበረሰብ ደረጃ ሰዎቹን እየዳኘ፣ እያስማማ፣ ተበዳይን እየካሰ፣ በዳይን እየቀጣ፣ በእኩልነት ላይ ተመሰርቶ ውሳኔ እያሳለፈ፣ አጥፊን እየቀጣ የሚቀጥልና ሰዎች በራሳቸው ፍላጎትና ተነሳሽነት ብቻ እየተመሩ ያሻቸውን ነገር እየፈፀሙ እንዳይቀጥሉ፣ ጉልበተኞች ጉልበት አልባውን እየበደሉ እንዳይኖሩ፣ ወዘተ... የሚያደርግ የፍትህ ማስፈኛ ዋና መሳሪያ ሆኖ እያገለገለ ያለ ነው።።

"ህዝቡ ሕግን አክብሮ፣ ለሕግ ተገዥ ሆኖ ማንም ሰርዓት አልበኛ እንዳሻው መሆን እንዳይችል በሚገድብ መልኩ ተዘጋጅቶ፣ በጋራ

ስምምነት ፀድቆ፣ ማኅበረሰቡ በጋራ የሚዳኝበትና ፍትህ የሚያገኝበት ዘዴ ነው የማህበረሰብ ሕግ።። በዚህ የማህበረሰብ ሕግና ሕገ-መንግስት፣ መንግስታት ሕዝባቸውን ይመራሉ፣ የሕጉን የበላይነትን ያስከብራሉ።። ሕግን ተፈፃሚ እንዲሆን ያስገድዳሉ።። ሰዎች ሰዎችን በመሰላቸው መንገድ ወይም በጦር መሳሪያ ሳይሆን በወረቀት በተፃፈ ሕግና ህገ-መንግስት አማካኝነት መምራት የሚችሉት በመንግስትና በሕዝብ የጋራ ስምምነት ስለፀደቀ ነው።። ይህንን ነው የማህበረሰብ ህግ የምንለው።።እናንተም የምታውቁት እሱኑ ነው።።

"እኛ ደግሞ የሕግ የበላይነት የምንለው ይህን ሳይሆን ሌላ ነው።። እኛና ቤተሰቦቻችን እንዲሁም ልጆችን አሜሪካ በጋራ ተስማምተን ያፀደቅነው ዘመናዊ ሕግ አለ።።ዓለም አቀፍ የፖለቲካ ህግ የሚባል።።

"እኛ የመላው ዓለምን ህዝብና መንግስት የምንቆጣጠርበት፣ የምናዝበት፣ የምንመራበት፣ የምናስተዳድርበት፣ ውሳኔ አሳልፈን የምንቀጣበት፣ የምንሾም የምንሽርበት፣ የሕጎች ሁሉ የበላይ የሆነ ሕግ! ይህኛው ሕግ ለዚህ ለመጨረሻው ዓላማና ግባችን መዳረሻ ሆኖ የሚያገለግለን ዋና መሳሪያችን ነው!

"ይህ የፖለቲካ ሕግ ያኛውን የማህበረሰብ ሕግ የምንጠብቅበትና የምናስጠብቅበት የምንቆጣጠርበትና ያልፈለግነውን ሕግ በአገር ደረጃ እንዳይረቅና እንዳይፀድቅ የምንከላከልበት ጭምር ነው።።

"በልዑላችን አማካኝነት የዘመናዊ ትምህርት ቀመሮች ተሰጥተውን በመላው ዓለም እንደዘረጋነውና ደረጃ በደረጃ እያሰራጨን እንዳስፋፋነው ሁሉ፣በዚያ አማካኝነትም ዓለማችን ማሰልጠን እንደተቻለው ሁሉ፣ በሂደትም በቴክኖሎጂ ውጤቶች ዓለማችን እንደተራቀቀችው ሁሉ፣ በተራቀቀ የገንዘብ ሲስተም ዓለማችንን በስርዓት መምራት እንደቻልነው ሁሉ፣ በስተመጨረሻ እነዚህን ሁሉ ነገሮች ጠቅልለን ለልዑላችንና ለራሳችን የመጨረሻ ዓላማ ጥቅም ላይ የምናውልበትን ሁኔታ መፍጠር የምንችለው በሕግና በሕግ የበላይነት አማካኝነት ነው!

"በዚህ መሰረት፣የገንዘብ የበላይነት ማለት፣የልዑላችን የበላይነት ማለት እንደሆነው ሁሉ፣የቴክኖለጂ የበላይነት ማለት የልዑላችን የበላይነት ማለት እንደሆነው ሁሉ፣የስልጣኔ የበላይነት ማለት

የልዑላችን የበላይነት ማለት እንደሆነው ሁሉ፣የህግ የበላይነት ማለት ደግሞ የልዑላችን የበላይነት ማለት ነው!

"እነዚህ ሁሉ ነገሮች ከእርሱ የተለዩትን ናቸው።በእርሱ አማካኝነት በምድራችን ላይ እንዲዘረጉ የተደረጉ ናቸው። ሂደው ሂደውም ለእርሱ የመጨረሻ ዓላማ ጥቅም ላይ የሚውሉ ናቸው!

"የሕግ የበላይነትም በየዘርፉ እየዘመነና እየተጠናከረ ቀጥሎ በመጨረሻም የእርሱን የመጨረሻ ፍላጎት ለማሳካት ጥቅም ላይ የሚውል አንዱና ዋናው የማስፈፀሚያ መሳሪያችን ነው። ስለዚህ ሰዎች በዘመናዊ ሕግና ሕገ-መንግስት ተመሩ ማለት በስተመጨረሻም በልዑላችን ለመጠቅለልና ለመገዛት ዝግጁ ሆነዋል ማለት ነው።

"ልብ በሉ፣ ክቡራን! የበላይ አካሉ ሕግ አለ፣ የልዑላችን ህግ አለ፣ ፣ እነዚህ ከሰው ልጅ አፈጣጠር ጋር እኩል የተደነገጉ፣ እኩል የታገቡ፣ ሁለት አይነት ሕጐች ሲሆኑ፣የበላይነቱን የያዘውና የዘመናዊ አስተሳሰብ ባለቤት እንዲሆን የተደረገው የዓለም ሕዝብ የመረጠው የልዑላችንን ሕግ ነው። ስለዚህ ዓለምና ሕዝቦቿ ወደዱም ጠሉም በምድራችን ላይ በዘረጋነው የሕግ የበላይነት ይመራሉ። እርሱንም ያከብራሉ፣ ለእርሱም ይገዛሉ።

"ዘዚህ መሰረት የመላው ዓለም ሕዝብና መንግሥታት በሕገ-መንግስትና በሕግ የበላይነት ተመሩ ማለት በተጥታ ተጠሪነታቸው ለእኛ ለሕግ ሰጭዎቹና ለዋናዎቹ የሕግ ባለቤቶች መሆኑ አያጠያይቅም።

"የማንም አገር መንግስት የማንም አገር ህዝብ ለእኛ ለባለስልጣናቹና ይህን ስርዓት ለዘረጋነው፣ ዘርግተንም ላሻሻልነው፣ የመገዛት ግዴታ አለባቸው። ሕጉን አርቅቀን ስንሰጣቸው፣ ያንን የሰጠናቸውን ሕግ ከላይ ሆኖ የሚጠብቅ ሌላ ሕግን ይዘንና አሰቀርተን ነውና መንግስታቱም ለዚህ ከላይ ሆኖ ለሚጠብቀው ዋና የፖለቲካ ሕግ የመገዛት ግዴታ አለባቸው።

"ከዚህ በኋላ በሚኖረው ጊዜ ሰናሻሽል እያሻሻሉ፣ ስናዛቸው እየታዘዙ ከመቀጠል ውጪ ሌላ እድል የለም። ይህን ለማድረግ ፈቃደኛ ያልሆነ ሕዝብና መንግስት በዚህ በእኛ እጅ ብቻ ባለው ዋና ሕግ፣ ‹‹ሕገ-ወጥ›› ብለን ሰይመንና ከስ መስርተን በቀላሉ መቅጣት ወይም ማጥፋት የምንችልበትን አሰራር ከዘረጋን ቆይተናል። ይህንን ነው እኛ ሕግና የሕግ የበላይነት የምንለው።

"የሰው ልጅ ደግሞ ወደ እዚህ ግዴታ ውስጥ የገባው ያኔውኑ ስለ ሕግ ካወቀበትና በምድራዊው ዘመናዊ ሕግ መተዳደርን ከመረጠበት ጊዜ ጀምሮ ነው። የበላይ አካሉን ሕግ ተላልፎ፣ የልዑላችን ህግ ከመረጠበት ጊዜ ጀምሮ ነው!

"እያችሁ? የሕግ የበላይነት በምድራችን ላይ ባይሰፍንና በዘመናዊ መንገድ በዓለም ላይ ባይዘረጋ ኖሮ የበላይ አካሉ ሕግ ብቻ ነበር የበላይነት ይዞ ይቀጥል የነበረው። ይህ ደግሞ ሊሆን የማይገባው ነበር! ልዑላችንም የቆመለት ዓላማ የዚህ የሕግ ጉዳይ ነው። አናም.....ሕግ የሚባል ከባድ መሣሪያ ታጥቀን ያስታጠቅንን ነንና ዓላማችንን ዳር ለማድረስ የሚያግደን አንዳች ነገር ሊኖር አይችልም። ‹‹እያንዳንዱ የክተማ ነዋሪ በዛሬው እለት በየቀበሌው እየሄደ እንዲመዘገብ ታዟል። በየቀበሌው ሄዶ ያልተመዘገበ፣ አሻራውን ያልሰጠ፣ የቀበሌው ነዋሪ የሆነ ግለሰብ ለሚደርስበት ችግር ኃላፊነቱን ይወስዳል›› ይህ ምንድን ነው? ትዕዛዝ ነው። የአገሪቱ መንግስት በሕግ የሚያስገድድበት ትዕዛዝ!

"ማኅበረሰቡ ቢወድም ባይወድም ቢፈልግም ባይፈልግም በሕግ ተገዶና አፍንጫውን ተይዞ የፈለግነውን ነገር በሙሉ የመፈፀም ግዴታ አለበት። ‹‹በነገው ዕለት ማንም ከቢቱ ሳይወጣ በመንግስት ተዘጋጅቶ የቀረበለትን የጤና መቆጣጠሪያ...›› ወይም፣ ‹‹ሕገወጥ ማኅበረሰቦችን ለመለየት ሲባል መንግስት ያዘጋጀውን ማይክሮ ቺፕ የተሰኘ ዘመናዊ መቆጣጠሪያ መሳሪያ እንዲጠቀም... አለዚያ በሕግ ጥላ ስር ... ›› ወዘተ... እየተባለ ነገሮችን መፈፀምና ማስፈፀም መቻል ለእኛ በጣም ቀላሉ ስራ ነው።

"በእኛ በኩል ያለውና በዋናነት የምናውቀው የምንጠብቀው፣ ለተፈፃሚነቱ የምንረባረብለት የሕግ የበላይነት ይህ ነው! ያለ ከልካይና ያለ ተቀናቃኝ ያሻንን መፈፀም የምንችልበት፣ ሁሉን ከእግራችን ስር የምናደርግበት፣ መላውን የዓለም ህዝብ በልዑላችን ስር አድርገን ለእርሱ የምናስገዛበት ፍልስፍና ነው፣የፖለቲካ ሕግ!

"ለዚህ የሕግ የበላይነት አልገዛም፣ በሕግ የበላይነት ስም ይህን ጉዳይ ዜጎቼ ላይ አላስፈፅምም፣ የሚል አካል ወይም መንግስት ካለ ወደ እኛ ሕግ መጥቶን በእኛ ሕግ እንቀጣለን።

"እምቢተኞችን ምን ስናደርግና ምን እያደረግን እንዳለ ደግሞ ከማንም በላይ እናንተ ታውቃላችሁ። ስለዚህ እምቢተኛ ወገኖችና ቡድኖች ቢኖሩ ምን ልናደርግ እስበናል? ከሆነ ጥያቄው፣

እንደዚያ አይነት ማኅበረሰብ የለምም አይኖርምም ነው መልሱ። ስንነካው የኖርነው መንግስትና ማህበረሰብ ሁሉን እሽ እንዲል ተደርጎ የተገነባ ስለሆነ! እምቢተኛ ማኅበረሰብ እንዳይኖር የሚያስችለን የሕግ የበላይነትን ለመላው ማኅበረሰብ አስተምረን አለማምደን ስለጨረስን።

"ስለዚህ እያንዳንዱ ዜጋ በሕግ አስገዳጅነት ይቀበላልና፣ ይህ ባይሆን ብለን ፈርተን ሌላ ያስቀመጥነው አማራጭ የለም። ሕግ ነው ሕግ ነው!

"የኢትዮጵያ መንግስት ከእንቢ ባዮች ጎን ቢቆምስ? ሀግ ማስከበር ያልቻለ ደካማ መንግስት ብለን እናባርረዋለና! ማባረር ብቻ አይደለም! ለሌሎችም ሙቀጣጫ አድርጎ ማስወገድን እናውቅበታለን! ይህ ደግሞ ሕጋዊ መብታችን ነው! በዚያች አገር እኛን የሚያስፈራን መንፈሳዊ ውጊያ እንጂ፣ ይህ አይነቱ ተግዳሮት አይደለም። እንዲያውም ይህ ከሃያል አገር መሪ የሚጠበቅ ጥያቄ አልነበረም።

"ከእርግጥ እንተ ብቻ አይደለህም፣ ብዙዎቻችሁ የኢትዮጵያ መንግስት፣ የኢትዮጵያ መንግስት ስትሉ እሰማለሁ፣ ሰምቸም እናደዳለሁ።

"የኢትዮጵያ መንግስት፣ የኢትዮጵያ መንግስት አትበሉ! አገሪቱ ላይ ንጉሳዊ አገዛዙ ካከተመ በኋላ መንግስት ኖሮ አያውቅም! ከዚህ በኋላም የኢትዮጵያ መንግስት የሚባል አይኖርም! የሚኖረው የእኛና የእናንተ መንግስት፣ በስተመጨረሻም የልዑላችን የሳጥናኤል መንግስት ነው!

"ከዚህ በኋላ በሚኖረው ጊዜ አገሪቱ ህልውና ኖሯት ሉዓላዊ አገር መሆኗ ከቀጠለ፣ ህዝቦቿ ተፋቅረውና ተስማምተው በጋራ ከቆሙ፣ ሐይማኖታቸውን ጠብቀው፣ የሐይማኖት ተቋሞቻቸውን አክብረውና አስከብረው እንደ ቀድሞው አንድ ሆነው ከቀጠሉማ ምኑን በቁጥር ስር አደረግናት? ተው እንጂ ክቡራን! በትንሹም በትልቁም አትደናገሩ!

"ለማንኛውም እናንተ በሙሉ ኃይላችሁ ወደ ስራ ስትገቡ የሚጠብቃችሁ የእኛ መንግስት እንጂ የኢትዮጵያ መንግስት አይደለምና አትስጉ!

"አገራቱን እንደ አገር አድርጋችሁ የምትቆጥሩትና የምትጠነቀቁት በሌሎች ሐይማኖታዊና መንፈሣዊ ጉዳዮች በኩል እንጂ ፖለቲካዊ ተግዳሮት ሊያሳስባችሁ አይገባም። ገባህ ወይ ሃንድ?"

"እምን ንግስት ሆይ፣ ገብቶኛል፣ ተመልሶልኛል።"

"ቶጥል" አሉ፣ አሮር እጃቸውን ወደ ደቡብ አፍሪካው መሪ ዘርግተው እየጠቆሙ።

ንግስቲቱ ብዙ ጊዜ ከ G 20 አገራት መሪዎች ውስጥ አክብሮት የሚያሳዩት ለአውሮፓ አገራት መሪዎችና ለሰሜን አሜሪካ አገራት ለካናዳና ለአሜሪካ መሪዎች ነው። ለላቲን አገሮችና ለሩቅ ምስራቅ አገራት መሪዎች፣ እንዲሁም ለዓረብ አገራት መሪዎችና ለብቸኛው ጥቁር ለደቡብ አፍሪካው መሪ ግን ብዙም አክብሮት ሲያሳዩዋቸው አይስተዋልም። ደፍረው አይግለጡት እንጂ፣ ለእነዚህ አገራት መሪዎች ብዙም አክብሮት እንደሌላቸው፣ የመጠየቅ ዕድል ሲሰጡ የሚያሳዩት ንቀት አዘል የፊት ገፅታ ያሳብቅባቸዋል። ምናልባትም የሚያነሱት ተልካሻ ጥያቄ እያበሳጫቸው ይሆናል።

"ቶጥል" አሉ እንደዋዛ፣ ጥቁሩን የደቡብ አፍሪካ መሪ በአንገት ምልክት እየጠቆሙ።

"አመሰግናለሁ ንግስት ሆይ፣ ክብር ለድል አድራጊው ልዑላችን። እ....የኔ ጥያቄ በዚህ ረቂቅ ፍልስፍና ብለው በደንብ በገለፁት ገንዘብ ዙሪያና አህጉሬን በሚመለከት ጉዳይ ነው። በብዙ የአፍሪካ አገራት ምናልባትም በሁሉም የአፍሪካ አገራት አሁን የገለፁዋቸው አይነት ህዝቦች በብዛት አሉ። ከአደን ህይወት ያልወጡ። እንደ በርካታ ኢትዮጵያውያን ራሳቸውን ከተፈጥሮ ጋር አዛምደው የሚኖሩ፣ ልብስ እንኳዋን መልበስ ያልቻሉ ብዙ ናቸው። ስለ ገንዘብ ጥቅምና ሁኔታ አይረዱም። ስለ ገንዘብም አያውቁም። ስለዚህ ሁኔታው በኢትዮጵያ ብቻ ያለ አይደለምና፣ በሌሎች የአፍሪካ አገራት ያሉ ተመሳሳይ ህዝቦችን ምን አትደንላቸዋል? ይህ የኢትዮጵያው የተቀናጀ የግብርናና የኢንደስትሪ ልማት የተባለው ዘዴስ በሌሎች የአፍሪካ አገራት ተግባራዊ ለማድረግ አልታሰበም? ይህ አሰራር በገጠሮችና በከተሞች ሊዘረጋ እንደሚችል አምናለሁ። ነገር ግን በአህጉራችን ብዙ የጫካ ውስጥ ነዋሪዎች አሉ። ለማሰልጠን እንኳ ሲሞክር ባህላችንን አንለትም ብለው እንደጠላት አይተው በመርና በቀስት እስከመዋጋት

የሚደርሱ ሚሊዮኖች አሉና እነሱንስ እንዴት ልናደርግ ነው ያሰብነው? በዚህ ዙሪያ የአሀጉሬ ህዝብ እጅግ እያሳሰበኝና እያሳዘነኝ ስለሚባኝ ምን እንደታተደ ባውቀው ደስ ይለኛል።

ለላው፣ የኢትዮጵያን ህዝብ እንዲህ ስንጠነቀቅለትና፣ ሰጋት እንደሚሆን እያሰብን እንደምንወያይበት ሁሉ፣ሰለ ሌላው የአፍሪካ ህዝብ የማንወያይበት ምክንያት ምንድን ነው? ሌላው የአፍሪካ አገር ህዝብ በእርግዋ ስጋት አይሆንም ተብሎ ታሰቧል? ለምን ተናቀ? አሀጉሪቱ ሰፊና ከ 1 ቢሊዮን በላይ ህዝብ የሚኖርባት ናት። ብዙዎቹም የበላይ አካሉ ሐይማኖት ተከታዮች ናቸው። ምናልባት አላውቅም.....ግን እንደሌሉ ያህል እየታሰበ ያለበት ሁኔታ ነውና ያለው ቅሬታ ቢጤ እየተሰማኝ ነው። እነዚያ ጥቁር ህዝቦች ለዓላማችን ተባባሪ መሆን የሚችሉ ትልቅ ህዝብ እንደሆኑ አስባለሁ። ነገር ግን አሁንም ድረስ የጥቁር የበታችነት አስተሳሰብ አለመቅረቱን እየታዘብኩ ነውና፣እንደ ጥቁር መሪነቴ እያሳሰበኝ ነው። በተለይም በዚህ ትልቅና የዓለማችን የመጨረሻው የእኩልነት መድረክ ላይ ይህን በማስተዋሌ ቅር መሰኘቴን መደበቅ አልቻልኩም። እርግጥ ነው ይገባኛል፣ ጎላችን ኢትዮጵያ ስለሆነች ነው። ሆኖም ስለ ኢትዮጵያ ይህን ያህል ሲባል፣ስለ ሌላው የጥቁር ህዝብ አገር ምንም አልተባለም። በአህጉሪቱ ሌሎች አገራትና ህዝቦች የሌሉ እስኪመስል ድረስ ምንም ሲባል አልሰማሁም። በማንነቴም ሲከበር አላስተዋልኩም። ሞራሽ ማንነት እንደሌለው ህዝብ ነው እየተቆጠረ ያለው። በክቡርነትም ዘንድ ይቅርታ ይደረግልኝና፣ ጥቁር ህዝቦች ለምን ተናቁ? ብዬ መጠየቅ አፈልጋለሁ።

ሰፊውና ታላቁ የአፍሪካ ህዝብ ምንም አስተዋጽኦ እንደሌለው አድርጎ ማሰቡስ ችግር አይፈጥርብንም ይላሉ? ብቻ....በመናቃቸው ሀዘን ቢጤ ሳይሰማኝ አልቀረምና፣ በዚህ ዙሪያ ማብራሪያ ቢሰጡበት እላለሁ፣ አመሰግናለሁ።" በማለት፣ በለቅሶ ቀረሽ ቅሬታ አዘል የፊት ገፅታ የታጀበ ጥያቄያቸውን አተረቡ።

ንግስቲቱም፣ "ሃሃሃሃ....ሃሃሃሃ...." በማለት አንጎታቸውን ወደ ላይ ቀና አድርገው የስላቅ ሳቃቸውን ሳቁ። ስላቃቸውም፤ ‹‹ኧረ ባክህ?! ተው እንጂ....?! አይ ሞኞ!! አንተም አህጉር አለኝ ህዝብ አለኝ ብለህ.....!ድንቄም!›› ተብሎ ሊተረጎም የሚችልና፣ ከባድ

ስድብ የተካተተበት ምላሽ ለመስጠት መዘጋጀትን የሚጠቁም አይነት ስላቅ ነው።

"ስማ እንጂ...." ሲሉ ጀመሩ። "ስማ እንጂ....አፍሪካ ውስጥ ከኢትዮጵያ ውጪ አገር ብለህ የምትጠራው የትኛውን አገር ነው? ህዝብ ብለህ የምትጠራውስ የትኛውን ህዝብ ነው? ልታሰለጥኑ ስትሄዱ የሚዋጓችሁ ጎላ ተር ህዝቦችስ ከእናንተ በምን ተሸለው ነው? እናንተስ ማን ሆናችሁና፣ መቸ ሰለጠናችሁና እነሱን ታሰለጥናላችሁ? ዶግሞስ መቸ ነው ለማሰልጠን የሞከራችሁት? አፍሪካ ውስጥ ደህና አገር የምትባለው የእናንተ አገር ናት። እፅም ደህና አገር የሆነችው አገርነቷ ከእናንተ ባለቤትነት ይልቅ የኛ ባለቤትነት ስለሚበልጥ ነው፣እናንተም ለአህጉራችሁ ህዝብ ተቆርቋሪ ሆናችሁ ማለት ነው.....? የሚል ምላሽ የሚያሰጥ አይነት ጥያቄ ነው ያነሳህው። ቢሆንም ግን እንደዚህ አይነት ምላሽ አልሰጥህም። ጥያቄህን ወድጀልሃለሁ። ልክም ነህ። ከኢትዮጵያ ጋር አነፃፅረህ መግለፅህ ግን ትልቅ ስህተት ነው! ከአፍሪካውያን የሚጠበቀው ሁሉም ስህተት ስለሆነ ግን እንዲ ስህተት አልቆጥርብህም።

"ስለ ኢትዮጵያ ይሄን ያህል የተጨነቅነው በዋናነት የልዑላችን ጎል ስለሆነች ነው። በሌላ በኩል ህዝቡ ከሌላው የአፍሪካ አገር ህዝብ የሚለይበት በርካታ ምክንያት ስላለ ነው። በምንም አይነት ሁኔታ ደግሞ የኢትዮጵያን ህዝብ ከሌላው የአፍሪካ አገር ህዝብ ልታነፃጽሩት አትችሉም! ብዙ ነገር አሳየኋችሁ እኮ!

"በአፊ ታሪክ ከብርድ ጋር የተደረገ አጭር ቃለ ምልልስ አለ።

‹‹ብርድ ወዴት ነህ?››

‹‹ወደለበሱት››

‹‹የተራቆቱትስ?››

‹‹እነሱማ በእጅ ናቸው›› አለ ይባላል።

"ስማ! ስለ ሌላው አፍሪካውያን የምንጨነቅበት ምንም ምክንያት የለም! ምናልባት ጎላችን ኢትዮጵያ ሳትሆን ቀርታ፣ሌላ የአፍሪካ አገር ብትሆን ኖሮ እንኳን፣ ምንም ሊያስጨንቀን፣ ምንም የጋራ ርብርብ ሊያስፈልገን፣ አይችልም ነበር። አፍሪካ በሙሉ የእኛ ነው! ህዝቡ የኔ የሚለው ማንነትም የለውም! ከጎላ ቀርነትም ተላቆ አያውቅም። ሱፍ በመልበስና እንግሊዝኛ በመናገር የሚገለፅ ማንነት የለም!

ሥራት ማንነት ያለውን ህዝብና የራሱ ማንነት የሌለውን ህዝብ
አንድ ለማድረግ መሞከር ደግሞ አጉል ራስን መዋሸት ይሆናል!
ሌላው ሁሉ ቢቀር እንኳን ኢትዮጵያውያን ከሌላው የአፍሪካ ህዝብ
በማንነት ብቻ ይበልጣሉ! እያሞገስኩ፥ እያደነቅሁ፥ እያበላለጥኩ፥
አይደለም ክቡራን! አንተም ቅር እንዳይልህ እውነታውን መገንዘብ
ስላለባችሁ ነው። የዚያች አገር ህዝቦች በማንነት ብቻ ከአፍሪካም፥
ከእስያም፥ ከመካከለኛው ምስራቅ ህዝቦችም ይበልጣሉ!
"ለምሳሌ ሌላው የአፍሪካ አገር ህዝብ እኛ ልናሰለጥነው ስንሄድ፥
«አልሰለጥንም» ብሎ ድርቅ ብሎ ቀጥሎ ቢሆን ኖሮ፥ ግፋ ቢል
ራቁቱን እየኖረ፥ አድኖ እየበላ፥ ወይም አርሶ አደር፥ አሊያም
አርብቶ አደር ሆኖ እየኖረ፥ በባህላዊ መድሐኒት ራሱን እያከመ
ቀጥሎ፥ እዚህ ዘመን ላይ ከመድረስ ውጪ ሌላ ተግዳሮት ውስጥ
የሚከተን ህዝብ ሆኖ አይገኝም ነበር።
"ኢትዮጵያውያኑ ግን እንደ ሌላው የአፍሪካ አገር በጎላ
ቀርነታቸው ብቻ ተወስነው ቢቀጥሉ እንኳ፥ ሌላ ችግር
መፍጠራቸውና ፈታኝና ተገዳዳሪ ሆነው መገኘታቸው አይቀርም!
ለምን? ማንነት ያላቸውና የነበራቸው ህዝቦች ስለሆኑ!
"እናንተ በጫካ ህይወት ተወስናችሁ በነበራችሁበት ዘመን፥
ኢትዮጵያውያኑ ከእናንተም ብቻ ሳይሆን፥ከሌላው ዓለም ህዝብ
በፊት የእነሱ ብቻ የሆነ ቁጥር ነበራቸው! የራሳቸው ብቻ የሆነ
ፊደል ነበራቸው! ሐይማኖት ነበራቸው! መንፈሳዊ ትምህርት
ይማሩ ነበር! የንግድ ልውውጥ ያካሂዱ ነበር! ጀልባ መስራት፥
ጀልባ መቅዘፍ፥ ዓሳ ማጥመድ፥ ይችሉ ነበር! የዘመን አቆጣጠር
የሚችሉ፥ ካላንደር ያላቸው፥ ክረምት በምን ወር መጥቶ በጋ
በመቼ እንደሚተካ አስልተው ቆጥረው መድረስ ይችሉ ነበር! መቸ
ዘርተው መቸ ማጨድ እንዳለባቸው ያውቁ ነበር! አርሰው
መብላት፥ ዘር ማስቀመጥ፥ ይችሉ ነበር! ማንበብ መፃፍ ይችሉ
ነበር! ታሪክን መፃፍና ፅፎ ለትውልድ ማስተላለፍ ይችሉ ነበር!
ከገናብና ከብርድ ራሳቸውን ለመጠበቅ ቤት መስራት ይችሉ
ነበር! ለበላይ አካሉ አምልኮ ግልጋሎት የሚውል ቤተ መቅደስ
መገንባት ይችሉ ነበር! ውስጡን በስእል ጥበብ ማስጌጥ ይችሉ
ነበር! የበላይ አካሉን ማመስገኛ ዜማ ነበራቸው! በራሳቸው ቋንቋ
ከመራቀቅ አልፈው ቅኔ ይቀኙ ነበር! ቅኔውን የሚፈቱ መንፈሳዊ
ምሁራንም ነበሯቸው!

"እናንተ በሕገ አራዊት የእኔኮር ዘይቤ ስትተዳደሩ፥ እነሱ ግን
መንፈሳዊ ህግ ነበራቸው! በላ ልበልሃ የሚባል አስደናቂ የዛፍ ስር
የዳኝነት ስርዓት ነበራቸው! በምን ወቅት ምን መብላት
እንዳለባቸው የሚያውቁ፥ የሚመገቡትን ምግብ መምረጥ የሚችሉ፥
የአመጋገብ ስርዓት የነበራቸው ህዝቦች ነበሩ!
"ጋብቻቸውን በስርዓት የሚፈፅሙ፥ አገራረዝ የተማሩ፥ ዘር
መቁጠር የሚችሉ፥ ትርጉም ያለው ስም ለልጆቻቸው የሚያወጡ፥
ማን ከማን እንደተወለደ የሚያውቁ፥ የቤተሰብ ትስስርን
የሚገነዘቡ፥ ዘር ማንዘራቸውን በአግባቡ መቁጠር የሚችሉ፥ ማን
ማንን ማግባት እንዳለበት መምረጥና መወሰን የሚችሉ ህዝቦች
ነበሩ! የሕይወት ተሞክሯቸውን፥ ፍልስፍናቸውን፥ በቃላት ቀርፅው
የሚያስቀምጡ፥ የዘልማድ የመግባቢያ ቋንቋ ብቻ ሳይሆን፥የሚፃፍ
ቋንቋ የነበራቸው ነበሩ! እሁንም በዚያው ስርዓት ቀጥለው ያሉ
ናቸው! ታዲያ ይህ ሁሉ ነገር የነበረው ህዝብ በአህጉራችሁ ነበረ
እንዴ? ማንነት የሚባለው ይህ ነው!!
"የሌላውን አፍሪካውያን ህዝብ ማንነት ከመጀመሪያው ጀምሮ እኛ
እናውቀዋለን! ይህ አይነት ማንነት ያለው ህዝብ በዚያች አህጉር
ጨርሶ አልነበረም! እኛ ደግሞ ማንነት የሌለውን በተለይ
ሐይማኖትና እምነት የሌለውን ህዝብ ልንፈራም፥ ልናከብርም፥
አንችልም! ማንነት የሌለው ህዝብ ኖረ ቀረ ለኛ ምንም ነው!
ዋናው ፈታኝ ህዝብ ሆኖ መገኘት አለመቻሉ ነው። የያዝነውን
ዓላማ ዳር እንዳናደርስ ፈታኝ ህዝብ ሆኖ ሊገኝ የሚችለው ደግሞ
የኢትዮጵያን አይነት ህዝብ ነው! ለምን? በመንፈሳዊ ህግጋት
ሲመራ ስለኖረና፥ ጠባቂም ስላለው!
"በተረፈ የሌላው አፍሪካ አገር ጥቁር ህዝብ ጌቶች እኛ ነን!
ጠፍጥፈን የሰራነው፥ ያሰለጠንነው፥ እኛ ነን። በእኛ ህግ ይመራል፥
እኛ ያልነውን ይሰማል። አልሰማ ካለ እናጠፋዋለን። ባለቤት ነና!
ፊደል ሳይቀር ቀርፀን የሰጠነው እኛ ነና! የእኛን ቋንቋና ፊደል
ነዋ የሰራ ቋንቋ ያደረገው! ከትንሹ ከዚህ ይጀምራል ማንነት! የኔ
የሚሉት ነገርና የኔ የሚሉት ባህል፥ የኔ የሚሉት ሐይማኖት፥ የእኔ
የሚሉት የአስተዳደር ስርዓት ያላቸው የአፍሪካ ህዝቦች ካሉ
ታሪካቸውን መናገር ይቻላል።
"ጥቁር አፍሪካውያን በየጫካው ተፈጥሮ የሰጠቻቸውን ፍራፍሬ
እየበሉ በጎላ ቀርነት ይኖሩ ነበር። ትልቁ ስልጣኔ ከአደን

ሕይወት ወጥቶ ዘላንነት በሚባለው በአርብቶ አደርነት ላይ የተመሰረተ ሕይወታቸው ነው። እልፍ ሲል የጎሳ መሪዎች እየተፈራረቁ ጎሳቸውን /ቤተሰባቸውን/ መምራት ነበር። እሱም ሽምገል ያለውን ሰው የበላይ አድርጎ የመቁጠርና የጎሳው መሪ አድርጎ የመቀበል ተራ ልማድ የፈጠረው ነው። ብዙ ከብት ያለው ተሰሚነት እየኖረው፣ በምግብ ቅድሚያ እንዲበላ እየተደረገ፣ በሚስት በኩል እንደ ልቡ ብዙ ሴት ማግባት እየቻለ፣ ወተት ለመጠጣት ቅድሚያ እየተሰጠው፣ ከታደነው አውሬ ልብ እና ኩላሊት እየተሰጠው.....ሲታይ፣ የበላይ ሽማግሌ እንደሆነ እየተቆጠረለት የቀጠለ አስቂኝ ስርዓት ነው የነበረው።

በተረፈ ፖሲሲ ቀርያ፣ ግብር ሰብስቦ፣ አገሩን እያለማ፣ እያሻሻለ፣ የሐይማኖት ተቋማት እየገነባ፣ ህዝቡን በሥነ-ምግባር እያነፀ፣ ታሪኩን በራሱ ቋንቋ እየፃፈ፣ ቋንቋውን እያሳደገ፣ የቀጠለ የጎሳ መሪ የለም።

"ይህንን ደግሞ የዱር እንስሳትም ያደርጉታል። እነ አንበሳ እነ ነብር በተመሳሳይ ሁኔታ ሽማግሌ ነበራቸው። ከታደነው የአውሬ ስጋ ሽማግሌ አንበሶች ቅድሚያ እንዲበሉ ይደረጋል። የበላያቸውን ይሾማሉ፣ ይሽራሉ። ሴት አንበሳ ስታረጅ ልጇ እየተከበረ፣በሌላ አገላለፅ የጎሳ መሪ እየሆነ፣ ወንዱ ነብር ሲያረጅ አክብሮት እየተቸረው.....ያው ነው!

"እንዲህ ነው ያገኘናችሁ! ከዚህ ስርዓት ነው ያወጣናችሁ! እንዲህ ሆናችሁ አገኘናችሁ፣ የአደን መሳሪያዎቻችሁን አስጥለን፣ ልብስ አለበስን! ሱፍና ከረባት አስለመድን። ትምህርት፣ ዘመናዊ ተሽከርካሪ፣ ቢሮክራሲ፣ ወዘተ... እያልን ብዙዎችን ከጫካ አውጥተን አሰለጠንን። የማይሃፍ ቋንቋቸውን በኛ ፊደል እየተካን መዝገበ ቃላት አዘጋጅተን እንዲፅፉ አደረግን። እንዲህና እንዲያ እያለ ተቀጥሎ እዚህ ዘመን ላይ ደረስን። ከዚህ በኋላ የት መሄድ ይችላሉ? ወደ ቀድሞው እንመለስ እንዳይሉ ረፍዷል። የአደን መሳሪያቸውን ጥለዋል። የአደን ስልቱም ጠፍቶባቸዋል። የሚታደን በቂ አውራም የለም። በስልጣኔና በእድገት እንዳያገሰግሱ ስልጣኔና እድገትን ከመሰረቱ አያውቁትም። ስልጣኔን የጀመሩት ከመሃል ነው። ስለ ልብስ አሰራር ሳያውቁ ነዋ በአንድ ጊዜ ሱፍና ከረባት ያለበስናቸው። እምን! ወደ ቀድሞ ባህላቸው መመለስ አይችሉም። ራሳቸውን ችለው ወደ ፊት

መግስገስ አይችሉም። በእንጥልጥል እንዳሉ ናቸው። በእንጥልጥል እንዲገኙ ስናደርግም በምክንያት ነው! በፈለግን ወቅት ከቆሙበት መሃል መንገድ ላይ ብድግ አድርገን ወደ ምንፈልገው አቅጣጫ መውሰድ፣ እንደልባችን መንዳት እንችላለን!

"እንዳልከው ግን ምናልባት ያኔ ሁሉንም ጫካ አላዳረስን ይሆናል፣ ጊዜ ወሳጅ የሆኑትን በሩቅ ጫካ የሰፈሩ ህዝቦችን አውጥተን ሳናሰለጥን እንደቀረንና አሁንም ድረስ በዚያው እንዳሉ እናውቃለን። የእነሱ ጉዳይ ግን ሊያሳስበን አይችልም። ጫካውን ስናቃጥልና ስናወድም አብረው የሚወድሙ ሊሆኑ ይችላሉ። ምንም ይሁን ሊያሳስብህ ግን አይገባም።

"ስለ ግንዘብ የማያውቁ፣ ራቁታቸውን የሚኖሩ፣ እናሰልጥን ብንል እምቢ እያሉ.....? ምን የሚሉት ሽንገላ ነው? ስለ ገንዘብ ቢያውቁ ባያውቁ ከምትዘርፉት ገንዘብ አታካፍሏቸው! ምን ማለትህ ነው?

"እያንዳንዳችሁ መሪዎች ባሁኑ ሰዓት ማሰብና ጠንክሮ መስራት ያለባችሁ ለልሁላችን የመጨረሻ ድል ሲባል የሚደረገውን ሂደትና ጥረት ብቻ ነው። ለዜጎቻችሁ ከተጨነቃችሁና ካሰባችሁ ይህንን ዓላማ በመደገፍና ዳር በማድረስ ነው ልትጠቅሟቸው የምትችሉት። በዚህ ድል አማካኝነት ነው የምድር ላይ ገሃነታችሁን ለዘላለም ማግኘትና ለህዝባችሁ ማስገኘት የምትችሉት! ይህ ካልሆነ ብታስቡላቸው ባታስቡላቸው ምንም ጥቅም የለውም! ስለዚህ ከዚህ በኋላ በሚኖረው ጊዜ ህዝቤ፣ አገሬ፣ አህጉሬ፣ የሚባል ዲስኩር ጥቅም የለውምና ተውት! ዓላማችን ላይ ብቻ ነው ማተኮር ያለባችሁ! ጭራሽ ደግሞ በአፍሪካ?! የአፍሪካ መሪ ሆነህ ህዝቤ? ይህማ ያስተዛዝባል! እስካሁን ሳትሉ ኖራችሁ ከረፈደ በኋላ.....ህዝቤ? ሆ.....ጉድ ሳይሰማ መስከረም አይጠባም አሉ....! ምናልባት እየቀለድክ ይሆን?"

"አይ ከልቤ ነው ንግስት ሆይ፣ትንሽ አሳዘኑኝ መሰለኝ....አላውቅም ብቻ ይቅርታ ይደረግልኝ" አሉና በሀፍረት ተውጠውም ቢሆን ፈገግ ለማለት ሞከሩ።

"ግዴለም፣ ነገሮችን ማስረዳት ስላለብኝ እንጂ ጥያቄህ ልክ ነው። ግን ደግሞ ገረመኝ። ከመቸ ጀምሮ የመጣ አፍሪካዊ አስተሳሰብ ነው? ብዙ አስብኩ። በአፍሪካ ህብረት ጉባዔያችሁ ለብቻችሁ መዶለት ጀመራችሁ እንዴ?"

"ኧረ በጭራሽ! ንግስት ሆይ፡፡" አዳራሹ በጋራ ሳቅ ተሞላ፡፡ ንግስቲቱም አብረው እየሳቁ፣ "ወይ ደግሞ እንዲህ ልታስቀን ፈልገህ መሆን አለበት፡፡" አሉ፣ ወደ ወደ ደቡብ አፍሪካው መሪ እየተመለከቱ፡፡

"አይደለም ንግስት ሆይ፣ትንሽ ተሰማኝና ነው መጠየቄ....."

"አአ ሊሰማህ አይገባማ! ይሄኮ ንገሩኝ ባይነት ነው! በአጭር መልስ የሚዘጋ ጥያቄም አይደለም ያነሳህው፡፡ ስለዚህ ዕውነቱን ሰፋ አድርጌ እነግርሃለሁና ተቀበል!

"ሌላው የአፍሪካ አገር ህዝብ በድንጋይ ዘመን ላይ ባለ ጊዜ ኢትዮጵያውያኑ ግን እንደዚያ አልነበሩም፡፡ ከሁሉም ቀድመው የበላይ አካሉ ተከታይ የሆኑና ሐይማኖት፣ ፊደልና የዘመን አቆጣጠር የነበራቸው ህዝቦች ነበሩ፡፡

"እንደ ሌላው የጥቁር አፍሪካ አገር ህዝብ ራቁቱን የተገኘ ህዝብ አይደለም! እንደ ሌላው የአፍሪካ አገር ህዝብ ማኅበራዊ ሥነ-ምግባር ሳይኖራቸው እንዲሁ በጎሳ ሲመሩ የኖሩ ህዝቦችም አይደሉም፡፡ ለረጅም ሺ ዓመታት ያንን መሠረት ያለው የአኗኗር ዘይቤ ተከትለው ሲኖሩ የቆዩና አሁንም ድረስ በዚያው የአኗኗር ዘይቤ ቀጥለው ያሉ ይበዛሉ፡፡ እነዚህ እምነትና ሐይማኖት የነበራቸውን ህዝቦች ከሌላው የአፍሪካ አገር ህዝቦች ጋር እያመሳሰሉ ማየትና ማነፃፀር በፍፁም አይቻልም፡፡ ለእናንተ ማንነታችሁን ከሰጠናችሁ፣ ልብስ ካለበስናችሁ፣ ገና 100 ዓመታችሁ ነው፡፡

"ከግብፅና ከጥቂት የሰሜን አፍሪካ ሙስሊም አገራት በስተቀር፣ ሌሎች ብዙዎቹ አፍሪካውያን የተፃፈ ታሪክ አላቸው? ወይስ ነበራቸው? አልነበራቸውም! እርግጥ ቋንቋ ነበረ፡፡ ባህልም ኋላ ቀርና ሀግ አልባ ነው እንጂ ይኖራል፡፡ ቋንቋና ባህል ደግሞ ወፎችም የዱር እንስሶችም አላቸው፡፡ ፊደል ግን አልነበረም! ፊደል ያገኛችሁት የዛሬ 50 ዓመት ነው! ቋንቋችሁን በኛ ፊደል መፃፍ የጀመራችሁት የዛሬ 50 ዓመት ነው፡፡ ራሳችን ባዘጋጀንላችሁ መዝገበ ቃላት! ከዚያ በፊት ቤተ-መፃህፍትም፣ የተፃፈ ሰነድም፣ የሐይማኖት ተቋማትም አልነበረም!

"ሌላው የአፍሪካ አገር ጥቁር ህዝብ ስለ ሐይማኖት ካወቀና ሐይማኖተኛ መሆን ከጀመረ ገና ሃምሳ ዓመቱ ነው፡፡ እሱንም በእኛ ሚሲዮኖች አማካኝነት ሆን ብለን እንዲያውቁ ስላደረግን

ብቻ! በሐይማኖት ስር ተሰባስበው፣ ተደራጅተው፣ እንዲጠብቁን በማሰብ፡፡ ስለዚህ ሌላው የአፍሪካ አገር ህዝብ፣ በሐይማኖት በኩል እንኳ ጨርሶ ሊያሳስበን የሚችል ህዝብ አይደለም፡፡

"ኢትዮጵያውያን ግን ለረጅም ሺ ዓመታት የበላይ አካሉ ሐይማኖት የነበራቸው፣ በህግ የሚተዳደሩ፣ በተደራጀ ዘመናዊ የንጉስ ስርዓት ሲመሩ የኖሩ ናቸውና ስጋት ሊሆኑ ችለዋል፣ነው ለማለት የተፈለገው፡፡

"በዚያች አገር ውስጥ በተለይ እነዚያ ያሳየኋችሁ በየቦታው መሸገው ያሉና ከበላይ አካሉ ጋር ጥብቅ ቁርኝት ፈጥረው ልዩ ልዩ መንፈሳዊ ጥበብን እየተቀበሉ የቆዩ ናቸውና፣ ከእነሱ ጋር መጠነኛ ግብግብ ይኖራል፡፡ ዓለምን በቃን ብለው የበላይ አካሉ ታማኝ ሆነው ከእርሱም ጋር እየተነጋገሩ፣ ከእርሱ በሚሰጣቸውም ጥበብ ብዙ ሥራዎችን እየሰሩ፣ ዓላማችን ለማደናቀፍ መጣራቸው አይቀርም፡፡ እነሱን ገዝግዞ መጣልና ምሽጋቸውን ማፈራረስ ከተቻለ ነገሮች እየቀለሉ ይሄዳሉ፡፡ እነሱንም መጠንቀቅ አለብን ነው፡፡ አቅልለን ያላየንበት ምክንያት አንዱ ይህ ነው፡፡ እንጂ ሌላውን የአፍሪካ ህዝብ ንቀን እነሱን አክብረን አይደለም፡፡ ሌላውን ሳንፈራ እነሱን ብቻ ፈርተንም አይደለም፡፡ የሚያሳስቡንና የምንጠነቀቀው እንዲህ ባለው መንፈሳዊ ጉዳይ የላቁ ሰዎቻቸው የሚገኙባት ምድር ስለሆነች እንጂ፣ሁሉም ህዝብ ያው ተመሳሳይ ህዝብ ነው፡፡ ሁሉንም የአፍሪካ ህዝብ ወደ አንድ ሲስተም እናመጣለን፡፡ አሰራሩንም በድፍን አህጉሪቱ እንዘረጋለን፡ ፡ሌላውን የአፍሪካ ህዝብ ወደ ምንዘረጋው ሲስተም በቀላሉ ማስገባት አይሳነንም፡፡ ምክንያቱም በእኛ ባህል፣ በእኛ ቋንቋ፣ በእኛ ፊደል፣ በእኛ ሐይማኖት፣ በእኛ ብዙ ነገር የተከበበና የኑሮውን መሰረት በእኛ የጣለ ስለሆነ በፈለግነው ዘዴና ጊዜ ወደ እኛ ማምጣት እጅግ ቀላል ስራ ነው የሚሆነው፡፡ የራስን ንብረት ብድግ አድርጎ እንደ መውሰድ ቀላል ስራ! የኢትዮጵያውያኑ ግን በጠቃቀስኳቸው ነገሮች ለየት ሊል ችሏል፡፡

"ይህ ደግሞ ለቅናት የሚዳርግ ሆኖ በአንድ ጊዜ ለህዝብህ እስከ ማሰብ ሊያደርስህ አይገባም፡፡ ሌላው ሁሉ ቀርቶ ማክሮ 6 የሚቀበለውን ፊደል መጠቀም የቻለው የእናንተ ህዝብ ነውና በሱ ብቻ ደስ ሊልህና ቅናትህን ልትተው ይገባ ነበር፡፡ ወይም የኢትዮጵያውያኑን ቋንቋ ማክሮ ስድስታችን ወደ ቢት ቀያይሮ

"ኢትዮጵያውያን በኢጣሊያ ቅኝ ያልተገዙበት ሚስጥር ይህ የእኛነት ሚስጥር ነው። የጋራ ባህል፣ የጋራ ሃብት፣ የጋራ ሐይማኖት፣ የጋራ ታሪክ ነበራቸውና፣ ያን ላለማስነካትና ላለማስደፈር ሲሉ፣ ‹‹እኛ›› ብለው በጋራ ተነስተው ለድል በቁ።

"ሁሉንም የዓለም ታሪክ ብታገላብጡ፣ እኔ ብሎ ተነስቶ ለድል የበቃ ሃይል እንደሌለ ትረዳላችሁ። ለዚህ ነው እኛም እኛ ብለን ለመነሳትና እናንተንም ለማሳተፍ የፈለግነው። እኛነት ለጣፋጭ ድል፣ እኔነት ለመራር ሽንፈት ይዳርጋል! ይህንን አትርሱ።

"እንደ ሩሲያው መሪ ብቻችሁን ለማፈንገጥም አትሞክሩ! እኔነት የትም ስለማያደርስ።

"አሁን ወንድማችሁ የደቡብ አፍሪካው መሪ ያነሳው ጥያቄ እኔነትን ተንተርሶ የመጣ ጥያቄ ነው። በራስህ መንገድ ሂድና ለጥያቄህ ምላሽ፣ ችግር ላልከው መፍትሄ፣ አበጅለት ቢባል ግን ብቻውን አይችልም። ከመላው አፍሪካዊ መሪዎች ጋር ተባብሮ እንኳ አይችልም። ቢችል ቀድሞውንም ይችል ነበራ! ማንም አልከለከለውም። ስላልቻለ ግን በእኛነት ጉባዔ ላይ እኔነትን የተመለከተ ጥያቄ በቁጭት ለማቅረብ ተገደደ።

"በእኛነት ጉባዔ ላይ እኔነትን የሚመለከት ጥያቄ ለምን ቀረበ? ስለ ሁሉም አገርና አህጉሮች፣ ስለ ሁሉም ህዝቦች በጋራ እየተወያየን ባለበት ጊዜ፤ እንዴት እንዲህ ያለ የአንድ አህጉር ቁጭት አዘል ጥያቄ ሊነሳ ቻለ? ጥያቄውስ በወንድማችሁ አእምሮ ውስጥ እንዴት መነጨ? ብንል፤ ምንጩ አንድ ነገር ብቻ ሆኖ እናገኘዋለን። ምንጩ የማንነት ቀውስ ነው። ‹‹አይዴንቲቲ ክራይሲስ!›› ይባላል። የማንነት ቀውስ ከምን ይመነጫል? ካለማወቅ! ከምን አይነት አለማወቅ? ከብዙ አይነት አለማወቅ! ማንነትን ለይቶ ካለማወቅ ጅምሮ፣እሱን በሚመለከት የተነገረን የሃሰት ወሬ እውቀት አድርጎ ይዞ እስከ መኖር በደረሰ አለማወቅ ምክንያት፤ የማንነት ቀውስ ሊከሰትብን ይችላል።

"አንድ ሰው ወይም ቡድን የማንነት ቀውስ ውስጥ ገባ ማለት ደግሞ እኔነቱ በጣም እያሳሰበውና ብዙ ጥያቄ እየፈጠረበት ይሄዳል። ጥያቄውን ለመመለስ የሚሞክረውና የሚመልሰውም ከራሱ እውቀት ተነስቶ ይሆናል።

"የራሱ እውቀት ደግሞ እውነተኛ እውቀት አይደለም። ስለዚህ እውቀት ያልሆነውን እውቀቱን ይዞ እኔ ብሎ በእኔነት ብቻውን

መዝግቦ መያዝና ሙተርንም አለመቻሉን፣ በዚህም የሰሚኑን ክፍል ህዝብ ማከሮ 6 በቀላሉ መቆጣጠርና መከታተል አለመቻሉን አስበህ ጥርስህን ልትነክስባቸውና፣ ፊደላቸውን በኛ ፊደል ተክተው መጠቀም የሚችሉበትን ዘዴ መመኘት፣ ስለዚያ ማሰብ፣ በአፍሪካውያን መሪዎች ጉባኤ ላይ ጥቆማ እየሰጠህ በዘዴ ስለመተግበር ማሰላሰልና የመፍትሄው አካል ለመሆን መጣር ሲገባህ፣ ሞራሽ ህዝቤ.... አህጉሬ.....ማለት ባልተገባ! ለማንኛውም አይዞህ አታስብ፣መሆን ያለበትን ሁሉ እኩል እናደርጋን። ክብር ለልዑሉ!"

"አሜን!"

"ሌላው ያነሳህው ጥያቄ እኔነትን ተንተርሶ የመጣና በውስጡም የማንነት ቀውስ የያዘ ጥያቄ ነውና እሱን ወደ ማብራራት አልፋለሁ።

"ከዙራን፣በማናችሁም መሪዎች ዘንድ የ ‹‹እኔነት›› ጥያቄ ሊኖር አይገባም። ብዙ ጊዜ በተለያዩ አገራት መሪዎችና ህዝቦች ዘንድ እንዲህ ያሉ የ ‹‹እኔነት›› ጥያቄዎች ይነሳሉ። ‹‹እኔ›› ተብሎ የተጀመረ ነገር ደግሞ ለውጤት በቅቶ አያውቅም። የእኔነት ጥያቄን አንስቶ፣ እኔነቱን እውን ለማድረግ ተነስቶ ታግሎ፣ ለውጤት የበቃና፣ እኔነቱን ያስከበረ ቡድንና ሃይል ኖሮ አያውቅም።

"እኔ ብለው ብቻቸውን የተነሱት በሙሉ ውጤታቸው ታይቷል። ውጤታቸውም ሄደው ሄደው ብቻቸውን መውደቅ ብቻ ነው። አይደለም የሰው ልጅ ልዑላችን እንኳን እኔ ብሎ አልተነሳም። ‹‹እኛ›› ብሎ ነው የተነሳው። እኛ ድቅሎችም ያን አካሄድ ለመሄድ አልተነሳንም። እኛ ብለን ተነስተን ነው እናንተን የህብረታችን አባል አድርገን ለጋራ ጥቅም፣ የጋራ ጉባዔ እያደረግን፣ ለጋራ ድል በጋራ እየሰራን ያለነው። ለምን? እኔነት ሳይሆን እኛነት ለድል ስለሚያበቃ!

"በረጅም ዘመን ታሪካችን ያን ሁሉ አገር በቅኝ ግዛት ስንይዝ ህዝቡ ‹‹እኔ›› እንዲልና እንዲከፋፈል እናደርግ የነበረው እኮ ‹‹እኛ›› ብሎ በጋራ ተነስቶ ዓላማችን እንዳያደናቅፍብን በሚል ነው። እኛ ብሎ ከተነሳ ያለ ጥርጥር ለድል ሊበቃና ሊመልሰን ይችላል። ህዝቡ በእኔነት ከተከፋፈለ ግን ሊመልሰን ሊገዳደረን አይችልም።

ይነሳል። በእኔነት ሲነሳ ደግሞ ለምን እንደሚነሳ በትክክል
አያውቅምና፣ እንዲሁ ብድግ ብሎ ጎል የሌለው ኳስ ጫወታ
መጫወት ይጀምራል። ጎል ብቻ አይደለም ተጫዋች በሌለበት
ብቻውን ይጫወታል። ተጫውቶ፣ ተጫውቶ፣ ሲደክመው ያርፋል
ቢባል አንድ ነገር ነበር። እንደዚያ አይደለም ክቡራን። ተጫውቶ
ተጫውቶ ሲደክመው ይወድቃል፣ ይጠፋል፣ ወይም ይሞታል።
ለምን እንደደከመውም አያውቅማ! ሲደክመው ለማቆም አይደለማ
ጫዋታውን የጀመረው። በቃ እንዲሁ እኔነት አሳስቦት በስሜት
ተነስቷልና፣ የሚያደርገውን የሚሰራውን አያውቀውምና፣ ዝም ብሎ
ይቀጥላል። ታዲያ ፍፃሜው ምን ሊሆን ይችላል? ግልፅ ነው
ክቡራን፣ውድቀት ብቻ!

ገረጅም ጊዜ ተሞክሯችን ካረጋገጥነው ሃቅ አንዱ ይህ ነው።
ለዚህ ነው አፍሪካውያንን በፊጠራ ወሬ እያሳበብን አንዱ ባንዱ
ላይ በቁሞት የሚነሳበትን ዘዴ እያመቻቸን ብዙ እኔነቶችን
ፈጥረን ሁሉን ፀጥ ለጥ አድርገን ከፋፍለን መግዛት የቻልነው።
ይህን ሰናደርግ ምን ማድረጋችን ነበር? በየሁሉም ውስጥ የማንነት
ቀውስ እንዲፈጠር ማድረጋችን ነበር። እዚህ ቀውስ ውስጥ
እንዲገቡ ማድረጋችን ነበር። የማንነት ቀውስ ደግሞ የምድራችን
ክፉ በሽታ ሆኖ በአንደኝነት የተመዘገበ ነው። ክፉ በሽታ ከመሆኑ
የተነሳ መዳኛ የለውም። መድሃኒት የሌለው በሽታ ሆኖ ግን
አይደለም። መድሃኒቱ የሚገኘው በራሱ፣ ቀውሱ በተፈጠረበት
አካል ውስጥ ስለሆነና ስለማይጠቀምበት ግን፣ እንደ መድሃኒት
አልባ በሽታ ሊቆጠር ችሏል! እመኑኝ የማይድን በሽታ ነው።
በጊዜ ሂደት እንኳን ሊለቅ የማይችል በሽታ ስለሆነም ነው
ወንድማችሁ አሁን ድረስ ጥያቄ እንደሆነበት የቀረውና በዚህ
ጉባዔ እስከማንሳት የደረሰው።

"የዚህ በሽታ ሰለባዎች ደግሞ መፍትሄውና ፍቱን መድሃኒቱ
በራሳቸው ውስጥ መኖሩን ስለማያውቁት፣ የማድ መድሃኒቱን
የሚፈልጉት ከሌሎች ነው።

"በዚህም ማንም ሃይል፣ ማንም ቡድን፣ ማንም ግለሰብ፣ ‹‹መድሃኒቱ
አለኝ›› እያለ ይጫወትባቸዋል። ማንም ተነሰቶ፣ ‹‹መድሃኒቱ
አለኝ›› ካላቸው ሰፍ ማለታቸው አይቀርም።

"በዚህ ደካማ ጎናቸው ምክንያትም የሁሉም መጠቀሚያ ለመሆን
ሙሉ በሙሉ ዝግጁ የሆኑ ይሆናሉ። ማንኛውም አካል ያሻውን

ነገር ‹‹መድሃኒት ነው›› እያለ ቢሰጣቸው ይውጣሉ። ‹‹ምርምር
ላይ ነኝና ልሞክርብህ ነው›› ቢባሉም እሽ ነው የሚሉት።
"በሽታው ተላላፊ በሽታ ነውና፣ የታማሚውም ቁጥር በየ ጊዜው
እየጨመረ መሄዱ አይቀርምና፣ አፊ ቀላጤዎች የዚህን በሽታ
ሰለባዎች አሰልፊው፣ መጠቀሚያ ከማድረግ አልፊው፣ በሽታውን
የሚያባብስ ሌላ መርዝ እንደ ልባቸው መውጋት፣ በጥብጠው
መጋት፣ በፍሬ እየመጠኑ ማዋጥ ይችላሉ! ስለ አወሳሰዱም ማዘዣ
ይፅፋሉ። ታማሚዎችም በተፃፊላቸው መሰረት የማይድን
በሽታቸውን በሃሰት ኪኒን እያከሙ፣ ለሌሎች ታማሚዎችም
እያከፋፈሉ፣ ሳያውቁት በሽታውን እያባባሱ፣ እያዛመቱ ይቀጥላሉ!
ባጭሩ ሁሉም ዶክተራቸው መሆን ይችላል ማለት ነው።
‹‹ዶክተር ነኝ መፍትሄ አለኝ ተሰለፉ›› ቢላቸውም ይሰለፋሉ።
ሰብዓዊነታቸው በሃሰት ፕሮፖጋንዳ ተገፍፎ ስለ ተጣለ፣ እንደ
ሰው ሳይሆን እንደ እቃ ጥርቅም ነውና የሚቆጠሩት ማንም
እንዳሻው በየመንገዱ እየጠለዘ ሊጫወትባቸውም ይችላል።
"የማንነት ቀውስ ክፉ በሽታ ነው ክቡራን። ይህንን ነው በአፍሪካ
ስናሰራጨው የኖርነው በሽታ! አሁን ድረስ አልዳንም! አሁን ድረስ
መድሃኒቱ በእጃቸው እንዳለ አላወቁም! ጭራሽ ሰው ሰራሽ በሽታ
መሆኑን እንኳ አላወቁም!!

"ለምሳሌ ይሄን ጥያቄ በዚሁ አዳራሽ አንድ ነጭ መሪ አንስቶት
ቢሆን ብላችሁ አስቡ። ነጭ መሪ ሆኖ ስለ አፍሪካ ህዝቦች
ተቆርቁሮ ይህንኑ ጥያቄ በዚሁ ጉባኤ አንስቶ ቢሆን ኖሮ፣
ወንድማችሁ የደቡብ አፍሪካው መሪ፣ በቀጥታ ዞር ብሎ ጠያቂውን
ያየው ነበር።

"ለአፍሪካ ተቆርቋሪ ሆኖ ይሄን ጥያቄ በማንሳቱም የደቡብ
አፍሪካው መሪ በአድናቆት ብቻውንም ቢሆን ያጨበጭብለት
ነበር። በፍቅር አይን እያየ ያመሰግነው ነበር። በዚሁ በቅፅበት
በዚሁ አዳራሽ ክልቡ ይወደዋል! ያለውን አክብሮትም ከአዳራሽ
ውጭ አግኝቶ ይነግረዋል። ጥያቄው የሚደነቅ እንደሆነ እየገለፀ
አብሮት ሻይ ቡና ይላል። ወዳጆች ይሆናሉ፣ እፍ ያለ ፍቅር
ውስጥ ገብተው እኛን ሳይጋብዙ ብቻቸውን እየተገባበዙም ሊቀጥሉ
ይችላሉ። ልክ ነኝ ወይ?" ብለው ጠየቁ።
"ልክ ነው ንግስት ሆይ እንደዚያ ነው የሚሆነው።" በማለት
የግዳቸውን ፈገግ ብለው መልስ ሰጡ።

"በዓለማችን ሶስት አይነት የቆዳ ቀለም ነው ያለው። ሶስቱም አይነት የቆዳ ቀለም ያላቸው ነገዶች በዚያች አገር የሚገኙት የስርጭቱ መነሻ ስለሆነች ነው። እዚያው የሚቀሩት ቀርተው ሌሎቹ በየአቅጣጫው ተሰራጭተዋል።

"ከዚያ በኋላ ግማሽ በአካባቢው ላይ ሰፍሮ ቀረ፣ ግማሹ ጉዞውን ቀጠለ፣ አንዳንዱ አምላኩን እንደ ተቀበለ ቀጠለ፣ አንዳንዱ አምላኩን መተውን መረጠ። አንዳንዱ መንፈሳዊ ህግጋትን ተቀበለ፣ ሌላው ሳይቀበል ቀረ። ሁሉም በየራሱ መንገድ እየሄደ፣ የመረጠውን ህይወት በመረጠው ስፍራ መኖር ጀመረ።

"አንዳንዱ የራሱን ባህል ፈጥሮ ራቁቱን መኖር፣ ሌላው ልብስ ሰርቶ መልበስ፣ አንዳንዱ መሰልጠን፣ አንዳንዱ መሰይጠን መረጠ፣ አንዳንዱ ፈላስፋ፣ አንዳንዱ የፈላስፋ አድማጭ፣ አንዳንዱ ጎበዝ፣ አንዳንዱ ሰነፍ፣ አንዳንዱ ጦረኛ፣ ሌላው ወሬኛ፣ ከፊሉ ሰልጣኝ ከፊሉ አሰልጣኝ፣ እየሆነ... ሁሉም በየፍላጎቱ ተጉዘ።

"በቃ እንደ ምግብ ምርጫ ውስጡ። አንዳንዱ ጎመን ይሻለኛል ብሎ መርጦ ጎመን መመገብ ጀመረ ብላችሁ አስቡ። ሌላው ስጋ ይሻለኛል ብሎ መርጦ ስጋ በላና ጎልምሶ ተገኘ። የጎለመሰው በኮሰመነው ላይ ተነስቶ ትግል ገጥሞ ቢረታው ስለ ተረችው ሃላፊነቱን የሚወስደው ማነው? እራሱ ነው!

"የቀድሞው ኑሮ በየሰዎች ምርጫና ፍላጎት የሚወሰን እንጂ፣ በሃኪም ትእዛዝ በላይንስ ምክር የሚወሰን አልነበረም። ሁሉም በየምርጫው ይኖር ነበር። ገሚሱ ሰውነቱን መተልተል፣ ገሚሱ አለመተልተል፣ ከፊሉ ከንፈሩን በሹል ድንጋይ በስቶ በሸክላ ማጌጥ፣ ሌላው ከንፈሩን ማስዋብ፣ አንዳንዱ ወርቅ ቀጥቅጦ ማጌጥ፣ አንዳንዱ ሰውነቱን አፈር በመቀባት ማጌጥ፣ ከፊሉ አርሶ መብላት፣ ከፊሉ አድኖ መብላት፣ አንዳንዱ ተራራ ሲመርጥ፣ ሌላው በሜዳ ሲኖር..... እያለ የቀጠለ ሂደት ነው ያለው። ሁሉም የየምርጫውን ውጤት እያገኘ የቀጠለ ነው። በተረፈ ሁሉም የሰው ልጅ እኩል ሆኖ የተፈጠረ ነው። ከዚያ በኋላ ለተከሰተው ነገር ሃላፊነቱን የሚወስደው እራስ እራሱ ነው። ወይም የየጎሳውና የየቤተሰቡ መሪ። እውነቱ ይሄ ሆኖ ሳለ፣ አሁን ላይ በተለይ አፍሪካውያን ያንን የቀድሞ የተሳሳተ ምርጫቸውን ማክም ወይም እንደ ልዩ ባህል ቆጥረው ማግኘን ፈልገው ይሁን.... ምን ይሁን... ባናውቅም

"አም ግልፅ ነው። ምክንያቱም በደካማ ጎኑ ነው የገባበት! ‹‹ልል ስል ቀደምከኝ!›› አይነት ነገር ነው የሚሆነው። ‹‹ይህ የመላው አፍሪካውያን ጥቁር ህዝቦች ቁጭት ነውና፣ለህዝባችን አሰበህ ይህን በማንሳትህ እናመሰግናለን። ወደ ፊትም አብረን እንታገላለን›› አይነት ግንኙነት ይመሰርታሉ።

"በሌላ አነላለፅ፣ ‹‹የበሽታችን አይነት ካወቀውማ ስለ መድሃኒቱም ያውቃል›› ተብሎ ይታሰብና፣ ማባባሻ መድሃኒቱን ለመዋጥ ወይም ለመወጋት መዘጋጀት ይከተላል። መርፌውን ተወግቶ ህዝቡንም ለማስወጋት ማስለፍን ያስከትላል።

"በዚህ አይነት ሂደት የታማሚዎችም የፈዋሾችም ቁጥር በየጊዜው እየጨመረ ቀጥሎ....ፈዋሾቹ እያተረፉ፣ መድሃኒት ፈላጊዎቹ እየከሰሩ፣ እየደከሙ፣ ወደ መጨረሻው አይቀሬ ውድቀት ይደርሳሉ።

"እባካችሁ! በሃያል አገር መሪ ግለሰብነታችሁ ደረጃ የማንነት ቀውስ ያለባችሁ ካላችሁ፣ አሁኑኑ በዚሁ ቅፅበት መድሃኒቱን መውሰድና፣ እዚሁ ድናችሁ መውጣት አለባችሁ።

"በእርግጥ ከሃያል አገራት ውስጥ የዚህ በሽታ ሰለባ የሆኑ ህዝቦች ያሉ አይመስለኝም። አፍሪካ ላይ ግን ያው.... ያለ ነውና ይህ ምክሬ በዋናነት የሚጠቅመው ላንተ ይመስለኛል። ከዚህ በሽታ ተላቀህ እንድትወጣ ከማሳሰቢያ ጋር ማስጠንቀቅ ይኖርብኛል። እንደ መልስም መፍትሄውን ባሮጉ ልናገር። መፍትሄው ስለ ሰው ልጅ አፈጣጠር ማወቅ ነው። ይህን ደግሞ ማወቅ የሚቻለው በሐይማኖት ነው።

"እውነታውን ማወቅና መቀበል ተገቢ ነው። ይህ ሽንፈት አይደለም ክቡራን። በዓለማችን ውስጥ አንድ የጋራ እውነት አለ፡ ሁሉም የሰው ልጆች ፍጡር መሆናቸው። ይሄን የሚክድ የለም። የዚህ የጠቀስኩት በሽታ ሰለባዎች ግን በጣም በበሽታው ከመዳከማቸው የተነሳ በዚህ እውነት ላይስማሙ ይችላሉ። ስላልተስማሙ ግን እውነታውን አይለውጡትም፣መድሃኒቱንም አያገኙትም!

"የሰው ልጅ በተለያዩ የቆዳ ቀለም እኩል የአካል ክፍሎች ኖረውት እኩል ሰው ሆኖ ተፈጥሯል። ስርጭቱ ከዚያች መከረኛ አገር ተነስቶ የቀጠለ ነው።

የሆነ የሆነ ነገር... ይላሉ። አሁን ወንድማችሁ እንዳነሳው አይነት ጥያቄ ብዙዎች ይጠይቃሉ። ጥቂሮች ዝቅ ተደርገዋል ይላሉ! "እርግጥ ነው እኛ ቀድመን ስልጥንን ወደ አልሰለጠነው አገር እየሄድን አሰልጥነናል። ዜጎችን ወደ አገራችን በባርነት እያጋዝን ብዙ ስራ እናሰራቸው ነበር። ይህ ደግሞ በጥቁር ብቻ አይደለም። በነጭም አገር አለ። ሀንድና ኬንያ፣ ኢንዱኒዥያና ኳታር፣ ወዘተ.....ሁሉም የኛ ግዛት ስለ ነበር ከነጭም ከጥቁርም ከሁሉም አህጉር ነው ያጋዝነው። ጉርምርምታው ብሶ የተገኘው ግን በጥቁሮች ነው!

"ቆይ እኛ ምን እናድርግ? ፈዛችሁ ደንዝዛችሁ ራቁታችሁን ነው ያገኘናችሁ! ይህ የማን ጥፋት ነው? አቅም ያላቸው፣ መደማመጥ የሚችሉ፣ ነገር የገባቸው፣ ኢትዮጵያውያንማ ‹‹አይሆንም!›› ብለው መለሱን እኮ! የሚጠብቁት ንብረት ነበራቸው። ራሳቸው ያፈሩት ብዙ ነገር ነበራቸው። ያ እንዳይወሰድባቸው ቢጠነቀቁ ቢከላከሉ ያምራል። ስለ እኩልነት ቢያወሩም ያስኬዳል።

"ሊላው የአፍሪካ ጥቁር ህዝብ እንዲያ ሆኖ ሲጠብቀን ምን ማድረግ ነበረብን? እነሱ ተንተርሰውት የሚተኙት ተራ ድንጋይ በኛ አገር ውድ ማዕድን ሆኖ አገኘነውና ወስደን ተጠቀምንበት! ደግሞም ብንወስድባቸው ባንወስድባቸው እነሱ አይጎዱም። ለእነሱ ያው ድንጋይ ነበር። ለዘላለም ድንጋይ ሆኖ ነበር የሚቀጥለው። ነገ ከነገ ወዲያ ስንሰለጥን እንጠቀምበታለን ማለት አይችሉም። አይሰለጥኑማ! እኛ ካላሰለጠናቸው ያን ባህላቸውን ብቻ ይዘው ነበር የሚቀጥሉት! ለማሰልጠን እንኳን አሻፈረኝ ብለው ስንት ፍዳ ነው ያየነው?

"ታዲያ.....ዝቅ ብናደርጋቸው ከፍ ብናደርጋቸው ያው ዝቅ ያሉ አልነበሩም እንዴ? ዝቅ የማለትን እና ከፍ የማለትን ትርጉም እንኳ ያስተማርን እኛ ነን። ያውም ትላንት! ከተፈጠሩ ከ7 ሺ ዓመት በኋላ! ይህ እየታወቀ በዛሬ ፖለቲከኞች ዘንድ የነጭ የበላይነት.... ይላልኛል...! ወደህ! እንዳውም መመስገን ነው ያለብን! ፈዘህ ደንዝዘህ ጠበከን እንጂ ሰልጥነህ አልጠበከን። በሊሊት መጥተን እንደ ሌባ አልዘረፍን።

"ሃያል ነን... ጦር ነበረን....እንዘምትለን። መክቶ መመለስ የእነሱ ድርሻ ነው አልቻሉም። የድሮው ዘመን ሀግ ደግሞ ይሄንን ይፈቅድ ነበር! ስለዚህ የበላይ ሆነን ገዛን! አሁንም የበላይ መሆን

እንችላለን። ግን በእኩልነት እያሳተፍን ነው። ይህን ካደረግን በኋላ እንደገና ተመልሶ፣ ያን ችግር አብሮ እንደ ተፈጠረ በሽታ አድርጎ እያዩ በየጊዜው ማላዘን ምን ይፈይዳል?

"ይህ አይነቱ የማንነት ቀውስ በተለይ በአፍሪካውያን ላይ በርትቶ ዛሬም ድረስ ቀጥሎ የሚገኝበት ዋነኛ ምክንያት ይህ ነው። ዛሬ ላይ ሆነው ራሳቸውን ቀድመው ከሰለጠኑት ጋር ያወዳድሩና፣ እንደነበሩ ሲገባቸው፤ ደርሰው መገንፈል ያዘወትራሉ።

"በየዕለቱ የመበለጥ ስሜት እየተሰማቸው ባለፈ ታሪክ እርር ድብን እያሉ እንደቀት ይኖራሉ። መቅናት ያለ ነው፣ቅናታችን የምንገልፅበትን መንገድ ግን ማጤን ያስፈልጋል።

"በቆዳ ቀለም ሳይቀር የተበለጡ የሚመስላቸው አሉ። ባሪያ አድርገው ገዙን የሚሉ አሉ። እንዴት ነው ነገሩ....? ዋናው ነገር ባሪያ ሆኖ ላለመገኘት መጣር መሰልጠን ራስን ማብቃት ነው እንጂ..... እንዲሁ እንደ ተፈጠረ ባለበት ተገኝቶ ምን መሆን ይቻላል? በዚህ መፀጸትስ ምን ይረባል? ከባርነት ለመውጣት መጣር ያለ ነው። እናንተ ደግሞ ሂትለር ባይነሳ መቸም ነፃ አትወጡም ነበር። የአፍሪካ አርበኛ፣ ፓን አፍሪካ፣ አትበሉ! እሱ እሱ፣ ጫዋታው ካበቃ በኋላ ነፃነቱን ቅርፅ የማስያዝ ስራ እንጂ ሌላ አይደለም።ራሳችን ነን ነፃነታችሁን የሰጠናችሁ! ርዕዮቱ ሲያበቃ ሁሉም ነገር አብሮ አበቃ።ታሪኩ ይሄ ነው። ታዲያ ስለ ምን እኩልነት ነው የምታወራን?

"ከዚህ በፊት በነበረው ዝግ ጉባዔ ለጳጳሳችሁ ያነሳህውን ጥያቄ በቀጥታ ስርጭት ተመልክቻለሁ! ለምን አናጠፋቸውም? ስትል አድምጫለሁ። ታዲያ ዛሬ ላይ ይህ ጥያቄ እንዴት ሊፈጠረብህና ጥያቄ ብለህ ልታቀርበው ተነሳህ?

"ክፉ በሽታ! ዛሬ እንኳን ነፃ ወጥተው እኩል መብት ኖሯቸው እያዩ የማይዋጥላቸው የበዙት፣ በሽታው ባሳደረባቸው ተፅእኖ ምክንያት ብቻ ሳይሆን፣ እውነታውን እያወቁት እንኳ ለመቀበል ባለመፈለጋቸው ነው። እውነታው ግን አንድ ነው፣እሱም ይህን በሽታ የፈጠረው ፖለቲካ መሆኑን አውቆ መፍትሄው ግን ከፖለቲካ ሳይሆን ከእምነትና ከሐይማኖት ተነስቶ ማሰብ መቻልና፣ምንም ማለት እንዳልሆነ መገንዘብ፣ተገንዝቦም በፖለቲካ እየተገረሙ ስቆ ማለፍና መረጋጋት መቻል ብቻ ነው።

"ብዙ ጊዜ በተላሉ የማንነት ቀውስ ውስጥ የሚገቡት ሐይማኖት የሌላቸውና ከእምነት ውጪ የሆኑ ህዝቦች ናቸው።
"አፍሪካውያንን በተላሉ የዚህ ሰለባ ማድረግ የቻልነውም በዋናነት ሐይማኖት አልባ ስለነበሩ ነው። የሆነ እምነት ይኖራቸዋል። ያ እምነት ግን እንዲህ በልምምድና በተጨባጭ ገጠመኝ አንድን አካል የበላይ አድርጎ የማምለክ ባህላዊ ዘዴ እንጂ፣እምነት ወይም ሐይማኖት ብለን የምንጠራው ተጨባጭ የሆነ ነገር አይደለም። ከአትዮጵያ ማዕታችን ከነበረችው ከግብፅ በሰተቀር ሌሎች ብዙዎቹ የአፍሪካ ጥቁር ህዝቦች አኛ ስናግኛቸው እንደዚያ ነበሩ። እምላክቸውን በየቋንቋቸው ስም ሰጥተው፣ እንዲህ በማምትና በይሆናል፣ዝናብ የሚያዘንብልን፣ ከብቶቻችን የሚያባዛልን፣ እያሉ የሆነ የሆነ እምልክ ያክሂዱ ነበር።
"ይህ ደግሞ እምነትም ሐይማኖትም አይባልም። ምክንያቱም ራሱን የቻለ ሐይማኖታዊ ሀግ የለውም። ተዕፎ የተሰጣቸው መመሪያ የለም። እምላክቸውን በውል አያውቁትም። እንዴት እንደሚሰራ፣ ከእነሱ ምን እንደሚጠበቅ፣ ምን ሲያደርጉ እንደሚቀጣቸው፣ ምን ሲያደርጉ እንደሚወዳቸው፣ ምን እንደሚጠላ፣ ምን እንደሚወድ፣ አያውቁም። ነቢያት ተነስተው ያስተማሯቸው ነገር የለ፣ ትንቢት አያውቁ፣ ስለ መጪው አልተረዱ፣ እንዲሁ ዝም ብሎ አማልክት ነገር።
"በዚህ ሁኔታ ውስጥ ሆነው ጥቃትን የልዑላችን ሚኖሮች አማልክት እየሆኑ እየተመለኩ፣ የልጆች እቃ እቃ ጫወታ አይነት ሲጫወቱባቸው ነው ያገኘናቸው።
"በአንዳንድ ቦታ ዛፍ ላይ የተሰቀለ የሰውና የእንስሳ አፅም፣ በሌላ ቦታ እንጨት ላይ የተንጠለጠለ የደረቀ የራስ ቅልና ቅልጥም የመሰለ አጥንት እየተመለከ፣ በሌላ ቦታ ወፉ ዛፉ አምላክ ሆኖ እየተሰገደለት፣ አሞራ አልፍ ባለ ቁጥር፣ ‹‹አማልክት አለፉ ወደ አደን እንሂድ›› እየተባባሉ፣ ሊያምኑት በሚከብድ አሰቲኝ ሁኔታ ውስጥ ሆነው ሲኖሩ ነው ያገኘናቸው።
"አቤ.....ት ያን ቅራትንበ ለማስጣል የነበረብን ትግ.....ል! አቤት.....የከፈልነው መስዋዕትን.....ት! ልብስ ልበሱ፣እምቢ! ብለኩት ብለ፣እምቢ! ዝናብ እንዳይጓዳችሁ ድንኳን ውስጥ አደሩ እምቢ! ይሄ ተራ የሰው አጥንት ነው፣አምላክ አይደለም አውርዱት፣እምቢ! ወር ከመውረወር መሳሪያ መተኮስ ይተላልና

እንኩ በዚህ አድኑ፣አምቢ! ከዳር እንሰሳ የባሱ ጎላ ቀሮች ሆነው ነው ያገኘናቸው! ይህ እንዴት ይረሳል? በብዙ ትግልና በብዙ ጥረት አይደለም እንዴ የቀየርናቸው? ከዚያ ሁኔታ አውጥተን ሰው አድርገን፣ አሰልጥነን፣ ብዙ ታሪክ አልፎ፣ ነፃም ወጥተው፣ በዓለም አቀፍ መድረክ እኩል እንዲሳተፉ እስከ ማድረግ ደርሰን እንኳን፣ አሁን ድረስ በሽታው ገና አለቀቃቸውም። ያገርማችኋል፣ በብዙ የአፍሪካ አገሮች ተራ ሰው መስዬ እዘዋወራለሁ፣ እንበኛለሁ። ‹‹ጎልድ ኢዝ ጎይት፣ ብላክ ኢዝ ዳይመንድ›› የሚሉ ጥቅሶችን በአፍሪካ ከተሞች በየታክሲው በየህዝብ አውቶብሱ ተለጥፎ አያለሁ። በደንብ የሚቸበችብ የታክሲ ላይ ስቲከር ይሄ ጥቅስ ያለበት ነው። ይሄ ጥቅስ የሌለበት የጥቁር ተሽከርካሪ የለም ማለት ይቻላል።
"ሞራሽ ከነሞቷ በላይ መሆን፣ አልፈው መሄድና በሃሳባቸው መብለጥ ያፈልጋሉ! አያችሁ? የበሽታው አደገኛነትና ዘላቂነት እዚህ ድረስ ነው!
"ከወርቅ ይልቅ ጥቁር ዳይመንድ እንደሚበልጥና፣ በጣም ውድ ማዕድን እንደሆነ ያሳወቅናቸው እኛ ነን። ያውም ትላንት! ከዚያ በፊት ስለ ሁለቱም ጥቅም አያውቁም ነበር። ተንተርሰውት ይተኙ የነበረ ለእነሱ የድንጋይን ያህል ዋጋ እንኳ ያልነበረውን ማዕድን እንደምሳሌ እያነሱ.....ይፎክራሉ!
"ያለፈ የጋርዮሽ ስርዓት የኑሮ ዘይቤያቸውን በእኛ ማሳበብ ይፈልጋሉ! ቅኝ ስለተገዙ ሳይሰለጥኑ እንዳቀሩ ያስባሉ። ‹‹ባንግላ ኖር፣ ሜና ባይኖርብን ኖር፣ የተፈጥሮ ሃብታችን ባይዘረፍ ኖር፣ እስካሁን የጎና የት እንደርስ ነበር›› እየተባለ ሊቀለድ መሆኑ ነው!! መቸ ነው ቅኝ የገዛናቸው? ትላንት እኮ ነው! ታዲያ ባይገዙ ኖሮ ይሄንንስ ማሰብ ይችላሉ ወይ? አይችሉም!
"ከዚያው ከጋርዮሽ ስርዓት ሳይወጡ የአሁኑ ዘመን ላይ ይደርሱ ነበር። ይህ በሆነበት ሁኔታ ጥቁሮችን ዝቅ አድርጎ የመመልከት አባዜ አሁንም አልቀረም.....ይባላል! እየተዋወቅን? ፊደላችንን ነጥቀው የእነሱን ፊደል እስከ መስጠት ደርሰው እንዳይባል፣ ፊደል አልነበራቸውም! ባህላችን ተበርዞ እንዳይሉ፣ ባህል የሚሉት አለማወቅን ነው! ቅርስ ብለው ሙዚየማቸው ውስጥ የሚያስቀምጡት ማፋ ቢል አውሬ መግደያ ሽል ድንጋይ፣ የነብር ቆዳ፣ የአንበሳ ቆዳ፣ እንጂ፣የስእል ጥበብ፣ የሐይማኖት መሳህፍት

ሰው ከእኔ ነብሱ በትልቅ ጉድጓድ ውስጥ ተቀረ። እናቱን ስለሚወድና በጣም ስላዘነ መሆኑ ነው። የእናቱን ጉዳቸኛ ለመቀበል እንዳይባል እናቱ የሞቱት አርጅተውና ታመው ነው፣ የደቡብ አፍሪካውያን ባህል ይኼ ነው ከቡራን። ዛካ ዙሉን ብዙዎቻችሁ ቢታረክ ታውቁታላችሁ። ታዲያ በዚህ ታሪካችን እንኩራ ነው እየተባለ ያለው? ወይስ ይኄን ባህላችሁን ባህል ብላችሁ ነው ተጭናችሁ፣ በሃይልና በጫና አስለውጣችሁ፣ እያላችሁ የምትወቅሱን?

ጓውኑቴ ይህ በሆነበት ሁኔታ ዝቅ አድርጋችሁን፣ ማንነታችን አጥፍታችሁ፣ ባህላችን አስለውጣችሁ፣ የባህል መረራ ተፈፅሞብን፣ መራታችን ተወስዶብን፣ እየተባለ ይመራል! ይህን ማለት ነውር አይሆንም?

ጎስለዚህ በዚህ በአሁኑ ዘመን እንኳ ከፍ ከፍ ብትሉ፣ ስልጣን ብትይዙ፣ የማንነት ቀውስ ያልኩት በሽታችሁ እስካልቀታችሁ ድረስ የምትዘረጉትን አስተዳደር ስርዓት እናውቃለን።

ጎእንደ ዛካ ዙሉ አይነት ጀብድ ነው ልትፈፅሙ የምትችሉት! ያን ልትፈፅሙብን! ልትበቀሉን! በቀሉ ደግሞ የሃሰት ወሬን ተንተርሶ የሚፈፀም በቀል ስለሚሆን በጣም ለትጣጭና በዓለማችን ያልተለመደ በቀል ነው የሚሆነው።

ጎደግሞም ስልጣን ይዛችሁ ታይታችኋል! እንኳን የነጭ የበላይ ሆናችሁ የራሳችሁን ወገን ላለፉት 50 ዓመታት የመራት ፅድል አማኝታችሁ መርታችሁ አይተናል!

ጎያዩነውም እንዴት እንደምትገርፉ፣ እንዴት እንደምትደፍሩ፣ እንዴት የሰው ስጋ እንደምትበሉ፣ ነው።

ጎማእከላዊ አፍሪካ በእነ ቦካሳ፣ በምስራቅ አፍሪካ በእነ ኢዲ አሚን ዳዳ የሰው ስጋ ስትበሉ አሳይታችኋል! ሁሉም ታይተዋል! አሁንም ድረስ እየታዩ ነው! ለክት የለሽና ሥነ-ምግባር ያልታከለበት የሐይማኖት አልባ ሰዎችን ጭካኔ ዛሬ ድረስ እየፈፀማችሁ አይደለም እንዴ? ያውም በድብቅ በሆነ፣ በአደባባይ! ታዲያ እንዴት ብሎ ነው ማህበራዊ ሥነ-ምግባር የማያውቅ ህዝብና ማህበራዊ ሥነ-ምግባር የሚያውቅ ህዝብ እኩል የሚሆነው? የአፍሪካውያን የእርስ በእርስ እልቂት በሙሉ የማንነት ቀውስን ተከትሎ በሚመጣ በሽታ ምክንያት የተከሰተ ነው ከቡራን! ይህ ሁሉ እልቂትና መፈናቀል ያን በሽታ በዚህ ዘመን ፖለቲካ

ከፈጠራቸውም፣ ከሳቸውም፣ በዚህ በዚህ ምክንያት..... እንዚህን ነገሮች ስመለከታቸውና ስረዳቸው..... እኔም እንደሆን ለመሆኑ በዘርፉ እኔም ሆንሳል እዝ በጀታው ማን አለ።

ገመ እንዲት ተፈጠር? ሕዳምና ቴዎን ብዚራቸው ምን ነበር? ሁለተኛውን ሲነው ልጅ ምራፍ ያስቀጠለው የናጎ እና የቤተሰቡ ብሔር ምን ነበር? ፍቱን መድሃኒቱ እንዚህን ጥያቄዎች ጠይቆ መልሱን ማግኘት ነው። መልሱም ግልፅ ነው። ሁሉም ሲመች የሰጀድ ዜተሰብ ሊጆች ናቸው። ይህን ማወቅ መቻል በእርግጥም ፈውስ ነው። ይህን ሕውቆ ሲሳው ነገር ሁሉ በራስ ችግር የመጣ መሆኑን ሕምኖ ንቆ መተው ነው።

ጎፓስቲስ ያመጣው በሽታ መሆኑን መረዳትና ሰቆ ማለፍ ነው። ከዚያ እኔ ኢጅራ ማን ደሃው ሙጭጭ እንዳሉ እንኳንንን....እንዳሉ አሰ! ስልጣን ደጨው የነጭ የበላይ መሆን ደፈልጋሉ!

ገሽ ደሁንላችሁ ዚቃ የበላይ ናችሁ ብለን ስልጣን ብንሰጣቸው ደግሞ ምን እንደሚከሰት አሰቡ! ምን አይነት የባህል ማስፋፋት ውሰዋ እንደሚገቡ ሰመገመት ሞክሩ!

ግዘላችን ደዳልሰናል! ቀደምት የአፍሪካውያን ባህልና ማንነት ደሚሉት የነበ ዛካ ዙሉን ዘመን ነው። ዛካ ዙሉ የእናንተ የአሁኗ የደቡብ አፍሪካ የነሳ መሪ ነበር። ስእናንተ ታላቃችሁ እሱ ነው። ታሪክ ጥሰው ሄትባሉ እሱን ነው የምታነሱት።

ጎዛካ ዙሉ፣ የዙሉ ማህበረሰብ ጎሳ መሪ ነበር። የመጀመሪያው ዛካ መሪኛ ነው። ያሚዋጋው በዲንጋይና ከእንጨት በተሰራ ጦር ነው። ውጊያ የሚገጥመው በአጎባቢው ካሉ ከሊሱች ጎሳዎች ጋር ሲሆን፣ ምንም አይነት ያሚያጋጭና ሰጠርንት የሚያበቃ ምክንያት ግን የሳቸውም። ዛካ ማን በቃ ጀግና ሰለሆነ ይዋጋል....። ወይ የአደን ዞታችን አትሻሙን ራቅ በሉ፣ ወይም በዚህኛው ዱር አትሰፉ፣ ወይም ሲላ እያደ እየተጣላ ይዋጋል።

ገና ዛካ ዙሉ ራቂቲን ሆኖ ራቂቲን የሚናርን ህዝብ ይገዛል፣ ያስተዳድራል። ወጣቶች ካደጉት አውሬ ልብ ልቡን የሚሰጡት ለእሱ ነው! በቃ ንጉስ ነው። ይህ ንጉስ ድንገት እናቱ ሞተችበትና በጣም አዘነ። በሃዘኑ ምክንያት አሰር ሺ የዙሉ ጎሳዎችን ከእነ ንብሳቸው ከሰር አንዋር እናቱን ከሳይ አድርጎ ቀበረ። አሰር ሺ

ለማከም የሚደረግ የአላዋቂዎች መፍትሄ ፍሰጋ እንቅስቃሴ
ውጤት ነው፤
"የማንነት ቀውስን በየ መድረኩ እያነሱ መሬሙሀና መቆጨት፣
እሱንም በዚህ ዘመን ፖለቲካ ለማከም መሞከር፣ በቢላዋ ሜዳ
ትልቅ ቁስልን እንደማከክ ይቆጠራል! ይሄን የሚሉ መሰል
አፍሪካውያን መሪዎች ካሉ ንገርልን፡፡ በሽተኞች! ብለህ ስደብልን!
ከጀማይካውያን እንኳን አይማሩም!
"በዚህ ዙሪያ ጃማይካውያንን በጣም አደንቃለሁ! ከፍተኛ የሆነ
የማንነት ቀውስ ውስጥ መግባት የነበረባቸው፣ በሽታው ከባድና
ዘላቂ ሆኖ ሊንጎባቸውና አንድ ባንድ እየመዘመዘ ሊፈጃቸው
ይችሉ የነበሩ ህዝቦች ጃማይካውያን ናቸው!
"እናንተስ መቸም ታሪክ፣ ባህል፣ ሐይማኖት፣ ባይኖራችሁም፣
ቢያንስ ቦታችሁን ታውቃላችሁ፡፡ አባት አያታችሁ የትኛው ዋሻ
ላይ ይኖሩ እንደነበር ታውቃላችሁ፡፡ ምክንያቱም የቀድሞው
ቦታችሁ ዛሬም ድረስ ሰላለና በአዳዲስ ስያሜ ተክልሎ ራሱን
የቻለ አገር ሆኖ ስለሚገኝ፣እዚያ አካባቢ የተገኛችሁ መሆኑን
ትገነዘባላችሁ፡፡
"እኛ የአፍሪካ አገሮችን በጂኦግራፊ ጥበብ እያካለልን የየራሳችንን
ስያሜ እየሰጠን ነው አህጉራቱን ያዋቀርናት፡፡ የቀድሞ ባህላዊ
ስሞች ዛሬ የሉም፡፡ እኛ ደግሞ ገና ስም ከማውጣችን በፊት ነው
ባሮችን ከየቦታው ማጋዝ የጀመርነው፡፡
"ለምሳሌ አንድ ጥቁር ዳጎንባዊ ነኝ ሊል አይችልም፡፡ ጋናዊ ነኝ
ቢል የአሁኗ ጋና ውስጥ ማለቱ ነው፡፡ መጀመሪያ ጎልድ ኩዌስት
ከዚያ ጋና ያልናት እኛ ነን፡፡ ስለዚህ ጋና ጋና ከመሆኗ በፊት
የነበራትን ዳንጎምባ የሚል ስያሜ እንዲያዘች የተጋዘ ባሪያ፣
ከነፃነት በኋላ ተመለስ ቢባል የት ይሄዳል? የትም ሊሄድ
አይችልም! ምክንያቱም ዳንጎምባ ሲባል፣ የአሁኗን ጋና ይዞ፣
ሞዛምቢክን አካልሎ ደቡብ አፍሪካን ይዞ...ሰፊ ጫካን የሚያካትት
ቦታ ስለሆነ መሄድም ማወቅም አይችልም! ከደቡብ አፍሪካ ይሁን
ከምእራብ አፍሪካ ከየት እንደመጡም አያውቁም፡፡ እንዲህ አይነቱ
ስያሜ በራሱ የመጣው በኋላ ስለሆነ ማንም የሚያውቅ የለም፡፡
ዛሬ ጃማይካ በምትባል አገር የሚኖሩ ህዝቦች ታሪካቸው ይህ ነው!
በጣም አሳዛኝ ታሪክ ሲከሰት ያየነው በእነሱ ዙሪያ ነበር፡፡ እነሱ

ግን ፈጥነው ወደ መፍትሄው በመሄድ፣ፍቅር ብለው ጠቅለለው
አርፍ አሉ!
"ጃማይካውያን ስረ መሰረታቸው አፍሪካ መሆኑን ያውቃሉ፡፡ የት
ቢባሉ ግን አያውቁትም! ያኔ ከየአፍሪካ አገሩ ሴቶችንም
ወንዶችንም ለባርነት እየመለመልን እንወስድ ነበር፡፡
የምንወስዳቸው ጥቁር ህዝቦች ሲደክሙና ሲዝሉ፣ በመንገድ ብዛት
በረሃብ በበሽታ ሲጎዱ፣ እግራቸው ሲቆስል፣ በተለያዩ ምክንያት
አካላቸው ሲጎድልና መድረስ እንደማይችሉ ስናውቅ፣ በአሁኗ
ጃማይካ ደሴት ላይ እንዲ እቃ እየጣልናቸው ነበር የምንሄደው፡፡
ስንመለስ አገግሞ ድኖ ያገኘነው ካለ ይዘነው እንሄዳለን፡፡
ፊረንሳይም ከግዛቷ፣ ቤልጀምም ከግዛቷ፣ እኛም ከግዛታችን፣
ከተለያዩ የአፍሪካ አገራት ወደ መርከብ ስንጭናቸው ደህና
እጃቸው የተቆረጠ፣ እግራቸው ቆስሎ መራመድ ሲያቅታቸው፣
ከተጫኑ በኋላ የተለያየ ችግር እንዳለባቸው ዘግይተን ስናውቅና
አካለ ስንኩል መሆናቸው ሲገባን፣ እንደማይጠቅሙን ስንረዳ
የምንጥለብት የቅኝ ግዛቶችና የባሪያ አጋገች የጋራ ቦታ የአሁኗ
ጃማይካ ነበረች፡፡ የአካለ ስንኩላን ባሮች መጣያ ገንዳ!
"በዚያ ሁኔታ ሆነው እዚያው እያገገሙ፣ እየተጋቡ፣ እየተዋለዱ፣
ኑሯቸውን ቀጠሉ፡፡ ብዙ ብዙ ታሪክ አለፈ፣ነፃነት መጣ፡፡ ነፃነት
ሲመጣ ግን የት መሄድ ይችላሉ? ረጅም ዓመታት አልፏል፣
ጫካቸው ተመንጥሮ ከተማ ሆኗል፡፡ የቀድሞ ስሞች ተሽረው በሌላ
ተተይረዋል፡፡ ከደቡብ ይምጡ ከሰሜን እያውቁም!
"ታናሽ ወንድም አውሮፓ፣ ታላቅ እህት አሜሪካ፣ ታላቅ ወንድም
ጃማይካ፣ በቃ ተዘባርቋል! አባት፣ እናት፣ አያት፣ የሚባል ነገር
የለም! መመለስ አይቻልም! ሙሉ በሙሉ ማንነት የሚባል ነገር
ሳይኖራቸው በአዲስ አገር፣ አዲስ ሕይወት፣ አዲስ ታሪክ፣ አዲስ
ማንነት፣ አዲስ ሐይማኖት፣ አዲስ ትንቢተኛ፣ አዲስ መዝሙር፣
አዲስ ባህል፣ ፈጥረው፣ ስለ ፍቅር ብቻ እያዜሙ ራሳቸውን
አሳምነው ችለውት መኖር ቻሉ!
"ጃ ማን፣ ያ ማን፣ ፒስ ማን፣ እያሉ ራሳቸውን ማረጋጋት ቻሉ፡፡
ስለ ዓለም አቀፍ ፍቅር የሚያትቱ ሬጌ ሙዚቃቸውን እየሰሙ፣
ጥያቄያቸውን እያዳፈኑ፣ ሰላማቸውን ለማግኘት ሞከሩ፡፡ እንዲህ

"ዋናው ነገር ከማንነት ቀውስ በሽታ ፈጥነው መዳን መቻላቸው ነው። መፍትሄውን በጊዜ ማወቃቸውና ተግባራዊ እርምጃ በጋራ ወስደው ጠፍተው ከመቅረት መዳናቸው ነው።

"በእኔ ማነኝ ጥያቄ ተብሰልስለው፣ በእኔነት ተነስተው፣ በማንነት ቀውስ ተበጥብጠው፣ ሊላውን ጥቁር ህዝብም አለመበጥበጣቸው ነው! በዝቅተኝነት ስሜት ተረብሸው ሌላውን አለመረበሻቸው ነው! የዝቅተኝነት ስሜት እየተሰማቸው በስነ ልቦና ቀውስ ታውረው፣ በየደቂቃው በየሰዓቱ ዝቅ ያሉ እየመሰላቸው፣ ከፍ ከፍ ለማለት የሚጣጣሩ ከንቱዎች ሆነው አለመግኘታቸው ነው!

"ዛሬ ሙሉ በራስ መተማመን ያላቸው ጥቁር ህዝቦች እነሱ ናቸው! ዘና ፈታ ያሉ ናቸው። ያ ማን፣ ጃ ማን፣ ፒስ ማን፣ ይላሉ አንጂ እንደ ብዙዎች አፍሪካውያን፣ "እናንተ እኮ ድሮ.....አህህህ..." እያሉ ጥርስ አይነክሱም! ቁና እንዲሉ ያደረጋቸው ደግሞ የበሽታውን ፍቱን መድሃኒት በጊዜ ስላገኙ ነው። አንዴ ይዘውታል። ያንበታበታል። ስለ ፍቅር የሚያወራን ደክትሪን መረጠዋል። አይገርማችሁም? ቀውሰው መገኘት የነበረባቸው እነሱ ሆነው ሳለ፣ ነገር ግን በተቃራኒው እናንተ ብሳችሁ ተገኛችሁ! ለምን መዳን ስለማትፈልጉና ስለታወራችሁ!

"ዘሪያቸ የሚኖሩ የፖለቲከኞቸው የፖለቲካም የሐይማኖትም ጥምር ፍልስፍና አንግበ ትንሺተኛ ሆኖ ተነሳ። ከአፍሪካ ነፃ ንጉስ ይነሳል፣ አፍሪካውያንን ነፃ ያወጣል፣አምላካችን አልተወንም፣ ነብይ አፍሪካ ይመልሳሉ፣ ቅኝ ገዥዎቻችን ከዚህ ጠፍተ ተሚሄዱቸው ይቆጠበሉ፣ የሙ ልጅ ዘፍ አንድ ነው፣ ደሀ ችሮር የፖለቲካ ችግርና የዘሪአዊውያን የቅኝ ግዛት ፍልስፍና ያመጣው ነውና አይተርፈም፣ አደጠችሁ..... ሚለት ጀመረ። አሳን ተቀብለው በጊዜ የመዚደ መሰሪያ የትንሺተኞቸውን ታሪክ ዘዘፈን ሚዜም ጀመሩ። ዘዘነት ዘለው አዜሙ....አደል ቀጠሉ። ሁሉም አልፎ ነፃ ሆነ። ዘፈሪከ ዓዋሮቸው ተገኙ። አደል ቀጠሉ። ሁሉም አልፎ ታቦ። ደሀን የታሪክ ዓዋሮቸው የኢትዮጲያው ንጉስ ነፃ ሆኖ አያገኛሙ አል ኃይለሰላሴን የትንሺተኞቸው ዘዘሙ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር ተቀብሉ። ይሰማቹ አይባላቹ ያ አይጸለም ቀሙ ነገር።

በጊዜ ሽክፍ ማለትና ራስን አስከመጨረሻው ለዘለቄታው ማላመን መቻልም መፍትሄ ሆኖ እንደሚገኝ ከእነሱ መማር ትችላላችሁ።

"ሌላ ምንም ምርጫ እንደሌለ ያውቃሉ። የድርው አስቀያሚ ፖለቲካ እንዳይደገም በመከላከል ቁስላቸውን እያከሙ፣ ሰለ ፍቅር እያዜሙ ቁጠሉ።

"ወደ በቀል ወደ ስድብ እንኳን አላመሩም። ፣ወደ ቀድሞው ስርዓት እንዳንመለስ ስለ ነፃነትና ስለ ፍቅር ብቻ እናውራ፣፣ በሚል ፍልስፍና ተመስነው ዛሬ ከእነ ችግራቸውም ቢሆን ከለላው ጥቁር ህዝብ እጅግ የተሻለና ጥሩ የሚባል ደረጃ ላይ መድረስ ቻሉ። ችግራቸው ያው የሌላው ጥቁር ህዝብም ዘንድ ያለ ችግር ነው። ሀሽሽ ነው። ምንም ይሁን ግን ከዚህ ከማንነት ቀውስ በሽታ ወጻያው ተፈውሰው ደነው አሁን ላይ በደንብ አግግመው ይገኛሉ። ይህ አሳዛኝ ታሪክ ነው! ምንም አይነት ማንነት የሌለበት አሳዛኝ ታሪክ! የአባታቸውን ስም ጠርተው የአያታቸውን አይጸጉሙም! ከዚያ በኋላ ግን አያስቀጠሉ መሄድ ቻሉ።

"ያን ቁስል ለማከም የሚያስችላቸውን መድሃኒት ፍለጋ ወደ ፖለቲካ አይዶለም የሄዱት። ወደ ሐይማኖት ነው! ወደ ይቅር ባይነት ነው!

"ማህበሌ የሚባል ፖለቲካቸው የፖለቲካም የሐይማኖትም ጥምር ፍልስፍና አንግበ ትንሺተኛ ሆኖ ተነሳ። ፣ከአፍሪካ ነፃ ንጉስ ይነሳል፣ አፍሪካውያንን ነፃ ያወጣል፣አምላካችን አልተወንም፣ ነብይ አፍሪካ ይመልሳሉ፣ ቅኝ ገዥዎቻችን ከዚህ ጠፍተ ተሚሄዱቸው ይቆጠበሉ፣ የሙ ልጅ ዘፍ አንድ ነው፣ ደሀ ችሮር የፖለቲካ ችግርና የዘሪአዊውያን የቅኝ ግዛት ፍልስፍና ያመጣው ነውና አይተርፈም፣ አደጠችሁ..... ሚለት ጀመረ። አሳን ተቀብለው በጊዜ የመዚደ መሰሪያ የትንሺተኞቸውን ታሪክ ዘዘፈን ሚዜም ጀመሩ። ዘዘነት ዘለው አዜሙ....አደል ቀጠሉ። ሁሉም አልፎ ነፃ ሆነ። ዘፈሪከ ዓዋሮቸው ተገኙ። አደል ቀጠሉ። ሁሉም አልፎ ታቦ። ደሀን የታሪክ ዓዋሮቸው የኢትዮጲያው ንጉስ ነፃ ሆኖ አያገኛሙ አል ኃይለሰላሴን የትንሺተኞቸው ዘዘሙ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር ተቀብሉ። ይሰማቹ አይባላቹ ያ አይጸለም ቀሙ ነገር።

ባህል፣ የሚደነቅ ማንነት፣ ረጅም ዘመን ያስቆጠረ ቀንድ እና ምናምን ነበረን አላሉም። እንዲህ እያሉ አልዋሸም። ውሸት ምንም ጥቅም እንደሌለው ገብቶዋቸዋል። በቃ ዋናው ፍቅር ነው አሉ! እነዚህ ሰዎች ሀሽሽ ቢያጨሱ፣ ጸጉራቸውን ቢያሳድጉ፣ ራሳቸውን በተለያየ ሱስ ቢደብቁ አይፈረድባቸውም።

"እንደ አውኖቹ አንዳንድ ኢትዮጵያውያን ንፁህ ለብሶ፣ ፀጉሩን ተስተካክሎ፣ ብሄር ከብሄር የሚያጋጭ ስድብ በቱሊሺኞን ከማሰራጨትና የቀድሞ አባቶቹን ከመሳደብ፣ እንደ እነሱ ፀጉርን ጠቅልሎ ሀሽሽ እያጨሱ በፍቅር መኖር መቻል እጅግ የተሻለ ነው።

"በዘረኝነትና በእኔነት ከመስከር በሀሽሽ መስከር የተሻለ ነው። በጉዳት ደረጃም ብንሄድ ከሀሽሽ ጉዳት የበለጠ ከባድ ጉዳት የሚያደርሰው የዘረኝነት ስካር ነው! የእኔነት ስካር ነው! እኔነት ስግብግብነት ነው! ጥቁር አፍሪካውያን ከእነሱ እንኳን አትማሩም!

"እዚህ ደረጃ ደርሳችሁ እኩል ከሃያል አገር ጋር እየተሳተፋችሁ እንኳን ከእኔነት አለመውጣት፣ ከበታችነት ስሜት አለመላቀቅ፣ የሚያኮራ ባህልና ሐይማኖቱን፣ ፊደልና ታሪኩን በግድ እንደተነጠቀ ህዝብ ሆኖና መስሎ መቅረብ፣ መቆጨትና መፀፀት ምን ማለት ነው? ማንን ለመዋሸት ነው? ምንስ ለማትረፍ ነው? ምን ካሳ ለማግኘት ነው? የሚሉ በርካታ ጥያቄዎችን የሚፈጥሩ አናዳጅ ጥያቄ ስላነሳህ ነው ብዙ ለማለት የተገደድኩት! ግልፅ ነው ወይ ደቡብ አፍሪካ?"

"እምን ግልፅ ነው ንግስት ሆይ፣መታረም አለብን። ያሉት ሁሉ ልክ ነው። ሁላችንም ጥቁሮች የተመሳሳይ በሽታ ሰለባዎች መሆናችን በደንብ የገባኝ ዛሬ ነው። አመሰግናለሁ ንግስት ሆይ።" በማለት፣ ከዚህ ርዕስ ቶሎ እንዲወጡ የሚማፀን ቃና ባለው ድምፀት አመኑና ተገላገሉ።

"ጎበዝ! እንዲህ ጥፋትን በጊዜ ማመን ብዙ ትርፍ አለው። ጊዜህን ቆጥበህ ለተጣይ ስራ ለመዘጋጀት ይረዳል። ከራስም ከተፈጥሮም ጋር ተጋጭቶ እድሜ ልክ እየተብሰለሰሉ ወጉር እየነፉ ከመኖር ያድናል። ዕውነትን መቀበል ብዙ ትርፍ አለው!ክብር ለልዑላችን!"

"ተጥል" አሉ ወደ ላውዴ ዓረቢያው መሪ እየጠቆሙ።

"አመሰግናለሁ ንግስት ሆይ ክብር ለልዑላችን። እኔ... በየደቂቃው፣ በየሰዓቱ፣ በየቀኑ፣ በየሳምንቱ፣ በየወሩ የሚከነክነኝ አንድ ጥያቄ ነው ንግስት ሆይ! ሐይማኖትን የማፈራረሱ ጉዳይ!

"እ..... ክቡርነትዎ እንደገለፁት ለአፈፃፀማችን የሚረዳው ዋናው ነገር የዚያን ህዝብ የጠበቀ ሐይማኖትና እምነቱን ማንኮታኮት መቻል ነው። ይህ ይሁን እንጂ ከተባለ ደግሞ ቀድም ሲል ያሳዩንን እነዚያን በአስር ሺዎች የሚቆጠሩ ለበላይ አካሉ ክብርና የአምልኮ ተግባር ሲባል የተገነቡ እጅግ አስደማሚ የሆኑ፣ በከበሩ ጌጣጌጦች የተንቆጠቆጡ፣ ክቡርነትዎ ገዳማት፣ አድባራትና አብያተ-ክርስቲያናት ብለው የገለፁዋቸውን የሐይማኖት ተቋማትና ቤተመቅደሶች የማፍረስ ሊኖርብን ነው። መቼም እነዚህ ቦታዎች ተጠብቀውና ተከብረው እስካሉ ድረስ፣ ወይም አሁን ባሉበት ሁኔታ እስከቀጠሉ ድረስ፣ህዝቡም ሐይማኖታዊ ሥርዓቱን መፈፀሙን መቀጠሉ አይቀርም። የእምነትና የሐይማኖት ተቋማቱ ሳይፈራርሱ ደግሞ በቀላሉ ምዕመኑን ወደ ልዑላችን ማምጣትና ወደ ራሳችን ክብ ማስገባት ሊከብድ ይችላል። ታዲያ እንዴት ነው ልናፈርስ የምንችለው? የሚል ጥያቄ በውስጤ ይመጣል። ስለዚህ የዚህን ዘዴ ቁርጥ አድርገው እንዲመልሱልን እፈልጋለሁ።

ሌላው ከዚህ ጋር አያይዤ ማንሳት የምፈልገው ጥያቄ፣ "የሐይማኖተኞቹን እምነት መሸርሸር፣ የሐይማኖታዊ ተቋማቱን ንብረት ከእነ ምዕመኑ መውረስና፣ የልዑላችን ንብረት ማድረግ፣ ብለው በገለፁት ዙሪያ ነው። በምን አይነት ዘዴ ነው ከእነ ውስጥ ቁሳቁሳቸው መውረስና የልዑላችን ንብረት ወደ ማድረግ የምናመጣቸው? ይህ ጥያቄ የዚያችን አገር ሐይማኖትና ሐይማተኞች በሚመለከት ነው። እና ዘዴውን ቢጠቁሙን።

"ሌላ በጣም የሚያስጨንቀኝ ተመሳሳይ ነገርም አለ። አሁን የእኛ ህዝብ ቁርዓንን ጣል ብንለው እይጥልም። የሌላው ዓለም ህዝብም መጽሐፍ ቅዱሱን ጣል ቢባል እይጥልም። እንዲያውም.... የዚህ ዘዴ ምን ሊሆን ይችላል? የሐይማኖት ተቋማቱስ እሽ ይፍረሱ እንበል፣ ነገር ግን የሐይማኖቱ መጽሐፍ እስካለ ድረስ ምዕመኑ የእምነት ተቋሙ ቢፈርስበት እንኳን በአማኝነቱ መቀጠሉ አይቀርም። መላው የዓለም ህዝብ ደግሞ በልዑላችን ስር ነው መሆን ያለበት። እና.....ግራ ግቡት ይለኝ ጀምሯል፣ንግስት ሆይ!

"ያ እንዳለ ሆኖ ግን በዋናነት ማለት የፈለግሁት፣የሐይማኖት ተቋማቱ ባለበት እንዳሉ ሆነው፣ የውስጥ ይዘቱን ሙሉ በሙሉ በእኛና በልዑላችን ታማኝ አገልጋዮች የመተካት ስራ እንሰራለን ነው። ቀሳውስትና ጳጳሳቱን፣ ዲያቆናትና ዘማሪውን፣ ፓስተርና ወንጌላዊውን፣ ሽህ እና ውዝዋዙን፣ አንድ ላይቀር ቀስ በቀስ እያፈራረሱ /እያባረሩ/ በእኛ ሰዎች የመተካት ሂደት በሁሉም ቦታዎች ተጠናክሮ ይቀጥላል ነው።

"በመጨረሻ ሙሉ በሙሉ ከእነ ውስጡ ንብረቱ፣ ከእነ ቦታውና ከእነ ማንቡ፣ የእኛ የግላችን የሚሆንበትን ሁኔታ ማመቻቸት ማለቱ ነው።

"ሐይማኖተኛው ቅዱሳን እያለ የሚጠራቸውን ጨምሮ፣ ከእምነት ተቋማት የጥበቃ ሠራተኞች እስከ ግንዘብ ያዥ ሁሉንም በልዑላችን ታማኞች እንተካለን። ሙሉ በሙሉ ተቋማቱ በእኛ ጠራርገን አስወጥተን በራሳችን ሰዎች በመመላት ነው፣ ከእነ ህንፃ ከነቁሳቁሱ የምንወርሳቸው። ከዚያ በኋላ የየቤተ-መቅደሱ የውስጥ ክፍል በልዑላችን ዓርማ እያሸበረቀ ይቀጥላል። ይህ እስኪሆ ድረስ ግን ውጪ በቀድሞው ይዞታ እንዳለ ሆኖና መስሎ እየታዩ፣ ያለመሳት የተዘጋጀ ምዕመንም በተገቢው መንገድ ሐይማኖታዊ ሥርዓቱን እየፈፀመ ቀጥሎ የሚቆይ ይሆናል።

"በስተመጨረሻ ያለ አንዳች ተቀናቃኝ መላው ቤተ መቅደስ የእኛና የልዑላችን እንዲሁም የልዑላችን ተከታዮች የአምልኮ ስፍራ ብቻ ወደ መሆን ይሸጋገራል። በሂደት ትምህርቶች ይለወጣሉ።

"በዚህ አይነት አካሄድ ሙሉ በሙሉ መውረስ ማለታችን እንጂ፣ በአንድ ጊዜ ምዕመኑን በትነን፣ ቤቱን አፍርሰን፣ ወርቆቻቸውን ዘርፈን፣... ለማለት አይደለም። ሁሉንም አንድ በአንድ ወደ እኛ የመገልበጥ ስራ ማለታችን ነው።

"በዚህ አይነቱ ዋንቃቄ በተሞላበት አካሄድ፣ ቅድም እንዳልኩት የምንብ አይነታቸውን ሳይቀር ለሌላ ግልጋሎት ልናውለው እንዳሰብነው ሁሉ፣ በአገሪቱ በሚገኙ በየ እምነት ተቋማቱ ውስጥ ያሉና፣ ምዕመኑ እንደ ውድ ንብረት የሚጠብቃቸውንና የሚንከባከባቸውን ንብረቶች ሁሉ ጠቅልሎ ወስዶ ለሌላ

ወይ እንደ ሰሚን ኮሪያ በየአገራችን ሐይማኖትን በህግ አንከለክል ነገር! ምናልባት በዚህ በኩል በክቡርነትዎና በቤተሰብዎ በኩል ቀድሞ የታቀደ ወይ የተጀመረ ስራ ይኖር ይሆን? አሰቲ በደንብ አፍታትተው ይንገሩን ንግስት ሆይ፣አመሰግናለሁ።" በማለት የንጉሩ ውል እንደጠፋባቸውና "ቄ.....ንቅ እንዳላቸው በሰውነት እንቅስቃሴም፣ በፊት ገፅታም፣ እያረጋገጡ ጠየቁ።

ሲያደምጡ ቆይና ምላሽ ወደ መስጠት አመሩ።

"እናንተ ዓረቦች ስትባሉ ማፍረስ የሚለውን ቃል የምታውቁት አገር በማፍረስ ትርጓሜ ብቻ ስለሆነ ይህን ጥያቄ በማንሳትህ አልደነቅም። የእናንተ ማፍረስና የእኛ ማፍረስ ግን በመጠኑ ይለያያል። ሆ.....ይሄኮ ፖለቲካዊ አጀንዳ አይደለም። አፍርሰን እንደገና ለመልሶ ግንባታ በጀት የምንመድብበት አይነት አካሄድ አታስመስሉው።

"እነዚህን የእምነት ቦታዎች ማፍረስ ሰንል፣ ህንፃና ግንቡን ማፈራረስ ማለታችን አይደለም። መዝረፍ ሰንልም ተደብቀን እየገባን ታቦታትንና ንዋዩ ቅዱሳትን አንድ በአንድ መሰረቅ ማለታችን አይደለም። የአገላለፅ ስህተት ከሆነ ይቅርታ ልጠይቅና በትክክለኛው ቃል ልግለፀው። ሙሉ ለሙሉ መውረስ ማለቱ ነው። ግንቡ ቢቆይ የኛው ነውና ይጠቅመናል እንጂ አይጎዳንም።

"እርግጥ ነው አንዳንዶቹ ቤተ-ክርስቲያን እና ገዳማት ያለባቸው ቦታዎች ለመንፈሳዊ ጦርነቱ ወሳኝ ቦታ ከሆኑና ካሰፈለጉን ያለ ርህራሄ ልናፈርስ እንችላለን። በቀጥታም ባይሆን በተዛዋሪ በራሳቸው ስህተት የነደደ፣ የተቃጠለ፣ እያስመሰልን ልናወድም እንችላለን።

"እውድመንም፣በቃጠሎው ምክንያትም የተሰማንን ሃዘን እየገለፅን፣ በወቅት ሰሚት ውስጥ የተዘፈቅን እያስመሰልን፣ ለመልሶ ግንባታ የሚሆን በሚል ሚሊዮን ዶላሮችን ልንለግስ እንችላለን። እኔም አያፍሩም ‹‹የእርዳታ እጃችሁን ዘርጉልን›› ማለታቸው አይቀርምና፣ግንዘቡንም ሰጥተን፣ ‹‹ይሄን የመሰለ ደብር በዚህ ጠባብና ለአደጋ በተጋለጠ ቦታ እንዲቆ ግንባችሁ?›› በሚል፣ ‹‹ብሌላ ቦተሻለና ሰፋ ባለ ቦታ እጅግ ዘመናዊ ህንፃ በንሃስ ግንቡበት›› እያልን በሚሊዮን የሚቆጠር ዶላር እየለገስን፣ ምትክ ቦታ እያሰጠን፣ ልናሰልቅቃቸው እንችላለን።

ለልዑላችን ዓላማና ተግባር የሚውሉበትን ሁኔታ ማመቻቸት
የምንችልበት ደረጃ እንደርሳለን። ሂደቱ ጊዜ ወሳጅ ቢመሰልም፣
በእኛ፣ በእናንተ፣ እንዲሁም በሌሎች አባላቶቻችንና የልዑላችን
ዓላማ አሰፈፃሚዎች የጋራ ርብርብ በሰከነ የሚጠናቀቅ ነው
የሚሆነው።

"ይህ የመጨረሻው መዳረሻችን ሲሆን፣ ወደ እዚህ ደረጃ
ከመሸጋገራችን በፊት ግን በርካታና ዘርፈ ብዙ የሆኑ ቅድመ
ሰራዎች ይኖራሉ።

"በእነዚህ ነጥቦች ዙሪያ ከእኛ የሚጠበቀው ፖሊሲዎችን መቅረፅ፣
ለአፈፃፀምና ለአተገባበር ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠር ነውና ያንን
ሰራ እየሰራን ነው።

"በኛ በኩል በህዝቡ ዘንድ ከፍተኛ ከበሬታ ያላቸውን የእምነት
ተቋማት እንዴት ማንኮታኮት እንዳለብንና በምን መልኩ ያን
ማድረግ እንደምንችል ቀድመን የተዘጋጀንባቸውና ቀድመን
የጨረስናቸው በርካታ ሰራዎች አሉ። እነዚያን ሰራዎች እንዴትና
በምን መልኩ እንደሰራናቸው በሰተመጨረሻ አሰረዳለሁ። እነሱ
እንዳሉ ሆነው ግን፣ በተግያነት ከእናንተ የሚጠበቁ ዘርፈ ብዙ
ሰራዎች ይኖራሉና፣ ከልዩ ልዩ የመሸርሸሪያ፣ የማደናገሪያና
የማፍረሻ ዘዴዎቻቸው ውስጥ ለጥቅማ ያህል ጥቂቶቹን
ለመጠቃቀስ ልሞክር።

"እነዚህን የእምነት ተቋማት ሰናንኮታኩት እንዴው በጥላቻና
በግልፍተኝነት አሊያም በማናለብኝነት ደርሰን በማተራመስ
አይደለም። መጀመሪያ የየሐይማኖቱን መሪዎች ሞራንቅላት
ማጠብ ያስፈልጋል። ተ

"ቀባይነትና ተሰሚነት ያላቸውን የየሐይማኖቱን አመራሮች
ከጳጳሳት አበስ ቀሳውስት፣ ከዲያቆናት አበስ ዘማሪ ሁሉንም ወደ
አሰደናቂ የቴክኖሎጂ ከተሞች እየጋበዙ፣ ናሳን የመሳሰሉ
ተቋማትን እያስጎበኙ፣ «የሰው ልጅ አምላኩ በሰጠው አእምሮ
ተጠቅሞ እዚህ ደረጃ ደርሷል» እያላችሁ ማሳየትና ማስደመም
ሲኖርባችሁ ይችላል። ዓለም አቀፍ የሐይማኖት ኮንፍረንስ
እያላችሁ መጥራት፣ እየጠራችሁ ማሳየት፣ የክብር እንግዳ በሚል
እነሱ በሚወዱት የግብዣ አይነት እየጋበዛችሁ፣ ወደ አውሮፓና
ወደ አሜሪካ እየጠራችሁ አሰንብጿቸው፣ አሰደምሚቸው። ጥቂት
ጥቂት ዶላር እየሰጣችሁም የሁለቱን አገራት የሐይማኖታዊ

ግንኙነት ለማሻሻል... እያላችሁ በእንክብካቤ ቅረቧቸው፣ ድንቅ
የተባሉ ጥበቦችን እያሳችሁ፣ እያስዳሰሳችሁ፣ አስደንቋቸው! ያኔ
እነሱ ተደንቀው ሂደው ሐይማኖተኛውን እንዴት እንደሚያስደንቁ
ታያላችሁ። ዓለም ስለደረሰበት ደረጃና ስለ እነሱ መደንዘዝ
ያዩትን ነገር እንደ ምሳሌ እየጠቀሱ፣ ማደግና መሰልጠን ምንም
ማለት እንዳልሆነና ይልቁንም በአምላካቸው የሚደገፍ መሆኑን
ከመጽሐፋቸው ጥቅስ እየጠቀሱ ያስተምሩላችኋል።

"አውሬ አውሬውን መልምላችሁ በልዑላችን ስጦታ በገንዘብና
በቴክኖሎጂ እያማለላችሁ መንጠቅና፣ አእምሯቸው ውስጥ ያለውን
የበላይ አካሉን ቃል እየጠረጋችሁ እያወጣችሁ በአዳዲስ
እውቀቶች መተካት ከቻላችሁ ቀጣይ ስራችሁን ታቀላላችሁ።
ይግሞም አስታውሱ ሁሉም በገንዘብ ለመግዛት ዝግጁ ናቸውና ይህ
ከባድ ስራ አይሆንም።

"ሌላው፣ የእምነት ተቋማቱን በአንድ ጊዜ ሳይሆን በሂደት ከጨዋታ
ውጪ ለማድረግ ቀላሉ ቅድመ ስራ፣ ምዕመኑ ወደየ እምነት
ተቋማቱ በመሄድ የሚያገኘውን ትምህርትም ሆነ ሌላ የአምልኮ
ተግባር በየቤቱ በቀላሉ እንዲያገኘው ማድረግ መቻል ነው።
ሐይማኖቱን ከእነ ሰባኪው ከእነ ስብከቱ በየ ቤቱ ማድረስ መቻል
ተቋማቱን ለመንጠቅና ለመውረስ የሚደረገውን ጉዞ ከማሳጠር
አልፎ፣ የእምነት ተቋማቱን አስፈላጊነት እርባና ቢስ ለማድረግም
ይረዳል።

"ይህም በልዑላችን የቴክኖሎጂ ውጤት አማካኝነት በቀላሉ
መሰራት የሚችል ስራ ነው። ሐይማኖታዊ ትምህርቱን ቤት
ለቤት ማድረስ! የተቋማቱን አላስፈላጊነት በተጨባጭ ማስገንዘብ!
በሂደትና በልምምድ የእምነት ተቋማቱን እሴት አልባ ማድረግ!
ቀስ በቀስ የሃይማኖት አባቶችን አላስፈላጊነት ማረጋገጥ! ከዚያ
በኋላ የቤት ለቤት ትምህርቱን መበረዝ! እየተባለ የሚቀጥል ስራ
ነው። ለዚህም በርከት ያለ ገንዘብ መድቦ መንቀሳቀስ
ያስፈልጋል።

"ማንኛውም ተራ ሰው በቀላሉ ሐይማኖታዊ የቴሌቪዥንና መሰል
ቻናሎችን መክፈት እንዲችልና ያሻውን አይነት ፕሮግራም
ማቅረብ እንዲችል ማድረግን ያካትታል። በተመሳሳይ ሐይማኖት
ተመሳሳይ ትምህርት ሲሰጥ ከቆየ በኋላ፣ ያንዱን ትምህርት
ከአንዱ እያጋጨ የሚያስተምሩ የሐይማኖት መሪዎችን በቀላሉ

ዋናዎቹ ኩባንያዎች ናቸው!" በማለት፣ በሰፊው የማድማዳ ላይ
ዘመናዊ ስክሪን ውስጥ እንደ መንኮራኩር የሚወነጨፉና አይነትና
ቅርፃቸውን እንዲህ ነው ብሎ ለመግለፅ የሚቸግሩ እጅግ ፈጣንና
ዘመናዊ ተወንጫፊ ተሽከርካሪዎችን በብርሃን ፍጥነት ጅው፣ጅው፣
ውር፣ ውር፣ ሲሉ አሳዩዋቸው፡፡
በዚህ አስገራሚ ትዕይንትም በሃያል አገራት መሪዎች በኩል
የመገረም ገፅታ ሲነበብ፣ በባለ ሃብቱና በሌሎች ተሰብሳቢዎች
በኩል ግን የደስታ ፈገግታ ነበርና የሚስተዋለው ከፊሎቹ
ተሰብሳቢዎች ለእነዚህ ምርቶች እንግዳ አለመሆናቸውን ለመረዳት
ተቻለ፡፡
ረዘም ላሉ ደቂቃዎች እነዚህን የቮልስ ዋገን እና የሃዮንዳይ አርማ
ያላቸው ተወንጫፊ አውቶሞቢሎች ሲያሳዩዋቸውም፣ አዳራሹ
ፈጥኖ ባላቋረጠ የአድናቆት ጭብጨባ ደመቀ፡፡
ጭብጨባው ቶሎ እንደማያቋርጥ የተረዱት አሮጊቷ የእንግሊዝ
ንግስት፣ በጭብጨባው መሃል ጣልቃ ገብተው ገለፃቸውን ቀጠሉ፡፡
ዋዓለም ህዝብ በእነ ናሳ ይፋዊ ስራ ይደነቃል፡፡ ከእነሱ በላይ
ብቃት ያላቸውን ካምፓኒዎች በቀድሞ ስራቸው ብቻ
እንዲታወቁና፣ በዚያው ተወስነው እሱኑ በሞዴል እያሻሻሉ
ስራቸውን ቀጥለው ያሉ መስለው እንዲቆዩ አድርገን እንጂ፣
ብዙዎች የዚህ ህብረትና የልዑላችን ዓላማ ደጋፊና አስፈፃሚ
ናቸውና ከፒራሚዳችን በተቀዳና ከፒራሚድ ቤተሰቦቻችን ጋር
በተደረገ የልምድ ልውውጥ አማካኝነት የስፔስ ሳይንስና ቴክኖሎጂ
ውስጥ የተካተቱ! አስገራሚ ደረጃ ላይ የደረሱ! የወደፊቱን
መንፈሳዊ ጦርነት ለማገዝ የሚችሉ አስደናቂ አስደናቂ
ምርቶቻቸውን የዓለም ህዝብ ባላወቀበት ሁኔታ ማምረት የቻሉ
ናቸው!!
"ይህ እንግዲህ አንድ ተራና የተለመደ አውቶሞቢል አምራች
ኩባንያ እንደሆነ የሚታወቅ ድርጅት ሆኖ ነው እንዲህ
ያስገረማችሁ፡፡ እነ ናሳ «ብሚስጥር» የት ደረጃ እንደደረሱ
ብናሳያችሁ ደግሞ ውስጣችሁን አብርታችሁ ካልሆነ በቀር
ልትረዱት ስለማትችሉ እሱን እናቆየው፡፡ ለጊዜው ግን እነዚህን
ኩባንያዎች ተዋወቋቸው!"

አሉና፣ በኩራት ሁለት እጆቻቸውን በግብዣ መልክ ወደ ስክሪኑ
ዘርግተው እያሳዩ ፈገግ ብለው ቆመው ትእይንቱን አብረው
ሲከታተሉ ቆዩ፡፡
በእርግጥም ማንኛውም የዓለም ህዝብ እነዚህን የህዋ ላይ
ተሽከርካሪዎች ቢያይና በአንድ በቮልስ ዋገን ተሽከርካሪ አምራች
ኩባንያ የተፈበረኩ ናቸው ተብሎ ቢነገረው ፍፁም ዘመናዊና ረቂቅ
ከመሆናቸው የተነሳ ነገሩን ሊያምን አይችልም፡፡
በተለያየ ቅርፅና መጠን ተሰርተው ውር ውር የሚሉና በፍጥነት
እየተገለባበጡ ወዲያና ወዲህ የሚወነጨፉ አብረቅራቂ
ተሽከርካሪዎችን ሲያዩ ከቆዩ በኋላም፣ ሁሉም በአንድነት
ተነስተው ሞቅ ያለ የጋራ ጭብጨባቸውን አሰሙ፡፡
"ተቀመጡ ክቡራን! ተቀመጡ" ሲሉ ቀጠሉ፡፡
ተሰብሳቢዎቹ ግርም፣ ድንቅ፣ እንዳላቸው፣ ዓይናቸውን ርግብ
ሳያደርጉ ሰፊው ስክሪን ላይ እንደተከሉ በየወንበሮቻቸው
ተቀመጡ፡፡
"አምን! በምድር ላይ በሚኝዙ በዘመናዊ ተሽከርካሪ አምራች
ድርጅትነታቸው ብቻ ታውቀው፣ ሌላ ምርት ውስጥ ያልገቡ
አስመስለን ያቆየናቸውን እነዚህን ኩባንያዎች ነው ወደዚያች ሞኝ
አገር ቅርንጫፍ መስሪያ ቤታቸውን በመገጣጠም ሽፋን ቀድመው
እንዲከፍቱ የምንልከው!
"ሁሉም ዓለም አቀፍ ታዋቂነትን ባገኙ የንግድ ምልክቶቻቸውና
ስያሜዎቻቸው ተጠቅመው ወደዚያች አገር በተራ ሽፋን
ተግባራቸው ለመሰማራት የተዘጋጁ ድርጅቶች፣ ፋብሪካዎች፣
ካምፓኒዎች፣ ኩባንያዎችና ተቋማት የደረሱበት ሚስጥራዊ ደረጃ
አሁን ባሳየኋችሁና ቀጥየ በማሳያችሁ ምሳሌ መሰረት የሚገለፁ
ናቸው!
"የቆሙትም ለአንድ ዓላማ ነውና በየዘርፉ ተሰማርተው
የሚጠበቅባቸውን ስራ ከእናንተ ከሃያል አገራት መሪዎች ጋር
በጋራ ሆነው ይሰራሉ፡፡ ስራቸውና ስራችሁም ህጋዊ ነው!
"የዓለም ማህበረሰብ ከብረት፣ ከመዳብ፣ ከነሃስ፣ ከብር፣ ከወርቅ፣
ውጪ ምን ያውቃል? እርግጥ ሲባል ይሰማል፡፡ አልማዝ፣
ዳይመንድ፣ ፕላቲኒዬም፣ ሜርኩሪ፣ ሲባል ይሰማል፡፡ ውድ
ማዕድናት እንደሆኑም ሊያውቅ ይችላል፡፡ ለምን ጥቅም
እንደሚውሉ ግን አያውቅም፡፡ እርግጥ ያውቃል፣ እውቀቱ ግን

እየመሰመሉ መልዕክትን ማስተላለፍ መቻል፡፡ ይህ ሲሆን ምዕመ
ልክ እንደየ እምነት ተቋማቱ በየገዛ ቤቱ መፍረክረክና መፈረካከስ
ይጀምራል፡፡
"ግን ለትን እኛ በሳይንስና በቴክኖሎጂ ጥበብ እያስደመምን
በትጨባጭ ለውጦችና ጥቅሞች እያሳመንን፣ እያጠመቅን፣ ያመ
የተጠመቀ እንዲት እንደሚድን እያሳየን፣ መቀጠል የምንችልበትን
ሁኔታ ማመቻችት በሚል ያዙት፡፡
"እስታውሱ! ሁሉም የበላይ አካሉ ተከታይ የሆነ ሐይማኖተኛ
በሐይማኖቱ በኩል ስስ ነው፣ ስሜታዊ ነው፡፡ ስለዚህ በአንዲት
ታል አማካኝነት ሙሉ ምዕመኑን ማተራመስ በጣም ቀላሉ ስራ
ነው፡፡ ይህን ማድረግም ወቅቱ የሚጠይቀን አንዱና ዋናው ስራችን
ነውና፣በኛ በኩል እንደ አቅሙ በጀት ተመድቦለት ከየሐይማኖቱ
መሪዎች ውስጥ ታዋቂ ታዋቂ የሆኑና ተቀባይነት ያላቸው ሰዎች
ተመልምለው ተዘጋጅተዋል፡፡ የኛ ብቻ ግን በቂ አይደለም፡፡
በየአገራቱ የተናጠል ግንኙነት፣ በዓለማችን ባለ ሃብቶችና የጥበብ
ሰዎች ጠንካራ የጋራ ርብርብ ተጠናክሮ መቀጠል ያለበትና፣
አይነትና ዘርፉን አስፍቶ ሊሰራበት የሚገባ ወሳኝ ጉዳይ ነው፡፡
"እናም በቀጣዮቹ አስር ዓመታት እኛ ከስር ሆነን ድንቅ
የሆነችውን የልዑላችን የጦርነት ከተማ ስንገነባ፣ ከላይም የጦር
ካምፖቻችንን ስናቋቁም፣ እነሱ በየቤታቸው እንዳሉ ይፍረከረኩና
ከእምነትና ከሐይማኖት ውጪ እየሆኑ ይጠብቁናል፡፡
"ይህን ለማድረግም ለሁሉም ሐይማኖተኛ ህዝብ ሐይማኖታዊ
ትምህርት የሚሰጥባቸው አስር ሺ የቴሌቪዥን ጣቢያዎችን
ለመክፈት የሚያስችለንን ዝግጅት ጨርሰን ወደ ተግባር እየገባን
ነው፡፡
"የበላይ አካሉን የሐይማኖት መጽሀፍ በየ እጅ ስልኩ እንዲገኝ
አድርገን ዋናውን እናስጥለዋለን" ተብሎ ከዚህ ቀደም በጳጳሳችሁ
እንደተገለፀላችሁ አይነት አካሄድ መሆኑ ነው፡፡ ይህም
ሐይማኖትንና ሐይማኖተኛውን ማንኮታኮት ከሚቻልባቸው
ዘዴዎች ውስጥ አንዱ ነው፡፡
"ይህ ብቻ አይደለም፡፡ የተፈሩ፣ የታፈሩና የተከበሩ የተባሉ
ትልልቅ የሐይማኖት መሪዎች ይቀሩና፣ እሳት የላሱ የልዑላችንን
ጥበብ በቅዕበት የተሞሉ ሰዎች ድንገት ደርሰው የሐይማኖት
መምህራን ይሆናሉ፡፡ እነሱም በአስደናቂ እውቀታቸው አስደማሚ

የሆነ ሐይማኖታዊ ስብከታቸውን ቀጥለው ተቀባይነታቸውን
እያስፋፉ ይቆዩና፣ በሂደት ስለ ዩንቨርስ፣ ስለ ፕላኔቶችና ስለ
ምድር ትስስር እየተነተኑ ቆይተው፣ በስተመጨረሻ አሳማኝ በሆነ
መንገድ ትምህርቱን በቅዕበት መበረዝ የሚችሉበት ደረጃ ደርሰው፣
የአፍራሽ ግብረ-ሃይልነታቸውን ሚና ይወጣሉ! ሂደው ሂደው
መላውን ምዕመን የሚያስቱት እነዚህ እሳት የላሱ የልዑላችንን
ጥበብ ተሞልተው ዓለምን እስከ ማስደነቅ ደረጃ የሚደርሱ
ኢትዮጵያውያን ናቸውና የአገሩን ሰርዶ ባገሩ በሬ የሚሉትን
ብሂል በተግባር ያሳዩናል፡፡
"እነዚህ ከራሳቸው ዜጎች መልምለን እውቀት ሞልተን
የምንልካቸው ብላቴኖች ስራውን ሲጀምሩ፣ እነዚያ የቀድሞ
ታላላቅ የተባሉ የሐይማኖት አስተማሪዎች ራሳቸው በአስደናቂ
እውቀታቸው ተደንቀው፣ ራሳቸውን የሚንቁበት ደረጃ ደርሰው፣
እነሱን በማድነቅ ተግባር የተጠመዱ ከመሆን አልፈው፣ የእነሱን
ልክነት ማረጋገጥ ቋሚ ስራቸው ወደ ማድረግ ይሸጋገራሉ፡፡
"በርካታ ሐይማኖታዊ ነገሮችን መናድ፣ ማፈራረስ፣ መንጠቅና
መውረስ የምንችለው በቴክኖሎጂ ውጤቶች እየተካን ነውና የህዝቡ
ተግዳሮት እዚህ ግባ የሚሉት እንደማይሆን ከወዲሁ
ላረጋግጥላችሁ እፈልጋለሁ፡፡ ቴክኖሎጂ ሲባል ስማርት ፎን፣
ማኅበራዊ ድረ-ገፅ፣ ቴሌቪዥን ማለት አይደለም፡፡ በስተመጨረሻ
ቅዳሴ በሮቦቶች አማካኝነት ሊከናወን እንደሚችልም
እያሰባችሁ...!!
"በዚህ ዓይነት ሂደትና የጋራ ርብርብ ብዙ ስራዎች ይሰራሉ፡፡ከዚህ
ጋር የተያያዘው ሌላኛው ዋና ሥራ ጭንቅላት አጠባ የምንለው
ነው፡፡
"አንድ ነገር ብቻ በአእምሮና በልቦናቸው ይዘው እሱኑ ሲቀባበሉ
የመጡትን ኢትዮጵያውያን፣ ያን ያረጃ ያፈጀ እምነትና ፍልስፍና
ከአእምሯቸውና ከልቦናቸው እየፋቅን አውጥተን ጥለን፣ አጥበንና
ወልውለን የአንድ የልዑላችን እውቀትና ጥበብ ናፋቂ፣ ፈላጊና
ተገዥ፣ የማድረግ ኃላፊነትና ግዴታ የተጣለብን ነን፡፡ ስለሆነም
ለረዥም ጊዜ ሳይፀዳና ሳይወለወል ለአንድ ነገር ግልጋሎት ብቻ
ውሎ የቆየን ነገር ወይም ቁስ፣ እንደ አዲስ ማድረግ (ሪስቶር)
ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ አንድን ዘመናዊ ተንቀሳቃሽ የእጅ ስልክ
"ሣርድ ሪሴት" እንደምናደርገውና የሜንናቸው መተግበሪያዎች

በአንድ በዓለማዊ ህግ በተግባር ለውጦ በማሳየትና መሻር በመቻል ነው!

"አምን! ገንዘብና ቴክኖሎጂ፣ ፖለቲካና የሕግ የበላይነት፣ ዘመናዊ ትምህርትና የፕሮፓጋንዳ ማሰራጫ ሚዲያ እስካሉ ድረስ መላውን የዓለም ሕዝብ በቀላሉ ማጥመድና መጠቅለል ይቻላል ስንል በእርግጠኝነት ነው።

"እነዚህ ሁሉ ነገሮች ደግሞ የእኛና የልዑላችን ቋሚ ንብረቶች ናቸው። ዓለምን እንዳሻን የምንዛወርባቸውና ቀድመን ያዘጋጀን የተዘጋጁባቸው ወሳኝ ዘዴዎች!

"ከዚህ ከመካከለኛው ምስራቅ ሳልወጣ ይህን የምለውን ነገር የሚያጠናክር ሌላ ምሳሌ ልጨምርላችሁና የሐይማኖት መጻሕፍት ሀጋጆን እንዴት መናድ፣ እንዴት መሻርና መሸርሸር እንደሚቻል ማስረዳቱን ልቀጥል።

"የመጀመሪያው የመካከለኛው ምስራቅ ወይም የዓረቡ ዓለም የነዳጅ ዘይት ሐብት የተገኘው በእኛ አማካኝነት ነበር። በልጃችን በአሚሪካ በኩል ያቋቋምነው በውሃ ቁፋሮ ላይ የተሰማራ ስታንዳርድ ኦፍ ካሊፎርኒያ የተባለ ድርጅት በ1960ዎቹ የመጀመሪያ ዓመታት የመጀመሪያውን ቁፋሮ በባህሬን ጀመረ።

"የባህሬን ህዝብ የሚፈልገው ውሃ ነውና ቁፋሮውም ውሃ ፍለጋ ነበር። ብዙ ጥልቀት ተቆፈረ። ውሃ ግን የለም።

"ተብሎ ተብሎ በስተመጨረሻ የሰረኛው አለት ድንገት ተፈረከሰና የነዳጅ ዘይቱ ድፍድፍ ታየ። ይህ የነዳጅ ዘይት ድፍድፍ ሲገኝ የባህሬን ንጉስና ሕዝቡ ተበሳጩ። ውሃ ባለመገኘቱ አዘኑ። ተስፋ ቆርጠውም ድርጅቱን አገራቸውን ለቆ እንዲሄድ ወይም ያን ገደል ደፍኖ ሌሎች ቦታዎች ላይ የውሃ ቁፋሮውን እንዲቀጥል ተማፀኑት።

"በእርግጥ እኛ ዘመኑን እየጠበቅን እንጂ አካባቢውን በቅኝ ግዛት በያዝን ወቅት አጥንቱን ጨርሰን የነዳጅ ክምችት መኖሩን አውቀን ሆነ ብለን ነበር ድርጅቱን የላክነው። እንጂ ውሃ እንደሌለ ጠፍቶን አልነበረም። በመጨረሻ የድርጅቱ ሰዎች የባህሬትን ንጉስ ስለ ነዳጅ ዘይት ጥቅም ማስረዳት ጀመሩ። ይህ ድፍድፍ ተፈላጊ ነገር እንደሆነና እንደሚሸጥ እንደሚለወጥ፣ ነዳጅ ተሸጠ በምትኩ ሰፋፊ የውሃ ፕሮጀክቶች ተነድፈው ውሃ ማግኘትና አገር ማልማት እንደሚቻል ወዘተ... አስረዳቸውና በግድ ተስማሙ።

ከራት እንጂ የሐይማኖቱ አስተምህሮ ስለ መሸርሸሩ አስቦ በቲሚት አሎታውን ሊያሰማ አይችልም።

"በዚህ ተግባር በአንድ በኩል ሙስሊሙ ኩራት እንዲሰማው ማድረግ ሲቻል፣ በሌላ በኩል በዚያች ድንቅ ሙስሊም የሳውዲ ሴት አርአያነት ሌሎቹም ቀስ በቀስና በሂደት ሽፍንፍናቸውን መግለጥ እንዲጀምሩ ማድረግ ተቻለ ማለት ይሆናል።

"ያች ሴት በአገርና በመንግስት ደረጃ እውቅና ሲሰጣትና ትልቅ ባለሥልጣን ሆና ስትታይ ደግሞ፣ የመሰጊድ ተጠሪዎችና የሐይማኖቱ መሪዎች፣ እንዲሁም ተራው ምዕመን፣ ነገ ከነገ ወዲያ ለእስልምና ሐይማኖት የራሷን አስተዋፅኦ ታደርጋለች ብለው በማሰብ፣ ከኩራት ያለፈ ደስታ ውስጥ በመግባት፣ ለዚያች ወገናቸው ድጋፋቸውን ማሳየታቸው አይቀርም። በሳውዲ ደረጃ ሲሆን ደግሞ በመላው ሙስሊም ጎብረተሰብ ዘንድ ሊፈጠር የሚችለውን ነገር ማሰብ ቀላል ነው!

"ሐይማኖትን ከእነ አስተምህሮው ለመሸርሸር ውስብስብ የመሰለ ቀላል ስራ ሲሰራ፣እንዲህ ባለ በማይጠረጠር ዘዴ የሐይማኖተኛውን ሞራል ጎን ለጎን በመጠበቅ ነው።

"በእንዲህ ዓይነቱ ልምምድ የቱርኳኑንም ሆነ የመጽሐፍ ቅዱሱን ቃላቶችንና ሕግጋቶችን፣ ደንቦችንና አስተምህሮዎችን፣ አንድ በአንድ እየመዘዙ፣ እየመዘዙ፣ እያወጡ በመጣል ከመጀመሪያው ምዕራፍ እስከመጨረሻው ምዕራፍ መቀጠል ይቻላል።

"ሐይማኖትን ከጥቅም ውጪ ለማድረግ አንዱና ዋናው ብልሀት ይህ ነው! ምክንያቱም፣ የሐይማኖት ተቋማቱ እስካሉ ድረስ፣ ሐይማኖተኛውም ሐይማኖታዊ ሥርዓቱን መቀጠሉ እንደማይቀረው ሁሉ፣ የሐይማኖቱ ዋና መጽሐፍ ከእነ ክብሩ፣ ከእነ ሀግጋቱ፣ ከእነ ተቀባይነቱ፣ ተጠብቆ እስቆየ ድረስ፣ የሐይማኖቱ መጽሐፍ ቃላቶች ተከብረው እየተተገበሩ እስከ ቀጠሉ ድረስ፣ ብዙ አይነት የመሸርሸርና የማፈራረስ ስራ ብንሰራም፣ አማኞችን በቀላሉ ኢ-አማኒ ወደ ማድረግ ማምጣት ያስቸግረናል።

"ሐይማኖተኛውን ህዝብ አጭሙን አስለውጠ ወደ ልዑላችን እምነትና ፍልስፍና ማምጣት የሚቻለው የሐይማኖት ተቋማቱን በመውረስና የሐይማኖቱን መሪዎች በኛ ሰዎች በመተካት ብቻ ሳይሆን፣ በዋናነት የሐይማኖቱን አስምህሮና ህግጋት አንድ

ምክንያቱም በዚያ ዘመን እንዲሁ ለእለት ጉርሰና ለመኖር ሲባል
የሚደረግ የንግድና የልውውጥ ልማድ እንጂ በባህሬንና በሊሎች
አገራቸች ሙስሊም አገራት ዘንድ ገንዘብ ሐራም ስለነበር ነው
አሻፈረን ብለው የነበረው፡፡ እናም በማድ ተለምነው ተስማሙ፡፡
"ከዚያ....የነዳጅ ዘይት ሐብቱ ተቆፍሮ እየወጣ አንድ በርሜል
ድፍድፍ በሃምሳ ሣንቲም መሸጥ ጀመሩ፡፡ ልጃችን አሚሪካም
የግሯውን ውል ተፈራረመች፡፡ ሁለት በርሜል በአንድ ዶላር
ሲሸጡ ቆዩ፡፡
"የባህሬኑ ንጉስ በሽያጭ የሚገኘውን ገንዘብ እየወሰዱ በሣርና
በጭቃ በተገነባው ትቢያ በወረረው ቤተ-መንግስቱ ማስቀመጥ
ጀመረ፡፡ ገንዘቡን እየተቀበለ ፍራሹ ውስጥ ነበርና የሚወሽቀው
አየገባው ሄደ፡፡ አውጥቶ መጣልም ተመኘ፡፡ አሁንም ሊላ አሰረጅ
ልክን ገንዘቡን በሥርዓት እያስቀመጡ ማጠራቀም እንዳለባቸው
ገልፀን ለማረጋጋት ብንሞክርም ሐራም ነው ብለው ክችች አሉ፡፡
"ሰፊውን ታሪክ ልተወውና ግን... ነገሩ በዚህ መንገድ ተጀምሮ
ቀስ በቀስ እየተለመደ፡ እየተለመደ፡ ወደ አጎራባች አገሮችም
ቱፋሮው እየቀጠለ፡ በመላው መካከለኛ ምስራቅ አገራት ያሉ
የነዳጅ ዘይት ክምችቶችን ያ ድርጅት ራሱ ኮንትራቱን ይዞ
መግዛቱንም ቀጥሎ ተጓዳኝ የልማት ፕሮጀክቶች እየተነደፈላቸው
የሙስሊም አገራት ቀስ በቀስ መልማት ጀመሩ፡፡
"የባህሬኑ ንጉስ ቤተ-መንግስቱን በደማ አፍርሶ በጣም ዘመናዊ
የሆነ በእብነ-በረድ፡ በመስታዎት፡ በመብራት በምናምን ያሸበረቀ
ቤተ-መንግስት ተገነባለት፡፡ አጥር እንኳን ያልነበረው የሳር ቤተ-
መንግስት በሰፊ ጊቢ ተከልሎ፡ጊቢውም በአረንጓዴ አትክልቶች
አምሮ የዓረቡ ዓለም የእውነት ንጉስ መሰለ፡፡ ብዙዎች ተደነቁ፡፡
በባህሬን አርአያነት ሁሉም የነዳጅ ዘይት ያላቸው አገሮች
በአስደናቂ ፍጥነት ከአፀራ ወጥተው ከአውሮፓ የሚስተካከሉ
ከተሞች ኖሯቸው፡፡
"ገንዘብ ሐራም መባሉ ቀረና የገንዘብን ጥቅም ከማንም ሕዝብ
በላይ የተረዱ ሆኑ፡፡ ገንዘብን በጣም ፈለጉት፡፡ ፋክክር ሆነ!
ሐራም ማለት የጅል ቋንቋ ሆነባቸው፡፡ ነግስታቱና ሕዝባቸው
ሰለጠኑ፡፡ መሠረተ-ልማቶች ተሰፋፉ፡፡ ሜራሽ ገንዘብ

እያወራቸው ሲሄድ በየጊዜው የነዳጅን ዋጋ እየጨመሩ፡ እየጨመሩ
አስቸገሩ፡፡
"እናም ያኔ በማማሸ ዶላር ይሸጥ የነበረው አንድ በርሜል ድፍድፍ
ዛሬ ላይ 300 ዶላር ደርሶ ይገኛል፡፡ በዚህ አይነቱ ታሪክ
አገራቱም እንዲህ አሽብርቀው፡ ነግስታቱም እንዲህ ዘምነው ተጥቅ!
ሳዑዲ አረቢያም በወርቅ የተገነባች ከተማ እስከ መምሰል ደረሰች፡
:ሊሎችም እንደዚሁ፡፡
"ይህ ሲሆን የየአገራቱ ሙስሊም ማኅበረሰብ ገንዘብን እስከ
ማምለክ ደረሱ፡፡ ከሌላ አገራት የቤት ሰራተኛን ላይቀር
ማስመጣት ያስቻላቸው ገንዘብ ነዋ!
"በዚህ ዓይነት መንገድ በጣም ተጠንቅቀውና አክብረው ከያዙት
ቱርዓን ይልቅ፡ ገንዘብን የበለጠ መውደድና ማሰብ ጀመሩ፡፡
በአካባቢው በአላህ ፈንታ ገንዘብ እየነገሰ ሄደ፡፡
"ስለዚህ ሐይማኖት ሲሸረሸር በረቀቀና በማይመስል በማይጠረጠር
ዘዴ ገንዘብንና ስልጣንን ጥቅም ላይ በማዋል ቁም ነገር
ለፊት በመላተምና የየሐይማኖቱን አስተምህሮ ደርሶ በማጥፋት፡
በመተቸት፡ በመከራከር፡ በማንቋሸሽ፡ አይደለም!
"ሐይማኖትን በሚመለከት አገርህ ሳዑዲ ዓረቢያ ጥሩ ምሳሌ
የምትሆነው የእስልምና ዋና መዲና ስለሆነች ነው፡፡
"ይቺ አገር የእስልምና መዲና ሆና ነገር ግን በነዳጅ ዘይት ገንዘብ
ስለከበረች ነዳጇንም፡ አገሯንም፡ ሜራሽ እስልምናዋንም
ለመጠበቅና ከጥቃት ለመከላከል ፈለገች፡፡ እስልምናን ለመጠበቅ
ብላም ከእኛ ብዙ ዘመናዊ ጦር መሳሪያዎችን መግዛት ጀመረች፡፡
ተወንጫፊ ሚሳኤል አልተራትም! ብዙ ገዛች፡፡ በስተመጨረሻ
ሠረኛ አገር ሆነችና ይሄው ዛሬ ከባባድ ሚሳኤል እያስወነጨፈች፡
የሙስሊም ወንድማማችነትን አሽቀንጥራ ጥላ፡ ሙስሊም አገራትን
በማተራመስና በመውጋት እያገዘችን ነው፡፡
"ወደ እዚያች ጎላችን ወደ ሆነች አገር ለመግባት የሰሚን ክፍል
የሆነችውን የሙስሊም አገር የመንን ዱቄት እያደረገች
እየተባበረችን ነው፡፡ ደግሞ ኃያል አገር ሆና ተቀላቅላናለችና
ሽፍንፍንን በመግለጥና በማስገለጥ ታግዘናለች፡፡
"ፎቶ ግራፍ እንኳ መነሳት የማይችሉትን የሳዑዲ ሴቶቿን
ሚንስቴር ባለስልጣን እያደረገች፡ ሌላም ሌላም መሰል
ሐይማኖታዊ ክልከላዎችን እያነሳች፡ ብዙ ታግዘናለች....፡፡ ልክ

አይደለሁም ወይ ንጉሳችን?" በማለት፣ ዓይኖቻቸውን ወደ
ጠያቂው አፍጥጠው ፈገግ ብለው ጠየቁ፡፡
"ልክ ነው ንግስት ሆይ፣እንደዚያ ነው፡፡" አሉና እግሮቻቸውን
አንፈራጠው በኩራት ደገፍ አሉ፡፡
"አዎን! የገንዘብ የበላይነት ማለት የልዑላችን የበላይነት ማለት
መሆኑን በዚህ አይነቱ ታሪክም ጭምር ማረጋገጥ ትችላላችሁ፡፡
"ሐይማኖትን በሚመለከት በኢትዮጵያም ሆነ በሌላው አገርና
አህጉር የሚሰራው ተመሳሳይ ስራ ነው፡፡ ገንዘብ!
"ሌላው ከሕግና ከፖለቲካ ጋር የተያያዘው የሐይማኖትና
የሐይማኖተኛውን እምነት፣ እንዲሁም ዶክትሪኑን የመሸርሸሪያ
መንገድ ከምንለው ውስጥ አንዱ እኩልነት የሚለው ቃል ነው፡፡
ኢትዮጵያ ስልሳ ከመቶው ክርስቲያን፣ ሠላሣ ከመቶው ሙስሊም፣
ቀሪው ከክርስትና ጋር የተያየዘ ሐይማኖት ያለው ህዝብ ያለባት
አገር ናት፡፡ ሙስሊምና ክርስቲያን በተቀራራቢ የቁጥር ደረጃ
ያለባት አገር መሆኗ ደግሞ ስራችንን ያቀለዋል፡፡
"ታዋቂ የሐይማኖት ሰዎችን ከፍ ያለ የፖለቲካ ስልጣን እንዲይዙ
ማድረግ ለፉክክርና ለእርስ በርስ ጥምምድ ጠቃሚ ነው፡፡ እርስ
በርስ በጠላትነት እንዲተያዩ ከማድረግ አልፎ፣ባስፈላጊው ጊዜ
አንዱን በአንዱ ላይ ለማስነሳትም ይረዳል፡፡
"ቀደም ሲል እንደገለፅኩት እኔ የምከተለውን ሐይማኖት የሚከተል
ታዋቂ ሐይማኖተኛ የፖለቲካ ስልጣን ሲያገኝ፣ እኔ
ለሐይማኖታችን ጥሩ ተግባር ሊያከናውን ይችላልና ድንቅ
ሹመት ነው፡፡ ብዬ ከማሰብ ውጪ ሌላ ነገር ማሰብ
እንደማላስቀድም ሁሉ፣ ከእኔ ውጪ የሆነን ሐይማኖት የሚከተሉ
ወገኖችም በተመሳሳይ የሚያስቡት ተቃራኒውን ነገር ነው፡፡ ‹‹ነገ
ስልጣኑን ተጠቅሞ የእኛን ሐይማኖት ሊበድል ይችላል›› አይነት
ፉክክር እንጂ የሚኖረው፣ ሐይማኖታቸው ይህን ይፈቅዳል? ወይስ
አይፈቅድም? የሚል አታካራ ውስጥ የሚገባ አይኖርም፡፡ ቢኖርም
በጣም ጥቂትና በብዙሃኑ ሃሳብ በቀላሉ መጨፍለቅ የሚችልና በኋላ
ቀር አስተሳሰቡ ተተችቶ የሚቀር ነው የሚሆነው፡፡
"የሴቶች እኩልነት የሚለውም ሌላው ሐይማኖታዊ አስተምህሮን
ከጥቅም ውጪ ለማድረግ የሚረዳና እንደ አንድ ግብዓት ሆኖ
የሚያገለግል ነው፡፡

"በነገራችን ላይ እነዚህን ሁሉ ነገሮች ቀደም ብለን አጀንዳ
አድርገን የተነሳነውና በዓለም ሕዝብ ዘንድ እንዲቀነቀኑ፣ በሕግና
በፖለቲካ ተካትተው እውቅና እንዲያገኙ ስናደርግ፣ ይህን
በስተመጨረሻ የሚጠብቀንን ዘርፈ ብዙ ስራ አስበን፣ ለዓላማችን
ማስፈፀሚያ እንዲረዳን ተገንዝበን የጀመርነው እንጂ፣ እውነት
የሴቶች እኩልነት አሳስቦን አልነበረም፡፡ በሴቶች እኩልነት ያደገች
ወደ ፊትም የምታድግ ዓለም የለችም፡፡ ዓለም በልዑላችን የጥበብ
ልገሳና በእኛ በድቅሎ እውቀትና ስልጣኔ እንጂ በወንድም በሴትም
ሰው አላደገችም፡፡" አሉና ፈገግ አሉ፡፡ አዳራሹ ውስጥ መጠነኛ
ጉምርምታ ተደመጠ፡፡ በጉርምርምታው መሃልም የጀርመኗ መሪ
ከት ከት ከት ብለው መሳቅ ጀመሩ፡፡
አሮጊቷ የእንግሊዝ ንግስት፣ "ምነው? አልተዋጠላችሁም እንዴ?"
በማለት ፈገግ እንዳሉ በሰርሳሪ ዓይኖቻቸው የጉባዔው ታዳሚዎች
ላይ አፍጥጠው ቆዩና፣ "ለነገሩ እኔም ሴት ነኝ ለካ..." በማለት
ያቺን የሽሙጥ ሳቃቸውን ስቀው ቀጠሉ፡፡
"ለማንኛውም እውነቱ ያልኩት ነው፡፡ ዛሬ የተመሳሳይ ጾታ
ጋብቻን በየሕጋችን ስናካትትና በየአገራቱ ሕገ-መንግስት ጫና
ፈጥረን ስናስፀድቅ የምንታየው ለልዑላችን ዓላማ ስለሆነ እንጂ፣
በተመሳሳይ ጾታ ጋብቻ አማካኝነት ዓለማችንን ልናሳድግ
ልናሰለጥን አይደለም፡፡
"በጾታ እኩልነት የሚመጣ የዓለም እድገት የለም ማለቴ ነው፡፡
ይህን ተግባር የምንፈፅመው እኮ በተመሳሳይ ዘዴ ነው፡፡ በጾታ
እኩልነት....፡፡ ሳቅሽን እንድትቋጭ አሳስባለሁ....፡፡ በሴት የተሰራ
ስልክ ወይስ ኮምፒተር ወይስ አውቶሞቢል ያለ ይመስልሻል?"
ብለው በመጠየቅ የጀርመኗን መሪ ዝም ካሰኙ በኋላ ቀጠሉ፡፡
"ወደ ነጥቤ ልመለስ፡፡ በሴቶች እኩልነት ዙሪያ የሚያጠነጥኑ፣
ፖለቲካ ነክ በሆኑ መነሻዎች አማካኝነት ሴቶችን ከወንዶች እኩል
የስልጣን ባለቤት ማድረግ ወሳኝ ከሚባሉት አንዱ የሆነና ሰዎችን
በኢ-አማኒነት ማስቀጠል የሚያስችለን መሳሪያ ነው፡፡
"እነዚህን መሰል ቅድመ ስራዎች በሚገባ ሰርተን፣ በዓለም አቀፍ
የሕግ ማዕቀፍ ውስጥ እንዲካተቱ አድርገን ያመቻቸነው አንድም
ለዚሁ የሐይማኖት ህግጋት ሽርሽራ ነው፣ ለማለት ነው
የፈለግሁት፡፡

"ያለ ሴቶች ተሳትፎ ዓለማችን አታድግም አትሰለጥንም የምንለው፣ ስናምታታ እንጂ፣ ዋና አጀንዳችን ሴት ልጅ ከባሏ ትማር የሚለውን ሐይማኖታዊ ህግጋትም አብሮ ለመገዝገዝ ነው ክቡራን፡፡

"ሴት ልጅ በሚስትነት ብቻ ሳይሆን፣ በባልነትም መሳተፍና ሚስት አግብታ መኖር የምትችልበትን ሁኔታ ስናመቻች ጭምር ነው ክቡራን፡፡

"ዋና ዓላማችን ሐይማኖታዊ ህግጋትን ስለ መሸርሸርና ስለ መሻር እስከ ሆነ ድረስ፣ ይህም አንዱ ዘርፍና ዘዴ ነውና በሃሳቤ ልትግባቡ ተግባብታችሁም በየ አሮቻችሁ ተግባራዊ ልታደርጉ ይገባል፡፡ አርአያ እየሆናችሁ ለሌሎች ማሳየት አለባችሁ፡፡

"በተለይ በዚያች አገር ለሴቶች እኩል እኩል የፖለቲካ ስልጣን የሚሰጡ መሪዎችን ማበረታታት፣ ‹‹በእኩልነት ዙሪያ ባሳዩት ለውጥ፣ ሴቶች ለዴሞክራሲ ያላቸውን አስተዋፅኦ ተገንዝበው አገራቸውን ለማሳደግ በሚያደርጉት ጥረት›› ወዘተ... እያላችሁ ማድነቅ፣ መሸለም፣ መጠነ ሰፊ የገንዘብ ድጋፍ ማድረግ፣ ለእናንተ የተሰጠ የቤት ስራ ነው፡፡ ሴት ባለ ስልጣናትን አንደኛ እያላችሁ ማበረታታትና መሸለም፣ ዓለም አቀፍ ወሬ አድጋችሁ በአድናቆት ማራገብ፣ በየመፅሔቱ የሽፋን ገፅ እያተማችሁ ማስደነቅ ይኖርባችኋል፡፡

"በእኛ በኩል ይህን ለማድረግ ዝግጁ የሆኑ ባለስልጣናትን አስተምረን፣ አሰልጥነን፣ ካዚጋጀንላችሁ ቀሪው ሥራ የእናንተ ነው፡፡

"ደግሞም አስታውሱ! በዓለማችን ባሉ አገራት በሙሉ የተመሳሳይ ጾታ ጋብቻ ሕጋዊ እንዲሆን ስናደርግና የሕግ ከለላ አግኝቶ በየ አገሩ እንዲንሰራፋ ጠንክረን የምንሰራው የዓለም ሕዝብ የበላይ አካሉ ተቃራኒ መሆኑን ማሳየት የሚጀምረው ከዚህ ስለሆነ ነው፡፡ ልዩ ትኩረት ሰጥተን በመላው ዓለም ተግባራዊ እንዲሆን እየተንቀሳቀስን ያለነው መላው ህዝብ የበላይ አካሉ ተቃራኒ መሆኑን በዚህ እንዲያረጋግጥ ስንል ነው፡፡

"እኛም በዚሁ መድረክ እሱኑ ተግባር የምንፈፅመው ለልዑላችን ታማኝ መሆናችን ለማረጋገጥና ለልዑላችን የበላይነት ስንል እንደሆነ ታውቃላችሁ፡፡ ስለዚህ ጉዳዩ የወንድ ለወንድ ጋብቻን ብቻ የሚመለከት አይደለም፡፡ ጎን ለጎን በጾታ እኩልነት ሳቢያ

ሴት ለሴት መጋባት የሚችሉበትንም አሰራር እየዘረጋን መሆኑን ማስታወስ አለባችሁ፡፡

"እንዳልኩትም በሁሉም የሐይማኖት መጻሕፍትና በበላይ አካሉ ሕግጋት "ሴት ልጅ ከባሏ ትማር" የሚል ቃል ነው ያለው፡፡ ይህን የሐይማኖት ቃል በፖለቲካ ዘዴና በእኩልነት ሰበብ በዓለም ላይ ማስቀረት ከተቻለ፣ ሌላውን የመጽሐፍ ቅዱስና የቁርዓን ቃላትስ እየጣሱ ማስቀረት ምኑ ይከብዳል?

"ግልፅ ነው ክቡራን፣ለዚህ ለመጨረሻ ዓላማ ሲባል ነው መጀመሪያ ከጓዳ ትውጣ፣ ቀጥሎ በሴቶች ተሳትፎ ዴሞክራሲን እንገንባ፣ የሴቶች እኩልነት ሲረጋገጥ የሆነ የሆነ ነገር ... ይሆናል እያልን ስናስተምር፣ ስንሰብክ፣ ስንደነግግ፣ የከረምነው፡፡ ይህን አሰራር በተለይ በኢትዮጵያ አጠናክሮ ማስቀጠል ተገቢ ነው፡፡

"አስተምረን አሰልጥነን የምንልካቸው ሴቶች ሁሉ ተልዕኮአቸውን ያለ አንዳች ጉርምርምታ በዚያች አገር ላይ መፈፀምና ማስፈፀም ቀላል የሚሆንላቸው ደግሞ የእናንተ የጋራ እገዛ ሲታከልበት እንደሆነ አትርሱ፡፡ ነገሩ በዓለም አቀፍ ደረጃ ድጋፍ ተችሮት በየ ሚዲያው ሲደነቅ ደግሞ ውስን አክራሪ ተቃዋሚዎች በዚያች አገር ቢኖሩና ስለ ሐይማኖታዊው ህግጋት እያነሱ ለመተቸት ቢሞክሩ እንኳን እነሱን በብዙሃኑ ዓለም አቀፍ የድጋፍ ድምፅ በቀላሉ መጫን ይቻላል፡፡

"በዚህ አይነት ዘዴዎች ሐይማኖታዊ ህግጋቶችንና ቀኖናዎችን አንድ በአንድ ከጫወታ ውጪ እያደረግን ስንቀጥል፣ ሙሉ አስተምህሮው እየተናቀ፣ እየቀረ፣ እየተረሳ፣ እየከሰመ፣ ይሄዳል፡፡ በስተመጨረሻ ሙሉ ለሙሉ ይተዋል እንደ ማለት ! ክብር ለልዑላችን!

"አሜን!"

"ስለዚህ ይህ አንተን ብቻ የሚያሳስብና የሚያስጨንቅ ጉዳይ አይደለምና አትረበሽ፡፡ ቀስ በቀስና በሂደት ሁሉን ነገር አመቻችተን በመቀጠል ላይ ነውና ያለነው ሙሉ ለሙሉ መሳካቱ ስለማይቀር ያን ያህል አያሳስብህ፣ አያብሰልስልህ፡፡

"እንደ አንድ አገር መሪና እንደ አንድ ንጉስ የሚሰጥህን የቤት ስራ በአግባቡ በአገርህ ላይ ተግብር እንጂ በቅርቡ ሁሉም ተሳክቶ ታየዋለህ፡፡"

"ቀጥል" በማለት ለቻይናው መሪ ዕድሉን ሰጡ፡፡

ጠብቆ የተከፋፈለውን ህዝብ ወደ ቀድሞ አንድነቱ የመመለስ ነገር ሊኖር ይችላል። ይህን ሁኔታ በገምታ ማየቱ ለእኛ ችግር አይፈጥርብንም ይላሉ? ሌላው ከዚህ ጋር የተያያዘው ጥያቄዬ፣ በዚያች አገር ላይ ለምንሰራው ስራና በዚያች አገር ውስጥ በጋራ ለምናከናውነው ሚስጥራዊ ተግባር የሚረዳን የህዝቡ መከፋፈል ነው? ወይስ የህዝቡ አንድ መሆን? በዚህ ዙሪያ ምርጫችን ሊሆን የሚገባው የቱ ነው? ምናልባት ምርጫችን በብሄር መከፋፈሉ ከሆነ፣ ያ ለዘመናት በአንድነትና በህብረት ተሳስሮ፣የጋራ ታሪኩን፣ የጋራ ባህሉን፣የጋራ ሐይማኖቱን፣ በጋራ ሲጠብቅና ሲከላከል የቆዩ አስቸጋሪ ህዝብ በተላሉ ከልቡ ሊከፋፈልልን ዝግጁ ነው ወይ? ይህ በራሱ ምን ያህል አስተማማኝ ነው? ምናልባት የምንመርጠው አንድነቱን ከሆነ ደግሞ፣ በብሄር የተከፋፈሉትን ህዝቦች በቀላሉ አንድ ማድረግ ይቻላል ወይ? በዚህ ዙሪያ ምርጫችንን ለያቱን አንዱን መርጠን ከሆነም፣የትኛውን መንገድ እንደመረጥን ቢነግሩንና ቢያስረዱን ጥሩ ይመስለኛል። የመረጥነው ዘዴ ስኬታማ ሆኖ እንዲቀጥል በእናንተ በኩል የተሰራ ስራ ካለም ከወዲሁ ብናውቀው መልካም ነው እላለሁ፣ አመሰግናለሁ።"

በዚህ ጥያቄ ንግስቲቱ ፊገግ ሲሉ ታዩ። ፊገግ ብለውም እንደልማዳቸው በሰፊው መድረክ ላይ በቁንጥ አረማመድ ወዲያ ወዲህ ሲሉ ቆይተው ቀጠሉ።

"ኢትዮጵያ ውስጥ ካሉ ህዝቦች በቁጥር የሚበልጠውን ብሔር እወክላለሁ፣ ወክዬም ለነፃነቱ እታገላለሁ፣ የሚል አንድ ምሁር ተብዬ ፖለቲከኛ በወኪሎቻችን አማካኝነት አስጠርቶን እንድ ጥያቄ አስጠየቅነው። ጥያቄውም አሁን ወንድማችሁ ካነሳው ጥያቄ ጋር ተያያዥነት ያለው ነበር። ‹‹እኩል ሆናችሁ በአንድነት መኖር? ወይስ የራሳችሁን መንግስት አቋቁማችሁ መገንጠል? የቱ ነው ምርጫችሁ?›› ተብሎ ተጠየቀ። የሰጠው መልስ ‹‹ለእኛ ሁለቱም ሊያዋጣን ይችላል›› የሚል ነበር። እንደኛው ጥያቄህ ይዤን ምላሽ ስላስታወሰኝ ነው ፊገግ ያልኩት።

"እ... ‹‹ለእኛ ሁለቱም ሊያዋጣን ይችላል›› የሚለውን ምላሽ ሰሰማ፣ አሁን በድንጉት ፊገግ እንዳልኩት ያኔም ብቻዬን በቆምኩበት ፊገግ ብዬ እንደነበር አስታውሳለሁ።

"እያችሁ? ራሱን ችሎ መምራት ይቻል አይቻል ያላወቀ ልምድ የሌለው ፖለቲከኛና ማኅበረሰብ ከዚህ የተሻለ ምላሽ ሊሰጥ

"አመሰግናለሁ ንግስት ሆይ፣ ክብር ለአሸናፊያችን። ቀደም ሲል የዚያችን አገር ህዝቦች እርስ በርስ ለመከፋፈል ሲባል በእናንተ በኩል ስለ ተሰራ ስራ በከፊል ተገልጸልናል። ነገር ግን አጥጋቢ ስራ ስርታችኋል ብዬ አላምንም። ምክንያቱም ጎላችን ያች አገር መሆኗ ድሮም ጀምሮ ይታወቅ ከነበረ፣ ከዚህም ያለፈ ስራ ቀደም ተብሎ መሰራት ነበረበት። ባለፈ ነገር መቆጨት ትርፍ ባይኖረውም፣ ቅኝ ይዞ አለመቆየቱ.... ስራችን እንዲከብድ የሚያደርግ ይመስለኛል። ሆኖም ግን አሁንም ረፍዷል ብዬ አላስብም። ስለዚህ ጊዜ ሳይወሰድ በተዛባሪ ፈጥኖ የፖለቲካ ቅኝ ግዛት ማድረግ ያስፈልግ ይመስለኛል። በዚህ ዙሪያ በክቡርነትዎና በቤተሰብም በኩል መጠነኛ የሆነ መዘናጋት ተስተውሏል ለማለትም እደፍራለሁ። እርግጥ ነው ህዝቡን ለመከፋፈል ተሞክሯል። ለዚህ የመከፋፈል ስራ ሲባልም ቀደም ተብሎ ስለ ተተከለው መሰሪ ችግኝ ቀደም ሲል በሰፊው ነግረውናል። ምንም እንኳ ችግኙ በአሁኑ ሰዓት ምን ደረጃ ላይ እንደደረሰና ምን አይነት ፍሬ አፍርቶ እንደሚገኝ ባናውቅም....። ስለዚህ እሱንም ቢያብራሩልንና የት ደረጃ እንደደረሰ ቢገልፁልን መልካም ነው እላለሁ።

ምክንያቱም እኔ ቅኝ ግዛት ይዛችሁ ማቆየት አለመቻላችሁ አሁን ድረስ እየቆጨኝ እንዳለ ነውና፣ ባለመዛዝድ ያጣነው ነገር እንዳለና እንደሌለ በደንብ መረዳት አፈልጋለሁ። ያጣነው ነገር ካለም ጊዜ ሳንወስድ ቶሎ በእጃችን ማድረግ እንዳለብን አስባለሁ። እኛም ከሌላው አገር በተለዩ የዚያች አገር ወዳጅ ነንና በዚህ በኩል የቤት ስራ ቢሰጠን ፈጥነን ለመፈፀም ዝግጁ ነን።

"ወደ ዋናው ጥያቄዬ ሳልፍ፣ ኢትዮጵያውያኑ አሁንም ድረስ በአንድ ሰንደቅ ዓላማ ስር ተሰባስበው ያሉ ህዝቦች ናቸው። ታዲያ.....በክቡርነትዎና በቤተሰብም በኩል ቀድሞ የተሰራው ስራ በትክክል የኢትዮጵያውያንን አንድነትና ህብረት ከስሩ መንግሎ ለመጣል አሰችሏል ብለን እርግጠኛ መሆን እንችላለን? እርግጥ ነው አንዳንድ የብሄር ክፍፍልን ተንተርሰው የሚነሱ ፀቦችና ሌሎች ፖለቲካዊ ችግሮች በአገሪቱ በየጊዜው ይከሰታሉ። ሆኖም ምሁራኖቻቸውና ፖለቲከኞቻቸው ተሰብስበው ይወያያሉ። ችግሩን ለመፍታት የሚያስችሉ የተለያዩ ሃሳቦችን እየሰነዘሩ የመፍትሄ አቅጣጫዎችን ይጠቁማሉ። ሂደቱ በዚህ ከቀጠለ ይግሞ ወቅት

አይችልም። በአንድ በኩል በየትኛው የመምራት ብሞክርው ራሱን ችሎ መምራት እንደሚችል አያውቅምና አርግጠኛ መሆን ይሳነዋል። በሌላ በኩል ነፃ ሆኖ መቀጠል ይፈልግና፣ ነፃ በመሆኑ ሊያጣው የሚችል ከሌላ ወገን የሚድ ማግኘት የሚያስፈልገው ጥቅም ሊኖር ይችላል። ያን ጥቅም ቢያጣ ሊፈጠርበት የሚችለውን ችግር አላጠናውምና፣ ቁርጥ ያለ አቋም ይዞ በአንዱ ውሳኔ መፅናትና መምረጥ ይሳነዋል። ይህ ከምን ይመነጫል? ካላችሁ፣ ምላሹ ከማሃይምነትና ካለማወቅ፣ ካለመዘጋጀትና ነፃነቱን የሚፈልግበትን ምክንያት በውል መርምሮ ካለመረዳት የሚመነጭ ችግር ነው።

"እናም ለእኛ ሁለቱም ሊያዋጣን ይችላል ልልህ ነበር አልልህም። ምክንያቱም በቀጥታ ይህን ምላሽ ከሰጠሁ ያን ጅል ፖለቲከኛ መሆኔ ስለሚሆን። ስለዚህ ነገሩን ለወጥ አድርጌ ከዚያ ብሄረሰብ ውስጥ እንዲህ የሚሉ ፖለቲከኞች እንዴት ሊፈጠሩ እንደቻሉና፣ ለምን እንዲህ ለማለት እንደተገደዱ በማብራራት ሁኔታውን ግልፅ ላድርግ።

"ከዚህ ውስጥም ምርጫችን የቱ ነው? ብለህ ላቀረብከውና ቀድሞ የተሰራ ስራ ካለ ቢነገረን ብለህ ለጠየከው ጥያቄ ሙሉ ምላሽ ታገኛለህ፣ታገኛላችሁ። ያኔ የተከልነውን የችግኙን እድገትና ውጤትም በሰፊው አስረዳለሁ።

"በረጅም ዘመን የቅኝ ገዥነት ታሪካችን በርካታ ተሞክሮዎችና በደንብ የተማርንባቸው አይረሴ አይረሴ ገጠመኞች አሉን።

ከእነዚህ ውስጥ በአፍሪካ ተሞክሯችን ያረጋገጥነውና ለውጤት ያበቃን አንድ የተለመደ አካሄድ ነበር።ያ አካሄድ በዚያ ወቅት ባሰብነው መንገድ መስራት ይቻል እንጂ፣ በአሁኑ ዘመን ላይ ሆኖ ሲታሰብ በጣም ኋላቀር የሆነና በመላው ዓለም የቀረ፣ነገር ግን በኢትዮጵያ ብቻ ዛሬ ድረስ እየተሰራበት ያለ አካሄድ ነው።

"የአንድ ቅኝ ገዥ አገር መንግስት አንድን አገር ሙሉ በሙሉ በቁጥጥር ስር ለማዋልና ተገዥ አገር ለማድረግ አንድ ወሳኝ የሆነን ቅድመ ስራ መስራት ይጠበቅበት ነበር።

"ይህን ቅድመ ስራ ያልሰራ ቅኝ ገዥ የፈለገውን ያህል ጦር መሳሪያና የሰው ኃይል ቢይዝ እንኳ ሙከራው ሁሉ እንደሚከሽፍበት ጥርጥር የለውም። ይህ ቅድመ ስራ ውስን ጊዜን፣ ውስን ገንዘብንና በጣት የሚቆጠሩ ሰዎችን ብቻ የሚጠይቅ ቀላል

ስራ ነው። ይህም ስራ ከቅኝ ግዛት በፊት ያቺን የምትፈለገውን አገር የህዝቦቿን ብሔር ቀድሞ ማጥናትና በዘዴ መከፋፈል የሚቻልበትን ሁኔታ አመቻችቶ መከፋፈል፣ ከፋፍሎም አንዱን ብሔር በአንዱ ብሔር ላይ በቂም በቀል ማስነሳት መቻል ነው። በብሄር ካለተቻለ በሐይማኖት፣ በሐይማኖት ካልተቻለ በቋንቋ መከፋፈል የግድ ነው።

"በዚያች አገር በሚኖሩ ብሔሮች መካከል የቆየ ቁርሾ ከነበረና እየተረሳ ካለ፣ እሱት በአዲስ መልክ መቀስቀስ፣ በዚያች አገር ምንም አይነት የብሔር ፀብ ካልነበረም እንደነበረ አድርጎ ፈጥሮና አቀናብሮ መንገርና ማስነገር ዋናው ቅድመ ስራ ነው። በዚያች አገር ምንም አይነት ብሔር ከሌለና የዚያች አገር ህዝብ አንድ አይነት ብሔር ብቻ ከሆነ ደግሞ፣ አንዱ ጎሣ ከሌላው ጎሣ አንደሚለይና፣ በግድ፣ በኃይልና በጫና ያኛውን ጎሣ ወደ አንድነት እንዲመጣ ያደረገው መሆኑን የሚገልፅ አሳማኝ የፈጠራ ታሪክ ወይም ወሬ ፈጥሮ ሰፊ የፕሮፖጋንዳ ስራ መስራት ያስፈልጋል። የፈጠራ ፕሮፖጋንዳውንም በሰነድ መልክ ማስቀመጥን ጨምሮ፣ የሃሰት ወሬውን እውነት አድርጎ ማቅረብ የሚያስችል ሐውልት እስከ ማቆምም ሊደርስ ይችላል። የምናሳምነው ማኅበረሰብ ደግሞ እጅግ ኋላ ቀር ማኅበረሰብ ስለሚሆን በቀላሉ የፈጠራ ወሬውን አምኖ ጥላቻውን ይጀምራል። ከዚያ በኋላ የመፍትሄ ሃሳቡንም ጠቁሞ፣ የሚፈለገውን እገዛም አድርጎ፣ ማስነሳትና ወደ ሚፈለገው ግብ በቀላሉ መድረስ ይቻላል። ሌሎች ዘዴዎችም ሊኖሩ ይችላሉ። አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ከዚያ ብሔር ተወላጆች በጣት የሚቆጠሩ ሰዎችን መልምሎ ወደ እዚህ ወደ ሰለጠኑ አገሮቻችን ማምጣትና ማስተማር ሊያስፈልግ ይችላል። ከዚያም አገሩ ገብቶ ፖለቲከኛ እንዲሆንና ለምስኪን ወገኖቹ ተቆርቋሪ ሆኖ እንዲቀርብ፣ የነፃነት ታጋዮቹ ሆኖ እንዲነሳ፣ ማድረግ ሊያስፈልግ ይችላል።

"ይህ ሁሉ ጥንቃቄና ቅድመ ስራ የሚያስፈልገው ያችን አገር በቁጥጥር ስር ለማዋል ሲባል ብቻ አይደለም። ሁሌም በቁጥጥር ስር ሆና በቋሚነትና በዘላቂነት ተገዥ እንደሆነች እንድትቀጥል ማድረግ ነው። ለዚህ ብቻ አይደለም። ያቺን አገር ወደፊት ለቅቀን ብንወጣና ነፃ አገር ወደመሆን ብትመለስ እንኳ፣ በቀጥታ

ያግኙትን ነፃነት በተዛዋሪ ነጥቆ እስከመጨረሻው የእኛ ተገዥ አድርጎ ለማስቀጠል ስለሚያስችል ነው።

"ምናልባት ያ ያሰለጠንነውና ያስተማርነው ቡድን ብሔሩን አንቅቶና ለስኬት በቅቶ በስተመጨረሻ እኛን ከድቶ በራሴ መስመር እንዛለሁ ቢልና ነፃ ሆኖ ቢቀጥል እንኳ፣ ያኛውን ያስነሳንበትን ብሔር ወይም ጎሣ ዘመን ጠብቀን እንደገና በዚህኛው ላይ እንዲነሳ ማድረግም ስለሚቻል ነው። ይህ አካሄድ ለዘመናት የሄድንበትና በስኬት ላይ ስኬት ሲያጎናፅፈን የመጣ ምትክ የለሽ ጥሩ ዘዴ እንደነበር በደንብ አስታውሳለሁ።

"ይህ ዘዴ ያልሰራው በአንዲት የአፍሪካ አገር ብቻ ነበር። ድሮ የኢትዮጵያ ግዛት በነበረችው በሶማሊያ! በነገራችን ላይ በተለያዩ ታሪካዊ አጋጣሚ ራሳቸውን የቻሉ አገሮች እየሆኑ ቀጥለው እንጂ፣ በኢትዮጵያ ዙሪያ ያሉት ጎረቤት አገሮች ብዙዎቹ፣ የቀድሞዋ ኢትዮጵያ ግዛት የነበሩ ናቸው። የትናንቷን ኤርትራ ጨምሮ ሶማሊያ፣ ጅቡቲ፣ ሱዳን፣ አልፎም እስከ የመን።

"እና አይረሴ ገጠመኞቻችን ካልኳችሁ ውስጥ አንዱ ይህ የሶማሊያ ጉዳይ ነበር። የሶማሌ ህዝብ የዓለማችን ብቸኛው ህዝብ ነው፣ አንድ ሐይማኖት፣ አንድ ጎሳ፣ አንድ ብሔር፣ አንድ ቋንቋ፣ አንድ ባህል፣ አንድ ሁሉም ነገር ያለው ብቸኛ ህዝብ!

እንደዚያ አይነት ህዝብ በየትኛውም አገርና አህጉር ገጥሞን አያውቅም። የሶማሌን ህዝብ መከፋፈል የቻልነው ከረጅም ጊዜ ትግልና ጥረት በኋላ ነው። እሱንም በእነዚያ ጥሩ ጥሩ ዘዴዎች ሳይሆን በሌሎች ዘግይተን በፈጠርናቸው አዳዲስ ዘዴዎች ነው፣

"ያንን በሁለንተናው አንድ የሆነ የሶማሌ ህዝብ በታሪክ አጋጣሚ ባገኘናቸው ክፍተቶች ተጠቅመን ማንኮታኮት ባንችል፣ አገሪቱ የት ደረጃ ላይ ትደርስ እንደነበር መገመት አይከብዳችሁም። ከማንም የላቀች ሃያልና አስፈሪ አገር ነበር የምትሆነው። ጂኦግራፊያዊ አቀማመጧን ስታይ የዓለማችን ስትራቴጂካዊ ቦታ ላይ ያለች አገር ናት። ህዝቡ በሐይማኖት አንድ ነው። ብሄር የለም። ይህም ሳያንስ በቂ የሰው ሃይል፣ በቂ የተፈጥሮ ሃብት፣ ከበቂ ወደብና ከበቂ የመሬት ስፋት ጋር ይዛ፣ በተንጣለለው የህንድ ውቅያኖስ ድንበር ቁጭ ያለች አገር ናት። በእነዚህ ነገሮቿ ብቸኛ የዓለማችን አገር ልትሰኝ የምትችል ናት። ስለዚህ ህዝቡን በብሄር መከፋፈል ስላልቻልን ሌሎች ዘዴዎችን መጠቀም

ነበረብን። ልዩነት ያልነበረውን ጎሣ ድሮ ልዩነት እንደነበረው አድርጎ በመተረክ መከፋፈል! ይህም ሳይሰራ ሲቀር በመሬት ስፋትና በማመል ብዛት እያልን እርስ በርስ በጎሣ እንዲጋጩ የማድረግ ስራችንን ቀጠልን።

"ብዙ ከብትና ግመል ያለውን ሃብታም ሶማሌ፣ ትንሽ ከብትና ግመል ካለው ሶማሌ ጋር፣ ሰፊ መሬት ያለውን የጎሣ መሪ፣ ጠባብ መሬት ካለው የጎሣ መሪ ጋር በሃሰተኛ ወሬ ማጋጨት ጀመርን።

"ያንተ አካባቢ ህዝብ ጥቂት ግመሎችና ጥቂት ፍየሎች የኖሩት፣ ያኔ በእያትህ ዘመን ያኛው የጎሣ መሪ ከዚህኛው ከእናንተ የጎሣ መሪ ጋር ባደረገው ጦርነት አሸንፎ ስለ ወረሰው ነው። እንጂ ቅድመ አያትህ የጎሣ መሪ በነበረ ጊዜ ያ ግዛት የእናንተ ጎሣ ግዛት ነበር። ያ ሁሉ የእንስሳ ሃብት የእናንተ ሃብት ነበር። ምልክቱም የፍየሎቻቸው መልክና ቀለም የእናንተን መምሰሉ ነው....." አይነት ትርክት ነው። "ስለዚህ ማስመለስ አለብህ። ያባትህን ክብር.....መልሰህ መሳናዐፍ ይኖርባሃል....." እያልን፣ ከመቀጠል አልፈን፣ ያኛውን ጎሣ ማጥቂያ የሚሆን የጦር መሳሪያ እስከ ማስታጠቅ የደረሰ እገዛ እያደረግን ቀጠልን።

"በዚህ ዘዴ ባስነሳናቸው ግጭቶች ምክንያት፣ በአንድ ጎሣ ተጠቃሎ የነበረ አንድ ህዝብ በጊዜ ሂደት እንድነቱ እየፈረሰ.... ሄደ። ጦርነት በዛ። ሁሉም የየራሱን ጦር መሳሪያ ታጥቆ ያልነበረን የጎሣ የበላይነት ለመጎናፀፍ እርስ በርስ መዋጋት ጀመረ። እንዲህ እንዲያ እያለ ቀጥሎ፣ ብዙ ታሪክ አልፎ፣ የሶማሊያን ምድር ለሶስት ተካፍለን በቅኝ ግዛት ይዘናት ቆየን። የቅኝ ግዛቱ ዘመን ካበቃ በኋላም እንደማንኛውም አፍሪካዊ አገር ነፃ ወጡ። ከነፃነት በኋላም ዘመናዊ መንግስት ተቋቋመ።

"አሁንም ሌላ ስጋት ተፈጠረብን። ወዲያው የቀድሞ ቅኝ ግዛት ታሪካችን አስታውሰን፣ "የቀድሞው የኛ የሶማሌ ግዛት እስከ አጋዬን ነው፣ስለዚህ አጋዬን የእናንተ ነውና ማስመለስ ብትችሉ ጥሩ ነው" በማለት ያን በቅኝ ግዛት ዘመናችን ተክለነው የወጣነውን ችግኝ፣ በርቀት ሆነን እንደ አዲስ መኮትኮትና ውሃ ማጠጣት ስንጀምር፣ ዒያድ ባሬ ሆዬ አጋዬንን ሊወስድ ወስዶም ታላቋን ሶማሊያ ሊመሰርት ፊለገና በኢትዮጵያ ላይ ጦሩን ሰብቆ ተነሳ። ጦርነት ከፈተ። በወቅቱ ኢትዮጵያውያን በወታደራዊው መንግስት ስር ነበሩ። አንድ አገር ወዳድ የሆነ ወታደር ነበር

አገራቱን የሚመራው። መንግስቱ ኃይለማሪያም የሚባል፣ ዚያድ ባሬን መከቱ አስከ መጨረሻው አንኮታኩቱት አሰቀረው። ታላቋ ሶማሊያ ቀርታ ብትንትኗ የወጣ ትንንሽ አገራት ሆነች፣ ሥራሽ መንግስት አልባ ሆነች። እሳም እፎይ አልን። ያች ብቸኛ አስፊሪ አገር በመጨረሻ የዓለማችን ብቸኛ መንግስት አልባ አገር ሆና ተገኘች!

"ሶማሊያን በቅኝ ግዛቱ ዘመን እኛ፣ ፈረንሳይና ኢጣሊያ በጋራ የገዛናት በአካባቢው ላይ ሶስታችንም ግዛት ስለነበረን ወደቧን ለመቀራመት አልነበረም። ፈረንሳይ ወይም እንግሊዝ ብቻዋን ይዛት ወደቡን በጋራ መጠቀም ይቻል ነበር። ነገር ግን ዋና ዓላማችን የነበረው ህዝቡንም አገሪቱንም መቆራረጥና መበጣጠስ ስለነበር ለሶስት ተቀራምተን ሶስት የተለያየች አገርና ሶስት የተለያየ ህዝብ ማድረግ እንዲቻለን ነው። በበርሃማው የኢጣሊያ ግዛት በኩል የነበረው ዕቅድ በከፊል ቢከሽፍም፣ የእንግሊዝና የፈረንሳዩ ሰምሮ በጅንቋ መለያየት ቻሉ። ቀስ በቀስም እንደገና በግዛትና በድንበር መጋጨት ጀመሩ። እኛ ግን እንዲህም ተበጣጥሰውልን እንኳ አንድ ሐይማኖት ሊያስተሳስራቸው ይችላልና፣ እንዳይከሰት ለመጠቀቅ አከራሪና ለዘብተኛ በሚል መከፋፈል ያስፈልገን ነበር። ያንንም አድርገን አልበቃንም፣ ሰጋቱም አለቀቀንም። ስለዚህ የትርምስ ቀጠና አድርጎ ማቆየት የግድ ያስፈልግ ነበርና እሱኑ ስራ ሰርተን እሁን ባለችበት ሁኔታ እንድትገኝ አደረግን። በረጅም ጊዜ ተሳክልን ማለት ነው። ሌላውን የአፍሪካ አገር ህዝብ ለመከፋፈል ግን እጅግ ቀላልና እንደ ሶማሌ ህዝብ ከፍተኛ ጥረት የማይጠይቅ ነበር!

"ስጋታችን የህዝቡ አንድነት ብቻ አይደለም። የባህር በር ያለው የአፍሪካ አገር በሙሉ የትርምስ ቀጠና መሆን ስላለበት ጭምር ነው። ኤርትራና ሶማሊያ ደግሞ ከእኛ ጥበቃ ውጪ ሆነው መኖር አልነበረባቸውም። ቀይ ባህርና ህንድ ውቅያኖስ፣ ድሮም፣ ዘንድሮም፣ ወደ ፊትም፣ ለእኛ የተለዩና ወሳኝ ስትራቴጂካዊ ዐቃቦቻችን ናቸው። ስለዚህ በእነዚህ ድንበሮች ያሉ አገራት በሙሉ እየተቆራቆሱና በእርስ በርስ ግጭት እየተጠፋፉ መኖራቸው አስፈላጊ ስለነበር እነዚያን ስራዎች ያለ እረፍት ሰንሰራ ኖረናል። ሰኪታማም ነን። ምን ለማለት ፈለጌ ነው፣ እንኳን ብዙ ብሄር ያላቸውን አገራት ሶማሊያንም እንዲህ አድርገን

መበታተን የቻልን ንቁና ጥንቁቆች ነን ለማለት ነው። እያንዳንዱን የአፍሪካ አገር ህዝብ በብሄር ሸንሽነን እሁን ድረስ በእኛ ቁጥጥር ስር አድርገነው የቆየን ነን። ለዚህ አንተኛም! እንዲህ ባለ የብሄርና የጎሣ ፖለቲካ ነው ሁሉም አገራት እንዳይቀሩ እንዲቀሩ ያደረግነው። በዚህ ዘዴ ነው ሁሉንም የዘላለም ቅኝ ተገዥ አድርገን ያስቀጠልነው። በዚህ ዘዴ ነው በሁሉም አፍሪካ አገር ለረጂድም ዓመታት የሚዘልቁ የእርስ በርስ ግጭቶች እንዲኖሩ ያደረግነው። በዚህ ዘዴ ነው ሁሉንም ፍላጎት አንድም እርምጃ እንዳይራመዱ አድርገን ያቆየናቸው። ይህንንም ስናደርግ በምክንያት ነው።

"ታዲያ እንደ ኢትዮጵያ ያለችውን 85 ብሄር ያላትን አገር ከፋፍሎ ማተራመስ የቀላሎች ሁሉ ቀላል ስራ አይመስላችሁም? ይመስላል። ግን ቀላል አልነበረም። ከሶማሊያ ብሰው ተገኙና ሌላ አድካሚ ስራ ውስጥ ከተቱን! ይህ ምትክ የለሽ ሆኖ ሲያገለግለን የነበረው በብሄርና በጎሣ የመከፋፈል ዘዴ ለረጅም ዘመናት ተሳስሮና ጠብቆ የቆየውን የኢትዮጵያውያን አንድነትና ህብረት በቀላሉ ሊያፈራርስልን ሳይችል ቀርቶ፣ ከአንድም ሁለት ጊዜ ያለ በቂ ዝግጅት በደካማዋ ኢጣሊያ ተሞክሮ ሊከሽፍ ቻለ። ሆኖም የቅኝ ግዛቱ ዘመን ካበቃ በኋላ፣ በዘመናዊው ዘመን ዘግይተንም ቢሆን ሙተግበር ችለናል። ያውም በራሳቸው ዜጎች አስፈፃሚነት! ይህን ለማድረግ ግን ረጅም መንገድ ተጉዘናል።

"በመጀመሪያ አንድነታቸውና ህብረታቸው የመነጨው ከምንድን ነው? የሚለውን ማጥናት ነበረብንና አጠናን። በአንድ ንጉሳዊ አገዛዝ ስር መሆናቸው አንዱ ምክንያት ነበር። ሌላው ሐይማኖት፣ ታሪክ፣ ባህል፣ ልማድ፣ ወዘተ....አንድ ያደረጓቸውን ነገሮች ተረዳን። ስለዚህ ቅድመ ስራው እነዚህን አንድ ያደረጓቸውን ነገሮች ከዚያች አገር ማጥፋት ወይም መፈረካከስ መቻል ነበር። ስልቱን ቀይረን፣ አፈፃፀሙን አዘምነን፣ አገባቡን ለወጥ አርገን፣ ወደዚያው ወደ ቀድሞ ዘዴዎችን መመለስና ህገቡን በብሄር መከፋፈል ነበረብን። ለዚህ ደግሞ ፍቱን መድሃኒቱ ወይም ብቸኛው መፍትሄ ዘመናዊ ትምህርት ነው። ምክንያቱም የቅኝ ግዛቱ ዘመን ስላበቃ በቀድሞው አይነት ዘዴ ዘልሎ ገብቶ መከፋፈል፣ ማተራመስ፣ ወይም በሃይል ይዞ ያን ዕቅድ መፈፀም

ሆነውና መስለው እንዲቆዩ ነው ያደረግነው። አሁንም ድረስ በዚህ ሁኔታ ውስጥ ነው ያሉት።

"እርግጥ ነው በዚያች አገር ለምንሰራው ዘርፈ ብዙ ስራ የሚያስፈልገን እንድነታችው ሊሆን አይችልም። አንድነቱ የተጠናከረና እርስ በርሱ የሚዋደድ፣ የሚደማመጥ፣ የሚተሳሰብና በጋራ ስለ አንድ አገሩ የሚያስብ ዜጋ ከኖረማ እንዴት ስኬታማ ስራ ልንሰራ እንችላለን? እንደዚያ አይሆንም ክቡራን። ተለያይተው እርስ በርስ ሲባሉ መቆየትና፣ እኛ ስንፈልግ፣ ለምንፈልገውና በምንፈልገው ዘርፍ ብቻ ለጊዜው አንድ እንዲሆኑ፣ እኛ ስንፈልግ ብቻ ተለያይተው እንዲበጣበጡ ሆነው ነበር መዘጋጀት የነበረባቸው። እኛም ያንን ነው ያደረግነው። ይህንንም እንደ ቀላል ስራ አትቁጠሩት። ምክንያቱም ይህን ለማድረግ 50 ዓመታት ያህል ነው የፈጀብን።

"ይህን ለማድረግ መጀመሪያ ያን ኋላ ቀር ህዝብ ትምህርት ቤት ከፍተን፣ መምህራኖቻችን ልከን፣ አዲስ የፖለቲካ ርዕዮተ ዓለም አስተምረን፣ የራሳቸው ተማሪዎች፣ በራሳቸው ንጉሥ እንዲነሱ ማድረግ ያስፈልግ ነበር። ያን አደረግን። ያን እድርገን ንጉሳዊ አገዛዙን ጣልን። ቀጥሎ የራሳቸው ተማሪዎች የራሳቸውን ህዝብ አነሳስተው፣ ራሳቸው በራሳቸው ህዝብ ላይ የሚነሱበትን ሁኔታ ማመቻቸት ያስፈልግ ነበርና ያንንም ማድረግ ቻልን። ሁሉንም ደረጃ በደረጃ አሳካን። ባቀድነው መሰረትም ብሄራዊ አንድነታቸውን አፍርሰን፣ አሁን ባሉበት ሁኔታ እንዲገኙ ማድረግ ቻልን።

"ይህን ማድረግ የቻልነው እንዴት ነው? በኢጣሊያ ተሞክሮ የከሸፈውን ሴራ እንዴት ዘመኑ ካለፈ በኋላ በዚያች አገር ላይ ተግባራዊ ማድረግና ማሳካት ቻልን? ወደሚለው ልለፍና ስለ ነፃነት ታጋዮች ጥቂት ነገሮችን ልግለፅ። ከዚያ በፊት ግን አንድ ጥቆማ ልስጣችሁ።

"ከንጉሱ ውድቀት በኋላ፣ በዚያ ወቅት ለነፃነት ታጋይ ነን ባዮቹ ኢትዮጵያውያን ሙሉ ድጋፍ ለማድረግ የቻልነው እንዲሁ አሳዝነውን ወይም ስለሌሎችን እይደለም። በሚስጥራዊ ውል እና በስምምነት ነው ድጋፍ ማድረግ የጀመርነው። ከከተማ ተባርረው ጫካ የገቡት የኢትዮጵያ ታጋዮች፣ ጫካ የገበቡበት ምክንያት የነፃነት ትግል አልነበረም።

አይቻልም። ስለዚህ የዓለምን የፖለቲካ ርዕዮት ለህዝቡ ማስተማር፣ ማሳወቅና ማሳየት የግድ ነው።

"ያን ህዝብ በዘመናዊ ትምህርት አማካኝነት ስለ ብሄር ብሄረሰቦች ማስተማርና ማንቃት ነው። ስለ እኩልነት እንዲሁም ማድረግ ነው። በዚያ ወቅት የነበረውን የፖለቲካ ርዕዮት ማስረፅ ነው። እንደ እነ ፍራንቸስኮ አይነት ፀሃፊዎችን አስነስቶ ስለዚያ እንዲተነትን ማድረግ ነው። ጊዜ ወሳጅና ትዕግስት የሚጠይቅ ቢሆንም፣ ታግሶ ይህን ማድረግ ግድ ነበር። ይህ ከሆነና ህዝቡ ብሄር ብሄረሰብ ወደሚል ፍልስፍና ከመጣ በኋላ ድል ማስመዝገብ ተቻለ ማለት ነው። ምክንያቱም ህዝቡን በብሄር መከፋፈል ከተቻለ፣ሐይማኖትም፣ ታሪክም፣ ባህልም፣ ልማድም፣ ... ህዝቡን በአንድነት ያስተሳሰሩትን ገመዶች በሙሉ መበጣጠስ ስለሚቻል ነው።

"የአንድን አገር ህዝብ በብሄር ከፋፈልከው ማለት ደግሞ፣ ቅኝ አንኳን ባትገዛው፣ በዚያች አገር የምትፈልገው ከቅኝ ግዛት ጋር የተያያዘ ጥቅማ-ጥቅም ሁሉ አይቀርብህም። ሁሉም ችግር፣ ሁሉም መርነት፣ ሁሉም ብጥብጥ፣ ስለሚሆን፣ በእርቅም፣ በእርጋታም፣ በመሳሪያ ሽያጭም፣ በማማከርም፣ የነፃነት ታጋዮችን በየጊዜው ከየብሄሩ እያስነሱ በመርዳትም፣..... እየተባለ በተዛባ ቅኝ ግዛት አድርጎ ማስቀጠል ይቻላል።

"እኛም በኢትዮጵያ ያደረግነው ይሄንኑ ነው። በተዛባ አገራቱን ቅኝ ግዛት አድርጎ የማስቀጠል ዘዴን ነው የተጠቀምነው። ስለዚህ ለእኛ ሁለቱም ሊያዋጣን ይችላል አልሃለው። ይህን ስልህ ግን እንደ እነዚያ ማሃይም ፖለቲከኞች ምርጫው ቸግሮን ወይም ግራ ገብቶን አይደለም። ምርጫችንን ቀድመን ለይተናል። አንዳንዴ አንድነታቸው፣ አንዳንዴ መከፋፈላቸው፣ እንደሚያስፈልገን አውቀናል። ስለዚህ ሁለቱንም መሆን የሚችለበትን ሁኔታ ነው ያመቻቸነው። ስናመቻችም ባሰፈለገን ጊዜ እየመረጥን ለመጠቀም እንዲያስችለን አድርገን ነው። ከዚህ አንፃር ነው ለእኛ ሁለቱም ሊያዋጣን ይችላል የሚል መልስ የምሰጠው።

"በዚህ መሰረት ሳይከፋፈሉ ተከፋፍለው፣ ተከፋፍለው ሳይከፋፈሉ አንድ ሆነው አንድ ሳይሆኑ፣ አንድ ሳይሆኑ አንድ ሆነው፣ ህብረት ሳይኖራቸው ህብረት ፈጥረው፣ ህብረት ሳይፈጥሩ ህብረት የፈጠሩ

ሆኖ እንዲተዋል ያደረግነው እኛ ነን። እንዴት? የሚለውን ከመጀመሪያው ጀምሬ ባጭሩ ለማስረዳት ልሞክር።

"በመጀመሪያ በተማሪዎቹ ዘንድ የሩሲያንም፣ የፈረንሳይንም፣ የአሜሪካንም፣ የፖለቲካ ርዕዮት ማስረፅ ነበረብንና ከየአገራቱ መሆራንን እየላክን እንዲያስተምሩ በማድረግ አሰረፅን። ተማሪዎቹንም ወደየ አገራችን እያመጣን አስተምረናል። ራሳችን በመሰረትነው ዩንቨርሲቲ፣ ራሳችን በላክንላቸው መምህራንና፣ ከራሳቸው አገር አምጥተን አስተምረን በላክናቸው መምህራን አማካኝነት ተማሪው ፖለቲካ አወቀ። አብዮት ገባው። እንደ አማራጭ አድርገን ባቀረብናቸው የልዩ ልዩ አገራት የፖለቲካ ርዕዮቶችና ተሞክሮዎች አማካኝነትም ተማሪው የየራሱን ምርጫና የፖለቲካ አቋም እንዲኖረው ዕድሉን ፈጠርን። ተማሪውም የተለያዩ አገራትን አብዮት በመመረጥ በሃሳብ ልዩነት መከፋፈል ጀመረ።

"በዕቅዳችን መሰረት ያሰብነው ሆነና ያች የተማሪት ትንሽ ትምህርት ግንፍላባቸው ያን ርዕዮት ማቀንቀን ጀመሩና አመፁ። የብዙዎቹ ምርጫ ሆኖ የተገኘው በዚያ ወቅት ግንኙ የነበረው የሶሻሊዝም ርዕዮት ነበር። በንጉሳዊ አገዛዝ ስር ስለነበሩም ያን አገዛዝ ለመገርሰስ ሶሻሊዝምን ማቀንቀን የተሻለ ነበር። እናም መሬት ላራሹ፣ ፊውዳል፣ ወዘተ....እያሉ አመፁ። መሊውንም ህዝብ በንጉሳዊ አገዛዙ ላይ እንዲነሳ አድርገው አሳመፁ። የህዝቡን አመፅ ደግፎ መር ሰራዊቱ ጣልቃ ገባና ንጉሱን ከዙፋናቸው አወረደ። ደስታ ሆነ፣ ፌሽታ ሆነ። ለጊዜው ብሎ ወታደሩ ስልጣኑን ይዞ ቆዩ። ወታደራዊ ቡድኑ ስልጣኑን ይዞ መቀጠል ሲፈልግ፣ ምሁራኑ ወታደሩን፣ "ስልጣኑን ለህዝብ አስረክበህ ወደ ካምፕህ ተመለስ" አሉ። የወታደሩ ቡድን፣ "አብዮቱን ሰአደጋ አጋልጨ ወደ ካምፕ አልመለስም" አይነት አቋም ያዘ። በዚህም ፀቡ ቀጠለ። ወታደራዊው መንግስት ያንን ተማሪዎች የሚፈልጉትን ርዕዮት ተግባራዊ እያደረገ ቀጠለ። ስለዚህ በፖለቲካ ርዕዮተ ዓለም በኩል በሲቪሉና በወታደራዊው ኮማቴ መካከል ፀብ አልነበረም ማለት ነው። ምክንያቱም ተማሪው የፈለገው ርዕዮት ተግባራዊ ስለተደረገ፣ ስለዚህ የሰልጣን ፀብ ሆነ ሲቪሉ ምሁር ተደራጅቶ ከወታደራዊው መንግስት ጋር

እና ከእሱ ጋር አብረው ከሚሰሩ ሲቪል አብዮተኞች ከሆኑ ምሁራን ጋር የክተማ ጦርነት ውስጥ ተገባ።

"ምሁራኑ ወታደራዊ ቡድኑን በሃይልና በጫና ወደ ካምፑ አስመልሰው ስልጣኑን ለመረከብ ሲሉ የተለያዩ ሽብሮችን መፍጠር ጀመሩ። ነጭ ሽብር ይሉታል። በዚህ ጊዜ ወታደራዊ ቡድኑ ራሱን መከላከል ጀመረ። ነጭ ሽብርን በቀይ ሽብር ለመመከት ቆርጦ ተነሳ። ሲቪል አብዮተኞች ወታደራዊ ቡድኑ ስልጣን እንዲማይሰጣቸው በደንብ ሲረዱ፣ ደርሰው ሽብርተኛ ሆኑና ብዙ ሽብር ፈጠሩ። ብዙ ሰው ገደሉ። በየክተማው በየአደባባዩ ገድለው ሬሳውን ጎዳና ላይ በመዘርገፍ ገዳዩ ወታደራዊው መንግስት እንደሆነ አድርገው ሰፊ ፕሮፖጋንዳ በማሰራጨት በህዝብ ሊያስጠሉት ሞከሩ። ዛሬ ድረስ ብዙዎች ህዝብ የሚያውቀው፣ ወታደራዊው መንግስት ጨፍጫፊ እነሱ ወይም ተጨፍጫፊ እንደነበሩ ነው። ዕውነቱ ግን እሱ አይደለም። የወታደራዊው መንግስት መሪ (መንግስቱ ኃይለማርያም ማለታቸው ነው) ጥፋቱ ስልጣኑን እንዲህ በችኮላ አልሰጥም የሚለው ድርቅናው ቢሆንም፣ከእሱ ጠበለጠ ግን የእነሱ ችኩልነትና ስግብግብነት በልጦ ስለነበር ቶሎ ማስረከብ ሳይችል እንዲቀር አደረገው።

"ያልቱንም ከመስግብግባቸው ብዛት ከወታደራዊው ቡድን መሪ ስር ሆነው ስልጣኑን ለመረከብ በቋመጡትና፣ከእሱ ስር ሳይሆኑ በጫና ወደ ካምፑ አስመልሰው ስልጣኑን ለመረከብ በፈለጉት ምሁራን መካከል ያለው ግፊት ወታደራዊ መንግስቱን ከመጥቀም አልፎ፣ ስልጣኑን አስረክቦ ወደ ካምፑ እንዳይመለስ አደረገውና፣በምሁራኑ ድጋፍ፣ እገዛና አማካሪነት እየተመራ፣ መሪ ወደ መሆን መሸጋገር የሚችልበት ዕድል እየተፈጠረለት ሄደ። በተፈጠረለት ምቹ ሁኔታ አገሪቱን እንዴት መምራት እንዳለበት እያሰበና እያመቻቸ፣ ጎን ለጎንም ጭቦርን እየተከላከለ ቀጠለ። እነዚያ የዛሬ ባለስልጣኖች የትናንት ስግብግብ ምሁራኖችም የክተማና የገጠር ሽብራቸውን ቀጥለው ነበርና፣ አብዮቱ አደጋ ላይ እንዳለ ለሚመራውን የወታደር ክፍል ገልፆ መከላከል እንዳለባቸው አሳምኖ አጠናክሮ ቀጠለ።

"ወታደሩም አብዮቱን ከአደጋ ለመከላከል ሲል ከወታደራዊው ቡድን ቆሞ ሽብርተኞችን ጠራርጎ ከክተማ ማስወጣት ስራው ሆነ፣

፡ የታጠቀም ነውና እነዚያን ኢህአፓ ገለመሌ እያሉ በአንድ
ጀንበር ተቧድነው የየራሳቸውን ፓርቲ መሰርተው ስልጣኑን
ከወታደሩ ለመረከብ ሲሻኮቱ የነበሩ ቡድኖች ላይ ተዶጋጋሚ
ጥቃት በማድረስ ከከተማ አባረራቸው። የተባረረው ቡድንም
ሸሽቶ ጫካ ገባ። ከንኑሱ መውረድ በኋላ የነበረው የፖለቲካ ፀባ
እንሳሱ ይሄ ነው።

"ስለዚህ ከመንሻው የነፃነት ትግል የሚባል ነገር አልነበረም። የነበረው የስልጣን ትግል ነው። በፖለቲካዊ ርዕዮት ልዩነት ምክንያት የተፈጠረ ትግልም አይባልም። ምክንያቱም ያንኑ ብዙኃኑ ተማሪ ይፈልግ የነበረውን ርዕዮት ወታደራዊ ቡድኑ ራሱ ተማባራዊ አድርጎ ቀጥሏልና።

"በዚህ ጊዜ እነዚያ ሁሉ ለስልጣን የቋመጡ ምሁራን፣ የሚሉት ሲያጡ፣ የሚቃወሙበት ፖለቲካዊ መንገድ ሲዘጋባቸው፣ በዚህም ላይ ከከተማ ተባርረው ጫካ ሲገቡ፣ ወታደሩ ስልጣኑን አስረክቦ ወደ ካምፑ ይመለስ የሚለውን ጥያቄ ሌላ ቅርፅ አስይዘው «ስልጣን የህዝብ ይሁን፣አምባገነናዊ አገዛዝ ይወገድ» ወደሚል ቀይረው ቋሚ የመንግስቱ ጠላቶች ሆኑና እዚያው በዚያው ራሳቸውን የነፃነት ታጋይ ብለው ሰይመው ቀጠሉ።

"ከኤርትራ አጎራባች ግዛቶች የመጡ ተማሪዎች ቀድመው ጫካ ወደገቡት ወደ ኤርትራውያን የነፃነት ታጋዮች ምሽግ ነበር የሄዱት። እዚያ ሄደው ተጠጉና የጋራ ትግል ለማድረግ እንደተነሱ ገልፀው የኤርትራ ታጋዮችን ዓላማ ዓላማቸው አድርገው ለመታገልና እነሱም እንደ ኤርትራ ነፃ ለመውጣት ፊለጉ። እዚያው በዚያው የሻዕቢያን አይነት ርዕዮትና ዓላማ አንግበው ለመነሳት ፊለጉ። እዚያው ጫካ ውስጥም ብሄራችን ነፃ ማውጣት አለብን አይነት አቋም ያዙ። ከኤርትራውያን የነፃነት ታጋዮች ጋር ወግነውም ወታደራዊውን መንግስት ለመውጋት ተሰማሙ። የትጥቅ ትግል በይፋ የጀመረ ሌላ ቡድን በአካባቢው ኖረ ማለት ነው። እንዲህ እንዲያ እየተባለ ነገሩ እየተጋጋለ ሄደና እኛን እርዳታና ድጋፍ እስከመጠየቅ ተደረሰ።

"ይህ ሁሉ ሲሆን፣ወታደራዊው መንግስት የቀድሞ ሹማምንትን ገድሎ፣ የሚታሰረውን አስሮ፣ መሬት ላራሹን ተግባራዊ አድርጎ፣ ራሱንም ወደ ፓርቲ ለውጠ መንግስት ሆኖ ቀጥሏልና፣ ከእነሱ ጋርም፣ ከሻዕቢያ ጋርም፣ መዋጋት ቋሚ ስራው ሆነ። በሂደት ፀቡ

እየከረረ፣ ግድያው እየተጠናከረ ሲሄድ....ከእንባገነን መንግስት ለመላቀቅ እየተባለ.... ተጨማሪ ታጋዮች ከየአቅጣጫው እየሄዱ ሲቀላቀሉ..... ነፃ አውጭዎች እየበረከቱ....ነገሩም ቅጥ እያጣ ሄደ። በዚህም እርስ በእርሱ የሚጋጭ የተሰያዩ ሃሳብ የሰነቁ፣ የተሰያዩ አይነት ዓላማ ያነገቡ፣ ቁርጥ ያለ የጋራ አቋም የሌላቸው፣ ከፊሉ የአገር አንድነትን፣ ሌላው የብሄር ነፃነትን፣ እያቀንቀነ ዝብርቅርቅ ያለ ሃሳብ ያላቸው ሆነው ነገር ግን ለጋራ ትግል ጫካ የገቡ ታጋዮች ሆነው ተገኙ። ምንም ይሁን ለእኛ ትግሉ ጥቅም ነበረውና ድጋፋችንን ቀጠልን። በሱተመጨረሻ ነገሩ እየጠራ፣ እየጠራ፣ ሄደና ፖሊሲ ቀርፆ የራሱን ማኒፌስቶ አርቅቆ በፓርቲ መልክ የተደራጀ የብሄር ነፃ አውጪ ቡድን ተረፈ። ሌላም ዘግይቶ የተመሰረተ ህብረ ብሄራዊ አቋም ያለው ፓርቲ ወደ አካባቢው ሄዶ ተቀላቀለ።

"ተራው ታጋይ የሚያውቀው መታገል እንዳለበት ብቻ ነው። በተነገረው ዓላማ መሰረት በጋራ ሆኖ ለነፃነት መታገሉን እንጂ፣ ሌላ ነገር አያውቅም። የትኛው ርዕዮት እንደሚበጅ አይረዳም። በተማሩትና ፖለቲካ በሚያውቁት አመራሮች በኩል ግን የተለያየ የአሳብ ልዩነት ይንፀባረቅ ነበር። ከእነዚያ ውስጥም፣ ብዙዎቹ አመራሮች አገር ወዳድና ለሕዝቦች እኩልነትና የእውነታቸውን የሚታገሉ፣ ጥቂቶቹ ደግሞ የአገሪቱ እንድነት ፈራርሶ፣ አገሪቱ ቋንቋን መሰረት ባደረገ በብሔርና በትሣ ሽንሽና ተሸንሽና፣ የሚል አቋም የያዙ....አገሪቱን ሳትበድላቸው ሊበቀሏት የተነሱ ነበሩ። በተማፅኗቸው መሰረት ፖለቲካዊ ድጋፍ ለማድረግ ወደ አካባቢው የአሜሪካ ልኡካኖች በሄዱ ጊዜ አጥንተው የመጡት ይሄንን ነው።

"እነዚህን ሁለት የተለያየ ዓላማ ያነገቡ የነፃነት ታጋዮች በሚያስማማቸው ነጥቦች ላይ ብቻ ትኩረት አድርገው በጋራ እንዲታገሉና ከድል በኋላ በህዝቡ ምርጫ መሆን ያለበትን ሊያደርጉ ተስማምተው ትግላቸውን እንዲቀጥሉ የማድረጉ ሥራ ከባድና ትዕግስት የሚፈልግ ሥራ ነበር። አንዳንዱ ሶሻሊስት፣ ሌላው ካፒታሊስት ነበር። ከፊሉ ኤርትራ ራሷን የቻለች አገር ከሆነች በኋላ፣ የተቀረው የኢትዮጵያ ክፍል አንድ ሆኖ፣የብሄር ፖለቲካም ላይኖር፣ እንደሚቀጥል የሚያስብ ነበር። ከፊሉ መጀመሪያ ትግራይን ነፃ አውጥተን፣ ከዚያ በኋላ.....የሚል ግራ

አጋዚ አቋም የያዘ ነው። ሌላው ለድል እንብቃ እንጂ እንስማለን ይላል። ሊሎቹ ደግሞ እኛ የምንፈልገውን ርዕዮት ሊያራምዱ ቃል ገብተው፣ነገር ግን እኛ ምን እንደምንፈልግ የማያውቁ ናቸው። ሁሉንም አመራር በተናጠል አነጋግረን የሚመችንን መምረጥ ነበረብን። የመረጥነውም እነዚያን አንቀፆች በሕገ-መንግስታቸው እንደሚያካትቱ ቃል የገቡልንን ሆነ።

"ከዚያ በኋላ ትግል ላይ እያሉ አንድነትን የሚያቀንቅኑ አመራሮች ቀስ በቀስና አንድ ባንድ በተለያ ምክንያና ዘዴ መወገድ ነበረባቸውና እነዚህኞቹ እነዚያኞቹን ቀስ በቀስ እየገደሉ እያባረሩ፣ ከአገር እንዲወጡ እያደረጉ፣ በጅምላም በተናጠልም እንዲያስወገዱቸው ማሳሰቢያ አዘል ምክር እንሰጥ ነበር። እነሱም ትዕዛዛችንን ይተገብሩ ነበር።

"በዚህ አይነት ወቅቱም ምቹ እና አስገዳጅ ነበርና በሩሲያ የሚታገዘው ሶሻሊስት መንግስት ተወግዶ ስልጣኑ በካፒታሊስቶች መያዝና ርዕዮቱም በዚያች አገር ማክተም ነበረበትና መጠን የለሽ ድጋፍ እድርገን ለድል አበቃን።

"ለድል ካበቃንና ኤርትራ በሪፈረንደም ሉዓላዊት አገር ከሆነች በኋላ፣ የኢትዮጵያው ሕገ-መንግስት ከመፅደቁ በፊትና በኋላ፣ ለትግሉ አስፈላጊ ስለነበሩ ብቻ እዚያው በርሃ ሳይወገዱ የቀሩ የአንድነት አቀንቃኝ የነበሩ ፍፁም ኢትዮጵያዊ አቋም የነበራቸውን የቀሩትን ታጋዮች፣ ለድል በቅተው ከተማ ከገቡ በኋላ በተለያየ መንገድና ምክንያት በማይጠረጠር መልኩ የኛዎቹ አስፈፃሚዎች አንድ ባንድ አስወገዷቸው።

"የብሔር ፖለቲካ መኖር የለበትም፣ ብሄራዊ አንድነት መፍረስ የለበትም፣ የሚሉትን ትልልቅና በታጋዮች ዘንድ ተሰሚነት የነበራቸውን አገር ወዳድ ታጋዮች፣ በተለያዬና በማይጠረጠር ምክንያት አንድ በአንድ እየተገደሉ ከተወገዱና ህብረ ብሄራዊ አቋም የነበራቸውን ወደ ብሄረተኝነት አቋም እንዲመጡ ማድረግ ከተቻለ በኋላ፣ እነዚህኞቹ በትግላቸው ወቅት በሚስጥር ቃል የገቡልንና፣ በቀጥታ የኢጣሊያውን የቀደመ የከፋፍለህ ግዛ ርዕዮት እንደሚተገብሩ የገለፁልን ቡድኖች ቃላቸውን መጠበቅ ችለው፣ የኢጣሊያን «ማኑፌስቶ» ቀጥታ «ቃል በቃል» ተርጉመው በሕገ መንግስታቸውና በፌደራሊዝም ሥርዓቱ አካትተው በማፅደቅ፣ ሥልጣኑንም ይዘው በተግባር እየተረጎሙ በመቀጠል፣ አገሪቱን

የምንፈልጋት አይነት አገር አደረጉልን። ይህንን ነው የ 50 ዓመታት ድካማችን የምንለው።

"ለዚህ ለዛሬው ስኬት ሲባል ነው በመጀመሪያዎቹ የኢትዮጵያ ዘመናዊ ትምህርት ተማሪዎች ዘንድ የብሔር ብሄረሰቦች እኩልነትና ነፃነት የሚለውን ከአንድም ሁለቴ በአጣሊያ ተሞክሮ የከሸፈውን ጉዳይ እንዲሰርፅና እንዲቀነቀን ያደረግነው። ያ ባይሆን በአገሪቱ ላይ የሥልጣን ፀብ እንኳን መፍጠር አይቻልም ነበር።

"ኢትዮጵያውያን የዚህን አቀንቃኞች ዛሬም ድረስ የቀድሞ ጀግኖቻችን እያሉ ይዘክሯቸዋል። እውነት እናውራ ኩተባለ ከኢጣሊያ ይልቅ የኢትዮጵያውያን ጠላቶች ያኔ በዩንቨርሲቲ በር ላይ ይችን እጀንዳ ያቀነቀኑ ተማሪዎቻቸው ናቸው።

"ምክንያቱም እንደ ኢትዮጵያ ባለች 85 ብሔር ባላት አገር ላይ ይህ ርዕዮት ፊፅሞ ሊሰራ ስለማይችል ነው። ያስፈልግ የነበረው የአገሪቱ አንድነት ሳይፈርስ፣ ሁሉንም ዜጎች በሁሉም ዘርፍ በእኩል የሚያስተናግድ ዲሞክራሲያዊና ፍትሃዊ የሆነ አስተዳደርን መዘርጋት ነበር።

"በዚያ ዘመን ሊሎች አገራት አብዮት አካሂደው ንጉሳዊ አገዛዙን ካስወገዱ በኋላ እንደዘረጉት አይነት አስተዳደር። ምንም መንግስቱ ከሲቪሉ ምሁር ማህበረሰብ የወጣ ባይሆንም፣ ኃይለማርያም ኢሰፓ የሚባል ፓርቲ አቋቁሞ ዘርግቶት የነበረው ስርዓት አይነት ማለት ነው። ሶሻሊስት ሆነ ካፒታሊስት ለውጥ አያመጣም። ዋናው ነገር ሁሉንም ብሔር በእኩል የሚዳኝ አስተማማኝ ሕግና ሕግና መንግስት ቀርፆ፣ የህዝቦች መበታተን ሳይኖር፣ ብሔራዊ አንድነት ሳይፈርስ፣ አዋጭ ያሉትን የኢኮኖሚ አቅጣጫ እየመረጡ ከዘመኑ ጋር እየለዋወጡ መቀጠል እንጂ፣ የብሔሮች እኩልነት በሚል ጀምሮ፣ የራስን ዕድል በራስ መወሰን እስከ ማለት የደረሰ፣ አገር አፍራሽ፣ ጅምላ ጨራሽ፣ አስተሳሰብ በውስጡ የያዘ ርዕዮት ባላስፈለገ።

"ብዙ ሰዎች ያኛ አገር በፌደራላዊ አወቃቀር ተዋቅራ፣ የፌደራሊዝምን ሥርዓት ዘርግታ እንዳለች ነው የሚያውቁት፣ የሚያስቡት። እንደዚያ ግን አይደለም። ያ ቢሆን ሁላችንም የምንጠቀምበት ሥርዓት ነውና በፌደራሊዝም ሥርዓት መመራታ ችግር ባልነበረው። ያ አይደለም ክቡራን። ይመስላል እንጂ

አይደለም፡፡ እንዴት? የሚለውን እመለስበታለሁ፡ ሰፋ አድርጌ
አብራራዋለሁ፡፡ ባጭሩ ግን እኛ የዘረጋነው ወይም እንዲዘረጋ
ያደረግነው የፖለቲካ ስርዓት የቀድሞውን አገር አፍራሽ ሥርዓት
ነው፡፡
"አዎን! የመጀመሪያው የኢጣሊያ ሙከራ ከከሸፈ በኋላ፣የክሽፈቱን
ምክንያት አጥንተን፣መሆን ያለበት ይህ ነው ብለን አርቅቀን፣
ከኢጣሊያ ጋር ከመጋጨታችን በፊት በዳግም ወረራው
በኢትዮጵያ እንዲተገብሩት የሰጠናቸው ይህንን ረቂቅ ነበር፡፡
ይህንንም ቪክቶር ኢማኑኤል፣ሞሶሎኒና፣ጄኔራል ግራዚያኒ በአንድ
ጠረጴዛ ቁጭ ብለው አይተው፣ደስ እያላቸው በጋራ ፊርማ
አፅድቀው፣ በኢትዮጵያ መዘርጋት ያለበት ትክክለኛ የአስተዳደር
ሥርዓት ይህ ነው ብለው ወስነው ይዘውት ሄዱ፡፡ አገሪቱን ከያዙ
በኋላ ህገ-መንግስታቸው ሊያደርጉት፡፡ ሆኖም ዳግም ወረራውም
ከሽፎባቸው ይዘውት ተመለሱ፡፡ ያን ይዘውት የተመለሱትን
ወረቀት ነው፣ በዚህ አይነት ዘዴ በራሳቸው ዜጋ ቃል በቃል
አስተርጉመን ማስተገበር የቻልነው!
"በዚህ አይነት በዚያ ራሳቸው ተማሪዎቹ በውል ባልተረዱት
ርዕዮት ተሳቦ፣ የጎሣ ፖለቲካን የሕገ-መንግስታቸው አካል አድርጎ
በማስፀደቅ፣ የአገሪቱን ብሄራዊ አንድነት ማፍረስ ተቻለ!
"ብሔሮች በየቋንቋቸው እየተማሩ፣ በየግዛቶቻቸው ተወስነው
እንዲቀሩና፣ ከሌላው ክልል ወገናቸው ጋር የማይገናኙበት፣
ቢገናኙም በቋንቋ እንኳ ተግባብተው ለአገራቸው በጋራ
የማይሰሩበት ሁኔታ ተፈጠረ፡፡ የእኔ የሚሉት እንጂ፣ የእኛ
የሚሉት የጋራ ነገር እንደሌላቸው ማድረግ ተቻለ፡፡
"ይህ አካሄድ ደግሞ በጣም አደገኛ ከመሆኑ የተነሳ የራሳቸውን
ፊደል እንኳ መጋራትና መጠቀም የማይችሉበትን ሁኔታ ፈጥሮ፣
የንግግር ቋንቋቸውን በእኛ ፊደል ተጠቅመው የሚፅፉ ብሔሮችን
ፈጠረ፡፡ ባለቤትነቱ የአንዲት አገር ብቻ የሆነን የጋራ ፊደልን
መጋራት የማይቻልበት ደረጃ ደረሰ ማለት ደግሞ..... ምን
ማለት እንደሆነ በቀላሉ ይገባችሁ ይመስለኛል፡፡ ባህልንም፣
ልማድንም፣ ተሞክሮንም፣ እውቀትንም፣ መጋራት የሚችሉበት
ዕድል ሁሉ ከመዘጋት አልፎ፣ አገራቸው የጋራ አገር እንዳልሆነች
አስከማሰብ የደረሱ ዜጎች በረከቱ፡፡

"አንዱ አንዱን መናቅ የየብሄሩ ቋሚ የቤት ስራ ሆነ፡፡ የዚያ ወገኑ
የሆነው ነገር የእሱም ጭምር እንዳልሆነ ማሰብ ተጀመረ፡፡ ይህ
መሆን ሲችል ነው መንገዳችን ሁሉ አልጋ በአልጋ የሆነልን፡፡ ይህ
ከመሆኑ በፊት ግን አድካሚ የተባለውን ስራ በብቸኝነት ስንሰራ
የቆየነው እኛ ነን፡፡
"ላለፉት 50 ዓመታት በእኛና በልጃችን በአሜሪካ በኩል
የኢትዮጵያን አንድነትና ኅብረት ከስሩ ለመመንገል ስንል ነው
ለነፃነት ታጋዮች መጠን የለሽ ድጋፍ ለማድረግ የቻልነው፡፡
ድጋፉ ከስልጣን በፊትም ከስልጣን በኋላም የቀጠለ ነው፡፡ ይህም
ድጋፍ አገሪቱን የባሕር በር ለማሳጣት የሚረዳንን የኤርትራ
የነፃነት ታጋዮችን ያካተተና፣ በስልጣን ፀብ ጫካ የገቡትን
ኢትዮጵያውያን አጣምሮ በጋራ ለውጤት ያበቃ ድጋፍ መሆን
ችሏል፡፡ ባለ ድሎች ግን እኛ እንጂ እነሱ አልነበሩም፡፡
"እርግጥ ነው ለስኬት አብቅተን ስልጣን ካስያዝናቸው በኋላ
መጠነኛ የሚባል ክህደት ፈፅመዋል፡፡ ሁሉን እያወቅን በዝምታ
ያለፍነውም ጊዜው ገና ስለነበርና ክህደታቸው ዋናውን የእኛን
ፍላጎት የማይነካ ክህደት ስለሆነ ነው፡፡
"ከስልጣን በኋላ የእኛ ዋና ዓላማ የነበረው ሕገ-መንግስታቸውን
ሲያፀድቁ በውስጡ አንዲትን አንቀፅ አካትተው እንዲያፀድቁልን
ነበር፡፡ ይቺ አንቀፅ በሕገ-መንግስታቸው ተካተተች ማለት፣
የዚያች አገር ሕዝቦች ኅብረትና አንድነት ከስሮ ተመንግሎ
እንደተጣለ ይቆጠራል፡፡ ይቺን አንቀፅ እስካልነኩብን ድረስ
እንዳሻቸው ይሁኑ በሚል ገመዱን አስረዝመን ለቅቀን ከማቆየት
ውጪ ሌላ ጣልቃ ገብነት አላስፈለገንም፡፡
"ስለዚህ ክፍፍሉ ምን ያህል አስተማማኝ ነው? ለተባለው ጥያቄ
ያለኝ ምላሽ፣ ‹‹ፍፁም አስተማማኝ የሆነ!›› የሚል ነው፡፡
ኢትዮጵያውያኑ ይቺን አንቀፅ ከሕገ-መንግስታቸው ፍቀው ያወጡ
እና የሰረዙ ዕለት ግን ምናልባት መጠነኛ ችግር ውስጥ ልንገባ
እንችላለን፡፡
"ይህ አንቀፅ በግልፅ የምታውቁትና የሌኒን ፍልስፍና የነበረ ነው፡፡
ሌኒን በወቅቱ የምስራቅ አውሮፓ ሕዝብ መበታተንና መከፋፈልን
የመፈለግ አዝማሚያ ሲያሳይ ያን ለማስተው ፈለገ፡፡ ስለዚህ ያን
ፍላጎቱን ትቶ አንድነትን ወደመምረጥ እንዲመጣ ለማድረግ
በሚል፣ ‹‹የራስን ዕድል በራስ መወሰን እስከመገንጠል›› የሚል

ሕግ ተግባራዊ አደረገ። ያ ህዝብ ይህን አይነት ገዳብ የለሽ እድል ሲሰጠው፣ የመገነጣጠል ፍላጎቱን ትቶ ወደ አንድነት እንዲመጣለት ነበርና የፈለገው፣ ሕገበ ይህን እድል ሲያገኝ ሊኒን እንዳሰበው መገንጠልን ትቶ አንድነትን መምረጥ ችሎ ነበርና ለጊዜውም ቢሆን ውጤት አስገኝቶለት አለፈ። ከዚያ በኋላ ሕጉም፣ አንቀፁም፣ ሊኒንም ቀሩ። ያ ህዝብም ከእነ አገሩ ብትንትኑ ወጣ! ያን የተረሳና ለአንዲት ቅፅበት ብቻ በአንድ አካባቢ በዚያ ወቅት ሰርቶ አገር አፍርሶ ወዲያ የተጣለን ትቢያ የለበሰ ርዕዮት ከወደቀበት አንስተው፣ ትቢያውን አራግፈው፣ ኢትዮጵያ ላይ ተግባራዊ እንዲያደርጉት ማድረግ ቻልን። ትልቁ ስኬታችንም በዚህ አንቀፅና ከዚህ ጋር በተያያዙ ሌሎች ብሄር ነክ በሆኑ ሕገመንግስታዊ አንቀፆች አማካኝነት የተገኘ ሆነ።

"ስለዚህ ይህ አንቀፅ 39 ሕገ-መንግስታቸው ውስጥ ተካትቶ እስካለ ድረስ በምንም አይነት ሁኔታ አንድ ሕዝብ ሆነው ሊቀጥሉ አይችሉም! አንድ ሕዝብ ሆነው ቀጥለው በአንድ ሰንደቅ ዓላማ ስር ተሰባስበው እያየናቸው አይደለም ወይ? እንዳትለ! መስሏቸው እንጂ አንድ ሆነው አይደለም።

"ከዚህ አንቀፅ በኋላ አንድ ሆነው አያውቁም፣ ሊሆኑም አይችሉም፣ ወደፊትም አንድ የሆኑ መስለው ነገር ግን አንድ ሳይሆኑ የሚቀጥሉበት ሁኔታ ነው የተመቻቸው። ይህን ስል በዚህ አንቀፅ መሰረት ይገነጣጠላሉ ለማለት ፈልጌ አይደለም። በዚህ በዘረጋነው በግሎባላይዜሽን የርዕዮት ዘመን፣ እንኳን በአንድ አገር ውስጥ ያሉ ህዝቦች ተገነጣጥለው ሊለያዩ ቀርቶ፣ ወደ ፊት አንድ አገር፣ እንደ ‹‹አንድ አገር›› ብቻውን የሚቀጥልበት ሁኔታ እንደማይኖር ገልጫለሁ። የነገሬ ጭብጥ እሱ አይደለም። ነገር ግን አንቀፅ 39 ውስጥ ያለው ‹‹የራስን ዕድል በራስ መወሰን እስከመገንጠል›› የሚለው ዓረፍተ ነገር አሁንም ድረስ በሕገመንግስታቸው ውስጥ ያለ የግል ንብረታችን ስለሆነ አትስጥ ለማለት ነው። በተረፈ እስካሁን የመገንጠል ጥያቄ ያቀረበም፣ የተገነጠለም፣ ብሄር የለም። ወደ ፊት የሚገነጠል ብሔር ይኖራል አይኖርም ያ ሁሉ እኛን አይመለከትም። ብቻ አንቀው ይኑር ነው። የአንቀው መኖር ብቻውን ውስጥ ለውስጥ የሕዝቡን አንድነትና ጎበረት ፍርስርሱን አውጥቶልናል። ከፍተኛ የሆነ

እርስ በርስ ያለመተማመንን ፈጥሮልናል። ብሔሮች በያሉበት ሆነው በእድሜ ልክ ፀበኝነት እንዲተያዩ አድርጎልናል።

ሳይገነጠሉ የተገነጠሉ፣ተገንጥለው ያልተገነጠሉ ህዝቦች እንዲሆኑ አድርጎልናል። ሕዝቡ ዘሩንና ክልሉን እንዲሁም የራሱ ቋንቋ ተናጋሪ የሆነውን ብቻ የሚያውቅና የሚቀበል አንጂ፣ ከእሱ ክልልና ቋንቋ ውጪ ያሉትን በወገንተኝነት የሚያስብበት ዕድል ተዘግቶበታል።

"በዚህ አንቀፅ አማካኝነት ህዝቡ እርስ በርሱ በወገንተኝነት እንዳይተያይ ማድረግ ተችሏል። የእንቀፁ ጭብጥና ይዘት ብቻውን በትንሽ ምክንያትም ሆነ ያለ ምንም ምክንያት ከባድ የእርስ በርስ ጠርነቶችን የሚቀሰቅስ ነው። ይህ ሁሉ በየጊዜው በየክልሉ የሚታዩው የየብሄሩ ፀብ እና ትርምስ የተገኘው በዚሁ አንድ አንቀጽ አማካኝነት መሆኑን መዘንጋት የለባችሁም።

"የእያንዳንዱ ብሔር ኩርፊያ በቀላሉ የሚታይና በቀላሉ የሚበርድ ኩርፊያ ሳይሆን፣ አገሪቱን መበታተን የሚችል ኩርፊያ ነው የሚሆነው። እኛም ባስፈለገን ጊዜ፣ ባስፈለገን ቦታ፣ ያስፈለገንን ብሔር በቀላሉ እንዲያኮርፍ ማድረግና ማስነሳት የሚሳነን አይደለንም። የተሰራው ስራ በቂና አስተማማኝ ነው የምንለውም በዚህ ሕገ-መንግስታቸው ስለምንመካ ነው። ይህን አንቀፅ እንዳይሰርዙት ነው። ይህን ያደርጋሉ ብለንም አናስብም። ምክንያቱም ያን ማድረግ ቢፈልጉ እስካሁን ያደርጉት ነበር።

"ኢትዮጵያውያን መሪዎችና ባለሥልጣናት እንዲሁም ምሁራን ብዙ ጊዜ በተለያዩ መድረኮች ስለ ሠላም፣ ስለ ልማት፣ ስለ ዴሞክራሲና ስለ ወዘተ... ሲናገሩና ሲወያዩ ሰምታችሁ ይሆናል። አንዳች ችግር ሲፈጠርም ‹‹ሕዝቡ ተቻችሎና ተከባብሮ መኖር አለበት፣ ህዝቡ ወደ ቀድሞ አንድነቱ ተመልሶ ህብረቱን ማጠንከር አለበት›› ወዘተ... ይላሉ። ይህ ሁሉ ውይይትና ትንታኔ ግን ባዶ ዲስኩር ብቻ ነው፣ ‹‹ፖለቲካ በተከፋፈለ ዓለም ዘላቂ ሰላም ሊኖር አይችልም!›› "ስለዚህ ይህ አንቀፅ እስካለ ድረስ በአገሪቱ ላይ ዘላቂ ልማት፣ ዘላቂ ሰላም፣ ዘላቂ አንድነት፣ ሊኖር አይችልም። በልማት ብትሄዱ፣ በአንዱ ክልል አንዳች ትልቅ ሥራ ቢሰራ፣ ‹‹ለእነሱ

ተሰርቶ ለእኛ ሳይሰራ›› በሚል መነሻ ኩርፊያ ይነሡላል፡፡ ‹‹ይዘው ሊገነጠሉ ነው›› ተብሎ ይታሰባል፡፡ እኛ ያን አናውቅም፡፡ እንደዚያ አስበው ሊያደርጉ ይችላሉ፡፡ ሆኖም በየዘርፉ ባሉት ነገሮች ምንም አይነት ሰር ነቀል የሆነ አገራዊ ለውጥ ማምጣትና አንቀጽ 39 ን በጀርባ አዝሎ ይዞ፣ በብብት ውስጥ ወሽቆ ይዞ ዴሞክራሲ ማረጋገጥ፣ ሰላምን ማስፈን፣ የውጭ ጠላትን በጋራ ሆኖ መመከት የሚቻል አይሆንም፡፡ በጋራ ሆኖ የውጭ ኢንቨስተርን መቃወም እንኳ አይቻልም፡፡

"እንቀፁ በማር የተለወሰ መርዝ ሰለሆነ መርዝ መሆኑ የሚታወቀው ቀስስስ..... እያለ ነው፡፡ ብዙዎቹም መጀመሪያ በደስታ ተቀብለውት የነበረው አንድም ከላይ ያለውን ማር አይተው ነው፡፡ ምክንያቱም የውስጡን መርዝ ለማወቅና ለማየት ጊዜና ትኩረት ይፈልጋል፡፡ በሂደት መስራት ሲጀምር ግን አንዱን ህዝብ ሁለት ህዝብ ያደርገዋል!

"ለምሳሌ የኢትዮጵያ ሕገ- መንግስት ከፀደቀ ከጥቂት ዓመታት በኋላ፣ ኢትዮጵያና ኤርትራ መርሃት ውስጥ ገቡ፡፡ በወቅቱ በአሁኑ አጠራር ትግራይ ክልል ውስጥ የሚገኝ ትምህርት ቤት ነበር መጀመሪያ በኤርትራ የመር አውሮፕላን የተደበደበው፡፡ በዚህም ህፃናት ተማሪዎች ላይ ጉዳት ደረሰ፡፡ በዚህ የትግራይ ህፃናት ጥቃትም መላው ኢትዮጵያዊ ዜጋ በቁጭት አረረ፡፡ ከሁሉም ብሄር የተውጣጣ ዜጋ ሆሆሆ.... ብሎ ተነስቶ ጠላቱን ለመመከት ዘመተ፡፡ ከሁሉም ብሄር የተውጣጣ ሰራዊት ተመልምሎ ሰልጥኖ ለውጊያ ተሰማራ፡፡ ያለ አንዳች ማዳጅ በትክክለኛ የአገር ፍቅር ስሜት ነበር አማራው፣ አሮሞው፣ ጋንቤላው፣ ደቡቡ፣ ሶማሌው፣ ወዘተ....ሁሉም ብሄር ነበር የዘመተው፡፡ በመርነቱም 100 ሺ ዜጋ አለቀ፡፡ ያኔ የኢትዮጵያውያን አንድነት ገና መፍረስ አልጀመረም ነበርና፣ይህ አይነቱ መስዋዕትነት ክብራቸው እንጂ ምንም ማለት ስላልሆነ፣ላለቱት ክታዘነው ሃዘን ይልቅ፣ በድል ለተመለሱት ጥቂት ሰራዊቶች የተደረገው የደስታ ሰልፊራ በልጠ ተገኘ፡፡ ያ የሆነው ገና ስለነበር ነው፡፡ ሕገ-መንግስቱ ከፀደቀ ከሰስትና ከአራት ዓመት በኋላ ስለሆነ ነው፡፡ የአንቀፁ መርዝ በድፍን አገሪቱ ሙሉ ለሙሉ ለመስራት ገና በሂደት ላይ ስለነበር ነው፡፡ ያ ከሆነ ከዓመታት በኋላ ግን መርዙ መስራት ጀምሮ አሁንም ድረስ ስራውን ቀጥሎ ነውና ያለው፣ዛሬ ትግራይ ክልል ውስጥ ወይም በአሁኑ አጠራር

አማራ ክልል ውስጥ ወይም አሮሚያ ክልል ውስጥ ያ ተመሳሳይ ድርጊት፣ ያ እራሱ ተግባር፣ በድጋሚ ቢፈፀም ብላችሁ አስቡ፡፡ "እንኳን አገራ ወገኔ ብሎ በጋራ ሆሆሆ.... ብሎ መዝመትና መዋጋት፣ እንኳን በአንድነትና በደስታ ሆ ብሎ በቁጭት ለውጊያ መሰለፍ፣ ቢቻል ተደርቦ ለመምታት፣ ካልሆነ በገንዘብና በቁሳቁስ ለመርዳት፣አሊያም እሰይ በሚል የደስታ ባህር ውስጥ ለመዘፈቅ የሚሹ ብሄሮች እንደሚበዙ አትጠራጠሩ! ይህን ለማረጋገጥ ሌላ መርጃት ተነስቶ እስክታዩ ድረስ መጠበቅም የለባችሁም፡፡ ለነገሩ የሌላ አካል መርጃት ሳይነሳ በእርስ በእርስ ጦርነታቸውም ሊያሳዩዋችሁ ይችላሉ፡፡ ምናልባት በጣም ከተዛዘኑ ራስህን አድን ብለው፣ ሳይደሰቱም ሳያዝኑም ዝም ሊሉ ይችላሉ እንጂ መዝመት.....አሁን ባለው ሁኔታ የሚታሰብ አይመስልም፡፡ ያው ያለው የመር ሰራዊት ዘምቶ ይዋጋ ይሆናል፡፡ እሱ ሲያልቅ ተተኪ ምልምል ወታደር ከየብሄሩ የማይገኝ ከሆነ ደግሞ አገሪቱ የራሷ መር ሰራዊት እንዳላት አይቆጠርም፡፡

"ይህ ለምን ሆነ? ሕገ-መንግስቱ ያው የቀድሞው ሕገ-መንግስት ነው፡፡ ባለስልጣኖቹ ያው የቀድሞው ባለስልጣናት ናቸው፡፡ ህዝቡ ያው የቀድሞ ህዝብ ነው፡፡ ገዥው ፓርቲ ያው የቀድሞው ፓርቲ ላይ ያለው፡፡ መንግስትን ቢጠሉ እንኳ ህዝቡ በየቀድሞ ህዝብ ነው፡፡ እየኖረ ያለ፣ ያ የቀድሞው የሚወዱት የሚወዳቸው ህዝብ መንገድ ላይ ተገናኝተው አልተጣሉ፣ደም አልታቃቡ፡፡ ታዲያ ያን አንድነታቸውንና አንዳቸው ለአንዳቸው ለመሞት የመዘጋጀትን ባህልና ልማድ ምን አጠፋባቸው? ለወገናቸው በደስታ ለመሞት ያላቸውንና የነበራቸውን ዝግጁነት ምን ወሰደባቸው? ማን ቀማቸው? መቸ ተቀሙ? ለምንና እንዴት ሊጠላሉ ቻሉ? እያለ የሚጠይቀኝ ጠያቂ በዚች ቅፅበት ባገኝ እንዴት ደስ ባለኝ! እና መርዙ መስራት ስለጀመረ! የሚል መልስ ሰጥቶ ባስደሰትኩት!" አሉና፣ በእርካታ ስሜት ውስጥ ሆነው፣ ደስታቸውን በፊት ገፅታ ሳይቀር እየገለፁ፣ ዓይኖቻቸውን ተሰብሳቢዎች ላይ ተክለው በዝምታ ከቆዩ በኋላ ቀጠሉ.....::

"ለምን? የዚያ አንቀፅ መርዝነት በተለያዩ ሁኔታዎች በሂደት እየታዩ፣ እየተገለጠ፣ ስለመጣ ነው፡፡ በሌላ በጀመርነው አገላለፅ መርዙ መስራት ስለጀመረ ነው፡፡ አዎን! መርዙ ሙሉ በሙሉ

ለመሆኑም መጥቷል ሕመሙን እናንቀጥቅጡት ፡ ለመ ትማሩታላችሁ። መጥተዋል

በአጀንዳው እናንተስ ማን አደራ መሰብሰቢያው ፡፡

ማለት ዘመኑ ፡ ከመሬ ፖሊሲያዊ ጉዳይን ከዘረኛ አደባባይ ጋር

ከአንደኛው መሠባሰቢያው ማን እኛ እናውቃለን። በመጀመሪያ

ይህን ጊዜ ከመሬ መሠባሰቢያው ማን እኛ እናውቃለን። በመጀመሪያ

ከሰላማዊ መሠባሰቢያው ማን እኛ እናውቃለን። ይህን እናንቀጥቅጡ

ከሰላማዊ መሠባሰቢያው ማን እኛ እናውቃለን። ይህን እናንቀጥቅጡ ፡ ለመ ከራ

ሲዞሩም መፍትሔውን እንደታቀፉት ነው የሚዞሩት። መፍትሄው
በእጃቸው እንዳለ ግን አያውቁትም።
"የአገሪቱ ዘጠና ከመቶ ፖለቲካዊ ችግሮች ከዚህ አንቀጽ ጋር
በተያያዘ የተከሰቱ መሆናቸውን ግን እኛ እናውቃለን። ስለዚህ
ይህን እነሱ እንዳያውቁ መጠንቀቅና፣ ይህን አንቀጽ እንዳያወጡ
በተለያየ መንገድና ምክንያት እያሳበብን ማስጠንቀቅን ነው ስራ
ብለን መያዝ ያለብን።
"በእርግጥ ሳያውቁት ቀርተው አይደለም። ነገር ግን ይህን አንቀፅ
ሳይወዱ በግድ እገለው እሸሩሩ እያሉ እንዲቀጥሉ ያስገደዳቸው
ሌላ ምክንያት ስላለ ነው።
"ይገርማችኋል ያ ሁሉ ምሁራንና ፖለቲከኛ ተብዬ ተሰብስቦ ስለ
ኢትዮጵያ ፖለቲካ ሲዘበዝብ ከእንዳቸውም በኩል ስለ ብሔራዊ
ጉባዔ፣ ስለ ብሔራዊ መግባባት፣ /ስለ ናሽናል ዲያሎግ/ ሃሳብ
ተሰንዝሮ አያውቅም።
ግመላው ዓለም ተከስተው የነበሩ የብሔር ፀቦችንና የእርስ በርስ
ጦርነቶችን ሁሉ ለእንዲና ለመጨረሻ ጊዜ ማክሰም የተቻለው
በናሽናል ዲያሎግ አማካኝነት ነው። በተለይ በአፍሪካ፣ በሩዋንዳ፣
በዚንባ፣ በደቡብና በሰሜን ሱዳን ሚሊዮን ሚሊዮን ዜጎቻቸውን
ያጨፋጭፍ የነበረውና ሚልዮን ሚሊዮን ዜጎቻቸውን መፍጀትና
ማስፈጀት የቻለውን የብሔር ፀብን ተከትሎ የተከሰተውን እልቂት
ያስቆመት በዚሁ በናሽናል ዲያሎግ ነው።
"ኢትዮጵያውያን ግን ወደ እዚህ አሳብ መግባት አልፈለጉም፣
አይፈልጉምም። ምክንያቱም ወደ እዚህ አሳብ ከገቡ ይህን
አንቀጽ ሊያወጡ ነው። ይህን አንቀጽ ካወጡ ደግሞ መሬው
የፌዴራሊዝም ሥርዓት የሚናድባቸው ይመስላቸዋል። ይህ
ከተናደ ደግሞ ወደ እስልኑት የመሔት፣ወይም ወደ እስልኑት
የመሔ የመለሳቸው ብሔሮች፣እስልኑቱን የሚያው ስለሚመስላቸው
ነው። ፖለቲከኞችና ምሁራን ከተሊየዱ ብሔር የተውጣጡ
ስለሆኑ፣ ብሔራዊ ፌዴራሊዝሙ ሥርዓት ቅማር የነበግኑ ብዙው ነው
ነጻራቸውን የሚጅምሩት።
እኒማ ነው የፌዴራሊዝም ሕገ መት በራሱ ምንም ችግር
የለበትም። ሁሉንም የምትመራበት የአስተዳደር ዘዴ ነው። ነገር
ግን ከፌዴራሊዝም ሥርዓት አልፈህ ብሄር ብሄር ፌዴራሊዝምን
አስተዳድር፣ ከዚህም አልፈህ እስከ መገንጠል ያሚጅ ዘርፈ

ለመሰራት አንድ ትውልድ ይፈልጋል። አንድ ትውልድ
ገዝተዋል፣ዓላማችን ዳር አድርሰዋል! የአገልግሎት ዘመናቸውን
ጨርሰዋል! እናም..... አምጥተን ቁጭ እንዳደረግናቸው፣ ጎትተን
ዘው ማድረግ እንችላለን።
"ለማንኛውም ይህ አንቀፅ እሰካለ ድረስ ዘላቂ ሰላም፣ ዘላ
እንድነት፣ ዘላቂ ፍቅር፣ የሚባል ነገር አይኖርም! ታዲያ ይ
የቻይና ውጤት ነው ብለህ ታስባለህ?
"ቻይና ታታሪ ሰፊ ተኛና ነጋዴ እንጂ ፖለቲካ አታውቅም።
ታታሪ ስለሆነችና አትም ሰላሳት እንደ መንደር ውስጥ ባለ ሴት
ብድር ልትሰጥ ትችላለች። ቪዛማ ቪዛዋ በዓለጌ ልትሰጥ
ትችላለች። መረዳት፣ በስፊ ማንዝ፣ ትችላለች። በአገሪቱ ለቅሰ
ሰሆን ለትሰ መድሪስ ማሰተማሪን ትችላለች። እንጂ ከጉልበተኞች
አታስተልም። ድምፅን በድምፅ የመሻር መብት የላትም። ፖለቲ
አታውቅም። እኛ ግን ጥርሳችን የነቀልነው በፖለቲካ ነውና በዚህ
ዙሪያ ለአናንተ ብዙ ብለን የምንሰጠው የሌት ሰራ የለም።
አርፋችሁ ስራችሁን ስሩ፣ አገሪቱን በብልጭልጭ ስራ
አያይቆታችሁ መደብራችሁን አስፋፉ፣ ሱቃችሁን መሉ።
ፖለቲካዊ ጣቀታውን ለእኛ ተውልን። ስለዚህ ተነባብሰው ስለ
ሰላም ስለ ልርቅ መሠየየታችው ሊያስቧህ አይገባም።
ምክንያቱም በየጊዜው ፖለቲካዊ ችግሮችን ለመፍታት ቢጠየ
ባይወዱም ምንም ዘላቂ መፍትሄ ማምጣት ስለማይችሉ ነው።
እንዲሁ ስይሰሙላ ካልሆነ በቀር፣ በየመድረኩ የሚወያዩት ሁሉ
በንቱ ቃላትና ከመሬ ሊዘል የማይችል ነው። ስራውን ቅድመ
ሰጠየተውን ግን ሙድ ይዘዋል። ልክም ነህ። እንዳልከው በየጊዜው
ይመጣሉ። እስር አልፎ አልፎም ሰላሰልሳናቱ መፍትሄው ችግሮቹ
የእኛን እጅ ሁል ይዘይታሉ። ...ምን እናድጎማን እያሉ
ይሰዘባሉ። ስንዝን እሳካችሁ እያለ ይማፀናሉ። የአይማኖት
አባቶችን ምክራለን ይላሉ። ኮሚኒመሙ ግን መሪዎች ሰየሳሉ
ሙትያትነው። በተኛ መፍትሄውን ሰትሉትም ስንሰው
ዘትንቸው እንደነበር ነው። ከመንታችን ሊነሳም ሰላቂ መፍትሔውን
ነው የሚሉት። መፍትሄውን ለማፈላለግ

ለመስራት እንድ ትውልድ ይፈልጋል። እንድ ትውልድ ገዝተዋል፣ዓላማችን ዳር አድርሰዋል! የአገልግሎት ዘመናቸውንም ጨርሰዋል! እናም..... አምጥተን ቁጭ እንዳደረግናቸው፣ ጎትተን ዘጭ ማድረግ እንችላለን።

"ለማንኛውም ይህ እንቀፅ እስካለ ድረስ ዘላቂ ሰላም፣ ዘላቂ እንድነት፣ ዘላቂ ፍትር፣ የሚባል ነገር አይኖርም! ታዲያ ይሄ የቻይና ውጤት ነው ብለህ ታስባለህ?

"ቻይና ታታሪ ስራተኛና ነጋዴ እንጂ ፖለቲካ አታውቅም። ታታሪ ስለሆነችና እቅም ስላላት እንደ መንደር ውስጥ ባለ ሱቅ ብድር ልትሰጥ ትችላለች። ሽቀጣ ሽቀጥ በዱቤ ልትሰጥ ትችላለች። መርዳት፣ በስራ ማገዝ፣ ትችላለች። በአገራቱ ለቅሶ ሲሆን ለቅሶ መድረስ ማስተዛዘን ትችላለች። እንጂ ከጉልበተኞች አታስጥልም። ድምፅን በድምፅ የመሻር መብት የላትም። ፖለቲካ አታውቅም። እኛ ግን ጥርሳችን የነቀልነው በፖለቲካ ነውና በዚህ ዙሪያ ለእናንተ ብቻ ብለን የምንሰጠው የቤት ስራ የለም። አርፋችሁ ስራችሁን ስሩ፣ አገራቱን በብልፅግና ስራ እያራቆታችሁ መደብራችሁን አስፋፉ፣ ሱቃችሁን ሙሉ። ፖለቲካዊ ጫዋታውን ለእኛ ተውልን። ስለዚህ ተሰብስበው ስለ ሰላም ስለ ዕርቅ መወያየታቸው ሊያሰጋህ አይገባም።

"ምክንያቱም በየጊዜው ፖለቲካዊ ችግሮችን ለመፍታት ቢወያዩ ባይወያዩ ምንም ዘላቂ መፍትሄ ማምጣት ስለማይችሉ ነው። እንዲሁ ለይስሙላ ካልሆነ በቀር፣ በየመድረኩ የሚወያዩት ሁሉ ከንቱ ቃላትና ከወሬ ሊዘል የማይችል ነው። ስራውን ቀድመን ጨርሰንዋል።

"ትዝብትህን ግን ወድጀዋለሁ። ልክም ነህ። እንዳልከው በየጊዜው በዚያች አገር ፖለቲካዊ ችግሮች ይፈጠራሉና፣ ስለ ሰላም ይወያያሉ። አልፎ አልፎም ባላስልጣናቱ መፍትሄው ቸግሯቸው የእኛን እገዛ ሁሉ ይጠይቃሉ። ‹‹ምን እናድርግ?›› እያሉ ይሰበሰባሉ። ሕዝቡን እባካችሁ እያሉ ይማፀናሉ። የሐይማኖት አባቶችን ምክሩልን ይላሉ። የሚገርመው ግን መሪዎች በየቤተ-መንግስታቸው ሲተኙ መፍትሄውን በጉያቸው ሸጉጠው ሙተኛታቸው ነው። ከመኝታቸው ሲነሱም ዘላቂ መፍትሔውን በጉያቸው እንደያዙ ነው የሚነሱት። መፍትሄውን ለማፈላለግ

ሲሆንም መፍትሔውን እንዲታቀፉት ነው የሚዘሩት። መፍትሄው በእጃቸው እንዳለ ግን አያውቁትም።

"የአገራቱ ዘጠና ከመቶ ፖለቲካዊ ችግሮች ከዚህ አንቀጽ ጋር በተያያዘ የተከሰቱ መሆናቸውን ግን እኛ እናውቃለን። ስለዚህ ይህን እነሱ እንዳያውቁ መጠንቀቅና፣ ይህን አንቀጽ እንዳያወጡ በተለያየ መንገድና ምክንያት እያሳበብን ማስጠንቀቅን ነው ስራ ብለን መያዝ ያለብን።

"በእርግጥ ሳያውቁት ቀርተው አይደለም። ነገር ግን ይህን አንቀፅ ሳይወዱ በግድ አገለው እሽሩሩ እያሉ እንዲተዉ ያስገደዳቸው ሌላ ምክንያት ስላለ ነው።

"ይገርማችኋል ያ ሁሉ ምሁራንና ፖለቲከኛ ተብዬ ተሰብስቦ ስለ ኢትዮጵያ ፖለቲካ ሲዘበዝብ ከአንዳቸውም በኩል ስለ ብሔራዊ ጉባዔ፣ ስለ ብሔራዊ መግባባት፣ /ስለ ናሽናል ዲያሎግ/ ሃሳብ ተሰንዝር አያውቅም።

"ባመላው ዓለም ተከስተው የነበሩ የብሔር ወቦችንና የእርስ በርስ ጦርነቶችን ሁሉ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ማክሰም የተቻለው በናሽናል ዲያሎግ አማካኝነት ነው። በተለይ በአፍሪካ፣ በሩዋንዳ፣ በኮንጎ፣ በደቡብና በሰሜን ሱዳን ሚሊዮን ሚሊዮን ዜጎቻቸውን ያጨፋጭፍ የነበረውና ሚልዮን ሚሊዮን ዜጎቻቸውን መፍጀትና ማስፈጀት የቻለውን የብሔር ፀብን ተከትሎ የተከሰተውን እልቂት ያስቆሙት በዚሁ በናሽናል ዲያሎግ ነው።

"ኢትዮጵያውያን ግን ወደ እዚህ አሳብ መግባት አልፈለጉም፣ አይፈልጉምም። ምክንያቱም ወደ እዚህ አሳብ ከገቡ ይህን አንቀጽ ሊያወጡ ነው። ይህን አንቀጽ ካወጡ ደግሞ ሙሉው የፌዴራሊዝም ሥርዓት የሚናድባቸው ይመስላቸዋል። ይህ ከተናደ ደግሞ ወደ እኩልነት የመጡት፣ወይም ወደ እኩልነት የመጡ የመሰላቸው ብሔሮች፣እኩልነቱን የሚያጡ ስለሚመስላቸው ነው። ፖለቲከኞችና ምሁራን ከተለያዩ ብሔር የተውጣጡ ስለሆኑ፣ ‹‹በፌዴራሊዝሙ ሥርዓት ችግር የለብንም›› ብለው ነው ነገራቸውን የሚጀምሩት።

"እርግጥ ነው የፌደራሊዝም ስርዓት በራሱ ምንም ችግር የለበትም። ሁላችንም የምንመራበት የአስተዳደር ዘዴ ነው። ነገር ግን ከፌደራሊዝም ስርዓት አልፈህ ብሄር ተኮር ፌደራሊዝምን ስታራምድ፣ ከዚህም አልፈህ እስከ መገንጠል የሚል ዕድል

ስትሰጥ፡ በዚህም ላይ 85 ብሔር ሲኖርህ፡ ይህም አልበቃ ብሎ፡ ተቀራራቢ ቁጥር የሌላቸው ብሄር ብሄረሰቦች በዝተውብህ፡ ብሄሮች እኩል የሰለጠኑ እኩል የተማሩ ባልሆኑባት አገርና፣ 85 % ህዝብ ያልተማረ ሆኖ፡ እኩል አይነት የግብርና ዘዴ በሌለበት፡ ተቀራራቢ ባህል በሌለበት፡ ዘመናዊ ትምህርት ሙሉ በሙሉ ያልተዳረሰባት አገር ይዘህ፡ በምግብም ራስህን ሳትችል፡ ከሁሉም በላይ ሁሉም ብሄር በአፍ መፍቻ ቋንቋው እንዲማር አድርገህ! መቶ በመቶ አስተማማኝ የሆነ ዲሞክራሲያዊ አስተዳደርን ብትዘረጋና እኩል ፍትህን ብታሰፍን እንኳን፣ አገርን እንደ ዘላቂ ሉዓላዊት አገር፡ ህዝቡን እንደ አገር ህዝብ አድርገህ ይዘህ ማስቀጠል አይቻልም!

"እንዱ ብሄር 40 ሚሊዮን፡ አንዱ ብሄር 40 ሺ፡ አንዱ ብሄር 5 ሚሊዮን፡ አንዱ ብሄር 5 ሺ ሆኖ፤ የብሄሮች ብዛትም ከ 80 በላይ ሆኖ፡5 ሚሊዮኑም በቋንቋው፡ 5 ሺውም በቋንቋው እየተማረ፡ ለአገዛዝ እንዲመች ብቻ ከየብሄሩ አንዳንድ ተወካይ ወደ ፌደራሉ እየጠራህ እያሳተፍክ ዲሞክራሲ? ጭራሽ ደግሞ ፍትሃዊ ምርጫ ባልተለመደበት አገር! በምክር ቤቱ አብላጫ ድምፅ ያገኘ ሕግ እያፀደክ፡ በአብላጫ ድምፅ ውሳኔ እያስተላለፍክ!

"በምክር ቤቱ አብላጫ ድምፅ ያለው፡ አብላጫ ድምፅ ያገኘ፡ እያሉ ለመቀጠልም እኮ ሌሎች ብዙ መስፈርቶችና ቅድመ ሁኔታዎች ሊኖሩ ይገባል፡፡ በፌደራላዊ አወቃቀር ስም ተመስርቶ፡ እንዲሁ ዝም ብሎ መፈትፈት.....አይቻልም፡፡ የኢትዮጵያ ፌደራሊዝም ውል የሌለው የልጆች ዕቃ እቃ ጫዋታ ነው ክቡራን፡፡ የፌደራሊዝምን ስርዓት ለመዘርጋት ብዙ ቅድመ ሁኔታዎች አሉ፡፡ እነሱን ሳታጠናና ሳታሟላ እንዲሁ ዘው ብለህ የምትገባበት አይደለም፡፡ አውሮፓውያን ስለተመሩበት አይደለም፡፡ ፌደራሊዝም በራሱ አንድ ብቻ አይደለም፡፡ ብዙ አይነት ፌደራሊዝሞች አሉ፡፡ ብሄሮች ራሳቸውን እያስተዳደሩ ሲባል ብዙ አይነት ትርጉም አለው፡፡ ብሄር ብሄረሰቦች የራሳቸውን ዕድል በራሳቸው የመወሰን መብት...ሲባል ብዙ አይነት ትርጉም አለው፡፡ የተለያዩ አፈፃጸም አለው፡፡ 5 ሺ ብሄሮች እንዴት የራሳቸውን ዕድል በራሳቸው ይወስናሉ? ያውም እስከ መገንጠል! 40 ሚሊዮን ህዝብ እንዴት እስከ መገንጠል የሚል ዕድል ይሰጠዋል? 5 ሚሊዮን ህዝብ ለብቻው የመገንጠል ዕድል፡ ብዛቱ 20 ሺ የሆነ የራሱ ቋንቋ፡ የራሱ፡ ባህል፡ የራሱ ምናምን፡ ያለውን ህዝብ

እንዴት እንደፈለክ የሚል ዕድል ትሰጠዋለህ? በዚህስ ህዝቡን ምን ትጠቅመዋለህ? አገሪቱን ምን ትጠቅማታለህ? ይህን የመሳሰለ አንቀፅ በሕገ-መንግስትህ እንዴት ሕግ ብለህ ታካትታለህ?

"ይህ የቅኝ ገዥዎች ሃሳብ የነበረ ነው፡፡ ቅኝ ገዥ ከሆንክ ብቻ ነው ይህን ልታደርግ የምትችለው፡፡ ከፋፍለህ ለመግዛት ብቻ ሳይሆን፣ነጣጥለህ ለማጥቃትና የዕድሜ ልክ ባለስልጣን ሆነህ ለመቀጠል ካላሰብክ በቀር፤ እንደ አንድ የራሱን አገር እንደሚመራ መንግስት ደፍረህ ይህን አታደርግም፡፡ በዚያች አገር የሆነው ግን ይህ ነው፡፡

"ይህ በሆነበት ሁኔታ ደግሞ ሁሌም ፀብ፡ ሁሌም ፖለቲካዊ ችግር፡ ሁሌም መከራ መኖሩ አይቀርም፡፡ ሁሌ ውዝግብ ነው፡፡ እንዲህ አይነት ነገሮች በየጊዜው ሲፈጠሩና ምሁራኖቻቸውና ፖለቲከኞቻቸው ውይይት ሲያካሂዱ ግን የችግሮች ሁሉ ምንጭ ሕገ-መንግስቱ ውስጥ ያሉ አንቀፆች መሆናቸውን ማወቅና ማሳወቅ ይፈራሉ፡፡

"በዚህ ሥርዓት እኩልነታቸው የተረጋገጠ የመሰላቸው የየብሔሩ መሪዎችና ተወካዮች፣«በፌደራላዊ ሥርዓቱ ላይ ችግር የለብንም፣ ፌደራሊዝሙ በራሱ ችግር የለበትም፡፡ ችግሩ ያለው...» በሚል ጀምረው ብዙ እንቶ ፈንቶ ውስጥ ይገባሉ፡፡ ከዚያም «ብሔራዊ ዕርቅ...» ብለው ጀምረው፣ ነካክተው ይተውታል፡፡

"ብሔራዊ ዕርቅም ሆነ ብሄራዊ መግባባት ደግሞ በውይይትና በቴሌቪዥን በሚቀርብ ተማፅኖ እዘል ውይይትና ማስጠንቀቂያ ወይም ማሳሰቢያ ዕውን ሊሆን አይችልም፡፡ ወደ ቀድሞው ብሔራዊ አንድነት ይምጡ ከተባለ፣የግድ ወደ ብሄራዊ መግባባት መጥተው፣ ብሔር ብሄረሰብ የሚለውን ለየብሄሩ ትተው፣ ቋንቋ ባህሉን ለየራሱ ለየብሄሩ ነፃ አድርገው ለቀው፣ በሕገ-መንግስታቸው ግን ብሔር ብሔረሰብ የሚለውን አስቀርተው፣ ይህን አንቀፅም ፍቀው አውጥው፣ መቀጠል የግድ ነው፡፡ ዘላቂ ሰላምና ዘላቂ አንድነት የሚያመጣው የናሽናል ዲያሎግ ትርጉም ይህ ነው፡፡ እነሱ ግን ይህን አንቀፅ ካወጡ ሙሉው የፌደራሊዝም ስርዓት የሚፈርስ ስለሚመስላቸው ይፈሩታል፡፡ ስለዚህ አያደርጉትም! ከዚህ ይልቅ ብጥብጡ ቢቀጥል ይመርጣሉ፡፡

"የፌዴራሊዝሙ ሥርዓት በምንም መልኩ ሳይሸራረፍና ሳይጓደል ይህን አንቀጽ እና ሌሎች ጥቂት ተመሳሳይ መሰሪ አንቀፆችን ብቻ

መቆየት የማይፈልጉ ፍሬዎች ሆነዋል። ዛፉ ቢኖር ባይኖር ግድ የሌላቸው ፍሬዎች ነው የበዙት።

"በጣም ተንሻፐርገው ለመሬት ቅርብ ሆነው በመገኘታቸው ምክንያትም ነው፣ ‹‹የዛፉ አካል ነኝ? ወይስ ብቻዬን በትዬ ፍሬ ሆኜ ዛፉ ላይ የወጣሁ?›› እያሉ፣ ‹‹እውነት ግን እኔ ማነኝ?›› በሚል ጥያቄ ውስጥ የገቡ ብዙ ፖለቲካ ወለድ ልሂቃን የበረከቱት። ይህ ያኔ የተከልነው ችግኝ የደረሰበት ደረጃ ነው። የአንድ አገር አንድ ህዝብን በብሄር ብቻ ላይሆን፣ በቋንቋውም ሳይቀር ‹‹በሕገ-መንግስት ደረጃ›› ሀጋዊ አድርገህ ከፋፈልከው ማለት ነገ ትልቅ ዛፍ የሚሆን ምርጥና መሰሪ የፖለቲካ ችግኝ ተከልክ ማለት ነው! አንድ አይነት ሆኖ የተለያዩ ፍሬ የሚፈራራ.....ገባችሁ? ለዚያ ነው ብዙዎች የዛሬ ፖለቲከኞች፣ ‹‹ለእኛ ሁለቱም ሊያዋጣን ይችላል›› የሚሉት። ምክንያቱም እርግጠኞች ስላለሆኑ ነው። ‹‹ከዛፉ አይደለንም፣ እየታዩ፣ ከዛፉ ብንሆን ሌሎች ፍሬዎች ወደ ላይ ባለው ቅርንጫፍ ብለው እኛ ለመሬት ቅርብ የሆንነው የዛፉ አካል ባንሆን ነው›› ብለው ያስባሉ። በሊላ በኩል፣ ‹‹የዛፉ አካል ካልሆንን እንዴት ከዛፉ ጋር ቅርንጫፍ ሆነን ተገኘን? እንዴትስ ፍሬያችን ተመሳሰለ?›› ብለው ይጠይቃሉ። በዚህ ምክንያት መሬት ወርደው ብቻቸውን መተከልና ብቻቸውን ዛፍ መሆን ይፈልጋሉ። ምናልባት የዛፉ አካል ሆነው ከሆነ ደግሞ የራሳቸውን ቅርንጫፍ ይዘው ወርደው መሬት ቢተክሉ፣ ራሱን የቻለ ሥር ላይኖራቸውና ደርቀው ሊቀሩ እንደሚችሉ እያሰቡ ይሰጋሉ። ስለዚህ ፍላጎታቸውን ስትጠይቋቸው፣ ‹‹ሁለቱም ሊያዋጣን ይችላል›› ይሏችኋል። እርግጠኞች አይደሉማ! እርግጠኞች እንዳይሆኑ አድርገናቸዋላ! እኛ ይሄን ባናደርግ ወደ እውነቱ ሊሄዱ ነው። እውነቱ ደግሞ የአንድ አገር አንድ ህዝብ መሆናቸው ነው!

"ቀደም ሲል በስፋት እንደገለጽኩት በዚያች አገር ሁሉም አይነት ብሄር፣ ሁሉም አይነት የሰው ልጆች የቆዳ ቀለም፣ ሁሉም አይነት መልክና ዐጉር፣ በርካታና የተለያዩ ቋንቋዎች ያላቸው ዜጎች ሲገኙ የቻሉት የሰው ዘር የታሪክ መነሻ ያች አገር ስለሆነች ብቻ ነው። "ለምሳሌ ናይጄሪያ ከ 400 በላይ ቋንቋና ብሄር አለ። ነገር ግን አንድ አይነት መልክና አንድ አይነት ፀጉር፣ አንድ አይነት

መገዘፍ ማውጣትና መቀጠል የሚቻልበት ሁኔታ እንዳለ ለእኔም ለእናንተም ለመላው ዓለም ህዝብም ግልፅ ነው። እነሱ ግን አላወቁትም ወይም ማወቅ አይፈልጉም።

"በእርግጥ እኛ ይህን አንፈቅድም። ቢያስቡት እንኳ ማስተዋችን አይቀርም። ነገር ግን የችግሩ መንስዔ እሱ፣ የችግሮች ሁሉ መፍትሄ እሱ እንደሆነ እያወቁ ለማውጣት አለመሞከራቸው፣ ወይም ዛሬም ድረስ ለማወቅ አለመፈለጋቸው በግሌ ያስገርመኛል፣ ይህን ካላወቁና ተግባራዊ ካላደረጉ ደግሞ ሌላ ነገር ያውቃሉ፣ ይተገብራሉ፣ ተግብረውም ወደ ዘላቂ ሰላም ይመጣሉ ብሎ መጠርጠርና መስጋት አያስፈልገንም። ስለዚህ ኢትዮጵያን እንደ አንድ ትልቅ አገር ሳይሆን፣ ዘጠኝ ትልልቅ ሰንደቅ ዓላማ ያላት የተበጣጠሰች አገር እንደሆነች እወቁ።

"ህዝቧም በአንድ ሰንደቅ ዓላማ ስር የተሰባሰበ አንድ ህዝብ ሳይሆን፣ ከ 90 ተከፋፍሎ ለዘለቄታው ሲናቆር የሚኖር ህዝብ እንደሆነ እወቁ። ያችን አገር እንዲህ አድርገን ያዘጋጀናት ደግሞ ለዚህ ለዛሬው ስራችን ምቹ እንድትሆን ሰንል እንደሆነ መረዳት አለባችሁ። ይህን የማድረጉ ሥራ ቀላል ያልነበረ መሆኑንም እንድታውቁልን እፈልጋለሁ።

"ይህ ነው ያኔ የተከልነው መሰሪ ችግኝ! ችግኙ አድጎና ለምልሞ በደንብ ፍሬ አፍርቶ እንዲገኝ አድርገናል ማለት ነው።

"በዚያች የድል ማግስት የተከሉት ችግኝ በጥሩ ሁኔታ ስር ሰድዶ አብቦና ለምልሞ፣ ፍሬ ማፍራትም ችሎ፣ ያፈራው ፍሬም ጎምርቶ እንዲህ ተንሻፐርጎ አውርዳችሁ ብሉኝ ግመጡኝ የሚልበት ደረጃ ላይ ደርሷል። አውርዳችሁ ካልበላችሁኝ በራሴ ጊዜ መውደቁ ነው እንደሚል ጣፋጭ ፍሬ ሆኗል። ይሄው በየቅርንጫፉ በስሎ እየጠበቀን ነው። በየቅርንጫፉ እንዲህ ደርሰው የሚታዩ ፍሬዎች ደግሞ እኛ ዛፉ ላይ መውጣት ሳያስፈልገን በቀላሉ ቆመን በእጃችን የምናወርዳቸው ፍሬዎች ናቸው።

"አዎን! ብዙዎች ፍሬዎች ለእኛ ቅርብ ናቸው። በጣም ቅርብ ከመሆናቸው የተነሳም የዋናው ዛፍ አካል መሆናቸውን እስከመርሳትና ከዛፉ ጋር ምንም እድል ፈንታ እንደሌላቸውና ምንም የሚጋሩት ነገር የነበረና ያለ እስከማይመስላቸው ድረስ ረግፎ ለመውደቅ እንጂ፣ ከዛፋቸው ጋር እንደተጣበቁ እንዳሉ

አገር እንዴት ይሄን ማድረግ ተቻለ? ይህን ሁኔታ ማን አመቻቸው? እኛ ነን! በፊደል ለውጥ ብቻ እንኳን ይህን ያህል ፖለቲካዊ ትርፍ አግኝተናል! ይህን ለማድረግም ብዙ ዋጋ ከፍለናል! ይህንንም ነው ኢጣሊያ ከአንድም ሁለት ጊዜ ሞክራ የከሸፈባትን እኛ ተግባራዊ ማድረግ ችለናል እያልን እርግጠኛ ሆነን የምንናገረው። ይህ ስኬታችን ነው፤ እንመካበታለንም!

“እነዚያን ሰፊ ህዝቦች ዛሬ ሂዳችሁ ይህን ጥያቄ ብትጠይቋቸውና፣ ‹‹ለምን የአገር በቀሉን ቀደምት ፊደል አትጠቀሙም?›› ብትሏቸው፣ ‹‹የኛን ቋንቋ ለመፃፍ የሚመቸው የላቲኑ ፊደል ነው›› ይሏችኋል። ‹‹የግዕዙን ፊደል ማለትም የአማርኛውን ሆሄ ብንጠቀም ብዙ ቃላቶችን ለመግለፅ አያስችለንም…›› የሚል መልስ ነው የሚሰጡዋችሁ። ዕውነቱ ግን እሱ አይደለም! ዕውነቱ እሱ እንዳልሆነ እነሱም ጠፍቷቸው አይደለም። ፊደሉ ሀ ለ ሐ መ… እያለ እስከ ሰባት የተለያየ አናባቢ አካትቶ የያዘ ፊደል ከመሆን አልፎ፣ ኃ፣ሟ፣ሯ፣ሃ፣ሿ፣ቁ፣ቧ፣ቷ፣ቿ፣ኁ፣ኋ፣ኧ፣ኟ፣ዃ፣ጎ፣ጓ፣ጔ፣ጕ፣ጘ፣ጟ፣ጧ፣ጯ፣ጷ፣ጿ፣ፏ፣ፗ፣ኗ፣ኟ፣ዟ፣ዧ፣ዷ፣ጇ፣ጧ፣ጯ፣ጷ፣ጿ፣ፏ፣ፗ፣ኗ፣ኟ፣ዟ፣ዧ፣ዷ፣ጇ፣ወ፣ዉ፣ዊ፣ዋ፣ዌ፣ው፣ዎ፣ዐ፣ዑ፣ዒ፣ዓ፣ዔ፣ዕ፣ዖ፣ኀ፣ኁ፣ኂ፣ኃ፣ኄ፣ኅ፣ኆ፣ኇ፣ኈ፣ኊ፣ኋ፣ኌ፣ኍ፣኎ ….አልፎ ተርፎ ሥ፣ሣ፣ ሦ፣ሧ፣ ረ፣ሩ፣ሪ፣ራ፣ሬ፣ር፣ሮ፣ሯ፣ሰ፣ሱ፣ሲ፣ሳ፣ሴ፣ስ፣ሶ፣ሷ፣ሸ፣ሹ፣ሺ፣ሻ፣ሼ፣ሽ፣ሾ፣ሿ፣ቀ፣ቁ፣ቂ፣ቃ፣ቄ፣ቅ፣ቆ፣ቋ፣ቌ፣ቍ፣ቈ፣ቊ፣በ፣ቡ፣ቢ፣ባ፣ቤ፣ብ፣ቦ፣ቧ፣ቨ፣ቩ፣ቪ፣ቫ፣ቬ፣ቭ፣ቮ፣ተ፣ቱ፣ቲ፣ታ፣ቴ፣ት፣ቶ፣ቷ፣ቸ፣ቹ፣ቺ፣ቻ፣ቼ፣ች፣ቾ፣ቿ፣ኀ፣ኁ፣ኂ፣ኃ፣ኄ፣ኅ፣ኆ፣ኇ፣ኈ፣ኊ፣ኋ፣ኌ፣ኍ፣኎ ያለው በጣም ሐብታም የሆነ፣ በዓለማችን ብቸኛው ሁሉን ገላጭ የሆነ ፊደል ነው። የዓለምን ቋንቋዎች በሙሉ፣ ወደ ውስጥ የሚዋጡትን፣ ወደ ውጪ የሚባሉትን፣ እንከን የለሽ በሆነ መንገድ መግለፅ የሚችል ነው። ቀደምት እና ብቸኛው የዓለማችን ፊደል ነው። ከግብፅ ዴሞግራፊ፣ ከግሪክ ሂሊዮግራፊ፣ በፊት፣ በጣም በፊት፣ የነበረ ዜጎችን ሊያኮራ የሚገባ ፊደል! ግን አይጠቀሙትም። ለምን? ፖለቲካ ስለሆነባቸው! የብሄር ጥላቻ ስለተፈጠረ! በዚህ ፊደል የሚጠቀሙት ሌላ ብሄሮች ናቸውና ፊደሉ የሌላ ብሄር እንጂ የእናንተ አይደለም ስለተባሉ ነው! ይልቁንም የጠላቶቻችሁን ፊደል መጠቀም…..እየተባሉ ስለተማሩ፣ ስለሰለጠኑ ነው። እንጂ ቃላቶቻቸውን ሳይገልፅላቸው ቀርቶ አይደለም! ያን ያውቃሉ። ያ ሐብታም ፊደል ቃላታቸውን ከመግለፅ አልፎ እስከመቀንጭ እንደሚያደርሳቸው አሳምረው ያውቃሉ። እንኳን በዚያ ሃብታም ፊደል በእኛው 25 ፍሬ ሆሄያት መጠቀም ችለዋል። ያውም በጣም አጣብቦውና አብቃቅተው ደብል ቫውልን እየተጠቀሙ! ስለማይገልፀው……? አይደለም! ‹‹ኢትዮጵያዊ ናችሁ፣ ለምን የኢትዮጵያን ፊደል አትጠቀሙም?››

ቀለም፣ አንድ አይነት ወዘተ…ያለው ነው። ያ እንደየ ጎሳው ተለያይቶ እንጂ ሌላ ታሪክ ኖሮ አይደለም።

የኢትዮጵያው ግን ከዚህ አይነቱ ብጥሰጣሽ ታሪክ ይለያል። ራሱን የቻለ ታሪክ ያለው ሰለሆነ ነው።

“ኢትዮጵያውያን ዜጎች በየትም አገር ቢገኙ ይለያሉ። ይታወቃሉ። ቀይ ሆነ ጠይም፣ጥቁር ሆነ የቀይ ዳማ፣ ሴት ሆነ ወንድ፣ሽማግሌ ሆነ ወጣት፣ኢትዮጵያዊ ኢትዮጵያዊ ነውና ያለ ንግግርና ያለ ሰላምታ ኢትዮጵያዊ መሆኑ ይለያል። ለምሳሌ አንድ ናይጀሪያዊ ሀጋዊ የመኖሪያ ፈቃድ ሳይኖረው ኬንያ ቢኖር የሚለየው የለም። አንድ ደቡብ አፍሪካዊ ጋና ቢኖር የሚለዩው የለም። ምናልባት ቋንቋውን ከቻለ በቋንቋው ልትለየው ትችላለህ። እሱንም ቀርበህ አነጋግረህ እንጂ ካልተነጋገርክ በርቀትም በቅርብም ልትለየው አትችልም። ቋንቋውን ከቻለማ መታወቂያን አለያዝኩም፣ግን ጋናዊ ነኝ ሊልህ ይችላል።

“ኢትዮጵያዊ ግን ቋንቋ ቻለ አልቻለ፣ጠቆረ ቀላ፣ ወጣት ሆነ ሽማግሌ፣ ስለ አገሪቱ ጥቂት እውቀት እስካለህ ድረስ እንዲሁ በርቀትም በቅርበትም በቀላሉ ኢትዮጵያዊ መሆኑን ትለየዋለህ። ለዚህ ነው በየትም አገር ሀገ ወጥ ሆነው መኖር ሳይችሉ እየቀሩ ቀብ የሚደረጉት።

“ኢትዮጵያውያን እንደ ጂንስና እንደ ኮካ ኮላ ጠርሙስ ያልገቡበት የለም። በስደትና በባርነት የትም አገር ይገኛሉ። ከሊላው ህዝብ በተለዩ ውኔታ ግን ሀጋዊ የመኖሪያ ፈቃድ ከሊላቸው ተደብቀው መኖር አይችሉም። ኢትዮጵያዊ ኢትዮጵያዊ ነው። ከሊላው የአፍሪካ አገር ጥቁር ህዝብ የተለየውና እንዲህ ተሰባጥሮ ሁሉም አይነት መልክና ቀለም ኖሮት ነገር ግን አንድ ህዝብ ሆኖ የተገኘው ራሱን በቻለ ታሪካዊ ምክንያት ነው።

“በሁለተኛው የሰው ልጅ ምዕራፍ የዓለም ህዝብ ስርጭት ከኢትዮጵያ ስለሚነሳ ብቻ ነው። እንጂ የተለያዩ አገራት ህዝቦች ሆነው አይደለም። ይህንን ዓለም አቀፍ እውነት ወደ ፖለቲካዊ ጫዋታ ስናመጣውና ለገዛ ዓላማችን ጥቅም ላይ ስናውለው ግን ነገር ተለወጠ!

“በዚያች አገር ፊደላችንን ፊደል አድርገው የያዙ ዜጎች በርካታ ናቸው ብያለሁ። ይህ ምን ማለት ነው? ምን ማለት ሊሆን ይችላል? እንዴትስ ይሄን ሁኔታ መፍጠር ተቻለ? ቅኝ ባልተገዛች

ስትሉ፣ ‹‹ቋንቋ ምን....ከተማባህበት በቂ ነው....›› ይሏችኋል፡፡ ‹‹የኛ ችግር ይሄ አይደለም፡፡ልማት፣ዴሞክራሲ፣...››እያሉ፣ ወደ እኛ ትምህርት አልፈው እንቶ ፈንቶ ትንታኔያቸውን ይተጥላሉ፡፡ "ይህ ማለት በዚያ ፊደል የተሣፈ የጋራ ታሪካቸውም የእነሱ ታሪክ እንዳልሆነ ነው የሚያሰቡት ማለት ነው፣ ይህ ማለት ምን ማለት ነው? ይህ ሁሉ የማን ሰራ ነው? ለምን ምንም እንዳልሰራን አድርጋችሁ ታስባላችሁ? በአገር አለመኩራት ማለት ይሄ አይደለም ወይ? የራስን ሃብት እስከመናቅ ያደረሰ ሰራ ነው የሰራነው፣ ይህን ማድረግ እንዴት ተቻለ?

"የራስን ዕድል በራስ መወሰን፣እስከ መገንጠል የሚል ፍልስፍና በውስጡ በያዘ፣ በብሄር ብሄረሰቦች መብት በተለወሰ ማሳያ መራር ፖለቲካችን እማካኝነት ነው ይህን ማድረግ የተቻለው፣ እኛ አንድን ነገር ስናሰጀምርም በዓላማ ነው፣ ስናስጨርስም በዓላማ ነው፡፡ በደመ ነብስ የምንንዝ አይደለንም፡፡ ውጤቱ ምን እንደሚሆንም ቀድመን እናውቃለን፡፡ ይህን ችግኝ ተክለናል፡፡ የትግ ፖለቲካ! የብሄር ብሄረሰቦች መብት! ብሄር ብሄረሰቦች ቋንቋቸውን፣ ባህላቸውን፣ ፊደላቸውን፣ ያለ ገደብ ማሻሻል፣ ያለ ተዕዕኖ ማሳደግ...

"የብሄር ፖለቲካ ወይም ብሄር ተኮር ፌደራሊዝም የራስን ሃብት በመናቅና በማጣጣል ብቻ ተወሰኖ የሚቀር አይደለም፡፡ የራስን ሃብት በራስ እጅ እስከ ማውደም ድረስ መሄድ ብንፈልግ እንኳ፣ ያን ለማድረግ የሚያስችል መሳሪያ ሆኖ ማገልገል የሚችል ነው፡፡ የራስን አገር እስከ ማውደም ድረስ ይሄዳል፡፡ የራስን ቅርስ የራስን ታሪክ ፍርስርስ ማድረግና፣ ‹‹እቃ እቃ ፍርስርስ አንድ እንጀራ ቁርስርስ›› የሚባለውን ሜዛታ መጫወት የሚቻለው በዚህ አይነቱ ርዕዮትና በዚህ አይነቱ መሰሪ ፖለቲካ አማካኝነት ነው፡፡

"ቀላል እንዳይመስላችሁ! የቀድሞ ታሪክህንም፣ የቀድሞ ነገስታትህንም፣ ሳይቀር እያበሻቀጥክ እስክ መስደብ ያደርሳል! አገራቱን ነፃ አድርጎ ያስረከበህን አባትህን በንቀት እየተሳደብክ ልትኖር የምትችለው የዚህ ፖለቲካ አራማጅ ስትሆን ብቻ ነው፡፡ በአጭር ዓመታት ነገስታቱን መሳደብ የቻለ ትውልድ የተገነባው በዚህ ዘዴ ነው፡፡

"ይህን ሁሉ ትርፍ ያገኘነው በሩብ ምዕተ ዓመት ውስጥ ነው፡፡ ኢትዮጵያውያንን እዚህ ደረጃ አድርሰናል! የዓመታት ድካማችን

ፍሬ ማለት ይህ ነው! ግባችሁ ወይ ክቡራን?" አሉ ወደ ተሰብሳቢዎች አፍጥጠው፡፡

"አዎን ንግስት ሆይ፡፡"የሚል ደመቅ ያለ የጋራ ድምፅ ተስተጋባ፡፡ ቀጥሎም ሞቅ ያለ የጋራ ጭብጨባ ተከተለ፡፡

ንግስቲቱ ቀጠሉ....፡፡

"ይህ አሁን ያለው የኢትዮጵያ ትውልድ ዛሬ ላይ ሆኖ የቀድሞ ነገስታቱን እየተሳደበ ያለ ትውልድ ነው! እኛን መከተሙ የመለሱትን ጀግኖች አባቶቻቸውን ነው የሚሳደቡት! ተጭነውናል እያሉ የሚወቅሱት! ይህ ትውልድ ብቻ አይደለም፡፡ ያ ትውልድም ጭምር ነው፡፡

"ኢትዮጵያውያን አንድ የለመዱት አገላለፅ አለ፡፡ ያ ትውልድ፣ ይህ ትውልድ፣ የሚሉት ነገር አላቸው፡፡ ያ ትውልድ የሚሉት እነዚያን የመጀመሪያዎቹን የዘመናዊ ትምህርት ተማሪዎች ነው፡፡ ይህ ትውልድ የሚሉት ይህን አሁን ያለውን ትውልድ መሆኑ ነው፡፡ ሁለቱም ትውልዶች አሁን ድረስ አሉ፡፡ እና...ይህ ትውልድ ያን ትውልድ ሲፈልግ ይወቅሳል፣ሲፈልግ ያሞካሻል፡፡ ያ ትውልድም ይሄኛውን ትውልድ ሲፈልግ ይወቅሳል፣ሲፈልግ መደናነቱ ግን አስፈላጊ አይደለም፡፡ ምክንያቱም ይህ ትውልድ፣ ትውልድ፣ የሚባል ነገር ስላልነበረና ስለሌለ ነው፡፡ እንዲህ እያለ ለመናገር ራስ ራሱን የቻለ ትውልድ ሊኖር ይገባል፡፡ ያ ትውልድ የእኛ ነበር፣ ይህም ትውልድ የእኛ ነው፡፡ ስለ የትኛው ‹‹ኢትዮጵያዊ›› ትውልድ ነው የሚያወሩት? በምኑስ ነው የሚወቃቀሱት፣ በምኑስ ነው የሚሞካሻሸት?

"ያን ትውልድ የቀረፅነው እኛ ነን፡፡ በራሳችን ትምህርት ቤት፣ በራሳችን የትምህርት ስርዓት፣ በራሳችን መምህራን፣ በራሳችን ርዕዮት፣ በራሳችን ባህል፣ በራሳችን ልማድ፣ ለራሳችን ዓላማ ስንል የፈጠርነው ትውልድ ነው ያለው፡፡ ሁለቱም ትውልድ አሁን ድረስ እኛ የሰጠነውን ነገር ብቻ ተሸክሞ ያለ ትውልድ ነው፡፡ ያ ትውልድ፣ ለማለት፣ እራሱን የቻለ ትውልድ ሊኖር ይገባል፡፡ ቻይና ‹‹ያ ትውልድ›› ብትል፣ የማ ኦ ሴቱንግን ዘመን ትውልድ መሆኑ ነው፡፡ ‹‹ይህ ትውልድ›› ብትል፣ የሁጂንታኦ ዘመን ትውልድ›› ማለቷ ነው፡፡ ትውልድን ከፋፍሎ ለመግለፅ ይህ አይነቱ የራስ ነገር ሊኖር ያስፈልጋል፡፡

"ከራሱ ህዝብ ጋር ሆኖ፣ በራሱ ተነስቶ፣ ራሱን አብቅቶ፣ ራሱን አስተምሮ፣ ራሱን አሰልጥኖ፣ የራሱን ፕሮግራም መቅረፅ ችሎ፣ የራሱን አገር ማዕከል ያደረገ አስተሳሰብ አመንጭቶ፣ የራሱን ዜጋ አሳትፎ፣ ከራሱ ህዝብ ጋር ለእራሱ የሚሆነውንና የሚበጀውን የፖለቲካ ፕሮግራም ቀርፆ፣ በራሱ አገር ተግባራዊ አድርጎ፣ የራሱን ፍልስፍና ሲያራምድ ኖሮ፣ የራሱን አልሚ አሳብ በራሱ አገር ጀምሮ፣ ራሱ ወድቆ፣ ራሱ ተነስቶ፣ ከራሱ ስህተት ተምሮ፣ ወጥቶ፣ ወርዶ፣ የራሱን ስራ መስራትና ለራሱ ትውልድ ማስተላለፍ የቻለ ትውልድ ሲኖር ነው፤ያ ትውልድ ማለት የሚቻለው፡፡ ይህ ትውልድ ማለት የሚቻለውም በተመሳሳይ፣ ከዚያኛው የራሱ ወገን ከሆነው ትውልድ የተቀበለውን አገር በቀል ጅምር ይዞ፣ የሚሻሻለውን እያሻሻለ፣ የተሳሳተውን እያስተካከለ፣ የጎደለውን እየሞላ፣ በዘመኑ ምክንያት ሳይካተት የቀረን ነገር እያካተተ፣ መቀጠል የቻለ ትውልድ ሲኖር ነው፣ ይህ ትውልድ ብሎ ለመግለፅ የሚቻለው፡፡ የራስ ጅምር፣ የራስ ዕቅድ፣ የራስ ራዕይ፣ የራስ ነገር ያስፈልጋል፡፡ ወይም ሊኖር ይገባል፡፡

"ያ ሲሆን ያ ትውልድ በስህተት የኢኮኖሚ ችግር እንዲፈጠር አድርጎ ከነበረ፣ ስህተት ሰርቶ ከነበረ፣ ወዘተ.....ምንም ችግር የለም በዚህኛው ትውልድ ይስተካከላል፡፡ ምክንያቱም አገሪቱ አለች፣ ብሔራዊ አንድነት አልፈረሰም፣ ባህል አልተበረዘም፣ የሚስተካከል እንጂ የማይስተካከል ችግር አይኖርምና ያ ትውልድ ይህ ትውልድ እየተባለ ይቀጠላል....፡፡

"ምንም የራስ ነገርና የራስ ጅምር በሌለበት ሁኔታ ግን ያ መጠቀም አስፈላጊ ላይሆን ይችላል፡፡

"ታዲያ የኢትዮጵያው ያ ትውልድ በራሱ የፈጠረውና ያዘጋጀው ነገር አለ እንዴ? የለም፡፡ የነበረውን ጥሎ የሚን መያዝ የጀመረ ትውልድ ነው የነበረው፡፡ ያንን ነው ያ ትውልድ የሚሉት፡፡ የነበራቸውን ነገር ይዘው ባላቸው ላይ መጨመር፣ ማስተካከል፣ ማሻሻል፣ ከዘመኑ ጋር ማዘመን፣ ቢችሉ መልካም፡፡ የሆነው ያ አይደለም፡፡ የነበራቸውን አጠቃላይ ነገር ጥለው እንደ አዲስ የእኛን ሙሉ ነገር ለመውረስ ነው የሞከሩት፡፡ ይህ ደግሞ አጉል ነው፡፡ "የቆጥ አወርድ ብላ...." ወደ ሚለው ተረት ይወስደናል፡፡

"ለማንኛውም፣እኛ ያዘጋጀነውንና ያቀረብንለትን ነገር የመምረጥ ዕድል ብቻ ነውና የነበረው፣ ያ ትውልድ የፈለገውን መርጦ አንስቷል፡፡ ምርጫውንም ለዚህኛው ትውልድ አስተላልፏል፡፡ ምርጫው ትክክል ይሁን አይሁን መረዳት የራሱ ድርሻ ነው፡፡ ብቻ ግን መርጧል! ወቀሳው በስህተታቸው ከሆነ ሌሎች እንዲሳሳቱ ሆነ ብለው ፈልገው ያደረጉት ነውና፣ የሌሎች ስህተት እንጂ በራሳቸው የፈጠሩት ስህተት አይደለም፡፡ እነሱም በወቅቱ እንደተሳሳቱ ላያውቁ ይችላሉ፡፡

"በገዛ ቤተሰብህ ያልተሰራ፣ ወይም እራስህ ያልሰራህው፣ አሊያም ሲሰራ ያላየህው ምግብ፣ ይመረዝ አይመረዝ ልታውቀው አትችልም፡፡ ከጉዳት በኋላ ነው መመረዙን የምታውቀው፡፡ ያ ትውልድ ራሱ ያልሰራው በሌሎች ተሰርቶና ተዘጋጅቶ የመጣ የተለያዩ ምግብ ቀረበለት፡፡ ከፊሉ የተመረዘ፣ ከፊሉ ያልተመረዘ ፡የተመረዘው የትኛው እንደሆነ ስለማያስታውቅ አንዱን መርጦ አነሳ፡፡ መራጩ ትውልድ መርዝ የሌለውን መምረጥ ከቻለ ከመመረዝ ይድናል፡፡ መርዝ ያለውን ከመረጠ ይመረዛል፣ ተጎጂ ይሆናል፡፡ ይህንንም ለማወቅ ግን እውቀት ያስፈልጋል፡፡ መራጩ ያ ዕውቀት ያልነበረው ከሆነ አይወቀስም፡፡ ያ ዕውቀት እያለው ተዘናግቶ ወይም በእምነት የተመረዘውን ከመረጠና ካነሳ ግን ሊወቀስ ይችላል፡፡

"ያ ትውልድ በመጠኑም ቢሆን ያ ዕውቀት ነበረው፡፡ ያ ዕውቀት ምንድነው? እኛ መርዝ የሌለው ምግብ እንደማናቀርብ ያውቅ ነበር! ሁሌም የተመረዘ ምግብ ብቻ እንደምናቀርብ የማወቅ ዕድል ነበራቸው፡፡ ከቀድሞ አባቶቻቸው ጀምሮ እኛ የምናቀርበው የተመረዘን ምግብ ብቻ መሆኑን በቀላሉ መረዳት ይችሉ ነበር፡፡ ከትናንቱ ታሪክ! ይህን ማስተዋል አልቻሉም ተሳሳቱ...ተንዱ፡፡ ከዚያ በኋላ ግን መመረዙ ቆይቶ ገባቸው፡፡ ገብቷቸውም ግን፣ እንደተመረዘ እያወቁም ግን፣ ለዚህኛው ትውልድ አልተመረዘም እያሉ መወገብ ጀመሩ፡፡

"የዚያ ትውልድ ስህተት ይህ ነው፡፡ የስህተቶች ሁሉ ስህተት ደግሞ፣ምርጫው የተሳሳተ እንደነበር እያወቀ መኳንና፣ ለማስተባበል መሞከር ነው፡፡ ይህን እንደ ሽንፈት ቆጥሮ፣ራሱን ከተጠያቂነት ለማዳን ሲል፣ አለማመኑ ደግሞ ይህኛውን ትውልድ ተሳስቶ ከማሳት አልፎ፣በስህተቱ እንዲቀጥል አድርጓልና፣

ከዚህኛው ትውልድ ይልቅ መወቀስ ያለበት ያ ትውልድ ነው። ይህም ግን አስፈላጊ አይደለም። አልፏል! ልትሉ ትችላላችሁ። አላለፈም.....።

"አሁን ድረስ «ያ ትውልድ» የሚለውን እየሰማ ነው፣ ይህ ትውልድ የቀድሞ ነገስታቱን አብሮ የሚሰድበው። ይህ ትውልድ ያ ትውልድ የሚለውን ሰምቶ ነው እንዲህ እርስ በእርሱ እየተባላ ያለው። ነገስታቱን ሳይቀር የሚሳደበው።

"ያው.....የዛሬ ፖለቲከኞች የትናንቱ ያ ትውልድ መሆናቸው ነው። «እኛ ተማሪ ሆነን በጋራ ያመጣነው ለውጥ ነው...» እያሉ፣ የሚከፈሉት ሁኔታውን እንደ ዝና የሚቆጥሩት የዛሬ ፖለቲከኞች፣ ውጭ አገር የተሰራ ሱፍና ከረባት አድርገው፣ የውጭ አገር ጫማ ተጫምተው፣ በባዶ እግራቸው ተጉዘው ነፃ ያወጧቸውን ነገስታት እየተሳደቡ የሚገኙበት ሁኔታ ነው ያለው። እነሱ የተማሩ የሚባሉት እንኳን ምንም ነገር ሳይሰሩ፣ እኛ በሰራነው ተሽከርካሪ ወንበር ላይ ቁጭ ብለው ይሳደባሉ! እኛ በሰራነው ቴሌቪዥንም ስድባቸው ይተላለፋል! ብሄርን ከብሄር እንዴት አድርገው እያጣሉ እንዳሉ ብታዩ ትደነቃላችሁ!

"በዚያች አገር ላይ ምንም እንኳን የብሄሮችን መከፋፈል ብንፈልገውም፣ ብናሰርፀውም፣ እዚህ ደረጃ ይደርሳል ብለን አስበን አናውቅም። እንዲህ ይገንናል ብለንም አልገመትንም። ኧረ እንዲህ መግነንም አልነበረበትም። ይህን ነቀርሳ ከተከልንባቸው ከሁሉም አገራት ህዝቦች እነሱ ብሰው ተገኙ! የቀድሞ ነገስታቶቻቸውን በብሄር ተካፍለው እስከ መሳደብ ደረጃ? በፍፁም አልጠበቅንም።

"ይገርማችኋል የኢትዮጵያ የቀድሞ ነገስታት ትልቁ ስራቸው ቤተ-ክርስቲያን መገንባት ነበር። ጥፋት ሰርተዋል ከተባለ ይህ ብቻ ነው ጥፋታቸው። እራቅ ወዳለ ግዛት እየሄዱ ያውም ዘመናዊ የመጓጓዣ ዘዴ በሌለበት በፈረስና በበቅሎ እየተጓዙ ከዚህ አይነቱ ራስን አፈር ከመቀባትና ከንፈርን ተልትሎ ራቁትን ከመኖር ወጥተው መንፈሳዊ ህግ ኖሯቸው እንዲኖሩ ለማድረግ ሲሉ በየቦታው የሐይማኖት ተቋም ይገነቡ ነበር።

"ይህን ለማድረግ ብዙ ዋጋ ከፍለዋል። በባዶ እግራቸው ተጉዘው ከዚያ ሰርዓት አልበኛ የግመት ህይወት ለማውጣት ሲሉ ቤተ-

ክርስቲያን ስለሰሩ ብቻ፣ዛሬ ላይ ብሽቅጥ ያለ ስድብ የሚሰደቡት በዚህ ሆኗል።

"የሌሎችን እምነት በሃይል እና በጫና ሞነውብን፣ ተሞነውን፣ እያሉ ሲያወሩ፣ ሲተቹና ሲሰድቡ ብታዩ፣ እንዴ ሰው ማዘናችሁ አይቀርም። ቋንቋችን ተሞኖ፣ ባህላችን እንዳናሳድግ ተከልክለን፣ ተፅእኖ ተደርጎብን፣ እየተባለ በየመድረኩ ሲዘለፉ ስሰማ እኔ እራሴ ማራ ይገባኛል! "እኔ እስከማውቀው ድረስ በዚያች አገር ላይ እንዲህ አይነት ጫና አልነበረም! በግድ ቋንቋ ያስለወጠ፣ ባህል ያስቀየረ፣ ንጉስ ለማስለወጥ ሞክሮ ከሽፎበታል። በተረፈ ሌላው ሁሉ የውሸት ወሬ ነው። ከምንም ሐይማኖት ወደ ክርስትና የመጡ ይኖራሉ፣በግድ ሳይሆን በፍላጎት። አስተማሪ ተመድቦ፣ ቤተ-ክርስቲያን ተሰርቶ፣ በሂደት ሲሞክር ቆይቷል። በወቅቱ ነገስታቱ ስራዬ ብለው የያዙት ሰው የማዳን ስራ ነበር። እሱም የመንግስት ሐይማኖት ስለሆነ ነው። ሌላ ምን አለ? ቋንቋቸው አሁን ድረስ መኖሩ ማስረጃ ነው፣ ባህላቸው አሁን ድረስ መኖሩ ማስረጃ ነው። ምሁሮቻቸውም ከሁሉም ብሄር የወጡ መሆናቸው ማስረጃ ነው።

"ትምህርትን ለአንድ ብሄር ብቻ የሚል ህግ አልነበራቸውም። ይህንን እኛ እናውቃለን። ዘመናዊ ትምህርት የጀመሩት ትናንት ነው። የትናንት ተማሪዎች የዛሬ ምሁሮች ከሁሉም ብሄር አሉ። ቄራሽ ምን ይላሉ፣«የአማራ ብሔር የበላይነት ነበረ!» ይላሉ! አሁን ድረስ በሳር ጎጆ የሚኖረው ያ ህዝብ ነው። የነገስታት ዘር እየተከታተሉ ስለነገሱ ብቻ፣ ሁሉም የዚያ ብሄር ተወላጅ ንጉስ ሆኖ ያለፈ ይመስላቸዋል። የንግስና ስርዓቱ ከአንድ የሰለሞን ዘረግ ከመመዘዝና ወደ ልጅ ልጅ እየተላለፈ ከመቀጠሉ ውጪ እያንዳንዱ አማራ ንጉስ የመሆን ዕድል በዙር እንዴ ደረሰው አድርገው ያወራሉ ያስወራሉ። እውነቱ ግን ይህ አይደለም! ሴሚቲኩም ለነገስታቱ ይገዛል፣ኩሽቲኩም ለነገስታቱ ይገዛል፣ ሁሉም ብሄር ለነገስታቱ ይገዛል። የእኛር ዘይቤው አንድ አይነት ነው። ሁሉም ብሄር ዛሬ ድረስ በባዶ እግሩ የሚሄድ በባዶ እግሩ የሚያርስ ነው! ይህ በራሱ ምስክር ነው! አማራ በትራክተር ሌላው ብሄር በበሬ እያረሰ ያለ ነው የሚያስመስሉት! መባል ከነበረበት አንድ ነገር ብቻ ነው! «ለእነሱ ቤተክርስቲያን ሰርተው

ለኛ ቤተ-ክርስቲያን ሳይሰሩ ቀሩ!» ብሎ መቆጨት ከሆነ ያስኬዳል፡፡ በተረፈ በሌላ ነገር መተቸት አይቻልም፡፡ ይህንን ደግሞ ብዙዎቹ የጎሳ መሪዎች እየተቃወሙ እንጂ ነገስታቱ በየዘመናቸው ሞክረዋል፡፡ መሞከር ብቻ አይደለም ሰርተዋል! በዚያ ዘመን ሌላ ምን ሊያደርጉ ይችላሉ? ሌላ ምን ተልእኮ ነበራቸው? ጎላቸው አንድ ነው! እሱም ይሄው የሐይማኖት ጉዳይ ብቻ!

"ይልቁንም ብዙዎቹ የኢትዮጵያ ነገስታት አትም እያጡና አገሩ ሩቅ እየሆነባቸው፣ መንንዣው እየቸገራቸው፣ ቋንቋቸውን የሚችሉ ሰዎችን እየመረጡ አብረው እየላኩ የእኛን ሚሲዮኖች ሳይቀር ወዳልቀናው አገር እየሄዱ ሐይማኖትን እንዲያዳርሱ ይማጸኗቸው ነበር፡፡ ቢያንስ መጽሐፍ ቅዱስን አስተምሩልን፣ ወይ ክርስቲያን ወይ እስላም አድርጉልን፡፡ ወደ መረጡት ሐይማኖት መልሱልን! እያሉ ይማፀኑ ነበር፡፡ እስልምናን ለሚያስተምሩና ለሚያስፋፉም፣ ክርስትናን ለሚያስተምሩና ለሚያስፋፉም፣ መንገዱ ክፍት ነበር፡፡ በሰሜንም፣ በደቡብም፣ በምስራቅም፣ በምዕራብም ለሚሲዮኖች ክፍት ነበር፡፡ «ሐይማኖት ልናስፋፋ ነው» ከተባለ ነገስታቱ እምቢ ብለው አያውቁም፡፡ በዚህ ዘዴ ነበር እንዳውም እኛ ሰላዮቻችን እንደልባቸው የሐይማኖት ማሊያ ለብሰው እንዲሄዱ የምናደርገው፡፡ ይህ ሀቅ ነው፡፡ የሐይማኖት ጫና ቢኖር ያ ሁሉ ሙስሊም፣ ያ ሁሉ ክርስቲያን፣ በዚያች አገር ባልተገኘ ነበር፡፡ የብሔር ብሄረሰቦች መብትና የሐይማኖት እኩልነት የመጣው በዚህ ስርዓት አይደለም፡፡ እንደዚያ ከሆነ በጂማ እኩል ሙስሊም እኩል ክርስቲያን፣ በጎንደር እኩል ሙስሊም እኩል ክርስቲያን ባልተገኘ ነበር፡፡ ከቤተ-ክርስቲያን ጎን መስጊድ ባልተገኘ ነበር፡፡ ከአማራ ጎን ትግሬ፣ ከኦሮሞ ጎን ጉራጌ፣ ከሌላው ብሄር ጎን ሌላ ብሄር ባልተገኘ ነበር፡፡ የብሔር ጫና ቢኖር ቋንቋም ባልተገኘ ነበር፡፡ የየብሄሩን ባህል መጫን ከነበረ አሁን ድረስ ምንም አይነት ባህል ባልታዬ፣ ባልተገኘ፣ ነበር!! የሙዚቃ መሳሪያዎቻቸው ተሰባብረው ጠፍተው በቀሩ ነበር፡፡ የቀድሞ ነገስታት ያን ማድረግ ቢፈልጉ ኖሮ ረጃጅም ነፃ ዓመታት ነበሯቸው፡፡ ሰፊ የማጥፊያ ጊዜ ነበራቸውና ያጠፉት ነበር፡፡ ያን ግን አላደረጉትም! የባፊ ዘመን የብሄር ፖለቲካ አራማጆች ግን ህዝቦች ከነገስታቱ ተደብቀው ቋንቋና ባህላቸውን አልጋ ስር

ውስጥ ተደብቀው ሲያስፋፉ የቆዩ ነው የሚያስመስሉት! በምን ጠልተው እንደሚያስጠሏቸው አላውቅም፡፡ የባሪያ ንግድ ከሆነ የባሪያ ንግድን የመሰረትነው እኛ፣ በህግ ያስቀረነውም እኛ ነን! አንድን ብሄር ነጥሎ ባሪያ የማድረግ ነገርም አልነበረም፡፡ አንዱን ብሄር ጨቁኖ አንዱን ብሄር ማግነን ጨርሶ አልነበረም! ሁሉም ውሸት ነው ክቡራን፡፡ እንዳልኩት፣ የመንግስት ሐይማኖት ክርስትና ስለነበር ነገስታቱ ቤተ-ክርስቲያን በመስራት ላይ ትኩረት ያደርጋሉ፡፡ መስጊድ ሲሰራ ግን ከልክለው አያውቁም፡፡ ሐይማኖት ሊያስፋፉ ሄደው እንኳ፣ ህዝቡ ወይም የጎሳው አመራር «የዚህ አገር ብዙው ህዝብ ሙስሊም ነውና እኛ የምንፈልገው መስጊድ ነው» ካለ መስጊዱ እንዲሰራ ያደርጉ ነበር፡፡ የትኛውን ጫና እንደሚያወሩትና በየትኛው የከረረ ጫና የቀድሞ ነገስታቱን እንደሚሳደቡ ግራ ይገባኛል፡፡

"በዚያ ዘመን አንድ የኢትዮጵያ ንጉስ የሚወደደውም፣ የሚወደሰውም፣ ሺ ዓመት ንገስ የሚባለውም፣ ለሐይማኖቱ ባደረገው አስተዋፅኦ ብቻ ነው፡፡ በሰራው ቤተክርስቲያን ልክ ነው! የኢኮኖሚ እድገት ባመጣ በምናምን አይደለም፡፡ ይሄን ይሄን ቋንቋ እኛ ትላንት ያስተማርናቸው ነው፡፡

"በተረፈ ነገስታቱ ግዛት የሚዘርፉበት ምንም ምክንያት የለምና አልዘረፉም! ቡና ዘርፈው ኤክስፖርት አድርገው እንደ ዛሬዎቹ ባለስልጣናት ገንዘብ አላጠራቀሙ! ኤክስፖርት የለ፣ ታክስ የለ፣ ግብር የለ፣ ምን የለ፡፡ ገበሬው ገብር ይባላል፣ ለካህናት ምግብ ጥቂት ጥቂት እህል እያዋጣ ይገብራል! የመሬት ባላባቶች አነስተኛ መሬት ያለውን ገበሬ ከምርቱ እያካፈሉ ያሳርሱ ነበር፡፡ ይሄው ነው ታሪኩ! እነሱ ግን አንድ ብሄር ብቻ ሲገብር እንደኖረ አድርገው ነው የሚያወሩት፡፡

"ነገስታቱ በሰሩት ቤተ መንግስት ተሰብስበው፣ የራሳቸውን ቤተ-መንግስት እንኳ ሳይገነቡ፣ እነሱን መዝለፍ ዋና ስራቸው አድርገው ከያዙት ሩብ ምዕተ ዓመት ሆነ ክቡራን! ይህ አይነቱ ቀውስ እንዲኖር ያደረገው በዋናነት የእኛ ስራ ቢሆንም፣ እዚህ ደረጃ ያደረሱት ግን በራሳቸው ጥበብ ነው፡፡ የሃሰት ጥበብ፡፡

"ይግረማችሁና ነገሩ በጣም ከመክረሩ የተነሳ ጭራሽ ታቦት ይዘው የተዋጉትን ሐይማኖተኛ ንጉስ፣ጡት ቆርጠዋል በሚል ተረት አራቅቀው፣የፈጠራ ታሪኩ በሐሰት በተፃፈበት የመጽሐፉ መቹት

ያስጥናኤል ጎል ኢትዮጵያ ቁጥር ሦስት

በሆነው አካባቢ፣ በንጉሱ እጅ የተቆረጠ ጡት የሚያሳይ ሀውልት በብዙ ሚሊዮን ብር ገንብተው፣ያ ትውልድ ያልናቸው ምሁራን ባሉበት መርቀው አጨብጭበው ሲከፍቱ ብታዩ ምን ይሰማችኋል? ሚኒልክን እኮ ነው! እንዴ ሰው አታዝኑም እንዴ? ወይስ ታሪክ አላንበባችሁም? ምኒልክን የሚያውቅ የለም? አጣሊያ ምንው ዝም አልክ?"

"እረ እናውቃለን ንግሰት ሆይ"

"እዘኑሞ ታዲያ! የምን ዝም ብሎ ማፍጠጥ ነው? ሚኒሊክ ማለት የማረከውን የእናንተን ጀኔራል አልበርቶኒን፣ ያን ሁሉ ጉዳት እንዳደረሰበት እያወቀ እንኳ የሮም ሀዝብ ካሁን አሁን ምርኮኛቹን ሊሰቅሏቸው ነው ብሎ ሲጠብቅ፣ ‹‹አምላካችን ይቅር ባይ ነውና ይቅር ብለንሃል፣ ሂድ ወዳ ሚስትህ፣ ይህንን የሚች ባልደረባህን የጀኔራል አርሞንዲ ሻምላም ወስደህ ለሚሰቱ በክብር ስጥልኝ›› ብሎ ከእነ ማእረጉ፣ ከእነ ሻምላው፣ በክብር የሸኘው ንጉስ ማለት ነው! በወቅቱ ምርኮኛ ጀኔራል ራሱ ማመን አቅቶት ነበር! የአጣሊያ ሀዝብም በንጉሱ ምህረት ተደንቆ፣የአድናቆት መፈክሩን ይዞ በመውጣት፣በሮም አደባባይ፣ ‹‹ሚኒሊክ ቪቫ›› በሚል መፈክር ከተማዋን ሲንጣት ነበር የዋለው!

"ይህ ንጉሥ-ነገስት እንኳን የሰው ጡት ያውም የዜጎቹን ጡት ሲቆርጥ ቀርቶ ታቦት ይዞ ጦር ሚዳ የሂደ የዓለማችን ብቸኛ ብልሀና አማኝ ንጉስ ነው! አያችሁ እምነት? ራስህን አድን መሆኑ ነው! ይህን ንጉስ እንደ እኛ የሚያውቀው የለም:: በየአለቱ የሚፅፉቸው ደብዳቤዎች ወደ እኛ ቤተ መንግስት ይደርሱ ነበር:: አውንም ድረስ አሉ:: በጣም ወዳጆችን ነበር:: ለአገሩ ያለው ፍቅርና ለህዝቡ ያለው ክብር ከንጉስ የሚጠበቅ አልነበረም! ከዓለማችን ደግና ሩህሩህ ንጉስ አንዱ፣ ምናልባትም ብቸኛው እሱ ነው:: ይህን ነው የዛሬ ፖለቲከኞች የሚሰድቡት ሳውቅን ሳይና ስሰማ፣ ‹‹አይ አሼምድ!›› እላለሁ የሚሰድቡ ሳውቅን ሳይና ስሰማ፣ ‹‹አይ አሼምድ!›› እላለሁ ብቻየን:: ስለ እነሱ እኔ አፍራለሁ! በእርግጥም ያሳፍራል! እንደዚያ አድርገው አዋርደው የመለሷቸው ጠላቶቻቸው እንኳን ስለ ስብዕናቸው ይመሰክራሉ! በቁጭት ተነሳስተው እንኳ እንዲህ ያለ ስም ማጥፋት ውስጥ አልገቡም! ይህ ታሪክ በየትኛውም የታሪክ ሰነድ ተመዝግቦ አይገኝም! በየትኛውም! ወደ እዚህ የሚጓጓ ታሪክ እንኳ የላቸውም! እንዴት እንዴት አድርገው

እንዳሰቡትና እንደፈጠሩት፣ያውም በአጭር ጊዜ! ግራ ግብት ይለኛል:: እንዳንዴማ በትክክል ልዑላችን በዚያች አገር እየነገሰ እንዳለም እረዳበታለሁ!

"ጊዜው ትናንት ነው፣ መቅሰት የማይቻልበት ትናንት:: የድሮ ታሪክ ቢሆን... መቸም ቢዋሽ ያስኬድ ይሆናል:: በአፈ ታሪክ.... እየተባለ ሃሰተኛ ወሬን ማሰራጨት ይቻላል:: ዕውፍ በነበረበት፣ ታሪክ ወዛፎች አገር አጥኝዎች በነበሩበት፣ ፎቶ ግራፍ ሳይቀር በነበረበት፣ በትናንቱ በሚኒሊክ ዘመን እንዲህ ያለ ተግባር ተፈፅሞ ነበር የሚል ውሸት ነው የሚዋሸው::

"ሚኒሊክ ዘመን የኛ ቆንሲሎች ኢትዮጵያ ውስጥ ነበሩ:: አገር እንዲህ ያለ ታሪክ ጨርሶ አልተፈፀመም:: ማንም ለዚህ አያቀርብም! እንዴት ሲታመንና ሲራገብ እንደቻለ ይገርመኛል:: "በነገራችን ላይ የኢትዮጵያን የመጨረሻዎቹን አራት ነገስታት በደንብ እናውቃቸዋለን:: እጅግ ሲበዛ ወዳጆቻችንም ነበሩ:: በየ አሉቱ ከሁሉም ነገስታት ደብዳቤ ይደርሰናል:: ስጦታ ይልኩልናል፣እኛም እንልክላቸዋለን:: መሰሪነታችን እና ሴራችንን አያውቁ ስለነበር፣ እንደ ክርስቲያን አጋሻ አገራት አድርው ስለሚቆጥሩን አቤቱታቸውን ሁሉ ለእኛ ብቻ ነበር የሚያቀርቡት፣ እኛን ሳያማክሩና ለእኛ ቀድመው ሳያሳውቁ አንዲትም ተግባር አልፈፀሙም:: አንዲት ጦርነት አላካሂዱም:: ከውጭ ጠላት ጋርም ይሁን ከአገር ውስጥ ጠላት ጋር ሲዋጉ ቅድሚያ ለእኛ በደብዳቤ ያሳውቃሉ:: የውጭ ጠላት ከሆነ፣‹‹ንግስት ቪክቶሪያ ሆይ፣የውጭ ጠላት መጥቶብኛልና ልዋጋ ነው›› ብለው ደብዳቤ ይፅፉልናል::የውስጥ ፀብ ከሆነ፣‹‹ንግስት ሆይ፣ሽፍታ ተነስቶብኛልና መስበሪያው ይፈለግልኝ::ልዋጋ ነው:: መሳሪያ ይላኩልኝ:: ወዳጅዎን አይርሱ...›› እያሉ ይፅፉልን ነበር! አጼ ቴዎድሮስም፣አጼ ዮሐንስም፣አፄ ሚኒልክም፣ሌሎቹም ይፅፉልን ነበር:: ደብዳቤዎቻቸውን አንድ በአንድ ላሳያችሁ እችላለሁ:: ሁሉንም ከእነ ዓላማቸው፣ ከእነ ፍላጎታቸው፣ ከእነ ፀባያቸው፣ ከእነ አስተሳሰባቸው፣ በጥልቀት እናውቃቸዋለን!

"የየአገሩ ንጉሶች ንጉሥ-ነገስት ለመሆን እርስ በእርስ ከሞኮራረፍና ከመፈራራት እንዲሁም አንዱ አንዱን አሸንፎ ከንጉስነት ወደ

"አያችሁ የሃሰት ፕሮፖጋንዳ ምን ያህል ከፋ ነቀርሳ እንደሆነ? የ7 ሺ ዓመት ታሪክ፣ ያውም የተዓፅ ታሪክ ያላት አገር፣ ፍርስርሷ የወጣው 25 ዓመት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ነው! አገር ማፍረስ ምን ያህል ቀላል እንደሆነ ተገንዘቡ! 25 ዓመት በአንድ ብቸኛ የቴሌቪዥን ጣቢያ እንድ አይነትና ተደጋጋሚ መንግስታዊና ሀጋዊ የሆነ ውሸት ሲጋት የኖረ ትውልድ ነውና፣ውሸትንም በሐውልት ቀርፆ ያስቀመጠ መንግስት ነውና መመለሻው ላይገኝ ይችላል! ይህ እንግዲህ ሁለቱን ትልልቅ ብሄሮች ለዘላለሙ ለማጋጨትና በስልጣን ለመቆየት ሲባል የተደረገ ነው! በዚህ አላበቁም ክቡራን! ለስልጣናቸው ሲሉ፣የራሳቸውን አንድ ህዝብም ከፍለውታል! አጣልተውታል! ይህን ያደረጉት የብሔራቸውን የበላይነት ለማረጋገጥና ለማስቀጠል አይደለም! የራሳቸውን የፓርቲውን የስልጣን የበላይነት ለማረጋገጥና ለማስቀጠል ሲሉ ብቻ ነው! በዚህ ሂደት ጥቂት የሌባ ባለስልጣናት ቤተሰቦች በኢኮኖሚ ከፍ ብለው ሲታዩ፣ ህዝቡ ብሄራቸውን እየጠቀሙ ያለ መስለው፡፡ ይሄም ለእነሱ ጥሩ ገጠመኝ ሆነላቸውና፣‹‹አዎ እንደዚያ ነው፣ለብሄራችን ስንል ነው›› ማለት ጀመሩና፣ሌላ የብሄር ንግድ ውስጥ ገቡ፡፡ ህዝባቸውን የመጫወቻ ካርድ አድርገው መቀጠሉ ተገቢ መሆኑን አምነውም፣አንድ ቋንቋ፣ አንድ ፊደል፣ አንድ ሐይማኖት፣ አንድ ባህል፣ አንድ ብዙ ነገር ያለውንና ለብዙ ሺ ዘመናት አንድ አይነት ነገር ሲጋራ የኖረውን አንድ ህዝብ ሁለት አድርገው ከፈሉት! መክፈል ብቻ አይደለም! ተመሳሳይ የጡት ቆረጣ ሃውልት አላቆሙም እንጂ፣ያንኑ ተመሳሳይ ስራ በሰሜኑ ህዝብ ላይም ከመፈፀም ወደ ኋላ አላሉም፡፡

"ያን በእግሩ እየተመላለሰ ይጠያየቅ የነበረን አንድ ህዝብ፣ በትራንስፖርት ዘመን እንደ ልቡ እየመጣ እንዳይጠያየቅ አደረጉት! የግዳማትና የአድባራት ግንኙነት ቆመ፡፡ ሐይማኖታዊ ግንኙነቱ ሳይቀር እየሻከረ በክላሽ ማመን እየተተካ ቀጠለ፡፡ አለመተማመንን አስፍነው በፍፁም ጠላትነት እንዲተያዩ አደረጉ! ወደ ቀድሞው ዘመን እየሄዱ፣ነገስታቶቻቸውንና ጀግኖቻቸውን እንደ ድርሻ መከፋፈል ጀመሩ፡፡ አሁላ አባ ነጋ የትግራ ጀግና፣ ገብርየ የአማራ ጀግና፣ እየተባሉ ሄዱ! ሚራሽ አፄ ዮሐንስ የትግራ ንጉስና ጀግና፣ አፄ ቴዎድሮስ የአማራ ጀግና ተብለው ተከፋፍለዋል እኮ! አው....ይህንንም አታውቁም ለካ! የሚገርም ነገር

ንጉሥነስትነት ለመሸጋገር ካልሆነ በቀር፣ ሌላ ሴራ የምትባል ነገር አያውቁም! አንዳንድ ጥፋቶችን የሚፈፅመት ይቺን ዓላማቸውን ዳር ለማድረስ ካልሆነ በቀር፣ አንዱን ብሄር ባንዱ ላይ ለማስነሳትና፣ አንዱን ብሄር በድለው አንዱን ብሄር ለመጥቀም ያደረጉት ምንም አይነት ጥረት ካለመኖሩም በላይ፣ወደ እዚያ የሚጠጋጋ አስተሳሰብ እንኳ ኖሯቸው አያውቁም! ሊያስቡትም አይችሉም! ለዋናው ንጉሥነገስት ገብር አልገብርም በሚል ፀብ ነበረ፡፡ይህም የነበረና ያለ የተለመደ ተግባር ነው፡፡ በተረፈ ሁሉም አገር ወዳድ፣ ሁሉም ሐይማኖት አፍቃሪ፣ በአገራቸው ህልውና የመጣባቸውን ጠላት አይምሬ ነበሩ!

"የኢትዮጵያ ነገስታት ሌላ የፖለቲካ ሴራና የዘር ማጥፋት ወንጀል ውስጥ ሊገቡ? በጭራሽ! የሚኖሩት ለምን ሆነና? ንግስናውንም ስልጣኑንም የሚፈልጉት ለገዢ፣ በቴሌቪዥን ለመታየት አይደለም፡፡ ከራሳቸው ኪስ ለመስረቅ አይደለም! መሬት ለመዝረፍ አይደለም! በዚያ ወቅት የህዝብ ብዛትም የለም፣የመሬት ጥበትም የለም፡፡ ሁሉም ነገር የሚደረገው ከሐይማኖት ጋር ለተያያዘ ቀና ተግባር ብቻ ስለነበር በሌላው ነገር ሰንፈው ይሆናል፡፡ ያም የሚያስተች አይደለም፡፡ ነገስታቱ ጥቂት የቤተ ክህነት ትምህርት እንጂ ዘመናዊ ትምህርት የተማሩ አልነበሩም፡፡ ስለዚህ ዓላማቸው አንድ ነው፡፡ ያለ ዘመናዊ ህግም ቢሆን፣ ሐይማኖታዊ ስርዓት ያለው ህዝብ ለመፍጠርና፣ ከአህዛብነት አውጥቶ ወደ ተጨባጩ አምላክ ለመመለስ ነው! ሌላ ራእይ ሰንቆ የተነሳ ንጉስ በየትኛውም ዘመን አልነበረም! ይህ ሁሉ ደግሞ ለሐይማኖታቸው ያላቸውን ቀናኢነት ነው የሚያሳየው፡፡ እንዲህ የሚጥሩለት፣ እንዲህ የሚሳሱለትና እድሜ ልካቸውን የሚሰሩለት ሐይማኖት ደግሞ መመሪያው፣ አስተምህሮው፣ ሰው ላይ ማፍ መፈፀምን በመቃወም ጀምሮ፣ በይቅር በሉ ቀጥሎ፣ ሰዎችን አክብሩ፣ አፍቅሩ፣ በሚል ዓረፍተ ነገር የሚዘጋ አስተምህሮ ነው፡፡ ቢያንስ ያን ያክበራሉና እንዲህ አይነቱን የእነ ‹‹ሻካ ዙሉን›› አይነት አረመኔነት በገዛ ህዝባቸው ላይ ሲፈፅሙ? የማይታሰብ ነው! ጭራሽ ደግሞ "ኢላክ! ሚኒሊክን በጡት ቆረጣ?! የሚያማ ትውልድ ተፈጥሮ አየን! ልብ በሉ! ይህ ታሪክ ከተፈጠረና ከተሰራጨ ገና ሩብ ምዕተ ዓመቱ ነው! በዚህ ዘዴም የ7 ሺ ዓመታት ታሪክን በአንድ ጀንበር ንደው

ነው። አጼ በካፋ የጎንደር ንጉስ፣ አጼ ዮሐንስ 4ኛ የትግሬ ንጉስ ተብለው ነው የሚታወቁት ገባችሁ?

"እነዚያ በእኛ ድጋፍ ስልጣን የያዙ ቡድኖች እንዲህ ብሎ የሚያስብ ትውልድ ነው የፈጠሩልን! ምንም ታሪክ የማያውቅ ትውልድ! ለማወቅም ፍላጎት የሌለው ትውልድ! ልወቅ ቢልም ዕድሉን እንዳያገኝ የተደረገ ትውልድ! ሆኖ እንጂ አጼ ዮሐንስ የአጼ ፋሲልና የአጼ በካፋ ዘር ናቸው። ከእቴጌ ምንትዋብና ከአጼ በካፋ ወንድም ከተወለደው ልጅ የተገኙ የልጅ ልጅ ናቸው! የጎንደር ነገስታት፣ የአክሱም ነገስታት፣ የሸዋ ነገስታት፣ የሚባል ነገር የለም። የመቀመጫ ከተማቸውን ነው የለዋወጡት! ዘራቸው ግን አንድ ነው። ይህ ቀፎ ትውልድ ግን በብሔር ተካፍሏቸዋል። የትግሬው ንጉስ፣ የአማራው ንጉስ፣ እያለ! እነሱንም ከፍሎ፣ እራሱንም ከፍሎ፣ ታሪኩን ተከፋፍሎ ተሊያይቷል! ነገር ግን አንድ ሀዝብ ነው። ወይም ነበር።

"በዚህ አጋጣሚ ስለ ነገስታቱ ታሪክ መጠነኛ ገለፃ ማድረግና፣ ስለ መጨረሻዎቹ ለሃሚትና ለስድብ ስለተዳረጉት ነገስታት ጥቂት ማለት ይኖርብኛል። በዚህም የኢትዮጵያውያኑ አንድነትና ህብረት፣ በሃሰተኛ ፖለቲካዊ ወሬ አማካኝነት እንዴት ከስሩ ተመንግሎ እንደተጣለ በጥልቀት ለመረዳት ሞክሩ።

"ልብ በሉ ክቡራን! የኢትዮጵያ ታሪክ በዓለም አቀፍ ደረጃ በግልፅ የሚታወቅ ነው። የነበረውም ስርዓት አንድ ነው። እሱም የኢትዮጵያ ነገስታት ከቀድሞው የሰለሞናዊው ስርወ-መንግስት የዘር ሃረግ እየተመዘዙ የሚነግሱ መሆናቸው ነው። ይህ ስርዓት ከቀዳማዊ ምኒሊክ ዘመን ጀምሮ እስከ አጼ ኃይለስላሴ ድረስ ለ 3 ሺ ዓመታት የቀጠለና ቋሚ ህግ ሆኖ ሲሰራበት የመጣ ነው። ስልጣኑ ከአንዱ ንጉሥ-ነገስት ወደ ልጁ፣ ከልጁ ወደ ልጅ ልጁ፣ እያለ የቀጠለ ስርዓት ነው የነበረው። ነገስታቱም ከአንድ ምንቂጥ የሚቀዱ ናቸው። በዚህ አይነት ብዙ ነገስታቶች የመናገሻ ከተማቸውን በፈለጉትና በመረጡት ቦታ እያደረጉ እየተፈራረቁ ነግሰዋል። ብዙዎቹ በቀድሞው ከተማ በአክሱም እየተፈራረቁ ሲነግሱ ከቆዩ በኋላ፣ የስልጣን ትግል ተደርጎ፣ ዮዲት ብለው በሚጠሯት ጠረኛ ሴት የተመራው ቡድን አሸነፈ። ድል ነአድ አሸናፊዎቹ የዛግዌ ስርወ-መንግስትን መሰረቱ። በዚያ ጊዜ ይህ

የመጨረሻው የአክሱም ንጉስ ወዶ ሸዋ ከጥቂት ወገኖቹ ጋር መጥቶ ከእነ ቤተሰቡ ገዳም ውስጥ ሲኖር ቆዩ። ከዛጉዬ ስርወ-መንግስት በኋላ፣ ስልጣኑ ወደ ቀድሞው ሰለሞናዊ ስርዓት ይመለስ ተብሎ በስምምነት ሲመለስ፣ የተመለሰው ለዚያው በሸዋ ላለው ለድል ነአድ የዘር ሃረግ ነውና፣ መቀመጫውን በሸዋ አድርጎ ቀጠለ። አክሱም የነገስታቱ መቀመጫ ከተማ መሆኗ ቀርቶ፣ ላስታም የነገስታቱ መቀመጫ መሆኗ ቀርቶ፣ ሸዋ የነገስታቱ መቀመጫ ሆነች ማለት ነው። የንግስና ስርዓቱ ግን በዚያው በቀድሞው የዘር ሃረግ እየተወራረሰ፣ የድል ነአድ የልጅ ልጆች ተክታትለው እየነገሱ ነው የቀጠለው።

"ልብነ ድንግል፣ ገላውዴዎስ፣ ወዘተ....የሸዋ ነገስታት ተብለው የሚታወቁት መቀመጫቸውን ሸዋ እንዳደረጉ ቀጠሉ። በመጨረሻ በልብነድንግል ዘመን፣ በ15ኛው ክፍለ ዘመን በቱርክ ከሚታገዘው ከግራኝ አህመድ ጋር በተደረገ ጦርነት የወቅቱ ንጉሠ-ነገስት ቆዩና ጎንደር ላይ ቤተ-መንግስታቸውን ገንብተው እዚያው ከተሙ። መቀመጫቸውን ጎንደር ላይ አድርገውም በተለመደው ስርዓት እየተከታተሉ መንገሳቸውን ቀጠሉ። በጎንደር እየተፈራረቁ ከነገሱት ነገስታት ውስጥ አንዱ አጼ በካፋ ናቸው። የአጼ ዮሐንስ የዘር ሃረግ የሚመዘዘውም ከአጼ ፋሲልና ከአጼ በካፋ ነው። ለዚያም ነው ንጉሠ-ነገስት ሊሆኑ የቻሉት! የዘር ሃረጋቸው ከዚያው ከነገስታቱ የዘር ሃረግ ባይሆን ኖሮ ፊፅሞ ሊነግሱ አይችሉም።

"ይህ ለማንም ግልፅ ነው። ራሳቸው በእጃቸው ፅፈው የላኩልን ደብዳቤም ይሄን ያረጋግጣል። «የአጼ ፋሲል እና የእነ በካፋ ልጅ ነኝ» እያሉ ነበር የሚፅፉልን።

"የመሳፍንቱ ዘር በየደረጃቸው ግራ አዝማች፣ ቀኝ አዝማች፣ ፊታውራሪ፣ ደጃዝማች፣ ራስ፣ ንጉስ፣ የሚል ሽመት እየተሰጣቸው በየአካባቢው ላይ የሚያስተዳድሩት ቦታ ኖሯቸው ይቀጥላሉ። እነዚህ የነገስታቱ የአክስት ልጅ፣ የአጎት ልጅ፣ የወንድም ልጅ፣ የእህት ልጅ፣ ወዘተ....ቅርብ ዝምድና ያላቸው ሲሆኑ፣ ንጉሠ ነገስት መሆን የሚችለው ግን በቀጥታ ከንጉሠ ነገስት የተወለደ ልጅ ከሆነ ነው። ንጉሥ-ነገስቱ ወንድ ልጅ ከሌለው፣ የወንድሙን ልጅ፣

ወይም የአሠሪን ሴጅ፣ ወይም ከሴት ሴጂ የሚጠለያ፣ ወንጀ ሴጅ መሆኑ ቅርብ የሆነው ተመርጦ ይነግሳል። ቅርብ የሆኑት ደግሞ ለቤተሰቧቸው ሰልጣን ይፎክራሉ። የመፎከር መብትም አላቸው። የየራሳቸውን መር የያዙ ሰለሚሆኑም ያሴመሰሳቸውን ንጉሥነስት አሰመርጀው ይነግሳሉ። ቀስክሩ የቤተሰብ ነው። አንዳይጨ እየተባለም ሴዩ ሰፍራ ተዘጋጅቷሳቸው ሐይማኖታዊ ሰርዓትን እየተማሩ ያድጋሉ። በዚህ ከህነት ሰውነት ቅሽም፣ የተሻለ ወሳይና አሰተውሎት ያሴው ሴጅ እየተመረጠ እየመጣ ይነግሳል። ታሪኩ ይህ ነው።

"ከዚህ መሰረት ዘመነ መሳፍንት የሚባሰው ዘመን አብዮቱ/ዘመነ መሳፍንት ማለት፣ራቅ ራቅ ያለ ዝምድና ጥሪ፣ችው መንገስ የማይችሉ እሰከ ደጃዝማችነት ማዕረግ የደረሱ መሳፍንት የበላይነቱን ይዘው፣በራሳቸው ፍላጎት የመረጡትን ንጉሰ ከመነ አምባ አምጥተው ማንገስና በበላይነት ሞግዚት ሆነው መግዛት የቻሰበት ዘመን ነው/ እነሱ እንኳ ዝምድናቸው ራቅ በማለቱ ምክንያት መንገስ እንደማይችሉ አውቀው መንገስ የሚገባቸውን የንጉሠነገስት ሌጆች እየመረጡ ያንግሱ ነበር። አንጂ የመር የበላይነት ሰላሳቸው ብቻ በዙፋን ላይ አልተቀመጡም። ደካማውን ሌጅ ንጉሠ ነገስት አድርገው እንደ ሉባቸው ያዙበት የነበረበት ዘመን ነው።

"የንግስና ሰርዓቱ እዚህ ድረስ ሀጋሚነቱ ታውቆ በመሳፍንቱም፣ በመኳንንቱም፣ በህዝቡም ዘንድ ይከበር ነበር ለማለት ነው። ዘመነ መሳፍንት በደጃዝማች ካሳ ሃይለ አማካኝነት አበቃ፣ሁለንም አሸንፎ፣ደጃዝማች ካሳ ሃይለ ሰልጣኑን መያዝ ያለና አጼ ቴዎድሮስ ፋን ተብሎ ንጉሠነገስት ሆነ።

"ከዚያ ዘመን እንደተለመደው በሸዋ ንጉሰ ሚኒልክ፣ በትግሬ ደጃዝማች ካሳ ምርጫ፣ በሞጃ ደጃዝማች አገለ፣ በጎጃም ንጉሰ ተክለሐማኖት፣ በልጓሙ ሊሳ ባለሰልጣንና ግሸ ነበረና፣ሰልጣኑ ለኔ ነው የሚገባው፣ ለዙፋኑ በትውልድ ቅርብ አኔ ነኝ፣የንጉሠ ነገስትነት ሰልጣኑ መሆን ያለበት ለእኔ ነው፣ የሚል የእርስ በርስ ቅንአት ተጀመረ። በዚህም ላይ የቴዎድሮስ የዘር ሃረግ በእናቱ በኩል አንጂ በአባቱ በኩል አልነበረምና እሰ ዙፋኑ አይገባውም፣ በሚል ከተለመዱት ተቃውሞዎች ከረር ያለ ተቃውሞ ሆነ፣ ብዙዎች ተናነሱ።

ተፎካሪዎች አንድ በተሰብ የዘር ሃረግ ያላቸው ናቸው፣ ልክ እኛ በዊንዶር በተመንግስት ሆነን አንዱን ልጃችን የአየርላንድ፣ አንዱን ልጃችን የዊልስ ንጉስ፣ አድርገን እንደምንሸመው ዙፋኑን ሰልጣኑን ሲሰት በምትኩ ሰልጣኑን ሰመረዋነው ለማዘረፍ አልነበረም። ለምሳሌ አጼ ዮሐንስ ፋንም፣ ዳግማዊ ምኒሊክም፣ አጼ ቴዎድሮስ እንዲወድቅና እነሱ እንዲነግሱ ይፈለጋሉ። ይህን ሲፈልጉና የመጭ እርድታ ሲጠይቁ ግን በሰሎች ሚና ቶሎ ወድተውላቸው እነሱ በዙፋኑ እንዲተኩ በማሰብ እንጂ፣ የአገራቱ ህልውና አደጋ ላይ ወድቆም ቢሆን ብቻ እንንገስ በሚል አይደለም። ሶስቱም ተመሳሳይ ስራ ለአገራቸው ሰርተዋል። ቴዎድሮስ ግብፅን ተዋግቶ መልሶዋል፣ የግንስም ግብፅና ቱርክን ተዋግቶ መልሶዋል፣ ሚኒልክም አጣሊያን ተዋግቶ መልሶዋል።

"በቴዎድሮስ ዘመን የዘረፍነውን ንብረት ለማዘረፍ አልነበረም የዮሐንስ የረዳን፣ አሰረኛ አሰፈላጉን እንደምንሂድ ብቻ ነበር የሚያውቀው። ሊሳ መሆናችን ቢያውቁ ኖሮ አርማጭ ነኝ ይሞኑን ነበር። ዛሬ ላይ ግን አውነታው ሊሳ መልክ ይዞ፣ አንዱ ትግሬ አንዱ አማራ ሆነው የተከፋፈሉና አገራቸውን አሳልፈው የሰጡ ነገስታት እንደሆኑ ተደርገው ነው የሚቆጥሩት፣ እንዲህ የሚያስቡ በርካታ ዜጎች በዚያች አገር ይገኛሉ።

"ይህን ታሪክ አሁን እየሰሙ ቢሆን ብለን ብናስብ፣ትግሬው የአጼ ዮሐንስን ታሪክ ብቻ ፣ አማራው የሚኒሊክንና የቴዎድሮስን ታሪክ ብቻ መርጦ ነበር የሚሰማው፡፡ በዚህ የድንቁርና ሁኔታ ውስጥ ነው ያሉት ከዙራን፡፡ ታሪኩ ግን ሌላ ነው! ዛሬ ላይ አጼ ዮሐንስ የትግሬ ንጉስ፣ አጼ ሚኒልክ የአማራ ንጉስ ተደርጎ እየታሰበ፣አንዱ አንዱን ንጉስ እየተቸና እያቃለለ ይገኛል፡፡ ከእነሱ የተሻለ ስራ ሰርተውም በተቹ እንዲሁ በባዶ ነው!

"እነዚያ ነገስታት ኢትዮጵያዊ ሆነው ሞተው፣ ለኢትዮጵያ አንድነት ሲሉ ደምተው፣ ለትውልዱ ሲሉ ያን ያህል ጥረት አድርገው ታሪኩንም አገሪቱን ጠብቀው አቆይተው አስርክበው ካለቁ በኋላ፣ይህኛው ትውልድ ራሱን በብሄር ከፋፍሎ እነሱንም ተከፋፈላቸው ማለት ነው!

"ያ ሁሉ የነገስታት ፉክክር የስልጣን ፀብ እንጂ ሌላ አለመሆኑ ተዘንግቶ ነገስታቱ ለየብሔራቸው ሲሉ እንደ ሞቱ ተደርጎ እየታሰበ ይገኛል! ብሄር የሚል ፍልስፍና ይዘው የተነሱ ልጆቻቸው፣ስለ ብሄር ፍልስፍና የማያዉቁትን ነገስታት ከብሄር ፖለቲካ ጋር እያገናኙ የፀብ ምንጭ፣ የመቆራረጫ ሰበብ፣ የመጠያያ ማእከል፣ አድርገው እርስ በእርስ የሚባሉ ህዝቦች ተፈጠሩ! አሉላ ትግሬ እንጂ ኢትዮጵያዊ እንዳልሆነ ተደርጎ ታሰበ፣ ተወራ፣ ተፃፈ! ሚኒልክ ለአማራ እንጂ ለሌላው ብሄር ግድ እንዳልነበረው ተደርጎ ጭራሽ ጡት ቆርጦዋል ተብሎ ተወራለት! እነ አብዲሳአጋ፣ የኦሮሞ ጀግና ብቻ ሆነው ቀሩ፡፡ ኦው...ለእንድ አፍታ ነገስታቱ ከመቃብር ተነስተው ይሄን ትውልድ ቢያዩት ምን ይሉ? እንዴት ያፍሩ?!

"የዛሬ ፖለቲከኞች በዚህ አይነት ሃሰተኛ ታሪክ ስልጣናቸውን ለዘላለም አስከብረው ለመቆየት ሲሉ ይህን አደረጉ፣አስደረጉ! በኢትዮጵያ ላይ የብሄር ፀበኝነት ተከሰተ፣እልቂት ሆነ! አማራና ትግሬ ተብለው ተከፍለው ከዓለም አገሮች አንደኛ የብሄር ፀብ ያለባት አገር ኢትዮጵያ እንድትሆን አደረጉ፡፡

"ይህ ሁሉ እንግዲህ ለፖለቲካ ስልጣን ሲባል የተፈጠረ ዘዴ ነው፡፡ በእኛ ያልተቋረጠ ድጋፍ ለድልና ለስልጣን የበቁት የአሁኖቹ ባለ ስልኖች፣ ያን የቀድሞ የኢጣሊያ የከፋፍለህ ግዛ ሀግ እንዴት በራሳቸው መንገድ እንዳራቀቁት አስቡ! መመለስ በማይቻልበት ሁኔታ ነው የሄዱበት! ‹‹ሽረ አውቀን የፈጠርነው ወሬ ነው›› ብለው

እውነቱን ቢናገሩ እንኳ፣ ህዝቡ አምኖ ተመልሶ ወደ አንድነቱ የሚመጣበት ሁኔታ እስከማይኖር ድረስ ነው በማሃይም አስተሳሰባቸው የራሳቸውን ተጨማሪ ብልሃት ጨምረው ያራቀቁት! ዛሬ ላይ እነዚህ ፖለቲከኞች እኛ ካሰብነው በላይ ርቀት ተጉዘው ሳይ፣ የጋቭሮቮውን ቀልድ ያስታውሰኛል!

"የጋቭሮቮ ተወላጅ የሆኑ አባትና ልጅ ወደ ምግብ ቤት ሄደው ምግብ በልተው እንዴት ሳይከፍሉ መውጣት እንደሚቻል ካሳየው በኋላ፣ልጁ በሁለተኛው ዙር ራሱ አሻሽሎ ትምህርቱን አዘምኖ ሳይከፍል ከመብላት አልፎ ‹‹መልስ ስጡና!›› ብሎ መልስ ተቀብሎ እንደወጣው ልጅ! ይህን ነው አድርገው ያሳዩን፡፡ ታዲያ እዚህ ደረጃ ካደረሱልን እንዴት ነው ስለ አስተማማኝነቱ የምንጠራጠረው? በፅኑ መሰረት ተገንብቷል እንጂ!

"ብዙሃኑ የኢትዮጵያ ህዝብ በዚህ አይነቱ የማንነት ቀውስ ውስጥ ያለ ነው! ዜጎች ራሳቸው የፈጠሩትን ትልቅ ቁስል በትልቅ ስለት የሚያኩ ሆነዋል! ሲጋቱ በኖሩት የሀሰት ወሬ ሰክረዋል! በዚህ የሰከረን ሰው ደግሞ ቁስልህን ልናክምልህ ነው፣ እነእገሌ የበላይህ ነበሩ፣ አሁን ዘመኑ ያንተ ነውና የበላያቸው ሁን ካላችሁት የበለጠ ይሰክራል! ታዲያ የሰከረን ሰው እንደልብ መጎተት ያቅታል? አያቅትም! አያችሁ? ዜጎችን በብሄር ስታጋጩ ሐይማኖትን ሳይቀር ማፍረስ ይቻላል! ያልኳችሁ ለዚህ ነው፡፡

"እንድ አይነት ሐይማኖት ይዘው ያን ቤተ-ክርስቲያን አቃጥሉ ብትሏቸው ቤተ-ክርስቲያኑ የሚገኘው በእነሱ ክልል ውስጥ ስላልሆነ ደስ እያላቸው ያቃጥሉታል! የብሄር ፀብ ማለት ይሄ ነው! የማይድን በሽታ! ለሁለቱ ብሄር የማይጠቅም ለእኛ ግን እጅግ አስፈላጊ! በዚህ በኩል ከሌላው የፍሪካ አገር በላይ እነሱ ውስጥ ነው በማንነት ቀውስ ሰክረው የሚገኙ ብሄሮች ያሉት፡፡

"ብዙዎቻችሁ ጎላችን የሆነችው አገር ኢትዮጵያ ጎላችን መሆኗ ያኔም ይታወቅ ከነበረ ለምን ቅኝ ተይዛ አልቆየችም? እያላችሁ ስትፀፀቱ ታዝቤለሁ፡፡ ቀደም ሲል በሰፊው የገለፅኩት መንፈሳዊ ምክንያት እንዳለ ሆኖ፣ቅኝ መያዝ ስለማንችል አልያዝናትም!ነገር ግን ከቅኝ ግዛት የሚገኝ አንዳችም ጥቅም አልቀረብንም፡፡

"ከቅኝ ግዛት የሚገኙት ጥቅሞች፣ርካሽ የሰው ጉልበት፣ የአገሪቱ ማእድናትና የተፈጥሮ ሃብቶች፣ ህዝቡን በቋንቋና በብሄር ከፍሎ በቋሚነት ተገዥ አድርጎ ማስቀጠልና በእኛ ሀግ እንዲኖሩ

ማድረግ፣ ያለ እኛ እርዳታና ድጋፍ እንዳይኖሩ ማስቻል፣ ያለ እኛ ትእዛዝና ፍላጎት ምንም ነገር እንዳያደርጉ ኮድኩዶ ማስቀመጥ ነው፡፡ ከእነዚህ ከቅኝ ግዛት ጥቅሞችና ፍላጎቶች አንዳቸውም ጎድለውብን አያውቁም፡፡

"ህዝቡን ለዘላለም ከፋፍለነዋል፡፡ የአገሪቱን አንድነት አናግተነዋል፡፡ የተፈጥሮ ሃብቷን አሁን ባሉት ባለስልጣኖች አማካኝነት እያገኘነው ነው፡፡ ምክንያቱም እነሱ እየዘረፉ በእኛ አገር ባንኮች ነው ቢሊዮን ቢሊዮን ዶላር የሚያስቀምጡት፡፡ እነሱ ማግኘት የሚችሉ ይመስላቸዋል፣ነገር ግን እርር ድብን ይሏታል እንጂ አንመልስላቸውም! ሲዊዝ ባንክ፣ ደች ባንክ፣ የማነው? የእኛ ነው! የሁሉም ባለስልጣን ሃብት በውጭ አገር ባንኮች ያለ ነው፡፡ የዘረፉት ብቻ ሳይሆን፣ ከእኛ በእርዳታና በብድር የወሰዱት ገንዘብ ሳይቀር ሳይውል ሳያድር ተመልሶ ወደ እኛ ባንኮች ነው እየገባ ያለው፡፡ እኛ ጅሎች ነን እንዴ ይህንን የማናውቅ? ሁሉም ተጠቃሎ በኛ ዘንድ ነው፡፡ ከጥቂት ሚሊዮኖች በላይ የሆነን የአፍሪካውያን ባለስልጣናት ገንዘብ በጭራሽ አንሰጥም፣ አንመልስም፡፡

"የተጠራቀመ የዘመናት ሃብትና ንብረታቸውን ቀደም ሲል በገለፅኩት ታሪካዊ አጋጣሚ ሙልጭ አድርገን ከእነ ታሪካቸው ዘርፈን ወስደናል፡፡ ርካሽ የሰው ጉልበት ከሆነ አሁንም ድረስ በዘመናዊ መንገድ ሚሊዮን ዜጎቿን ወደ እኛ አገር እያጋዝን ባሪያችን አድርገን ያለን ነን፡፡ ዜጎቿ በአውሮፓና በአሜሪካ ነው ያሉት፡፡ በከፍተኛ ባርነት ተሰማርተው ዝቅ ያለውን ስራ እየሰሩ በእሱም ደስተኛ ሆነው የሚኖሩ ናቸው፡፡ ከእጅ ወደ አፍ በሆነ ኑሮ! ማንም ከዚህ ልውጣ ቢል አይችልም! ዝቅ ሲሉ ከፍ ከፍ ሲሉ ዝቅ እያደረጉ ኮድኩዶ ማስቀመጥን እናውቅበታለን! ሌላ ምን ቀረ ከቅኝ ግዛት የሚገኝ ትርፍ? ምንም! ስለዚህ በቅኝ ግዛት ስር ሆና ቆየች አልቆየች ምንም ማለት አይሆንም፡፡ እንዲያውም ትርፍ አለው! ቅኝ ግዛት ሲያዝ በትንሹም ቢሆን ወጪ አለው፡፡ ግንባታዎች ይኖራሉ፡፡ መንገድ፣ ቢሮክራሲ፣ በመጠኑ ማሰልጠን፣ ወዘተ... ወጪ አለው፡፡ ኢትዮጵያውያን ፀፀትን በቀልድ መልክ ሲገልፁ፣ "ባልመጣሁ አለች ጣሊያን!" ይላሉ፡፡ ኪሳራዋ እየገባቸው፡፡ ከዚህ ፀፀት ነው የዳንነው ክቡራን፡፡ ስለዚህ ቅኝ እንደተገዛች ቁጠሩት ለማለት ነው፡፡ ይገባኛል ብዙዎቻችሁ

የቋንቋው ጉዳይ እንደ ከነከናችሁ፡፡ ነገር ግን ገዝተናቸው ቢሆንና ቋንቋችንን ቋንቋቸው አድርገው መጠቀም ቢችሉ እንኳ፣ከነፃነት በኋላ ወደ ቀድሞ ፊደላቸው ሊመለሱ እንደሚችሉ ማሰብ አለባችሁ፡፡ ይህ ደግሞ ብዙ አያሳስባችሁ፡፡ በቅርቡ ማድረግ ያለብንን አድርገን ወደ ማክሮ 6 እንደምናስገባው ወይም የእኛን ፊደል እንዲጠቀሙ ማድረግ አይሳነንም፡፡ ዋናው የሰሜኑ ክፍል ህዝብ ሁብረት አለመፍጠሩ እንጂ ሌላው የሚያሳስበን አይደለም፡፡ ስለዚህ.....እንዲህ እንዲህ ባሉ ምክንያቶች ሳቢያ ቀድሞ ያልተሰራ ስራ እንዳለ እያሰባችሁ አትፀፀቱ፣ አትስጉ፡፡ ዋናው ስራ በደንብ ተሰርቷልና ስላችሁ በእርግጠኝነት ነው፡፡

"ግልፅ ሆነልህ ወይ ቻይና?"

"እምን ንግስት ሆይ፡፡"

"ቀጥል" በማለት ተከታዩን ዕድል ለብራዚሉ መሪ ሰጡ፡፡

"አመሰግናለሁ ንግስት ሆይ! በእውነቱ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በየጊዜው የሚነገሩን ሚስጥሮችና የምናያቸው የልዑላችን ስጦታ የሆኑ ግኝቶች ሁሉ በእጅጉ እያስደሰቱን የምንገኝ እድለኞች ነንና ልዑላችንን እጅግ አድርገን ማመስገን አለብን፡፡ የቤት ስራዎቻችንንም እስከ መጨረሻው ለመወጣት በቁርጠኝነት ደስ እያለን ነው መዘጋጀት ያለብን! ክቡርነትዎና ቤተሰብዎም ዓለምንና ህዝቦቿን እያሰለጠናችሁ እዚህ አድርሳችኋልና ልትመሰገኑ ይገባል፡፡ የምናያቸው ነገሮችም ለድላችን ምን ያህል እንደተቃረብን የሚያረጋግጡ ናቸው፡፡ እና ደስታዬ ወደር የለውም፡፡ በዚህ ደስታ ውስጥ ሆኜም ጥቂት ጥያቄዎችን ልጠይቅ ፈለግሁ፡፡ .....ይገርምዎታል...ጎላችን ያች አገር መሆኗ ከተነገረን ጀምሮ ስለ አገሪቱ የፖለቲካ ሁኔታ ከማጥናት ውጪ ሌላ ስራ አልሰራሁም ማለት እችላለሁ፡፡ በጥናቴ ውስጥ እንደተረዳሁት ከሆነ ደግሞ አገሪቱ የምትመራበት የፖለቲካ ርዕዮት ለየት ያለና ያልተለመደ፣ እንዲያውም ጨርሶ ሊገባኝ ያልቻለ ሆኖ ነው ያገኘሁት፡፡ በበኩሌ አብዮታዊ ዴሞክራሲ የሚባል የፖለቲካ ርዕዮት እንዳለ አላውቅም፡፡ አብዮትና ዴሞክራሲ ደግሞ በአንድ ላይ ተጣምረውና ተስማምተው መቀጠል አይችሉም፡፡ ምን ማለታቸው ነው? ሶሻሊዝም እንዳይባል አገሪቱ የነፃ ገበያ ፖሊሲን ትከተላለች፡፡ ካፒታሊዝም እንዳይባል ትልልቅ የመንግስት ተቋማት በመንግስት ስር ሆነው ነው የሚገኙት፡፡ እንደገና

ልማታዊ መንግስት የሚሉት ነገርም አለ። በዚህ ግራ በገባው የፖለቲካ ርእዮተ ዓለም በምትመራ አገር ደግሞ በተለይ የውጩን ግንባታ የሚመለከቱ ስራዎችን ለመስራት ዕድል አይሰጥም። የፖለቲካ መመሪያቸውን ማስለወጥ እስካልተቻለ ድረስ ነፃ እንቅስቃሴ ማድረግ የምንችልበት ሁኔታ አልታይህ ብሎኛል። ታዲያ....ፕራይቬታይዜሽን ባልተፈቀደበት ሁኔታ እነዚህን እቅዶቻችንን እንዴት እንደ ልብ ተንቀሳቅሰን መፈፀም እንችላለን? በዚህ ግራ በገባው ርዕዮት ሲመሩስ እንዴት ዝም አላችኋቸው? ይሄን ጉዳይ እግረ መንገድህን ቢያብራሩልን ደስ ይለኛል። ምናልባት ሌላ የታሰበበት ጉዳይ ካለም አያይዘው ቢመልሱልን መልካም ነው።

"ተከታዩ ጥያቄዬ የጎረቤት አገራትን የሚመለከት ነው። በኢትዮጵያ ዙሪያ ያሉ የምስራቅ አፍሪካ ጎረቤት አገራት በሙሉ ለማለት በሚቻልበት ሁኔታ በእርስ በርስ ጦርነትና ግጭት ውስጥ ያሉ ናቸው። በአገራቱ መካከልም ኩርፊያ ይስተዋላል። በተለይ የኤርትራው መሪ ደረቅ ቢጤ ይመስለኛል። ከአሸባሪ መሪዎች ተርታ ተመድቦም አይቻለሁ። እኛ ደግሞ አንዱን ወዳጅ አንዱን ጠላት አድርገን መቀጠል ያለብን አይመስለኝም። በዚህ ዙሪያ ያሉ ችግሮች ለሰራችን መሰናክል ሊሆኑብን አይችሉም ወይ? በተለይ ለውጩ ግንባታ የሚውሉ ጥሬ እቃዎች በእነዚህ አገራት ማለፋቸው የግድ ነውና የመጓተት ነገር እንዳይኖር ከወዲሁ ማድረግ ያለብን ነገር ያለ ይመስለኛል። እርግጥ ክቡርነትዎና ቤተሰብዎ ይህን ሳያስብበትና ሳይዘጋጅበት እንደማይቀር አምናለሁ። ስለዚህ እንደተጓረፉ ለማስቀጠል ወይስ አስታርቆ ለማስማማት ነው የታሰበው?

"ሊላው፣ በጂቡቲና በኤርትራ የቀይ ባህር ድንበር ላይ ሰፋፊ የጦር ካምፖች በሃያል አገራቱ በኩል ይቋቋማሉና፣ የሃያል አገራት ርብርብ በዚያች አገር ዙሪያ ሲሆን ትኩረት አይስብም ወይ? ሊላውና የመጨረሻው ጥያቄዬ፣ ቁሳቁሶቻችን እነዚህን ወደቦች አልፈው ወደ መሃል ከተማ ሲገቡና ተራግፈው በየ ካምፖቻችን ሲሰራጩ ከመንግስታቸውና ከህዝቡ እይታ ውጪ አይሆኑምና በዚህ ዙሪያ ምን ታስቧል? የሚሉ ጥያቄዎች ነው ያሉኝ፣ አመሰግናለሁ።"

"መልካም፣ ምስጋናህን ተቀብለናል። ደስታህንም እንጋራለን።

"አገራቱ የምትመራበት የፖለቲካ ርዕዮት ለአንተ ብቻ ሳይሆን ለሕዝቦቿም ግልፅ አይደለም። መጠነኛ ክህደት ፈፅመውብናል ያልኳቸውም ይህንኑ በሚመለከት ነው።

"አብዮት ማለት ግና በትግል ላይ ያሉ ቡድኖች ወይም ፓርቲዎች አሊያም ነባ አውጭዎች ለስልጣን ያልበቁ መሆናቸውን የሚያሳይና በእንቅስቃሴ ላይ መሆንን የሚጠቁም ነው። ዴሞክራሲ ማለት ደግሞ ዴሞክራሲ ማለት ነው። አብዮታቸው ተሳክቶ ለስልጣን በቅተው አገራቱን በዴሞክራሲያዊ መንገድ እየመሩ መሆናቸውን የሚገልፅ ነው። ስለዚህ አብዮታዊ ደሞክራሲ የሚባል ነገር ሊኖር ባልተገባ ነበር።

"ነገር ግን በዚህ የፖለቲካ ርዕዮት አሳበው የቀድሞ ለዘብተኛ ቅኝ ገዥዎችን የፖለቲካ ስርዓት መዘርጋታቸው ነው። ይህ አይነቱ የፖለቲካ ርዕዮት ተግኝው ህዝብ አንሰራርቶ ህብረት ፈጥሮ ቅኝ ገዥዎችን እንዳያባርር ሲባል በአንድ ወቅት ጥቅም እንደ መዋል ብሎ ነበር። በውስጡም ሌላ ትርጉም አለው። ቅኝ ገዥዎች የያዙትን አገር ‹‹እያለሙ ይዞ መቀጠል›› ተብሎ ተተርጉሞ ያውቃል። ይህንን መነሻ አድርገው ነው አብዮታዊ ዲሞክራሲ ካሉ በኋላ፣ ልማታዊ መንግስት የሚል ሃሳብ የጨመሩበትና ፕራይቬታይዜሽንን የከለከሉት።

"ልማታዊ መንግስት በራሱ ሁለት አይነት ነው። እንዱ የቻይናው አይነት ልማታዊ መንግስት ማለት ሲሆን፣ ሌላው የኢትዮጵያው አይነት ልማታዊ መንግስት ነው። ይህም ‹‹አገሪቱን እያለማሁ መቀጠል ያለብኝ እኔ ብቻ ነኝ›› የሚል እንድምታ ያለው ርዕዮት ሲሆን፣ የስልጣን ሽግግር አይፈቅድም።

"ትልልቅ የመንግስት ተቋማትን በስሩ አድርጎ ካልቀጠለ ስልጣኑን እንደተነጠቀ ስለሚቆጠር ዋና ዋና የመንግስት ተቋማትን በብቸኝነት ይዞ ይቀጥላል። አብዮታዊ ዴሞክራሲ ማለት ቀጥታ ትርጉሙ ዘላለማዊ ወይም ዘላቂ የሆነ አንባገነናዊ ስርዓት ማለት ነው።‹‹አብዮቱን ለመጠበቅ....›› እንደሚባለው፣ ልማቱን ለማስቀጠልና፣ የተገኘውን ነፃነትና ዴሞክራሲ መልሶ ለቀድሞው አካል ወይም ብሄር ወይም መንግስት አሳልፎ ላለመስጠት የሚደረገው ትግል ቀጣይነት እንዳለው የሚጠቁም ነው። ማብቂያ የሌለው ዘላለማዊ ትግል እንደማለት ነው። በአንድ ፓርቲ የበላይነት ብቻ እየተመራ መቀጠል ያለበት አገዛዝ ማለት ነው።

ከእንድ ልማታዊ ፓርቲ ውጪ ሌላ ፓርቲ አያሰፈልግም ብሎ እንደ መደምደም ነው። ሰለዚህ አብዮቱንም እየጠበቅሁ፣ ዲሞክራሲንም እያሰፋፋሁ፣ የተገኘውንም ነፃነት ከአብዮት ቀልባሾች እየተከላከልኩ፣ ያለ ማንም ጣልቃ ገብነት ሰፈልግ እያለግሁ....ሰፈልግ....እያጠፋሁ....ያሻኝን እያደረግሁ እስከ መጨረሻው መቀጠል እንደ ማለት ነው።

"በዚህ ርዕዮት አማካኝነት በዲሞክራሲ ሰም፣ በብሄር ብሄረሰቦች እኩልነት ሰም፣ ራሳቸውን የሌላው ብሄር ጠባቂ አድርገው እነሱ ከሌሉ ብሄሮችም ካሉ እንደማይቆጠሩ አድርጎ በማሰብና በማሳሰብ አብዮተኛ እንደሆኑ መዝለቅና መቀጠል እንዳለባቸው እየተናገሩ ነው። ይህን የተገነ ነፃነትና ዲሞክራሲ ከእነሱ ውጪ ማንም መጠበቅ እንደሌለበት እያሳሰበ ነው። እነሱ ከወረዱ ዲሞክራሲውም አብሮ እንደሚሞት እያስጠነቀቁ ነው። ሰልጣኑ ከእንድ ከእንድ ፓርቲ ውጪ መውጣት እንደሌለበት እያስተማሩ ነው። ነፃነታቸውን ያገኙ ብሄሮች ከእነሱ ውጪ ህልውና እንደሌላቸው እየነገሩ፣ ከእነሱ ሰር ሆነው እነሱን እየታዘዙ ከመኖር ውጪ ሌላ አማራጭ እንደሌላቸው እያረጋገጡ በቅኝ ገዥነት የመቀጠል ሰልት ነው።

"መሰሪ ርዕዮት ሰለሆነ ይሄ ነው ብሎ መግለፅ ይከብዳል። እንዳውም ባይገባችሁ ነው የሚሻለው። አንተም ሰለዚህ እቃ እቃ ጫዋታ ማሰብህን አቁም። ይሄን በማጥናትም ጊዜህን አታጥፋ፣ እኛንም በመጠየቅ አታድክመን።

"ያነሳህው ጥያቄ ግን ተገቢ ነው። ምክንያቱም እነዚህን እቅዶቻችንን ለመተግበር ከታሰበ በአብዮታዊ ዴሞክራሲ ስም፣ ካፒታሊስት ነኝ ብሎ ነፃ ገበያን የማይፈቅድ፣ ሶሻሊስት አይደለሁም እያለ ትልልቅ የመንግስት ተቋማትን ለግሉ ዘርፍ የማይሰጥ አምታች መንግስትን የሚደ ማሰወገድ ያሰፈልጋል። ፕራይቬታይዜሽን በከፊል ሳይሆን ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ባልሆነባት አገር እንደ ልብ መሆን ላይቻል ይችላልና። ለማንኛውም ይህን ርዕዮት ሲያራምዱ እያዬን፣ ኢ-ዲሞክራሲያዊ አገዛዝ መሆኑን እያወቅን፣ ዝም ያልናቸው በምክንያት ነው።

"እነሱ ይህን ያደረጉት አገራቱን እንደ ልብ ለመዝረፍ ሲሉ ብቻ እንደሆነ ሰላወቅንና የሚዘርፉት ገንዘብ የትም እንደማይሄድ ሰለተረዳን ነው በዝምታ ማለፋችን።

ዋሽንግተንን ርዕዮት በከፊል ፈቅዷው የራሳቸውን ፓርቲ ነጋዴ አድርገው ለመነገድ ሰላሰቡና አገራቱን በፓርቲው የንግድ ሥርዓት ስር አድርገው የአገራቱን ሀብትም፣ የአገራቱን የመሪነት ስልጣንም፣ እስከ መጨረሻው በብቸኝነት ይዘው ለመቀጠል ሲሉ የቀመሩት መሰሪ ቀመር ነው።

"ገዥ ፓርቲ የንግድ ተቋም ኖሮት ከቀጠለ ደግሞ በምንም አይነት ሁኔታ በዚያች አገር ዴሞክራሲም፣ የሕግ የበላይነትም፣ ፍትሐዊነትም፣ የኢኮኖሚ እድገትም ሊኖር አይችልም። እነሱ እያደረጉ ያሉት ይሄንን ነው። ሰዘህ ነው ያን ግራ የገባውን ርዕዮት ፊጥረው አንተንም ሌላውንም ግራ ያጋቡት። ሰዘህ ነው በአብዮታዊ ዲሞክራሲ ስም ፕራይቬታይዜሽንን ሳይፈቅዱ የኖሩት። ይህ ማለት ሁሉን ነገር ከእግር በታች አድርጎ የንግድ ተቋማቸውና እነሱ ብቻ የበላይ ሆነው የመቀጠል ዘዴ ነው።

"በዚህ አይነቱ ስርዓት አገራቱ የምትለማው የእነሱ የንግድ ተቋም ብዙ ቶን ሲሚንቶ አምርቷል ማለት ነው። ብረታ ብረቶችና ስሚንቶዎች አሉ ማለት ነው። ባለ ሃብቱ ሀንዛ እንዱገነቡ ከፊቀዱ የግንባታውን ቁሳቁስ አምርተው ወይም ከውጭ አስገብተው ለመሸጥ ቋምጠዋል ማለት ነው። ምንም አይነት ነገር ሲያደርጉ የንግድ ድርጅታቸው ባለው የምርት መጠንና አይነት በመመራትና በመታዘዝ እንጂ ለአገሪቱ ልማት በማሰብና ልማቱን በመፈለግ አይደለም። በዚህም ምክንያት ነገም ለዚያች ለሚመሯት አገር ተመሳሳይ ምርት መሸጥ ስለሚፈልጉ በአገሪቱ ውስጥ ዘላቂና ጠንካራ ልማት ሊኖር አይችልም። የራሳቸውን አገር ራሳቸው ቅኝ ግዛት ሲይዟት እንደ ማለት ነው። ቅኝ ገዥዎች ቅኝ የያዙትን አገር ማዕድናትና እጠቃላይ ንብረት እየዘረፉ ወደ አገራቸው እንደሚያሸሹት ሁሉ፣ እነሱም የአገሪቱን ሃብት በብቸኝነት እየዘረፉ ወደ ፓርቲያቸው የንግድ ድርጅት ማሸሽ ነው የያዙት።

"በህዝብ ስም ያቋቋሙትን የፓርቲውን የንግድ ድርጅት ካፒታሉን ማደለብና በየ ዓመቱ የሚገኘውን ትርፍ ውስን ባለስልጣናቶች ብቻ የሚካፈሉበትን አሰራር ነው የዘረጉት። ይህ ድርጅት ደግሞ

"ይህን ግራ የገባው አሳሪ ርእዮት በአገራቱ እንዲቀር ሳናደርግ፡ እዚያን ያረጁ ያፈጁ አንጋፋ አንጋፋ ሙሰኛ ባለስልጣናትን ሳናስወግድና ይህን መሰሪ ድርጅት ሳናፈራርስ፡ እኛም እንደ እነሱ ሁሉን ነገር ከእግራችን ስር ሳናደርግ፡ እንዴት ብለን ይህን ሁሉ እቅዳችንን በተግባር ሙተርጎም እንችላለን?

"ብረት ሲገባ እኛ እናስገባለን የሚል፡ አውቶሞቢል ሲባል እኛ አለን የሚል፡ በራሱ ሀግ የሚመራ፡ ለራሱ ዝርፊያ የራሱን የህግ ከለላ የሰጠ፡ የራሱን ድርጅት በአገራቱ ሰራዊት የሚያስጠብቅ የተደራጀ የማፊያ ቡድን ባለበት አገር ዘው ብለን እንገባም። የንግድ መረባቸውን ከእነ አብዮታዊ ዴሞክራሲያቸው ይዘው ሹልክ ካሳሉ ዕቅዳችን ተፈፃሚነት አይኖረውምና እነሱንም፡ ኩተታቸውንም፡ ጠራርገን ጫካውን መንጥረን ነው በነፃነት የምንገባው።

"ትልልቅ የመንግስት ተቋማትን የእኛ ባለ ሐብቶች የሚይዙበትን ዓለም የሚያውቀውን ትክክለኛውን የካፒታሊዝም አሰራር ቀድመን ዘርግተን ነው የምንገባው። አለዚያ መሰናክል መሆናቸው አይቀርም። በእቅዳችን ላይ ደግሞ እንዳች መሰናክል ሊኖር አይገባም። በእኛ ስራ መሰናክል የሚሆን ሁሉ ደግሞ ፀቡ ከእኛ ጋር ነው። ከእኛ ጋር የተጣላ ደግሞ እንዴት እንደሚሆን ስለምታውቁ መንገር አያስፈልገንም። ስለዚህ የቅድመ ስራችን አንድ አካል አድርገን ቀድመን የተዘጋጀንበት ሁኔታ ነውና ያለው አትስጋ፡ አትስጉ እላለሁ።

"የጎረቤት አገራትን በሚመለከት ወደ አነሳሀው ጥያቄህ ልለፍና ምላሽ ልስጥ።

"በኢትዮጵያ ዙሪያ ያሉ ጎረቤት አገራት አሁን ያሉበት ሁኔታ ጥሩ አይደለም። ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር ፀብ ናት። ይህ ፀብ ደግሞ የሰሜኑን ክፍል አገባባችንን እንዲሁም የውስጥና የውጭ ግንባታችንን ሊያደናቅፍ ይችላል። ሱዳንም በተመሳሳይ በሰሜንና በደቡብ ተከፍለው እንኳ ብጥብጡ ዛሬ ድረስ አለና በዓላማችን ላይ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሚፈጥረው ተፅዕኖ ሊኖር ይችላል። ኬንያም በሙስና ምክንያት ማንም ግለሰብና ቡድን በጥቂት ገንዘብ ያሻውን ተግባር መፈፀም የሚችልባት የሽብር ቀጠና ናት፡ ፡ የሶማሊያንም ጉዳይ የምታውቁት ነው። ጅቡቲም፡ ሶማሊላንድም፡ በተመሳሳይ ስርዓት አልበኝነት የነገሰባቸው አገራት

ከሲሚንቶ እስከ ብረታ ብረት፡ ከቆርቆሮ እስከ ጥጥ፡ ከቡና እስከ ጅንጅብል፡ ሁሉንም ዘርፎች ያካተተና ጨረታ ተጫርቶ መንግስ የሚሰራ ድርጅትን ሳይቀር በውስጡ አቅፎ የያዘ፡ አገራቱን በስሩ አድርጎ የቀጠለ የግሎ ፓርቲ ድርጅት ነው።

"እራሱ ጨረታ አውጪ፡ እራሱ ጨረታ አሸናፊ፡ እራሱ አምራች፡ እራሱ ዋጋ ተማኝ፡ እራሱ ሰሪ፡ እራሱ አሰሪ፡ እራሱ በጀት አፅዳቂ፡ እራሱ እቃ አቅራቢ፡ እራሱ የልማት ዕቅድ ነዳፊ፡ እያለ የቀጠለ ነው።

"በግልፅ እንደምታውቁት ግሎ ፓርቲ ነጋዴ መሆን የለበትም። መሆን ካለበት እንኳን የዋጋ ግሽበትን ለመቆጣጠርና ተወዳዳሪ ሆኖ ቀርቦ የአገሪቱን ኢኮኖሚው ለማረጋጋት ሲል ብቻ መሆን የሚኖርበት ነው። በሌላ አገላለፅ ለአገሪቱ ጥሩ በማሰብ ብቻ ነው፡ የእነሱ ግን ይህ አይደለም። ቀጥተኛ ዝርፊያ ነው።

"በዚህ አይነት ዘዴ ነው የሕዝቡንና የአገሪቱን ሀብት በቀጥታ ወደ ንግድ ድርጅታቸው ገቢ ሲያደርጉና የግል ኪሳቸውን ሲያደልቡ የኖሩት። የሚያሳዝነው ነገር የዚያ የንግድ ድርጅት ትርፍ በጣት የሚቆጠሩ አንጋፋ ባለስልጣናት ለየግላቸው የሚከፋፈሉት መሆኑ ነው። ይህ ሲሆን ደግሞ ተቀናቃኞቹን ማጥፋት ግዴታ ይሆናል። ሌላው ባለ ሐብት የእነሱ ድርጅት አሯሯጭ እንዲሆን እንጂ በማናቸውም ዘርፍ በልጧቸው አልፏቸው ሊሄድ አይችልም። ባንኩም የእነሱ ስለሆነ የውጭ ምንዛሬ ክምችቱን ለአሯሯጭ ነጋዴዎች ጥቂት ጥቂት እየሰጡ ለራሳቸው ግን ያለ ገደብ ይጠቀማሉ፡ ይተምናሉ፡ ያዛሉ፡ ይመራሉ... ወዘተ... ይህ አደገኛ አካሄድ ነው ከቡራን። ምክንያቱም ይህ የንግድ ተቋም እስካለ ድረስ እኛ በየትኛውም ወደብ ያሻንን ጥሬ እቃ እንደ ልባችን ማስገባት አንችልም።

"በአንድ ከውጭ በሚገባ ዕቃ ሶስት መቶና አራት መቶ ፐርሰንት ቀረጥ የሚጥሉ ስግብግቦች ስለሆኑ ብቻ ሳይሆን፡ ይሄንንም ስራ እኛ ራሳችን ነው የምንሰራው ወደ ማለትም እንደሚሸጋገሩ አርግጠኞች ነን። እኛን ራሱ ከእነሱ የንግድ ተቋም ስር አድርገው አሯሯጭ ለማድረግ እንደሚሞክሩ ግልፅ ነው። ስለዚህ በእኛ እገዛ ለስልጣን የበቁ ያረጁ ያፈጁ ሙሰኛ ባለስልጣናት በሙሉ ተጠራርገው መወገድ አለባቸው።

ናቸው፡፡ ስለዚህ ወደ ኢትዮጵያ የምናደርገውን የውስጥ ለውስጥ እንቅስቃሴም ባይሆን፣ለውጨ ስራ በየ ወደቦቹ በምናስገባቸው ቁሳቁሶች ላይ መጠነኛ ችግር. ሊፈጥሩ ይችላሉ ብሎ ማሰብ ብልህነት ነው፡፡

"ይህ ሁሉ ግን እኛን የሚያሳስብ ጉዳይ አይደለም፡፡ ደጋግሜ ለመግለፅ እንደሞከርኩት፣ ከዚህ በኋላ በሚኖረው ዘመን ተቆራርሶና ተገነጣጥሎ መኖር፣ አገርን እንደ አገር ከልሎ ይዞ በብቸኝነት እየመሩ መቀጠል የሚቻልበት ሁኔታ የለም፡፡ ተወደደም ተጠላም በግሎባላይዜሽን ርዕዮት ሁሉም ወደ አንድነት በሂደትም ወደ ውህደት ይመጣል፡፡ እንኳን አገርን "የኔ አገር" ብሎ ከልሎ መያዝ ይቅርና፣ የመገበያያ ገንዘብን እንኳ "የኔ ብቻ" ብሎ ወስኖ ጥቅም ላይ ማዋል የማይቻልበት አዲስ የምድር መንግስት ስለማቋቋም ነው ጉባዔያችን፡፡ ስለዚህ ኢትዮጵያ በብር፣ ኤርትራ በናቅፋ፣ ሶማሌ በሽልንግ፣ ጅቡቲ በፍራንክ፣ ተከፋፍሎ መገበያየት ሊቻል ቀርቶ፣ በዓለም አቀፉ ዶላር እንኳ እየተገበያዩ መቀጠል የማይቻልበትን አሰራር ነው ‹‹ወደፊት›› የምንዘረጋው፡፡

"ገና የወረቀት ገንዘብ ሊቀር አይደለም እንዴ? ታዲያ ማን ጀግና ነው አገርና ድንበሬን ከልዬ ሉዓላዊነቴን አውጃለሁ ብሎ ብቻውን መቀጠል የሚችለው? ይህ አያሳስባችሁ ክቡራን፡፡ የአሜሪካና የኤርትራ ህዝብ ‹‹የእኔ›› የሚሉት አገርና ንብረት ሳይኖራቸው፣ ሁሉም የጋራቸው ሆኖ፣ በወደ ፊቱ የዲጅታል ሲስተም ተጠቃለው አንድና አንድ ብቻ ሆነው፣ በአንድ ባህል፣ በአንድ ሐይማኖት፣ በአንድ ገንዘብ፣ በአንድ ሕግ፣ በአንድ አለቃ እየተመሩ ሊኖሩ ተዘጋጅተዋልና አያሳስባችሁ፡፡ ያ ርዕዮት ቀርቷል፡፡ አሁን ሌላ ርዕዮተ-ዓለም ነው ያለው፡፡

"ምስራቅ አፍሪካም ሆነ ሌሎች የአፍሪካ አገራት መንግስታትና ህዝቦች በየራሳቸው ፍላጎትና ሕግ መተዳደራቸው ቀርቶ ከዚህ በኋላ በሚኖረው ጊዜ በእኛ ሕግና አሰራር ብቻ የሚጠቃለሉ ስለሚሆኑ በማናቸውም መንገድ መሰናክል ሆነው መገኘት የሚችሉበት ሁኔታ አይኖርም፡፡ ስለዚህ ወደ እዚያ ሽግግር ከማለፋችን በፊት ሁሉንም አገራት በቅርቡ አስማምተን እናስታርቃለን፣ እናዋህዳለን፡፡ አዋህደንም የጋራ ግንባታው ተባባሪ እናደርጋቸዋለን፡፡

"አስታውሱ፣ እነዚህ አገራት እርስ በርስ ተሳስረውና ተስማምተው በጋራ ተጠቃሚ መሆን የሚችሉበትን እድል ዘግተንባቸው የቆየነውና፣ አጣልተን፣ ገነጣጥለን ያቆየናቸው በምክንያት ነበር፡፡ ያን ቀደም ብለን ባናደርግ ኖሮ ዛሬ በጋራ ከፍ ከፍ ብለው መሰናክል ሊሆኑብን ይችሉ ነበር፡፡ ነገር ግን ኮድኩደን አስቀምጠን ያቆየናቸው አገራት ናቸውና፣ ኮድኩደን እንዳቆየናቸው ሁሉ በዘመን ቀመራችን መሰረት እንድ እናደርጋቸዋለን፡፡ አንድ የምናደርጋቸው ግን ለእኛ በሚመች መልክና ሁኔታ ብቻ ነው፡፡

"ወደ መስማማት መምጣት የሚኖርባቸውም ግዙፍ ግዙፍ የሆኑና ያልተለመዱ የግንባታ ቁሳቁሶች በትላልቅ መርከብ እየተጫኑ ወደ አገሪቱ የሚገቡት በኤርትራና በጅቡቲ እንዲሁም በጠቀስኳቸው አጎራባች አገራት ስር ባሉ የባህር በሮች አማካኝነት ስለሆነ ነው፡፡ ቁሳቁሶች ሲገቡ ደግሞ ያለ ምንም ተቃውሞ በእሽታና በደስታ እንጂ፣ የእቃው አይነት፣ ምንነቱ፣ ክብደቱ፣ ወዘተ..... የሚል ትኩረት እንኳን እንዳይኖር በሚል ነው፡፡ እነዚህ ቁሳቁሶች በተለይ ለውጨ ግንባታ የሚውሉት በትልልቅ ኮንቴነርም ይሁን በሌላ፣ በአይነታቸው ተገቢው ቀረጥ ተከፍሎባቸው በፍጥነት እንዲያልፉ የግድ ወዳጅነቱ ጠበቅ ያለ መሆን ስለሚገባው ጭምር ነው፡፡

"ከወደብ በኋላ ተራግፈው በከተማ አውራ ጐዳናዎች ሲጓጓዙ ላልከውም ቀድመን ተዘጋጅተናል፡፡ ማናቸውም አይነት ግዙፍ ግዙፍ ቁሳቁስ ከመርከብ ወርዶ የሚጫነው በባቡር ከሆነ በቀጥታ ሄዶ የሚያርፈው ባቡር ጣቢያ ይሆናል፡፡ ያ ባቡር ጣቢያ ቀድሞ የእኛ እንዲሆን የማድረግ እቅድ ስላለ አያሳስብም፡፡ በእያንዳንዱ የባህርና የደረቅ ወደብ መዳረሻ ቦታ የእኛ ሰዎች ቀድመው ይሰፍራሉ፡፡ የሚሰፍሩትም በተለያዩ የኢንቨስትመንት ስም ነው፡፡ በማይጠረጠሩ ታማኝ አገራት አማካኝነት በኢንቨስትመንት መንደር ስም ከአገሪቱ መንግስት ጋር በፐርሰንት ሽሪክ በመሆን ምቹና ሰፋፊ የመዳረሻ ቦታዎችን እንይዛለን፡፡ በሽፋን ስራቸው ለወደብ ቅርብ የሆኑ ትልልቅ ዘመናዊ ሆቴሎች፣ አሊያም በባለ ሐብቱ ኢንቨስትመንት በተሰሩ ዘመናዊ ቪላዎች፣ እየተሳበቡ ትልልቅ ግንባታዎች ይከናወናሉ፡፡ ትልልቅ መንደሮች ይመሰረታሉ፡፡ እነዚያ ዘመናዊ መንደሮች ዋና አገልግሎታቸው

የእኛ ንብረት ማራገፊያና መከዘኛ ሆነው መቆየት ነው። እነዚያን
ቁሳቁሶች በመጠን፣ በቅርፅ፣ እያዘጋጁ ተራ ሸቀጥና ለተራ
የኢንደስትሪ ልማት የሚውሉ ቁሳቁሶች እያስመሰሉ ማዘጋጀት
የሚቻልባቸው፣ የሚራገፉ ቁሳቁሶች እየተቆራረጡ
የሚስተካከሉባቸው፣ ተስተካክለውም ወደ ሚፈለገው ቦታ መሄን
የሚቻልባቸው ሰፋፊ መጋዘኖች ይኖራሉ።

"በሰሜኑ ክፍል በቀይ ባህር በኩል የሚገቡ ቁሳቁሶችንም
በተመሳሳይ ከወደብ ተራግፈው፣ በየብስና በባህር መጓጓዣ
መንገዶች ተጓጉዘው በቀጥታ የሚራገፉት በእኛ ቤቶች ውስጥ ብቻ
የሚሆንበትን ሁኔታ ነው የምናመቻቸው።

"ይህን ስናደርግ ለውስጥ ለውስጡ ግንባታችን በየመን በኩል
መግቢያችን ስናመቻች ያየን እንደሌለ ሁሉ፣ ከግብፅ ተነስተን
ውስጥ ለውስጥ ሰንገሰግስ የሚመለከተን እንደማይኖር ሁሉ፣
በሱዳንና በኬንያ ድንበሮች ስንገባ እንደማንታይ ሁሉ፣ በኤርትራና
በጅቡቲ ወደቦች በኩልም ለላዩ ግንባታ የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶቻችን
በነፃነት ማስገባትና ማሰራጨት ቀላል ይሆንልናል ማለት ነው።

"ለምሳሌ በጅቡቲ ወደብ የሚገባ ሚሳኤልም ይሁን የጨርቃ-ጨርቅ
ጣቃ፣ መስታወትም ይሁን ታንክ፣ ኬሚካልም ይሁን እህል
ከመርከብ ወርዶ፣ በባቡር ተጭኖ፣ በሀጋዊ መንገድ ወደ አገሪቱ
ዋና ከተማ ሲገባ፣ የባቡር ጣቢያ መጻረሻ ላይ ቀድመን
በምንገነባው መንደር /መጋዘን/ ነው የሚራገፈው።

"የሚራገፍበትን ቦታ እራሱን ሙሉ ጊቢውን በዘመናዊ መንደር
ግንባታ ያዝን ማለት፣ንብረቶቻችን በቀጥታ ወደ ቤታችን እየገቡ
ይራገፋሉ ማለት ነው። ከገቡ በኋላ እዚያው እያመቻቹ፣ ወደ
ሚፈለጉ ቦታዎች ጭኖ ማድረስና ለሚፈለጉበት ዓላማ ጥቅም ላይ
ማዋል ቀላል ስራ ይሆናል። ስለዚህ ዋናው ስራ ቀድሞ መጻረሻ
ቦታዎችን የኛ ማድረግ መቻሉ ላይ ነውና እሱን እናደርጋለን፣
ስለዚህ ማንም ትኩረቱን እኛ ላይ ሊያደርግ አይችልም።

"ይህ ብቻ አይደለም። ርዕዮቱን ካሰለወጥን በኋላ ባለሃብቶቻችን
እንደ ልባቸው ስለሚገቡ፣ ዋና ከተማዋ ለባለሃብቶቻችን ምቹ
ትሆን ዘንድ የተለያዩ አዳዲስና ዘመናዊ መንደሮች ይገነባሉ።
ዋና ከተማዋ አምራ ተውባ እንድትገኝ እናደርጋለን። ሁሉን
አይነት አገልግሎት ማግኘት የሚቻልባቸው የባለሃብቱ ቢሮዎች፣
ቅርንጫፍ መስሪያ ቤቶች፣ በሀጋዊ መንገድ ዘመናዊ ሆነው

እንዲገነቡ እናደርጋለን። ባለሙያዎቻችንም እንደ ልባቸው
መጠን፣ መግባት፣ ባሻቸው ዘመናዊ ሆቴል መዝናናት፣ ባሻቸው
ቦታ የየራሳቸውን ዘመናዊ መንደር ገንብተው መኖር የሚችሉበት
ሁኔታ ይመቻቻል። ሁሉንም የከተማ ውስጥ ቢሮዎችና መንደሮች
እናስተሳስራለን። ሁሉም በየተሰማሩበት ዘርፍ ስራቸውን
ይሰራሉ፣ በጋራ ትብብር ወደ ዋና ዓላማቸው ይገሰግሳሉ። ሁሉም
ነገር ደግሞ ሀጋዊ ነው። ስለዚህ ምንም የሚያሰጋ ነገር የለም።

"በቀይ ባህርና በህንድ ውቅያኖስ ድንበሮች በእነ ጂቡቲ በኩል
የጦር ኃይሎቻችን የምናቋቁመውም በአሳማኝ ምክንያት ስለሆነ
የተለየ ትኩረት ሊደረግባቸው አይችልም።

"ጅቡቲና በቀይ ባህር ዙሪያ በሃያል አገራቱ በኩል የጦር ኃይሎች
ከዘመናዊ የጦር መርከቦቻችን ጋር በአካባቢው ስናሰማራ በሺዎች
የሚቆጠሩ ስልጡን ሰራዊቶች ስናሰፍር፣ ተወንጫፊ ሚሳኤሎችን
በዘላቂነት ለማረጋገጥ በሚል ነው።

እርግጥ ነው በምስራቅ አፍሪካ ያን ያህል የዓለም ስጋት የሆነ
የሰላም መደፍረስ የለም። ቢኖርም በእኛ ደረጃ የሚመከት
ጠንካራ ሃይል አይደለም።

"ትልቁ አሸባሪ አልሻባብ የምንለው የኛው ቡድን ነው። ሆኖም
እነሱ የታጠቁት መሳሪያ የነብስ ወከፍ መሳሪያ እንጂ ጀትና
ሚሳኤል ይዘው የሚዋጉ አይደሉም። በእኛ ደረጃ የሚመከት አሰጊ
የሆነ የአሸባሪ ቡድንም በዚያ ቀጠና የለም። ነገር ግን የቀጠናውን
ሰላም በዘላቂነት ለማረጋጋትና አስጠብቆ ለማቆየት የሚለው
ሽፋናችን የአካባቢውን አገራት ድንዙዝ መሪዎች ለማሳመን ከበቂ
በላይ ነው። በዚህም ላይ የጦር ኃምፖች ሲቋቋሙ በነፃ ስላልሆነና
በሊዝ ሽያጭም በኩንትራትም ስለሆነ፣ መሪዎቹ ገንዘብ
ስለሚያገኙ ትኩረታቸው ገንዘቡ ላይ እንጂ ሴራችን ላይ ሊሆን
አይችልም። በዚህ አይነት ዘዴ በከተማቸውና በየገጠሩ
እንደልባችን ስንዘምት፣ ቁሳቁሶቻችን ስናሰራጭ፣ የጦር ልምምድ
ስናደርግ፣ በተለየ ትኩረት የሚያሰጋ አይኖርም።

"በአካባቢው ላይ ይህ አይነቱን ነፃ እንቅስቃሴ ማድረግ እንዲቻለን
ጭምር ነው የየአገራቱን መንግስታት ወደ እርቅ የምናመጣቸው።
ይህን ማድረግ ደግሞ ለእኛ ቀላሉ ስራ ነው።

"የኤርትራው መሪ ደረቅ ነው፣አዎ ደረቅ ነው፡፡እና ምን ይጠበስ? ድርቅናው በመወገድ ይተካል፡፡ይህ ዘመን የፌስ ቡክ ዘመን ነው፡፡ ሳይከለክል ፌስ ቡክን ዘግተን ፌስቡክ ከለከለ ብለን አሳምፀን እንድናስወግደው? ወይስ በቀጥታ እንድናስወርደው ትፈልጋለህ? ምርጫህን ንገረኝ አሁኑኑ!"

"ንግስት ሆ....ጥያቄዬ ያ ሳይሆን...እኔ ማለት የፈለግሁት..."

"አይዞህ ዘና በል፣ማንም ምንም እንደማያመጣና ባሻን መንገድ ያሻንን ተግባር መፈፀምና፣ የፈለግነውን የአገር መሪ በፈለግነው መንገድና ዘዴ ማስወረድና ማስወገድ እንደምንችል ላሳውቅህ ፈልጌ ነው ያስመረጥኩህ፡፡" በማለት አረጋጉት፡፡

"አንድ ሰው የቤቱን ክፍሎች አንድ በአንድ በቁልፍ ቆልፎ ቁልፉን ይዞ እንደሚሄደውና፣ በፈለገ ጊዜ መጥቶ ቁልፉን ከኪሱ አውጥቶ አንድ በአንድ መክፈት እንደሚችለው ሁሉ፣ እኛም የእነዚያን አጎራባች አገራት ልክ እንደ ቤት ክፍሎች አንድ ባንድ ቆልፈን የወጣን ስለሆንን፣ ባሻን ጊዜ ተመልሰን መክፈትና መግባት እንችላለን፡፡ ቤቱን ቆላልፎ የሄደ ሰው የሚመለሰው በፈለገው ጊዜ እንደሆነው ሁሉ፣እኛም በፈለግነው ጊዜ የመመለስ መብት ያለን ነን፡፡ ባለቤት ነንና አትስጉ ለማለት ነው፡፡ ገባህ ወይ ብራዚል?"

"በሚገባ ንግስት ሆይ፡፡"

"ክብር ለልዑሉ!"

"አሜን!" ሞቅ ያለ የጋራ ድምፅ.....፡፡

"መልካም፣ የ G 20 አገራት መሪዎች ላነሳችኋቸው ጥያቄዎች አጥጋቢ ምላሾችን የሰጠሁ ይመስለኛለ፡፡ ሌሎች ተሰብሳቢዎች ራሳችሁን ከሃያል አገራት መሪዎች ጋር አስተዋውቃችሁ የጋራ ቃል ኪዳን ፈጽማችኋልና፣ በየተሰማራችሁበት ዘርፍ ምን ምን አይነት ስራ እንደሰራችሁና ዝግጅትና ጅምራችሁ የት ደረጃ ላይ እንደደረሰ ይፋ ታደርጉልናላችሁ፡፡ እንዴት በጥምረት ልትሰሩ እንደተዘጋጃችሁም ሪፖርታችሁን ታቀርባላችሁ፡፡ ከዚያ ቀጥሎ ጥያቄዎቻችሁን በተመሳሳይ ታቀርባላችሁ፣ እኔም አጥጋቢ ምላሾችን እሰጣለሁ፡፡ ከዚያ በኋላ ይሆናል የዘንድሮውን ዝግ ጉባዔያችን የምናጠናቅቀው፡፡

ከዚያ በፊት ግን፣ አንድ መቅደም ያለበት ጉዳይ አለና እሱን እናስቀድም፡፡ አንድ ለየት ያለና ያልተጠበቀ አስደሳች ነገር ነውና የምናስቀድመው፣ ወደዚሁ ‹‹ሰርፕራይዛችን›› እናምራ ክቡራን፡፡ "ያችን የልዑላችን ዓላማና ዒላማ የሆነች አገር በአገዛዛቸው ስር አድርገው ያለ አንዳች ስስትና ያለ ምንም ቅድመ ሁኔታ እንካችሁ ብለው ሊሰጡን የተዘጋጁትን እንግዶች ትተዋወቋቸው ዘንድ ወደ መድረኩ እንዲመጡ እንጋብዛቸው!" አሉና፣ ሁለት እጆቻቸውን ወደ መድረኩ ዘርግተው እንዲመጡ ጥሪ አቀረቡላቸው፡፡ በዚህ ጊዜ የአዳራሹ ብርሃን ደብዘዝ ማለት ጀመረና፣በአዳራሹ ግራና ቀኝ ያሉት ሁለት ሰፋፊ በሮች በራሳቸው ጊዜ ወደ ላይ እኩል ተከፈቱ፡፡

በተከፈቱት ሁለት በሮች፣ ሴቶቹ በቀኝ በኩል፣ ወንዶቹ በግራ በኩል፣ ሆነው፣ በእኩል እርምጃ ተሰልፈው የሚመጡ በርከት ያለ ቁጥር ያላቸው ኢትዮጵያውያን መታየት ጀመሩ፡፡ በጥቁር ሱፍ፣ በቀይ ሸሚዝ፣ በቀይ ከረቫት፣ ደምቀው፣ ቀይ ካባ የመሰለ የመመረቂያ ጋወን ደርበው፣ በእኩል እርምጃ እየተራመዱ ወደ መድረኩ አቀኑ፡፡ ደረጃዎቹን ወጥተውም መድረኩ ላይ በረድፍ ቆሙ፡፡

አዳራሹ ለአፍታ ያህል በዝምታ ተውጦ ከቆየ በኋላ ንግስቲቱ፣ ኢትዮጵያውያኑን ማስተዋወቃቸውን ቀጠሉ፡፡

"እነዚህ የምታዩዋቸው ኢትዮጵያውያን ረዘምና አጠር ላሉ ዓመታት በውጭ የትምህርት እድል ሰበብ ከኢትዮጵያ መልምለን ያመጣናቸው ናቸው፡፡ ባቀረብንላቸው ሃሳብ ተስማምተውና ፈቃደኝነታቸውን ገልፀው የተመለመሉና በእኛ አማካኝነት የሰለጠኑ ናቸው፡፡

"አገራቸው ላይ በተለያዩ መንግስታዊና መንግስታዊ ባልሆኑ ተቋማት የኃላፊነት ዘርፎች ላይ ተመድበው ሲሰሩ የነበሩና አሁንም ድረስ ቦታቸውን ያልለቀቁ ናቸው፡፡ ከሐይማኖት ተቋማት ጀምሮ እስከ ህክምና ዘርፍ፣ ከመገናኛ ብዙሃን ዘርፎች ጀምሮ እስከ ኪነ ጥበብ ዘርፍ፣ ከፖሊስ ባልደረባነት ጀምሮ እስከ ባለ ማዕረግ ወታደር፣ ከሚንስትርና ከዲኤታ ሚንስትር ጀምሮ እስከ ኢኮኖሚስት፣ ከግብርና ዘርፍ ባለሙያ እስከ ሳይንስና ቴክኖለጂ፣ ከደህንነት ሹም እስከ አምባሳደር፣ አንድም ዘርፍ ሳይቀረን ከሁሉም የተውጣጡ እንዲሆኑ አድርገን የመለመልናቸው

ናቸው። አሁንም ድረስ በሰራ ላይ ያሉና፣ ሰራቸውን በውክልና እያሰሩ ለትምህርት ወደ እኛ የመጡ ናቸው።

"ወደ እኛ መጥተውም ከባዱንና ፈታኝ የተባለውን ስልጠና ሰልጥነው፣ ስልጠናቸውንም በብቃት ተወጥተው፣ በእኛ የተመረቁና የተባረኩ ናቸው። ትምህርትና ስልጠናቸውም ሁሉንም አይነት ዘርፍ ያካተተ ነበር። የሚመረቁበት ማዕረግም ዶክትርና ነው።

"የልጃችን የአሜሪካው የስለላ ድርጅት ሲ አይ ኤ እንዚህን ኢትዮጵያውያን ሌት ተቀን በማሰልጠን የከፈለው ዋጋ ቀላል አይደለም።

"ሲ አይ ኤ በታሪኩ ለእነዚህ እሁቶችና ወንድሞች የሰጠውን ስልጠና ለማንም አልሰጠም። ከሰዎች የሳይኮሎጂ አቅም በላይ እንዲሆኑ አድርገን አሰልጥነናል። እነዚህ ኢትዮጵያውያን ያለ አንዳች ስህተት ተልዕኳቸውን መፈፀም የሚችሉ መሆናቸው በደንብ ተረጋግጦ፣ ሁሉንም ፈታኝ ፈታኝ ፈተናዎች አልፈው የመጨረሻ ደረጃ ላይ የደረሱ ብልህ፣ ንቁና አስደናቂ የሆኑ ዜጎች ናቸው። እነዚህን ኢትዮጵያዊ ልጆቻችንን ነው ዛሬ በፈታችሁ አቁመን የምናስተዋውቃችሁ።

"እነዚህ ምልምል አባላት የዚህ ድንቅ አጀንዳችን አስፈፃሚዎች አይደሉም። መንገድ ጠራጊዎች ናቸው። ወደ ፊት ስራቸው እየታየ ከፍ ከፍ እያሉ የሚሄዱ ናቸው።

"በእኛ በኩል እነዚህን ዜጎች ቀጥቅጠን አሰተምረንና አሰልጥነን እዚህ ደረጃ አድርሰን አቅርበናል። በእጅጉ የምንተማመንባቸውና ሙሉ እምነት የጣልንባቸው ናቸው። በራሳቸው አንደበት ደግሞ የሚሉትን ይላሉና አድምጧቸው።" በማለት ሁለት እጆቻቸውን ወደ ንግግር ማድረጊያው ዘርግተው ስለ ራሳቸው ገለፃ እንዲያደርጉ ጋበዙ።

በዚህ ጊዜ በረድፍ ከቆሙት ወጣትና ጎልማሳ ኢትዮጵያውያን መካከል፣ መሃል ላይ ቆሞ የነበረው ጎልማሳ ቆፍጠን ብሎ እየተራመደ ወደ ንግግር ማድረጊያ ቦታው አቀና። ገና ንግግር ሳይጀምርም ከተሰብሳቢዎች በኩል ሞቅ ያለ የደስታ ጭብጨባ ተስተጋባለት።

"ወደ እዚህ ወደ ተቀደሰ ህብረት የጠራን የታመነ ነው፣አሜን!?" ሲል፣ ጀመረና ሌላ ሞቅ ያለ ጭብጨባ አሜን ከሚል ከባድ ድምፅ ጋር እንዲለገሰው በዓይናቸው ተማፀነ። እነሱም መሻቱን

አልነፈጉትም፣ "አሜን!" የሚል የጋራ ድምፅ አሰምተው፣ ሁሉም በጋራ ቆመው በረጅሙ አጨበጨቡለት።

እስኪጠግብ ከተጨበጨበለት በኋላ በትህትና፣ "ተቀመጡ ከቡራን" በማለት ተሰብሳቢዎቹን አስቀምጠ፣ ተመራቂዎቹን ወክሎ ስፊ ገለፃውን ማድረግ ጀመረ.....።

****** ****** ******